# አማርኛ

## እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## (፰) 8ኛ ክፍል

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የትምህርት ሚኒስቴር**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ**
**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለከተማ ዐውድ ተስማምቶ የቀረበ**


**አስማምቶ አዘጋጆች**

ፍሬህይወት አባይነህ አፋ

ፍስሐ የለምፍርሃት ስመኝ

**ጥራት ተቆጣጣሪ**

ፍሬህይወት አሠፋ ከበደ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለማዓቀፍ የልማት ድርጅት (United States Agency for International Development (USAID)) በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮና በREAD - TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ስራ የተከናወነው አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም (General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II) ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ናቸው።

USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE

ISBN: 978-99944-2-547-1

# የይዘት ማውጫ


መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ) .............................. iv

ምዕራፍ 1

የሥራ ሥነምግባር .............................. 1

ምዕራፍ 2

ቅርስ .............................. 24

ምዕራፍ 3

ሰብዓዊ እሴቶች .............................. 44

ምዕራፍ 4

ባህላዊ ግጥሞች .............................. 67

ምዕራፍ 5

ሥነሕዝብ .............................. 92

ምዕራፍ 6

በርሃማነት .............................. 119

ምዕራፍ 7

የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ .............................. 144

ምዕራፍ 8

የሴቶችን አቅም መገንባት .............................. 168

ምዕራፍ 9

የአየር ንብረት .............................. 192

ምዕራፍ 10

ተውኔት .............................. 218

ሙዳየቃላት .............................. 248

ዋቢዎች .............................. 252

# መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ)

ይህ መጽሐፍ ከ5ኛ እስከ8ኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋዉ በብቃት ማንበብ፣ መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት አካል ነው። የመጽሐፍ ዝግጅቱም፣ ተማሪዎች እንዴት ማንበብና መጻፍ እንደሚችሉ፣ መማር ፈጠራዊና አስደሳች እንዴት እንደሚሆን፣ የትምህርትቤት ውስጥ ተግባራት እንዴት መማርን እንደሚያግዙና እንደሚያጐለብቱ በተደረጉ ጥናቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ስለነዚህ የክፍል ደረጃዎች ሥርዓተትምህርትና ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሽፋን መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርትቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## የሥርዓተትምህርቱ መሠረታዊ መርሖች፤

1. ተማሪዎች በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች ይማራሉ (እያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ የምንባብ ይዘትና የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን ይሸፍናል።)
2. ተማሪዎች ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡና ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመሥረት ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም።
3. ሁሉም የቋንቋ ትምህርት ከእነዚህ የምንባብ ይዘቶች፣ ርዕሰጉዳዮችና ምንባቦች ጋር የተያያዘ ነው።
4. ተማሪዎች በርካታ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም ተግባራቱን በቀላሉ በተገቢ ሁኔታ ለማከናወንና ራሳቸውንም በትክክል ለመግለጽ አይቸገሩም፤
5. ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሠሩ ተማሪዎች ይማራሉ።
6. ተማሪዎች በምዕራፎቹ ይዘቶችና በርዕሰጉዳዮች ላይ ተመሥርተው የቀረቡ ጽሑፎችን በሚያዳምጡበት፣ በሚያነቡበትና አዳዲስ ቃላትን በሚተዋወቁበት ጊዜ የቃላቱን ፍቺዎች ይማራሉ፤ ይረዳሉ፤ ይጠቀሙባቸዋልም። እነዚህን አዳዲስ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜም የበለጠ ይረዷቸዋል፤ የቋንቋ ችሎታቸውንም የበለጠ ያበለጽጋሉ።

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በጋራ መማር

ተማሪዎች በትምህርትቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል።

1. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ።
2. በትምህርትቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይኼንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ።
3. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤
   - ምንባቡ ምን ዓይነት የምንባብ ይዘት ይሸፍናል?
   - በምን ዓይነት ርዕሰጉዳይ ላይ ያተኩራል?
   - ከዚህ የምንማረው ምንድን ነው?
   - ስለርዕሰጉዳዩ በተጨማሪ ምን እናውቃለን? ስለርዕሰጉዳዩ በዜና ወይም ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ የሰማነው ምንድን ነው? ስለርዕሰጉዳዩ በሌላ ቦታ ምን አንብበናል?
   - ስለርዕሰጉዳዩ ወይም ርዕሰጉዳዩ በምንባቡ ውስጥ በቀረበበት መንገድ ላይ በግል ያለን አስተያየት ምንድን ነው?
   - በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ ስለርዕሰጉዳዩ ምን ማወቅ እንፈልጋለን?
   - ስለርዕሰጉዳዩ በተለየ ሁኔታ ምን ለመሥራት እንፈልጋለን?
4. በምንባቡ ውስጥ ስላጋጠሟችሁ ቃላት የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያዩ፤
   - የዚህ ቃል ፍቺ ምንድን ነው?
   - ቃሉስ ምንባቡን ለመረዳት ረድቶኛል?
   - በተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ውሏል?
   - እንዴትስ በሕይወቴ ውስጥ ልጠቀምበት እችላለሁ?
5. ስለርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ።
6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ።

7. ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ።
8. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ።
   - ትምህርቱ ከባድ ነው/ነበር?
   - ትምህርቱ ቀላል ነው/ነበር?
   - ለቋንቋ ትምህርቱ ጠቃሚ ነው/ነበር?
   - ልጆቹ ቀጥሎ ምን መማር ይፈልጋሉ?
9. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው፤ ለምሳሌ፣ የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ተሰድረዋልወይ? በዓርፍተነገሮች ውስጥና/ወይም መካከል ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋልወይ? ወዘተ.
10. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው።
11. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ እንዲጽፉ አበረታቷቸው።

## የመጽሐፍ ይዘቶች አደረጃጀት

### ትምህርቶች

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በምዕራፍ ተደራጅተው ቀርበዋል። እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት፣ እያንዳንዱም የምንባብ ይዘት ሦስት ርዕሰጉዳዮችና አራት አራት ምንባቦች አሉት። የምንባብ ይዘቶቹና ርዕሰጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋቸው እንዲናገሩ፣ እንዲያዳምጡ፣ እንዲያነቡና እንዲጽፉ እንደመነሻ ያገለግሏቸዋል።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ ምዕራፍ የሚያዳብሯቸው ክሂሎች ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። ወላጆች ምናልባት ስለነዚህ ክሂሎች ጥያቄዎች ካሏችሁ ልጆቻችሁን ወይም መምህሮቻቸውን ጠይቃችሁ ማብራሪያ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ልጆቻችሁን እንዴት መርዳት እንደምትችሉ ከመምህራን ጋር ተወያዩ።

## የቃላት ጥናት

ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን፣ የቃላቱን የተለያዩ የመዋቅር አካላት፣ ለተለያዩ አጠቃቀሞች የሚያሳዩትን የቅርጽ ለውጦች ይማራሉ።

## አንብቦ መረዳት

ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ እንዴት ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡና እንደሚረዱ ይማራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመሥረተው በሚዘጋጁ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። እነዚህም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- ምንባቡ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማንበብ በፊት መገመት፣
- አስፈላጊ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመንባብ፣ የማንበብ ሂደትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስለምንባቡ እንዲናገሩ፣ የግል ሀሳባቸውንም እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- በምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ የተውኔት ጽሑፎችን ሰጥቶ እንዲከውኑ ማድረግ።

## ቃላት

ተማሪዎች በሚያነቧቸውና በሚያዳምጧቸው ምንባቦች ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተምረው ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡-

- የቃላትን ንበት፣ ፍቺና የተለያየ አጠቃቀም ይማራሉ፤
- ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ሌሎች ቃላት ይማራሉ፤
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ (ለምሳሌ በቤት ወይም በማኅበረሰብ አካባቢ) በሚፈጸሙ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ቃላቱን ይጠቀማሉ።

## መጻፍ

ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች በግል ወይም በቡድን ይጽፋሉ። የሚጽፏቸውም ጽሑፎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የተለያዩ የጽሑፍ ዓይነቶችን፣ ለምሳሌ ተራኪ፣ ገላጭና አወዳዳሪ ወይም አነፃፃሪ ጽሑፎችን መጻፍ፣
- ሃሳባቸውን እንዲጽፉ፣ እንዲከልሱ (እንዲያርሙ) እና ለኅትመት ዝግጁ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- የጽሑፍን የተላያዩ ቁምነገሮች፣ ለምሳሌ በቃላት ውስጥ ፊደላትን በአግባቡና በትክክል መጻፍ፣ ቃላትን በትክክል ማንበብ፣ አጥረው የተጻፉ ቃላትን ወዘተ መረዳት።

## አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ጽሑፎችን ለደረጃቸው ተገቢ በሆነ ፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማለትም የምንባቡን መልዕክት በሚገልጽ ስሜት ደረጃ ድምፅ በማሰማት ያነባሉ።

## ቃላዊ ክሂሎች፣ ማዳመጥና መናገር

ተማሪዎች በሚያነቡትና በሚያዳምጡት ጽሑፍ ላይ ትኩረት ማድረግንና መረዳትን ይማራሉ። በተጨማሪም በሚያዳምጡትም ሆነ በሚያነቡት ጽሑፍ ላይ በተመሠረቱ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። የሚሠሯቸውም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የማዳመጡ ምንባብ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማዳመጥ በፊት መገመት፣
- ቁልፍ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ሂደትና የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በማዳመጥ ምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለማዳመጥ ምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለማዳመጥ ምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስላዳመጡት ምንባብ መናገር፣ የግል ሀሳብን ማቅረብ፣
- በማዳመጥ ምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን መከወን።

## ሰዋስው

ተማሪዎች የቋንቋውን የተወሰኑ መዋቅራዊ ክፍሎች ለምሳሌ፣ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን፣ የአሁንና የኃላፊ ጊዜ ግሶችን፣ ቅጽሎችን፣ ተውሳከግሶችን፣ ነጠላና ድብልቅ ዓረፍተነገሮችንና አጠቃቀማቸውን ይማራሉ።



# የሥራ ሥነምግባር

ምዕራፍ 1

## ሥራ የችግር መፍቻ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | አካል-አቸው-ን | አካላቸውን |
| ለ | ይፈጥር-ል-አቸው-አል | ይፈጥርላቸዋል |
| ሐ | ይጠበቅ-ብ-አቸው-አል | ይጠበቅባቸዋል |
| መ | እናሸንፍ-አቸው-አል-ኝን | እናሸንፋቸዋለን |
| ሠ | አዕምሮ-አቸው-ን | አዕምሯቸውን |
| ረ | ተ-አካሚ-ዎች-አቸው | ታካሚዎቻቸው |

## ማንበብ

### ሥራ የችግር መፍቻ

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግበር**

ከቀደመ ዕውቀታችሁ በመነሳት ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ስጡ።

ሀ. ሥራ

ለ. የሥራ ዕድል

ሐ. ጉልበት መጠቀም

መ. የሥራ ሥነምግባር

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር 1

መምህራችሁን እየተከተላችሁ «ሥራ የችግር መፍቻ» የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሁለት አንቀጾች ሁለት ጊዜ አንብቡ።

### ተግባር 2

«ሥራ የችግር መፍቻ« በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከሶስተኛው አንቀጽ ጀምራችሁ በየአንቀጾቹ መጨረሻ ቆም እያላችሁና የአንቀጾችን መልዕክት እያጠቃለላችሁ አንብቡ። ያልተረዳችሁት አንቀጽ ሲኖር በድጋሚ በማንበብ ለመገንዘብ ሞክሩ።

## ሥራ የችግር መፍቻ

ሥራ የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲሉ የሚያከናውኑት ተግባር ነው። ተግባሩም የተፈጥሮ አካባቢን ለተሻለ ኑሮ በማመቻቸት ለውጥ ማምጣት ያስችላል። በመሆኑም ሰዎች ሥራ ለመሥራት አካላቸውንና አዕምሯቸውን ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም በትምህርት መታገዝ ያስፈልጋቸዋል። ትምህርት ዕውቀትን በመጠቀም አዳዲስ ግኝቶችን ለማፍለቅ ስለሚያስችል ሰዎች መማር አለባቸው።

ሥራ ከዕለትተዕለት ህይወት ጋር የተቆራኘ ነው። አቅደውም ሆነ ሳያቅዱ ሰዎች ከሥራ ተለይተው አያውቁም። በዕለትተዕለት የሚያከናውኗቸው እንደመመገብ፣ መራመድና የግልና የአካባቢ ንፅህና መጠበቅ የመሳሰሉት ተግባራት ህይወት በሥራ የተጠመደች መሆኗን ያመላክታሉ። ሰዎች ሥራ የሚጀምሩት ምንነቱን ሳይረዱት ገና በሕጻንነት ዕድሜያቸው ነው። «ይህን አቀብይኝ፣ ያንን ዝጋው፣ ውኃ ስጠኝ ወዘተ» ሲባል ሥራ ተጀምሯል ማለት ነው። እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ጉልበትን መጠቀም ያስፈልጋል።


ሥራ ዘመን የማይሽረው የሰው ልጆች ተግባር ነው። ይሁንና የሥራው ባህርይ ከሰው ልጆች ዕድገትና መሻሻል ጋር ብዙ ለውጥ እያመጣ ይሄዳል። የአኗኗር ሥርዓት በተለወጠ ቁጥር ለኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮች ይለወጣሉ። ይህን ለማሟላት ደግሞ ጉልበትንና ችሎታን በመጠቀም ውጤታማ መሆን ይቻላል። ካልሠሩ ልብስ፣ መጓጓዣ፣ ትምህርት፣ ሕክምና ወዘተ. ማግኘት አይቻልም። ከዚህም ለመኖርና ህይወትን የተሟላ ለማድረግ ሥራ አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ሥራ በባህሪው መረዳዳትንም ይጠይቃል። የሰው ልጆች በማኅበራዊ ህይወታቸው አንዳቸው በሌላቸው ላይ ጥገኛ ናቸው። ይህም ሥነምግባራዊ ግዴታን ለመወጣት ያስችላል፤ ከሌሎች ጋር ተግባብቶና ተስማምቶ ለመሥራት ለሥራ ሥነምግባር መገዛት የግድ ይላል። የራስን ሀሳብ ማካፈል፣ የሌሎችንም መቀበልና ለለውጥ መሥራት አንዱ የሥራ ሥነምግባር ነው። በግላችን የማንወጣቸውን ተግዳሮቶች

በጋራ በመሥራት እናሸንፋቸዋለን። <u>ማኅበራዊ</u> ህይወት ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ ነገር ሲሆን ካለሱ ህይወት ሙሉ አትሆንም። አሁን ያለንበት የዓለማችን ተጨባጭ ሁኔታ በኅብረት እንድንሠራ ያስገድደናል። በጋራ መሥራት የጋራ ተጠቃሚነትን ያመጣል። ለአብነት «የሠርቶ መለወጥን የሴቶች ማኅበር» መጥቀስ ይቻላል። ከታች ከሠንጠረዡና ከግራፉ ለመረዳት እንደሚቻለው ሴቶች በማኅበር ተደራጅተው በግ ያረባሉ፤ ፍራፍሬ ያመርታሉ፤ ንብ ያንባሉ። በዚህም ገቢያቸውን ያሳድጋሉ።

«የሠርቶ መለወጥ የሴቶች ማኅበር» የአራት ዓመት ገቢ መግለጫ በሥራ ዓይነት

| የሥራ ዓይነት | የገቢ መጠን በዓመተምሕረት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 2000 | 2001 | 2002 | 2003 |
| በግ ማድለብ | 154,000 | 148,643 | 225,345 | 345,678 |
| ዶሮ ማርባት | 256,000 | 168,900 | 137,875 | 224567 |
| ፍራፍሬ ማምረት | 175,800 | 200,000 | 178,456 | 980,450 |
| ንብ ማነብ | 345,879 | 387,600 | 398,450 | 500,765 |




ሥራን በፍላጎትና <u>በተነሳሽነት</u> መሥራት ውጤታማ ያደርጋል። ነገርግን ከውስጥ ባልመነጨ ፍላጎት በሌሎች ግፊት ወደሥራ ቢገቡ ተነሳሽነቱ ከሌለ የተሰማሩበትን <u>የሥራ ዕድል</u> የማጣትና ከሥራ መቀነስ ያጋጥማል። በዚህም ደስታ ይታጣል። የማይሠሩ ሰዎች ደስታ የሚያጡት በሰዎች እይታ ብቻ ሳይሆን በራሳቸውም ህሊና ውስጥ ነው። ስለዚህ በመሥራት ነፃነትን ማግኘት ያስፈልጋል።

ነፃነት ተገኘ ማለት የሚቻለው ከሌሎች ገንዘብና ቁሳቁስ ርዳታ ወጥቶ በመሥራት በራስ ገቢ መኖር ሲቻል ነው። በራስ ገቢ መኖር ነፃ የሚያወጣው ከሌሎች ጥገኝነት ብቻ ሳይሆን ከህሊና ወቀሳ ነው። ይህም ደስታን ከማጎናጸፉም በላይ በራስ መተማመንን ይፈጥራል።

የሰው ልጆች ችግርንና መከራን በሥራ አማካይነት አሸንፈው ደስታን መጎናጸፍ እርካታን ይፈጥርላቸዋል። ለዚህም ነው፣ ብዙ አድካሚ ሥራን ከሠራን በኋላ በውጤቱ የምንረካውና የምንደሰተው። አስተማሪዎች ከብዙ ድካም በኋላ ተማሪዎቻቸው በከፍተኛ ውጤት ሲያልፉላቸው ይደሰታሉ፤ ሀኪሞችም ታካሚዎቻቸው ሲፈወሱላቸው ይደሰታሉ፤ ምግብ አዘጋጆችም የሠሩት ምግብ ሲደነቅላቸው ይደሰታሉ፤ በመሆኑም ሥራን አስደሳች የሚያደርገው ድምሩ ሳይሆን ውጤቱ ነው።

(በደ/ብ/መ/ሙ/ማ/ኮሌጅ ማኅበራዊ ሳይንስ ት/ክፍል። *ለሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ለመለያ 212 ኮርስ ማስተማሪያነት የተዘጋጀ፣ ዓመተምሕረት የሌለው፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በ2001 ዓ.ም. ቅናሽ አሳይቶ በሚቀጥሉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት ዕድገት ያሳየው በየትኛው የሥራ መስክ የተገኘው ገቢ ነው?

ለ. በ2002 ዓ.ም. ዝቅተኛ ገቢ የተገኘው በየትኛው የሥራ መስክ ነው?

ሐ. ለሁለት ተከታታይ ዓመታት እየቀነሰ ሄዶ በሶስተኛው ዓመት ጭማሪ ያሳየው በየትኛው የሥራ መስክ የተገኘው ገቢ ነው? ይህ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?

መ. «ሰዎች ከሥራ ተለይተው አያውቁም» የሚለውን አባባል «እከሌ/ሊት ሥራ የለውም/ላትም» ከሚለው አባባል ጋር በማገናዘብ አብራሩ።

ሠ. እናንተ የንግድ ሥራ መሥራት ብትፈልጉ በሠንጠረዡ ከቀረቡት የሥራ መስኮች መካከል በየትኛው ትሠማራላችሁ? ለምን?

ረ. «የሥራ ባህርይ ከሰው ልጆች ዕድገትና መሻሻል ጋር ለውጥ እያመጣ ይሄዳል» የሚለውን ሀሳብ በምሳሌ አስደግፋችሁ አስረዱ።

## 2ኛ ቀን

### ቃላት

## ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተነሳሽነት
ለ. ሥራ
ሐ. ጉልበትን መጠቀም
መ. የሥራ ዕድል
ሠ. ገቢ
ረ. ማኅበራዊ

### ተግባር 2

ምንባቡን መሠረት በማድረግ በ«ሀ» ረድፍ ለተሰጡት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺቻቸውን በ«ለ» ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. መታገዝ | ሀ. ፋታ ያጣች |
| 2. የተያያዘ | ለ. በድንገት |
| 3. ማሰልጠን | ሐ. ምሳሌ |
| 4. የተጠመደች | መ. መደገፍ |
| 5. መጠቀም | ሠ. ማስተማር |
| 6. በቅጽበት | ረ. የተቆራኘ |
| 7. መረጻጻት | ሰ. ሥራ ላይ ማዋል |
| 8. አብነት | ሸ. መተጋገዝ |
| | ቀ. ውጤት |

### ተግባር 3

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተግዳሮቶች
ለ. በግል
ሐ. ማካፈል
መ. ከሥራ መቀነስ
ሠ. ነፃነት


## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት መጻፍ

#### ተግባር

የሚከተለውን የቢጋር ክብ መሠረት በማድረግ ሀሳቦቹን አስፋፍታችሁ በምክንያትና ውጤት የተዋቀሩ ሁለት አንቀጾች ጻፉ።




### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን ወደአሉታዊ ቅርፅ መለወጥ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት በአሉታዊ ቅርፅ ጻፉ።

ምሳሌ፡- «ለወጠ» የሚለው ቃል በአሉታዊ ቅርጽ ሲጻፍ «አለወጠም፣ አለወጠችም፣ አለወጥንም፣ አለወጥኩም፣ አለወጡም፣ አለወጣችሁም፣ አለወጥሽም፣ አለወጥክም» ይሆናል።

ሀ. መከረ

ለ. ፈለገ

ሐ. ጠበቀ

መ. ጠቀመ

ሠ. ነቀለ

ረ. ሠራ

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ሥራ የችግር መፍቻ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የሠንጠረዥ መረጃዎች የሚነበቡት እንዴት ነው?

ለ. ሠንጠረዥን በማንበብ ብቻ የተሟላ መረጃ ማግኘት ይቻላል? እንዴት?

### ማንበብ

**ተግባር**


የሚከተሉትን ተግባራት በቅደምተከተል አከናውኑ።

ሀ. የምንባቡን የመጀመሪያ ሦስት አንቀጾች ሁላችሁም ድምፅ በማሰማት ሁለት ጊዜ አንብቡ።

ለ. ከምንባቡ ውስጥ ያለውን ሠንጠረዥ መምህራችሁን በመከተል በፍጥነት ደጋግማችሁ አንብቡ።

ሐ. ጥንድ ጥንድ በመሆን የሚከተለውን ግራፍ በማነጻጸር አንብቡ።

## የዓለም ሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከ1930-2010




(ኢ.ብ.ክ.መ.። ትምህርትቢሮ። 1996። *ሕብረተሰብ ትምህርት 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ፣* መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## ማዳመጥ

## የጥንካሬ ተምሳሌት

### ቅድመማዳመጥ

### የምንባብን ሀሳብ መገመት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «የጥንካሬ ተምሳሌት» በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሑፍ ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል?

ለ. በጥንካሬው/ዋ ተምሳሌት የሆነ ወንድ/የሆነች ሴት ታውቃላችሁ? የጥንካሬው/ዋ መገለጫ ምንድን ነው?

ሐ. ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።



## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

«የጥንካሬ ተምሳሌት» የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ያነቡላችኋል፤ ዋናዋና ሀሳቦችን እየመዘገባችሁ በትኩረት ተከታተሉ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. እናት አካባቢዋን ትታ የኮበለለችበት ምክንያት አሳማኝ ይመስላችኋል? ለምን?

ለ. እናንተ እናትን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

ሐ. እናት ባትኮበልል ኖሮ ምን ትሆን ነበር?

መ. እናት ለስኬት የበቃችው እንዴት ነው?

ሠ. በሥራ ውጤታማ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው? ለምን?

ረ. እናት የኮበለለችው በወላጆቿ ምክንያት ነው፤ ስለዚህ ወላጆቿ እናትን አይወዷትም ማለት ነው?

ሰ. ቀጥሎ በቀረበው የቢጋር ምስል ውስጥ በየሳጥኑ የተጓደሉትን ምክንያቶች ወይም ውጤቶች በመጻፍ አሟሉ።




## ሰዋስው

### አዎንታዊና አሉታዊ ዓረፍተነገር

ዓረፍተነገሮች እንደሚከተለው በአወንታዊ ወይም በአሉታዊ ሊጻፉ ይችላሉ።

ምሳሌ፡-

| አዎንታዊ ዓረፍተነገር | አሉታዊ ዓረፍተነገር |
|---|---|
| ሀ. ድንቅነሽ መጽሐፍ ገዛች። | ሀ. ድንቅነሽ መጽሐፍ አልገዛችም። |
| ለ. ተዋበ እንጨት ይፈልጣል። | ለ. ተዋበ እንጨት አይፈልጥም። |
| ሐ. መሐመድ መጽሐፍ እያነበበ ነው። | ሐ. መሐመድ መጽሐፍ እያነበበ አይደለም። |

## ተግባር 1

የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአሉታዊ ዓረፍተነገር ለውጣችሁ ጻፉ።

ሀ. ቃኘው ምሳ በልቷል።

ለ. ማሚት ነገ ትመጣለች።

ሐ. ሀና መጽሐፍ እየጻፈች ነው።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን አሉታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአዎንታዊ ዓረፍተነገር ለውጣችሁ ጻፉ።

ሀ. መላኩ ወደ10ኛ ክፍል አላለፈም።

ለ. ሰላም ጥልፍ አትጠልፍም።

ሐ. ዳውድ ቁርስ እየበላ አልነበረም።

## ተግባር 3

አምስት አዎንታዊ ዓረፍተነገሮች ከመሠረታችሁ በኋላ ወደአሉታዊ ዓረፍተነገሮች ቀይራችሁ በደብተራችሁ ጻፏቸው።

## ማንበብ

### ገቢን ማሳደግ

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

ለሚከተሉት ቃላት በቃላችሁ ፍቺ ስጡ።

ሀ. መቆጠብ  ሐ. ስኬት  ሠ. መረዳጃ  ሰ. ውጣውረድ


ለ. መዋጮ  መ. ማስተዛዘኛ  ረ. ሐሴት

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

ቀጥሎ «ገቢን ማሳደግ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ፣ ሀሳቡን መረዳታችሁን ለማረጋገጥ ራሳችሁን ጥያቄ በመጠየቅና ሀሳቦችን ርስበርስ በማስተሳሰር ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### ገቢን ማሳደግ



ፍቅር የመረዳጃ ዕድር ከተቋቋመ ብዙ ዓመት ሆኖታል። ዕድሩ የተቋቋመበት ዓላማ በችግር ጊዜ ለመረዳዳትና ለመተጋገዝ ነው። አባላቱ በሙሉ ሴቶች ሲሆኑ ቁጥራቸው 30 ነው። በየወሩ አምስት አምስት ብር ማዋጣት ጀመሩ። የገንዘብ አቅማቸው እስኪጎለብት ድረስ ግን ለሀዘን መረዳጃና ለእንጀራ የሚሆኑ ግብዓቶችን ከየቤታቸው በማምጣት ይረዳዱ ነበር። ሆኖም በየቤቱ የሚደረገው መዋጮ የዓይነትም ሆነ የጥራት ችግር አጋጠመው። ችግሩን ለማቃለል በማሰብም የዕድሩ ኮሚቴ አባላቱን ለማማከር ስብሰባ ጠራ።

በውይይታቸውም ለማስተዛዘኛ እንጀራና የወጥ ግብዓቶች በአንድ ቦታ እንዲዘጋጅ ተስማሙ። ከአባላቱ መካከል መደበኛ ሥራ የሌላቸው አምስት የቤት እመቤቶች በስምምነት ተመረጡ። ሥራውን ለመጀመርም አቅማቸው ሲጠናከር የሚመልሱት ከዕድሩ ተቀማጭ ገንዘብ ተቀንሶ ብድር እንዲሰጣቸው ተወሰነ።

አምስቱ የቤት እመቤቶች ከዕድሩ በተሰጣቸው ገንዘብ በአንዳቸው ቤት የባልትና ውጤቶችን እያዘጋጁና እንጀራ እየጋገሩ አባላቱ ሀዘን በደረሰባቸው ጊዜ ማቅረብ ጀመሩ። ዝግጅታቸውም ባልትናቸውን ይበልጥ እያስተዋወቀላቸው መጣ። ታዋቂነታቸውም ከጊዜ ወደጊዜ ጨመረ። የተበደሩትን የዕድር ገንዘብ በመመለስ በራሳቸው ገንዘብ መነገድ ጀመሩ። በዚህም የተነሳ የሌሎች ዕድር አባላትን ትኩረት መሳብ ቻሉ። በርካታ ዕድሮችም ደንበኞቻቸው ሆኑ። ገቢያቸውና የደንበኞቻቸው ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ ተጨማሪ የመሸጫና የማከፋፈያ ሱቅ አስፈለጋቸው። የቀበሌው ኃላፊዎችም ጥረታቸውን በማየት የማከፋፈያና የመሸጫ ሱቅ አከራዩአቸው። ይህም ከሌሎች ደንበኞች ጋር ይበልጥ እያስተዋወቃቸው መጣ። ሆቴሎች፣ ሕጻናት ማሳደጊያዎችና በአካባቢያቸው ያለው ዩኒቨርስቲ ደንበኞቻቸው ሆኑ።

የአባላቱ ገቢና ሀብት እያደገ ስለመጣና የመሸጫ ቅርንጫፍ ሱቆች በተለያዩ ቦታዎች ስለከፈቱ፣ ተጨማሪ ሠራተኞችን መቅጠር አስፈለጋቸው። ለማኅበሩ ሂሳብ፣ ጥበቃ፣ ንብረት ክፍል፣ ገንዘብ ያዥና የሽያጭ ሠራተኞችን ቀጠሩ። አባላቱና ሠራተኞቻቸውም ያለመታከት ጠንክረው በመሥራታቸው ትርፋማነታቸው እየጨመረ መጣ። ኑሯቸውንም አሻሻሉ። በሂደትም የዝግጅቱን ሥራ ለቅጥር ሠራተኞች በመተው፣ የአስተዳደሩን ሥራ መሥራት ጀመሩ።

አንድ ቀን በቀበሌያቸው የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ለስብሰባ ተገኙ። ከቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽሕፈትቤት የመጣው ባለሙያ ተጨማሪ ሥራ በመሥራት ገቢን እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል ያደረገውን ገለፃ አዳመጡ። ከዚያም አባላቱ የገቢ ምጥጥን በማሠራትና ያላቸውን ካፒታል ለመንግስት በማሳወቅ ብድር የሚያገኙበትን መንገድ አመቻቹ። በሆቴል የሥራ ዘርፍ ለመሥራት አስጠንተው ለሚመለከተው ክፍል አቅርበው ተፈቀደላቸው። ከቆጠቡት ገንዘብ በተጨማሪ ከባንክ በመበደር ሥራቸውን ጀመሩ።

አካባቢው የቱሪስት መስህብ በመሆኑ ሆቴሉ የቱሪስቶችን ፍላጎት ሊያሟላ የሚችልና ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ መገንባት ነበረበት። ከተወሰኑ ዓመታት ውጣውረድ በኋላ ግንባታው በመጠናቀቁ አስፈላጊውን ቁሳቁስ አሟልተው ሥራ ጀመሩ። ለሆቴሉ ሠራተኞች መቅጠር አስፈላጊ ስለሆነ ቀደም ሲል ሥራ እንዲጀምሩ ካበረታቷቸው የማኅበሩ አባላት መካከል ችሎታና አቅም ያላቸውን የሥራ ባለቤት አደረጉ። ለጓደኞቻቸውም የሥራ ዕድል በመፍጠራቸው ሐሴት ተሰማቸው። ሆቴሉም ተመርቆ ሥራ ሲጀምር ለአካበቢው ማኅበረሰብና ለቱሪስቶች ጥሩ የመዝናኛ አማራጭ ሆነ።

በትንሽ ገቢ የተነሱት አምስት አባላት ትልቅ ባለሀብት በመሆን ከራሳቸውና ከቤተሰባቸው አልፈው የሌሎችን ህይወት መለወጥ ችለዋል። ሌሎች የአካባቢው ኗሪዎችም እነሱን አርአያ በማድረግ በሥራ መለወጥ እንደሚቻል ራሳቸውን አሳምነው ወደሥራ ገብተዋል። ሥራን አክብሮ መሥራት ለትልቅ ስኬት ማድረሱን የዕድሩ አባላት ምስክሮች ናቸው።

አባላት ጠንክረው ሠሩ፤ በሥራ ትርፍ አገኙ፤ በትርፋቸውም ይበልጥ ተለወጡ። ያን ያሳለፉትን የህይወት ውጣውረድ አልፈው ትልቅ ደረጃ መድረሳቸው ይበልጥ ደስተኛ አደረጋቸው። ከራሳቸው በተጨማሪ ለሌሎቹ የሥራ ዕድል በመፍጠር የተሻለ ህይወት እንዲመሩ ማድረጋቸውም እርካታን ፈጠረላቸው።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ።**

ሀ. ሰዎች የዕድር አባል ባይሆኑ ምን ይሆናሉ?

ለ. የሆቴል ሠራተኞች ሲቀጠሩ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የዕድሩ አባላት የሥራ ባለቤት እንዲሆኑ የተደረገው ለምንድን ነው?

ሐ. በንግድ ሥራ ገቢና ወጪን እንዴት ማመጣጠን ይቻላል?

መ. የአምስቱ የቤት እመቤቶች የአሁኑና የቀደመ ህይወታቸው እንዴት ሊነጻጸር ይችላል?

ሠ. በምንባቡ የታሪኩን መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ ክፍሎች የሚገልጹ ሦስት ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡-

1. ዕድር፡- በችግር ጊዜ ለመረዳዳት የሚቋቋም ማኅበር (ተቋም)
2. ገቢ፡- ሥራ በመሥራት የሚገኝ ገንዘብ/ሀብት

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ደንበኛ | መ. የገቢ ምንጭ | ሰ. ባልትና |
| ለ. ብድር | ሠ. ግብዓት | ሸ. ኢንተርፕራይዝ |
| ሐ. የሥራ ባለቤት | ረ. አቅራቢ | ቀ. ካፒታል |

#### ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ዐውድ መሠረት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ገቢ ለ. ትርፍ ሐ. ስኬት መ. ሀዘን

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

«የዕድር ጥቅም» በሚል ርዕስ መነሻ፣ መካከልና መጨረሻ ያለው ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን በተለያየ ቅርፅ መጻፍ

#### ተግባር

በምሳሌው መሠረት የራሳችሁን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ «አወቀ» የሚለውን ቃል በተለያየ ቅርጽ ጻፉ።

| ተውላጠስም | ቃላትን በተለያዩ ቅርጾች መጻፍ | | | |
|---|---|---|---|---|
| እኔ | አገዝኩ | አሳገዝኩ | ታገዝኩ | ተጋገዝኩ |
| እኛ | አገዝን | አሳገዝን | ታገዝን | ተጋገዝን |
| አንተ | አገዝክ | አሳገዝክ | ታገዝክ | ተጋገዝክ |
| አንቺ | አገዝሽ | አሳገዝሽ | ታገዝሽ | ተጋገዝሽ |
| እናንተ | አገዛችሁ | አሳገዛችሁ | ታገዛችሁ | ተጋገዛችሁ |
| እሱ | አገዘ | አሳገዘ | ታገዘ | ተጋገዘ |
| እሷ | አገዘች | አሳገዘች | ታገዘች | ተጋገዘች |
| እነሱ | አገዙ | አሳገዙ | ታገዙ | ተጋገዙ |

## 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ገቢን ማሳደግ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሚከተለውን የቅድመንባብ ጥያቄ በቃላችሁ መልሱ።

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን ያነበባችሁት ምንባብ ርዕስ ምን ነበር? መልዕክቱስ?

### ማንበብ

**ተግባር**

«ገቢን ማሳደግ» የሚለውን ምንባብ ድምፅ በማሰማት ተራበተራ አንብቡ፣ የሐረጋት አከፋፈልን ተከትላችሁ እንደየሥርዓተነጥቦቹ ባህርይ የጽሑፉን ድምጸት ጠብቃችሁ በትክክል አንብቡ።

## መናገር

### ተዘጋጅቶ ንግግር ማድረግ

#### ተግባር

በተሰማሩበት ሥራ እንዴት ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ምክንያት እያቀረባችሁ በቡድን ተወያዩ። በጋራ የተስማማችሁበትን ሀሳብ በቡድን ተወካዮቻችሁ አማካይነት በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### መጠይቃዊ ዓረፍተነገር

#### ተግባር 1

ሦስት ሐተታዊ ዓረፍተነገሮች በመጻፍ በምሳሌው መሠረት የተለያዩ መጠይቃዊ ዓረፍተነገር ጻፉ።

ምሳሌ፡-

«ዘነበች ትናንት ከገጠር ከእህቷ ጋር በፈረስ ለሥራ ፈጥና መጣች።»

ሀ. ዘነበች መጣች?

ለ. ዘነበች መቼ መጣች?

ሐ. ዘነበች እንዴት መጣች?

መ. ዘነበች በምን መጣች?

ሠ. ዘነበች ለምን መጣች?

ረ. ዘነበች ከየት መጣች?

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ሐተታዊ ዓረፍተነገሮች ወደመጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች ለውጣችሁ በደብተራችሁ ጻፏቸው።

ሀ. ሐዋና ጣይቱ እየሮጡ ወደትምህርትቤት መጡ።

ለ. እንዳልካቸውና ከድር ኳስ መጫወት ይወዳሉ።

ሐ. መንግስቱ ዛሬ ጧት ስለረፈደበት ከጓደኛው ጋር እየሮጠ ሄደ።

መ. ካሌብ አምና መኪና ለመግዛት ወደባህር ዳር ሄዶ ነበር።

ሠ. ሥራ ለስኬት እንደሚያበቃ የዕድሩ አባላት አረጋገጡ።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ተ-ጠቃሚ-ነት | ተጠቃሚነት |
| ለ | ግብአት-ኦች-ኣችን | ግብአቶቻችን |
| ሐ | መሠረት-ኧ-ልማት-ኦች | መሠረተልማቶች |
| መ | ውጤት-ኣማ-ነት | ውጤታማነት |
| ሠ | ልማድ-ኦች-ኣችን | ልማዶቻችን |
| ረ | መሥራት-ኣቸው-ን | መሥራታቸውን |
| ሰ | አካባቢ-ያቸው-ን | አካባቢያቸውን |
| ሸ | ማኅበር-ኧ-ሰብ-ኣዊ-ነት | ማኅበረሰባዊነት |

## ማንበብ

### ጠንካራ የሥራ ባህል

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ጠንካራ የሥራ ባህል» የሚለው ምንባብ ምን መልዕክት የሚያስተላልፍ ይመስላችኋል?

ለ. ሥዕሉን በመመልከት የተገነዘባችሁትን ተናገሩ።

## የማንበብ ሂደት

«ጠንካራ የሥራ ባህል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦችን ምክንያትና ውጤት ግንኙነት እያስተዋላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ። በየመካከሉ መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን ጥያቄዎች እየመለሳችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ።

### ጠንካራ የሥራ ባህል



ጠንካራ የሥራ ባህል ሰዎች ለሥራ ካላቸው አመለካከትና ፍላጎት ይመነጫል። ጠንካራ የሥራ ባህል በተሰማሩበት የሥራ መስክ ተግቶ በመሥራት ውጤታማ መሆንን ያመላክታል። ሠራተኞች ከሚፈጥሩት የሥራ ተነሳሽነትና ፍቅር አንጻር ይወሰናል። ለግለሰብ፣ ለማኅበረሰብና ለሀገር ዕድገት ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ጠንካራ የሥራ ባህል የግለሰብን የገቢ መጠን በማሳደግ ኑሮን ለማሻሻል ይጠቅማል። በተሰማሩበት የሙያ መስክ ጉልበትንና ዕውቀትን በአግባቡ በሥራ ላይ ማዋል፣ ምርታማነትን በማሳደግ ገቢን ለመጨመር ይረዳል። ገቢ ባደገ መጠንም የአኗኗር ዘይቤ ይለወጣል። የጤና፣ የትምህርት፣ የፍጆታ ግብዓቶች በማሟላት ደስተኛ ቤተሰብን ይፈጥራል። የቤተሰብ ፍላጎት ሲሟላም ቤተሰባዊ ሰላምና ደስታ ይሰፍናል። ደስተኛ መሆንም በተሰማሩበት ሙያ በራስ የመተማመን

ስሜት ያጎለብታል። ለአዲስ የፈጠራ ሥራ በመነሳሳት በየሙያው የተሻለ ሥራ ለመሥራት ያስችላል።

ጠንካራ የሥራ ባህል ማኅበራዊ ዕድገት ያመጣል። የማኅበረሰቡ አባላት በመረዳዳትና በመተጋገዝ የታቀደን ሥራ በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል። አንዳቸው ያላወቁትን ከሌሎች በመማር የሚያጋጥማቸውን ተግዳሮት በመፍታት ውጤታማ ይሆናሉ። ጉልበትንና ግብዓቶችን በጋራ ከተጠቀሙ ብዙ ጊዜ የሚወስድን ሥራ በወቅቱ ለመጨረስ ይችላሉ። በመሥራታቸው በራስ የመተማመን ስሜትን በማዳበር አካባቢያቸውን ለመለወጥና ለማሳደግ ይነሳሳሉ።

«ደቦ» የተሰኘው የሥራ ባህል ለዚህ በምሳሌነት ያገለግላል። የሥራ መሣሪያን ጉልበትንና ጊዜን በጋራ በመጠቀም ብዙ ቀን ይፈጅና ያደክም የነበረን ሥራ በአጭር ጊዜ ለመጨረስ ያስችላል፤ ማኅበረሰባዊ ግንኙነትን በማጠናከር ተባብሮና ተጋግዞ የመሥራት ልምድን ያዳብራል። ጠንካራ የሥራ ባህል የሀገር ዕድገትን በማፋጠን ማኅበራዊ ዕድገትን ያመጣል። ዜጎች በምጣኔሀብታቸው እያደጉ በሄዱ ቁጥር የሀገሪቱ ልዩ ልዩ ገቢዎች ይጨምራሉ። ከሕዝብ የሚገኝ ገቢም አዳዲስ መሠረተልማቶች ለምሳሌ ትምህርትቤቶች፣ ዋና ዋና መንገዶችና የውስጥ ለውስጥ የኮብልስቶን መንገድ፣ የጤና ተቋሞች ወዘተ ለመስራት ያስችላል። ለሥራ ፈላጊዎችም አዳዲስ የሥራ ዕድል ይፈጥራል። ይህም በራሱ የሥራ ባህልን እያዳበረ ይሄዳል። እንደዚህ ባለው ግንኙነት ኑሮ እየተሻሻለ ይሄዳል።

**ጠንካራ የሥራ ባህል የሀገር ዕድገትን በማፋጠን ማኅበራዊ ዕድገትን ያመጣል።**

በአጠቃላይ ጠንካራ የሥራ ባህል የግለሰብን ብሎም የማኅበረሰቡን የገቢ መጠን ያሳድጋል፤ ህይወትን በአግባቡ ለመምራትና የቤተሰብን ፍላጎት ለማሟላት ያስችላል። የግለሰብ ለውጥና ዕድገት የቤተሰብን ብሎም የማኅበረሰብ ዕድገት ያመጣል። በዚህም የሀገር ምጣኔሀብት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ ስለሚሄድ መሻሻል ይታያል። የሀገር ምጣኔሀብት ዕድገት ደግሞ የዜጎችን ኑሮ ይለውጣል፤ መሠረተልማቶችን ያስፋፋል፤ ዜጎችን የትምህርት፣ የጤናና የመሳሰሉት ማኅበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ያደርጋል።

ጠንካራ የሥራ ባህልን በማዳበር በአስተሳሰባቸውና በዕውቀታቸው የበሰሉ፣ ከአልባሌ ነገሮች የጸዱና የመልካም ሥነምግባር ባለቤት የሆኑ ጤናማና የተማሩ ዜጎች ማፍራት ይቻላል። ስለዚህ ጠንካራ የሥራ ባህልን በማጠናከርና በማስፋፋት የማኅበረሰቡን ተጠቃሚነት ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

(በደ/ብ/መ/ሙ/ማ/ኮሌጅ ማኅበራዊ ሳይንስ ት/ክፍል። *ለሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ለመለያ 212 ኮርስ ማስተማሪያነት የተዘጋጀ፣ ዓመተምሕረት የሌለው፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።*)


## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «ጠንካራ የሥራ ባህል» ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. «ጠንካራ የሥራ ባህል ጠቀሜታዎች» በሚለው ጥቅል ሀሳብ መነሻነት ምንባቡን መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ያለውን የቢጋር ክብ አሟሉ።




ሐ. በሰውና በሥራ መካከል ያለውን ተጠየቃዊ ግንኙነት ግለጹ።

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዓውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

1. ለሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡- ህይወት ⟶ ኑሮ

ሀ. ደቦ | ሐ. አልባሌ | ሠ. ተነሳሽነት
ለ. ፍጆታ | መ. መረዳዳት | ረ. የአኗኗር ዘይቤ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ደቦ | ሐ. አልባሌ | ሠ. ተነሳሽነት |
| ለ. ፍጆታ | መ. መረዳዳት | ረ. የአኗኗር ዘይቤ |

2. ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ዐውድ መሠረት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ልማት | መ. መሻሻል | ሰ. ጠንካራ |
| ለ. ሰላም | ሠ. ማኅበራዊ | ሸ. ማፋጠን |
| ሐ. ማሟላት | ረ. ተጠቃሚ | |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት መጻፍ

**ተግባር**

«የሥራ ጠቀሜታ» በሚል ርዕስ በምክንያትና ውጤት ስልት ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ሦስት አንቀጽ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አዳምጦ መጻፍ

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት አዳምጣችሁ በትክክል ጻፉ።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ጠንካራ የሥራ ባህል

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ3ኛው ሣምንት፣ በ7ኛው ቀን «ጠንካራ የሥራ ባህል» በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ አንብባችኋል፡-

ሀ. ምንባቡን ለመረዳት የተጠቀማችሁባቸው ብልሀቶች ምን ምን ናቸው?

ለ. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

## ማንበብ

### ተግባር

«ጠንካራ የሥራ ባህል» የሚለውን ምንባብ ሥርዓተነጥቦችን ጠብቃችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ በፍጥነት አንብቡ።

## መናገር

### በተሰጠ ርዕስ ንግግር ማድረግ

### ተግባር

ስለጠንካራ የሥራ ባህል ጠቀሜታ በቡድን ተወያይታችሁ የተስማማችሁባቸውን ነጥቦች በተወካዮቻችሁ አማካይነት በንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ዓረፍተነገሮችን በዓይነት መመደብ

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች አዎንታዊ፣ አሉታዊ ወይም መጠይቃዊ መሆናቸውን ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

ሀ. ጠንካራ የሥራ ባህል ማኅበራዊ ዕድገት ያመጣል።

ለ. በጥገኝነት መኖር አያዋጣም።

ሐ. ደቦ ለምን ይጠቅማል?

መ. የመሠረታዊ ልማቶች መስፋፋት የሥራ ዕድል ይፈጥራል።

ሠ. ሠዎች ካልሠሩ ምን ይሆናሉ?

ረ. በራስ ተነሳሽነት ሥራ መሥራት ምርታማነትን ያዳብራል።

ሰ. የመጀመሪያውን ምዕራፍ አንብበን አልጨረስንም።

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት በ2ኛ መደብና በ3ኛ መደብ በብዙ ቁጥር ቅርጻቸውን እየለዋወጣችሁ በትክክል ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ከፈተ | ሐ. ወሰነ | ሠ. ጀመረ |
| ለ. አሰበ | መ. አጋጠመ | ረ. አደገ |



# ምዕራፍ 2

ቅርስ

ድንቅነሽ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| ቅሪተ-አካል-ኦች | ቅሪተአካሎች |
| ጥንት-አዊ-ነት-ኡ-ኣ | ጥንታዊነቷ |
| ይገነዘብ-ኡ-ብ-ኣት-ኣል | ይገነዘቡባታል |
| ጥንት-ኧ-አመጣጥ-ኣቸው-ን | ጥንተአመጣጣቸውን |
| መስህብ-ነት-ኡ-ኣ | መስህብነቷ |
| ሀላፊ-ነት-ኣችን-ን | ሀላፊነታችንን |
| ይጠበቅ-ብ-ን-ኣል | ይጠበቅብናል |
| አውስትራ-ሎ-ፒቲከስ አፋሬንሲስ | አውስትራሎፒቲከስ አፋሬንሲስ |
| ክፍል-ኦች-ኡ-ኣ-ን | ክፍሎቿን |
| ብሄር-ኣዊ-ነት-ኡ | ብሄራዊነቱ |
| አድናቆት-ኡ-ኣ-ን | አድናቆቷን |

# ማንበብ

## ድንቅነሽ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ድንቅነሽ» የሚል ቃል ታውቃላችሁ? «ድንቅነሽ» ምን ማለት ይመስላችኋል? የቃሉን ፍቺ ከተረዳችሁ «ድንቅነሽ» ከሚለው ርዕስና ከሥዕላዊ መግለጫው ተነስታችሁ ፅሑፉ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ተናገሩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቅርስ | ቅሪተአካል | ቁፋሮ | ጥንታዊ |

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ «ድንቅነሽ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁን እየተከተላችሁ ድምፅ በማሰማት በትክክል አንብቡ።

## ድንቅነሽ



ሉሲ በጥንታዊነቷ በዓለም ተወዳዳሪ የሌላት አስደናቂ ኢትዮጵያዊ የሰው ቅሪተአካል ናት። ጥንታዊ ያሰኛትም ከዚህ በፊት በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ በተለያዩ ጊዜያት ከተገኙት ቅሪተአካሎች ረጅም ዕድሜ በማስቆጠሯ ነው። የሉሲ ዕድሜ ከ3.2 ሚሊዮን ዓመታት በላይ እንደሆነ ሳይንሳዊ ምርምሮች አረጋግጠዋል።

ሉሲ የተገኘችው በኢትዮጵያ ሰምጥሸለቆ አፋር ክልል «ሀዳር» በሚባለው በረሃማ አካባቢ ነው። አገኛኘቷም የአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን ሂደታዊ ነበር። የተመራማሪ ቡድኑ እ.አ.አ. ከ1972-1974 በቦታው ቁፋሮ በማካሄድ የተለያዩ የአጥንት ክፍሎቿን በማሰባሰብ የአሁኗን ሉሲ ለማግኘት ችሏል።

የሉሲ ስያሜ ምክንያታዊ ነበር። የተመራማሪ ቡድኑ ረጅም ጊዜ ከወሰደው አድካሚ ቁፋሮ በኋላ ዋናውን የቅሪተአካሏን ክፍል ባገኘበት ወቅት ያዳምጠው በነበረው ዘፈን ውስጥ «ሉሲ» የሚል ቃል

በተደጋጋሚ ይሰማ ነበር። ከዚህ በመነሳት ደስታውን ለመግለፅ «ሉሲ» የሚል ስያሜ ሰጥቷታል። የስያሜው ትርጉምም በሰማይ ላይ ያለች ዕንቁ ማለት ነው። የሉሲ መገኘት ለኢትዮጵያውያንም ልዩ ደስታን ስለፈጠረ በሀገርኛው የደስታ መግለጫ ባህል መሠረት «ድንቅነሽ» የሚለውን ኢትዮጵያዊ መጠሪያ አግኝታለች። ሳይንሳዊ መጠሪያዋ ግን አውስትራሎፒቲክስ አፋረንሲስ ይባላል። ድንቅነሽ በሴት ጾታ የመጠራቷ ምክንያትም በቁፋሮው መጨረሻ ወቅት ከቅሪተአካሉ 40% ውስጥ የሴት ቅርፅንና አቀማመጥን የሚያሳየው የዳሌዋ ክፍል ስለተገኘ ነው።

ድንቅነሽ አብዛኛው የአካል ክፍሏ ተሟልቶ የተገኘች ቅሪተአካል ናት። በተመራማሪ ቡድኑ ግምት መሠረት ድንቅነሽ በህይወት እያለች ቁመቷ 1.1 ሜትር፣ ክብደቷ 29ኪ.ግ ሲሆን፣ ትላልቅ ጥርሶች፣ ጠጣ መሰል ፊትና ትንሽ የአንጎል መጠን ነበራት።

ድንቅነሽ የሰው ዘር መነሻ መሆኗን ያረጋገጠች ኢትዮጵያዊ የተፈጥሮ ቅርስ ናት። የሰውን ልጅ ጥንተአመጣጥ የምትተርክ በመሆኗ ዓለማቀፋዊ ቅርስ ናት ለማለት ይቻላል። ድንቅነሽን ለመጎብኘት የማይጓጓ ሕዝብ የለም። ለምሳሌ በኢትዮጵያና በአሜሪካ መንግስት መካከል በተደረገ ስምምነት ድንቅነሽ አሜሪካ ድረስ በመሄድም በበርካታ አሜሪካውያን ተጎብኝታለች። በዚህም ኢትዮጵያ የሰው ዘር መነሻ ሀገር መሆኗን ለዓለም ሕዝብ አስተዋውቃ ወደሀገሯ ተመልሳለች።

በሀገር ውሰጥም በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ብሔራዊ ሙዚየም ድንቅነሽን ለመጎብኘት የሚጎርፈው የሀገር ውስጥና የውጪ ሃገር ጎብኚ ቁጥር በርካታ ነው። ሁሉም ጎብኚዎች ለድንቅነሽ ያላቸው አድናቆት ተመሳሳይ ነው ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም ጥንተአመጣጣቸውን ይረዱባታል፤ ስለሰው ልጅ አዝጋሚ ለውጥ ይገነዘቡባታል።

በአጠቃላይ ድንቅነሽ በመስህብነቷ ተተኪ የሌላት ቅርስ ናት። ስለዚህም ቅርሷን ተንከባክቦና ጠብቆ ከትውልድ ወደትውልድ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። ለዚህም ኢትዮጵያውያን በሙሉ የዜግነት ሀፊነታችንን መወጣት ይጠበቅብናል።

(ኤልሳ ጆብሰን። መስከረም 2013። ከአፍሪካን ሪፖርት ድረገጽ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት <u>ምክንያት</u> እየሰጣችሁ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ድንቅነሽ» ስያሜዋን ያገኘችው ከአካባቢው ኗሪዎች ነው።

ለ. ሀዳር የድንቅነሽ ሌላ ስም ነው።


ሐ. የሰዎችን ጾታ በዳሌያቸው ስፋት ማወቅ ይቻላል።

መ. ድንቅነሽ ለሀገር ዕድገት አስተዋፅኦ ታደርጋለች።

ሠ. ድንቅነሽ በሰዎች ተፈልጋ የተገኘች ሰውሠራሽ ቅርስ ናት።

## ተግባር 2

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ ምንባቡን መሠረት በማድረግ በትክክል አሟሉ።




## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

## ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ድንቅ (አንቀጽ 3)

ለ. ግኝት (አንቀጽ 3)

ሐ. ዓለማቀፍ (አንቀጽ 5)

መ. መተረክ (አንቀጽ 5)

## ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላት/ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተመልሳለች (አንቀጽ 5)

ለ. ረጅም ዕድሜ (አንቀጽ 1)

ሐ. ተፈጥሯዊ (አንቀጽ 5)

መ. መነሻ (አንቀጽ 5)

ሠ. ተገኘ (አንቀጽ 3)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ጽሑፍን አሳጥሮ መጻፍ

**ተግባር**

ሀ. «ድንቅነሽ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ሦስተኛውንና አራተኛውን አንቀጽ የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም አሳጥራችሁ ጻፉ።

ለ. «ድንቅነሽ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አምስተኛውንና ስድስተኛውን አንቀጾች በአራት ዓረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን በትክክል መጻፍ

**ተግባር 1**

ቀጥሎ ባለው ዓረፍተነገር ውስጥ ፊደል የሚደጋገሙ ቃላትን ለይታችሁ ጻፉ።

- «ንግግር በምናደርግበት ጊዜ የገፀባህርያት ምልልስ ካለ ድግግሞሽ እንዳይበዛ በጥንቃቄ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።»

**ተግባር 2**

በሚከተሉት ፊደል ደጋሚ ቃላት «-አሽ» የሚል ቅጥያ በመድረሻቸው ላይ በመጨመር አዲስ ቃል መሥርታችሁ ጻፉ።

| ምልልስ | ቅልልም | ክትትል | ልውውጥ | ድብብቅ |
|---|---|---|---|---|

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ድንቅነሽ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን «ድንቅነሽ» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሷቸውን ሀሳቦች ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

ጥንድ ጥንድ በመሆን አንዱ/ዷ ሲያነብ/ስታነብ ሌላው/ዋ ደቂቃ በመያዝ «ድንቅነሽ» የሚለውን ምንባብ ድምፅ በማሰማት አንብቡ። አንዱ/ዷ ሲያነብ/ስታነብ ሌላው/ዋ ሐረግ አከፋፈልና ሥርዓተነጥብ ተጠብቆ መነበቡን ይከታተል /ትከታተል።

## ማዳመጥ

## ታላቁ የአንዋር መስጊድ

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ሀይማኖታዊ ሥርዓቶችን የሚያካሂዱበት ቦታ ምን ይባላል?

ለ. በአንዋር መስጊድና በወሌ መሀመድ መስጊድ መካከል ያለውን ልዩነት ተናገሩ?

ሐ. ጥንታዊ የሆኑ ቅርሶችን እንዴት መንከባከብ የሚቻል ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

«ታላቁ የአንዋር መስጊድ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በቅድመንባብ ጥያቄዎች የሰጣችኋቸውን መልሶች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እየሞከራችሁ አዳምጡ።

### አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ታላቁ አንዋር መስጊድ በአዲስ አበባ በየትኛው የገበያ ማዕከል ይገኛል?

ለ. ታላቁ አንዋር መስጊድ መቼ ተመሠረተ?

ሐ. በመርካቶ ገበያ የሚገበያዩበት እነማን ናቸው?

መ. ታላቁ አንዋር መስጊድ አርብ አርብ ሞቅ ደመቅ የምትለው ለምንድነው?

ሠ. ታላቁ አንዋር መስጊድ ከተመሠረተ ስንት አመታትን አስቆጠረ?

ረ. ታላቁ አንዋር መስጊድ የተሠራባቸውን ዋናዋና ቁሳቁሶች ጥቀሱ።

## ሰዋስው

### ተውሳከግስና ጠቋሚ መስተዓምር

**ተግባር 1**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ተውሳከግስና ጠቋሚ መስተዓምር የሆኑትን ለይታችሁ አውጡ፤ ለመልሳችሁም ምክንያት ስጡ።

ሀ. ያቺ ጠይም ልጅ በትምህርቷ ጎበዝ ናት።

ለ. ሠራተኛው ከጣራው ላይ ክፉኛ ወደቀ።

ሐ. አምና የገዛኋት ላም ነጭ ጥጃ ወለደች።

መ. እነዚያን ተማሪዎች ጥራልኝ።

ሠ. ይህ ነገር ጥሩ አይመስለኝም።

ረ. ገንዘብ ካገኘሁ ያንን መጽሐፍ እገዛዋለሁ።

**ተግባር 2**

ጠቋሚ መስተዓምርና ተውሳከግስ ያላቸው አምስት ዓረፍተነገሮች በደብተራችሁ ጻፉ።

## ማንበብ

### ቅርሶች

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስለቅርስ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቁትን ተናገሩ።

ለ. ስንት ዓይነት ቅርሶች አሉ?

ሐ. ቅርስ ለአንድ ሀገር ዕድገት ምን ጥቅም አለው ብላችሁ ታስባላችሁ?

መ. በምንባቡ ያሉትን ሥዕሎች ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምታችሁ ተናገሩ።


### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

ቀጥሎ «ቅርሶች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የአንቀጾቹን ዋናዋና ሀሳቦች እያጠቃለላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

### ቅርሶች


ቅርሶች ሰዎች በግልም ሆነ በጋራ ባሳለፏቸው የታሪክ ወቅቶች ያካባቷቸው ህዝባዊ ሀብቶች ናቸው። ቅርሶች፣ ሰዎች በቅድመታሪክና በታሪክ ዘመን ያሳዩትን የዕድገት ደረጃ ይገልፃሉ። ስለሆነም ታሪክ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ከትውልድ ወደትውልድ ከሚተላለፉባቸው መንገዶች ቅርሶች ተጠቃሾች ናቸው። ቅርሶች ሰውሠራሽና ተፈጥሯዊ በመባል በሁለት ይከፈላሉ።




ሰውሠራሽ ቅርሶች የየዘመኑ ሰዎች የፈጠራ ጥበብ ያረፈባቸው ሀውልቶችን፣ ውቅር አብያተክርስቲያናትን፣ በነገሥታት የታነጹ ግንቦችን ያካትታሉ። እነዚህ ቅርሶች የየዘመኑ ሥልጣኔና ጥበብ ጥልቀትንና የደረሰበትን ደረጃ ያሳያሉ። በኢትዮጵያ ከሚታወቁት ሰውሠራሽ ቅርሶች መካከል የአክሱም ሐውልቶች፣ የላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት፣ የፋሲል ግንብና የጀጎል ግንብ ይጠቀሳሉ።

የአክሱም ሐውልቶች በትግራይ ክልል በአክሱም ከተማ ይገኛሉ። ሐውልቶቹም የተሠሩት ከ200 ዓመተ ዓለም እስከ 700 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የአክሱም ሐውልቶች በጥበባቸው በዚያን ዘመን ከተቀረጹት ሐውልቶች ሁሉ የላቁና ወደር ያልተገኘላቸው ናቸው።

በአማራ ክልል የሚገኙት የላሊበላና የፋሲል ቤተመንግሥት በኢትዮጵያ ከሚጠቀሱ አስደናቂ ቅርሶች መካከል ናቸው።



የላሊበላ አብያተክርስቲያናት የታነጹት በ12ኛው መቶ ክፍለዘመን መጀመሪያ በንጉሥ ላሊበላ ሲሆን ብዙዎቹ አብያተክርስቲያናት ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍለው የተሠሩ ናቸው። ውቅር አብያተክርስቲያናቱ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት በዓለም ቅርስነት ተመዝግበዋል።




የፋሲል ቤተመንግሥት ደግሞ ሌላኛው ሰውሠራሽ የኢትዮጵያ ቅርስ ነው። የፋሲል ቤተመንግሥት የታነፀው በ17ኛውና በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩት ነገሥታት ነው። የፋሲል ቤተመንግሥት ግቢ ስፋት 70,000 ካሬ ሜትር ሲሆን በውስጡም በዚያን ዘመን የነበሩ የስድስቱ ነገሥታት ቤተመንግሥቶችና በርካታ የህንጻ ፍርሥራሾች ይገኛሉ። ግቢው ቀደም ሲል 12 በሮች ነበሩት። እነሱም እንኮዬ በር፣ ዕቃ ግምጃ ቤት በር፣ ፊት በር (ጃን ተከል በር)፣ ወንበር በር፣ ተስካር በር፣ አዛዥ ጥቁሬ በር፣ አደናግር በር፣ ኳሊ በር፣ እምቢልታ በር፣ ፈረስ ባልደራስ በር፣ እርግብ በር፣ ቀጭን አሸዋ በር ይባላሉ። በአሁኑ ጊዜ ግን አገልግሎት የሚሰጡት በጣሊያን ጊዜ የተሠሩት ሁለት በሮች ናቸው።

ሌላው ሰውሠራሽ ቅርስ የሐረር ጀጎል ግንብ ሲሆን የሚገኘውም በሐረሪ ክልል ነው። ግንቡ የታነፀው ከ1551-1552 በታላቁ አሚር ኑረቢን ሙጃሂድ ነው።



ግንቡ ያረፈው በ48 ሄክታር ላይ ሲሆን 3334 ሜትር ርዝመትና 3.66 ሜትር ከፍታ አለው። አምስት መግቢያና መውጫ በሮች አሉት። በውስጡ ከ359 በላይ ጠባብ መንገዶች ሲኖሩት መንገዶቹ ርስበርሳቸው የሚገናኙና ጥልቅ ጥበብን የተላበሱ ናቸው።

ተፈጥሯዊ ከሆኑት የኢትዮጵያ ቅርሶች አንዱ ኤርታኤሌ ነው። ኤርታኤሌ በረሃማ በሆነው የአፋር ክልል የሚገኝ ተፈጥሯዊ እሳተገሞራ ነው። እሳተገሞራው የተለያዩ ተፈጥሯዊ ህብረቀለማትን በመፍጠር ለአካባቢው ልዩ ውበት ያጎናፅፋል። በተለይም በጨለማ ወቅት እንደንጋት ወጋገን በሩቅ ሲታይ ልዩ ስሜት ይፈጥራል። የፍንዳታው ነጎድጓዳዊ ድምፅና እንደርችት ወደላይ የሚወረወረው ፍንጥቅጣቂ አካባቢውን በህብረቀለም ሲያስጌጠው ልዩ ደስታ ይፈጥራል። ይህም ተፈጥሮን አስገራሚና አስደናቂ ያደርጋታል።



ሌላው የተፈጥሮ ቅርስ ደግሞ ሶፍኡመር ዋሻ ነው። ዋሻው በደቡብ ኢትዮጵያ በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን ይገኛል። በኢትዮጵያ ካሉት ዋሻዎች ሁሉ ረጅሙ ሲሆን፣ 15 ኪሎ ሜትር ርዝማኔና ከ42 በላይ የመግቢያ በሮች አሉት። የበሮቹ መኖር ዋሻውን አስገራሚና አስደናቂ የተፈጥሮ ክስተት ማሳያ እንዲሆን አድርገውታል።

በአጠቃላይ ሁሉም የኢትዮጵያ ሰውሠራሽና ተፈጥሯዊ ቅርሶች የኢትዮጵያን የታሪክ፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የሥልጣኔ ሂደት በግልፅ የሚያሳዩ ሀብቶች ናቸው። ስለሆነም ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል።

(አብክመ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ። 1991። *የአማራ ክልል የቱሪስት መስህቦች (አጭር ቅኝት)*፣ ገጽ 81-85 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በተፈጥሯዊና በሰውሠራሽ ቅርሶች መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።

ለ. ቅርሶች ባህልን፣ ወግን፣ እምነትን ከትውልድ ወደትውልድ ያስተላልፋሉ ሲባል ምን ማለት ነው?

ሐ. ከክርስቶስ ልደት በፊት ተጀምሮ ከክርስቶስ ልደት በኋላ የተጠናቀቀ የኢትዮጵያ ሰውሠራሽ ቅርስ ማን ይባላል?

መ. ስለኤርታኤሌ በሚገልጸው አንቀጽ ውስጥ «የፍንዳታው ነጎድጓዳዊ ድምፅ» በሚለው ሐረግ የተገለፀውን ከምታውቁት ድምፅ ጋር በማወዳደር ምክንያታችሁን ስጡ።

ሠ. በምንባቡ መሠረት በተፈጥሮ ቅርስነት የተጠቀሰውን ዋሻ አስደናቂ ያደረጉት ባህርያት ምን ምን ናቸው?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን መመደብና ፍቺ መስጠት

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት የቢ.ጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም ሰውሠራሽና የተፈጥሮ ቅርስ በማለት በሁለት ምድብ መድቧቸው።

ሀ. አክሱም ሐውልት

ለ. ላሊበላ

ሐ. ውቅር አብያተክርስቲያናት

መ. ፋሲል ግንብ

ሠ. ኤርታኤሌ

ረ. ሶፍኡመር

**ተግባር 2**

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ፍቺ ስጡ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ጥልቀት | መ. ፍርስራሽ | ሰ. ክስተት |
| ለ. የታነፁ | ሠ. የላቀ | ሸ. ተፈልፍለው |
| ሐ ጥበብ | ረ. ንጋት | ቀ. ህብረቀለማት |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ምንባብን አሳጥሮ መጻፍ

**ተግባር 1**

«ቅርሶች» በሚለው ምንባብ ውስጥ ሁለተኛውን አንቀጽ በጥልቀት አንብባችሁ የሚከተለውን የቢ.ጋር ሠንጠረዥ በትክክል አሟሉ።




## ተግባር 2

«ቅርሶች» የሚለውን ምንባብ ሀሳብ በሦስት አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትና ቅጥያዎችን አጣምሮ መጻፍ

## ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት ከቅጥያዎች ጋር አጣምራችሁ ጻፉ።

| ዋና ቃል | መድረሻ ቅጥያ | የተጣመረው ቃል |
|---|---|---|
| ትክክል | -ኧኛ | ትክክለኛ |
| በር | -ኧኛ | |
| እግር | -ኧኛ | |
| ወንጀል | -ኧኛ | |
| ግንብ | -ኧኛ | |

## 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ቅርሶች

#### ቅድመንባብ

## ተግባር

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን «ቅርሶች» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሷቸውን ዋናዋና ሀሳቦች ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

ሀ. «ቅርሶች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪያውን አንቀጽ የሐረግ አከፋፈል ጠብቃችሁ ድምፅ በማሰማት መምህራችሁን እየተከተላችሁ አንብቡ።

ለ. «ቅርሶች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ፣ የሐረግ አከፋፈሎችንና ሥርዓተነጥቦችን ተከትላችሁ ተራበተራ አንብቡ።

## መናገር

### አንቀጽ ገምግሞ ንግግር ማድረግ

### ተግባር

«ቅርሶች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ቅርሶች በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት ብቻ ናቸው? ሌላ ካለ በዝርዝር ተናገሩ።

ለ. በቡድን በቡድን ሆናችሁ በመወያየት በምንባቡ ያልተጠቀሱ ሌሎች የምታውቋቸው ተፈጥሯዊ ቅርሶች ካሉ በተወካያችሁ አማካይነት በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

ሐ. «ታሪክ፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ከትውልድ ወደትውልድ ከሚተላለፉባቸው መንገዶች ቅርሶች ተጠቃሾች ናቸው» የሚለውን ዓረፍተነገር በሌላ አባባል በቃላችሁ ተናገሩ።

መ. በየቡድናችሁ በመሆን የጽሑፉን ሁለተኛ አንቀጽ ገምግማችሁ የግምገማ ውጤቱን በቃላችሁ ተናገሩ።

## ሰዋስው

### መስተፃምር፣ መስተዓምርና ተውሳከ ግስ

#### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ወደረኛ መስተፃምሮች በምሳሌው መሠረት አውጥታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- «አለሚቱ ከሥራ መጣችና ምግቧን አዘጋጀች።» በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ «ና» አያያዥ መስተጻምር ናት።

ሀ. አንተ ወይም እሷ ጥያቄውን መመለስ ትችላላችሁ።

ለ. ምሳህን ብላና ትንሽ አረፍ በል።

ሐ. አስቴርና መሐመድ የቤትሥራቸውን ቀድመው ጨርሰዋል።

መ. ደብተር ወይም እስክርቢቶ ገዝተህ ና።

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት መስተፃምር፣ ተውሳከግስና መስተዓምር በማለት በሦስት መድቧቸው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዛሬ | እነዚህ | እንጂ | ና |
| ግን | ግምኛ | ሆኖም | ቶሎ |
| ማታማታ | ያች | ያ | ስለዚህ |

#### ተግባር 3

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ተውሳከግሶችንና መስተዓምሮችን ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።

ሀ. ምንባቡን እንደገና በጋራ አንብቡ።

ለ. ያቺ ልጅ በጣም ጎበዝ ናት።

ሐ. ሰውየው ክፉኛ ወደቀ።

መ. እነዚያን መጽሐፎች አመጣኻቸው?

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| አስ-ጎብኝ-ኣችን | አስጎብኛችን |
| አገልግሎት-ኣቸው-ን | አገልግሎታቸውን |
| ማዕዘን-ኣት | ማዕዘናት |
| ነበር-ኡ-ኣቸው | ነበሯቸው |
| አብያተ-ክርስቲያን-ኣት | አብያተክርስቲያናት |

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት አጣምራችሁና ነጥላችሁ አንብቡ።

| አጣምሮ ማንበብ | ነጣጥሎ ማንበብ |
|---|---|
| አስደናቂዎቹ | አስደናቂ-ዎች-ኡ |
| እንድንጎበኝ | እንድ-ን-ጎበኝ |
| እንደተገነዘብነው | እንደ-ተገነዘብነው |
| ሁለተኛውን | ሁለት-ኧኛ-ው-ን |

## ማንበብ

### አስደናቂዎቹ ቅርሶች

#### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የምንባቡን ርዕስና «አገርህን እወቅ፣ የእንጦጦ ተራራ፣ መጎብኘት፣ ማድነቅ» የሚሉትን ቃላትና ሐረጋት መነሻ በማድረግ የምንባቡ ሀሳብ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«አስደናቂዎቹ ቅርሶች» የሚለውን ምንባብ በእያንዳንዱ አንቀጽ መጨረሻ ቆም እያላችሁ የአንቀጹን መልዕክት በአዕምሯችሁ እያጠቃለላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ።

## አስደናቂዎቹ ቅርሶች

ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ከባህር ጠለል በላይ 3200 ሜትር ከፍታ ላይ እንገኛለን። ዳግማዊ ምኒልክ ከአንኮበር ወደ እንጦጦ ቤተ መንግስታቸውን ሲያዘዋውሩ ያለምክንያት አልነበረም። ስፍራው ለዘመቻም፣ለአስተዳደርም ምቹ ነው። እንጦጦ ጥቅጥቅ ባለ ባህር ዛፍ የተሸፈነ ነው። ለዚህ ይመስላል ሰዎች በተለይም የውጪ ፀሀፍት የአዲስ አበባ ሳንባ ያሉት። ደኑ ትንፋሹን (ኦክሲጅኑን) ቁልቁል ወደ ውቧ ሸገር እፍ ይልባታል። እናም በዚህ አይነት የከተማችን ንፁህ አየር ምንጭ እንጦጦ ነው ቢባል ሀሰት አይሆንም። ታዲያ እንጦጦ ሳንባ ቢባል ያንስበታል እንጂ ይበዛበታል? ይላሉ። እንጦጦ ጫካ ምንጭነቱ ለንፁህ አየር ብቻም አይደለም። ለከተማችን ዋነኛ የማገዶ መገኛ ስፍራም ነው።



እንጦጦ አናት ላይ ሆነው አዲስ አበባን የዝቅዝቅ ሲመለከቷት ውበቷና ግርማ ሞገሷ ይበልጥ ይደምቃል። እቴጌ ጣይቱ ከእንጦጦ ወደ ሸገር መውረዳቸውና እዚህም ምኒልክ መናገሻቸውን እንዲቆረቁሩ ማድረጋቸው ትክክል ነው ያስብላል። ጎብኚዎች የእንጦጦን ተራራ ለመውጣት አቀበቱን ሲያያዙት በመጀመሪያ ሽሮ ሜዳን ያገኛሉ። ይህ ደግሞ የሞቀ የባህል አልባሳት የደራ ገበያ ስፍራ ነው።

እንጦጦን ለመውጣት ጉዞ የጀመረ ጎብኚ ይህን ስፍራ መርገጡ የግድ ነው። አዲስ አበባ የመጣ ጎብኚ የሽሮ ሜዳን ገቢያና የእንጦጦ ተራራን ሳይጎበኝ ወደ መጣበት መመለስ አይታሠብም።

እንጦጦ አናት ላይ ከወጡ በአየሩ ይማረካሉ፤ ነፋሻ ነው። ደኑ አይን ይስባል። የአዕዋፍ ድምፅ ይመስጣል። ሁከትና ግርግር የሌለበት ሰላማዊ ስፍራ ነው። ይህ ስፍራ በውድድር ሜዳ የአገራቸውን ስም የሚያስጠሩ የብርቅዬ አትሌቶቻችን የስልጠና ስፍራም ጭምር ነው። ይህን ያጋጠመው ጎብኚ ከእነርሱ ጋርም የመገናኘት እድል ይገጥመዋል።

እንጦጦ አዲስ አበባን ከዳር እስከ ዳር ፍንትው አድርጎ ያሳያታል። እንጦጦ ላይ ከተገኙ ከዚህም ሌላ ታሪካዊቷን የእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ገዳም ጎብኝተው ይመለሳሉ። በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ያለውን ታሪካዊ ሙዚየም ጎብኝተው፣ የዳግማዊ ሚኒልክንና የእቴጌ ጣይቱን ታሪክ አውቀው ይመለሳሉ። ወደ ሽገር ሲንደረደሩ ደግሞ ኑሮን ለማሸነፍ ደፋ ቀና የሚሉና በጀርባቸው የባህር ዛፍ ቅጠላቅጠል እና ቅርንጫፍ የተሸከሙ ከኑሮ ጋር ግብግብ የገጠሙ ሴቶችን ያገኛሉ። ይህ ስፍራ አዲስ አበባን በሚረግጡ ቱሪስቶች በከፍተኛ ደረጃ የሚጎበኝ ስፍራ መሆኑን ጥናቶች ያመለክታሉ።

ጎብኚዎች እንጦጦ ሲደርሱ የአዲስ አበባን ጓዳ ጎድጓዳ ማየት ይችላሉ። የዳግማዊ ምኒልክን ቤተ መንግስትም የመጎብኘት እድል ያገኛሉ። በጉብኝቱም ወቅት አፄ  ምኒልክ በህይወት ዘመናቸው ሲገለገሉባቸው የነበሩ ካባ፣ ጫማ፣ አልጋ፣ አልባሳት፣ የተለያዩ የብራና ጽሁፎች ወዘተ. ይገኛሉ፤ በዚህም ከኢትዮጵያ ሰፊ ታሪክ በጥቂቱም ቢሆን ያውቃሉ። የምኒሊክ ቤተመንግስት ብዙም ሰፊ የሚባል አይደለም ሆኖም ግን በአበቦች ያማረና የደመቀ ነው።  ሙዚየሙም ጥሩና የአገሪቱን ታሪክ የሚያሳይ ነው። እንጦጦ ላይ የሚደረገው ሽርሽር በጣም አስደሳች ነው። በአካባቢው ያሉ ሰዎችን መመልከት በእጅጉ አስደሳች ነው። ተራራውን ለመውጣት 45 ደቂቃ ያህል ይወስዳል።

(የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። 2007።
ባህል ቱሪዝም። ገፅ 32-33 መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የእንጦጦ ተራራ ከአዲስ አበባ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ከባህር ወለል በላይ በስንት ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል?

ለ. እንጦጦ ታሪካዊ ቦታ ነው የተባለው ለምንድን ነው?

ሐ. ለአዲስ አበባ ከተማ ንፁህ አየር ምንጭ ነው የተባለው ማነው?

መ. ከእንጦጦ ተራራ ላይ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች እነማን ናቸው?

ሠ. ኑሯቸውን ለማሸነፍ ደፋ ቀና የሚሉት ሴቶች ምን ሲያደርጉ ይስተዋላሉ?

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ከቅርስ ጋር የተያያዙ ቃላትን ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. በኢትዮጵያ በርካታ የመስህብ ቦታዎች በዓለማቀፍ ቅርስነት ተመዝግበዋል።

ለ. የአክሱም ሐውልት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው።

ሐ. ድንቅነሽ በዓለም ረጅም ዕድሜ ያላት ቅሪተአካል ናት።

መ. እንጦጦ ከሚታወቅባቸው አንዱ ጥቅጥቅ ባለደን መሸፈኑ ነው።

ሠ. እሳተገሞራ ካስፈሪነቱ ባሻገር የቱሪስት መስህብ መሆኑን ለማረጋገጥ ኤርታኤሌን መጎብኘት ይበቃል።

### ተግባር 2

በቡድን በመወያየት የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ጻፉ።

ሀ. ምንጭ (አንቀጽ 1)

ለ. ማገዶ (አንቀጽ 1)

ሐ. ይስባል (አንቀጽ 3)

መ. ጓዳ ጎድጓዳ (አንቀጽ 5)

ሠ. አቀበት (አንቀጽ 2)

ሰ. ብርቅዬ (አንቀጽ 3)

ረ. ፍንትው (አንቀጽ 4)

ሸ. ሲንደረደሩ (አንቀጽ 4)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ጽሑፍን አሳጥሮ መጻፍ

**ተግባር**

ሀ. ጥንድ ጥንድ በመሆን «አስደናቂዎቹ ቅርሶች» የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያ ሁለት አንቀጾች ዋናዋና ሀሳቦች ጨምቃችሁ በቢጋር ሠንጠረዡ አስፍሩ።

ለ. «አስደናቂዎቹ ቅርሶች» የሚለውን ምንባብ በሦስት አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ።

### የአፃጻፍ ሥርዓት

**ተግባር**

ሀ. የመሀል ፊደላቸውን የሚደግሙና «-ኦሽ»ን የሚቀጥሉ አምስት ቃላት ፈልጋችሁ በትክክል ጻፉ።

ለ. «-ኧኛ» የሚል ቅጥያ የተቀጠለባቸው አምስት ቃላት ፈልጋችሁ ጻፉ።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### አስደናቂዎቹ ቅርሶች

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«አስደናቂዎቹ ቅርሶች» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሷቸውን ነጥቦች ጥቀሱ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«አስደናቂዎቹ ቅርሶች» የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያ ሁለት አንቀጾች ሁለት ሁለት እየሆናችሁ ተራበተራ ድምፅ በማሰማት በፍጥነትና በትክክል አንብቡ።

## መናገር

### አንቀጽን ገምግሞ መናገር

#### ተግባር

በ2ኛው ሳምንት፣ በ6ኛው ቀን በተለማመዳችሁት መሠረት «አስደናቂዎቹ ቅርሶች» ከሚለው ምንባብ ሦስተኛውን አንቀጽ በመገምገም ውጤቱን በቃላችሁ ተናገሩ።

## ሰዋስው

### ተውሳከግስ፣ ጠቋሚ መስተዓምርና መስተፃምር

#### ተግባር

1. በ«ሀ» ረድፍ የቀረቡትን ቃላት ሰዋስዋዊ መጠሪያ በ«ለ» ረድፍ ከቀረቡት በመፈለግ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ነገርግን | ሀ. ተውሳከግስ |
| 2. እነዚያ | ለ. ጠቋሚ መስተዓምር |
| 3. ያቺ | ሐ. መስተፃምር |
| 4. ወይም | |
| 5. ቶሎቶሎ | |

2. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ተውሳከግሶች፣ ጠቋሚ መስተኣምሮችና መስተጻምሮች ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. እነዚህን ወንበሮችና እነዚያን ጠረጴዛዎች ቶሎቶሎ አፅዷቸው።

ለ. በፍጥነት መሥራት ጥሩ ነው፤ ሆኖም እንደገና ላለመሥራት ማስተዋል ያስፈልጋል።

ሐ. የክፍል ተሳትፎህ ጥሩ ነው፤ ነገርግን አንዳንድ ጊዜ የቤትሥራ አትሠራም።



# ምዕራፍ 3

## ሰብዓዊ ዕሴቶች

### አረጋውያንን ማክበር

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን


## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር 1**

በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ቅጥያዎችን ከቃላት በመነጠል አንብቡ።

ምሳሌ:- ሊበዛባቸው





ሀ. አክብሮታችን

ለ. እየተከተላችሁ

ሐ. ጎልማሳነት

## ተግባር 2

በተሰጠው ምሳሌ መሠረት ቃላትን ከቅጥያዎች ጋር በማጣመር ጽፋችሁ አንብቡ።




ሀ. እየ-ተናገር-ኣችሁ-ኣት

ለ. እየ-ተከተለ-ሽ

ሐ. ርቆ-ብ-ኣችሁ-ኣል

# ማንበብ

## አረጋውያንን ማክበር

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

## ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አረጋውያን ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. በቤታችሁ አካባቢ ከአረጋውያን ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት አላችሁ?

ሐ. ለአረጋውያን ምን ማድረግ ይጠበቅብናል ብላችሁ ታስባላችሁ?

### የማንበብ ሂደት

## ተግባር 1

«አረጋውያንን ማክበር» የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሦስት አንቀጾች መምህራችሁን እየተከታተላችሁ አንብቡ።

## ተግባር 2

ከአንቀጽ አራት ጀምሮ ያለውን የምንባብ ክፍል ተራበተራ ቃላት ሳትደግሙ፣ ፊደላት ሳትገድፉ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

### አረጋውያንን ማክበር

የአረጋውያንን ቀን ለማክበር የተገኛችሁ ውድ አረጋውያንና የስነዜጋ ክበብ አባላት፣ ጤና ይስጥልኝ! እንደምን ሰነበታችሁ? ዓለምነሽ በለጠ እባላለሁ። የመጣሁት ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ነው። የመጣሁበት ዓላማም አረጋውያንን በሚመለከት ከእናንተ ጋር ለመወያየት ነው። በንቃት እንደምትከታተሉኝ እምነቴ ነው።

በባህላችን መሠረት ታናናሾች ታላላቆችን ማክበር አለብን። በዕድሜ የሚበልጡንን ሰዎች በትህትና ማናገር፣ መቀበል ማስተናገድና ቅድሚያ መስጠት ይጠበቅብናል። በአካባቢያችን ያሉ አረጋውያን፣ አያቶች፣ አባቶች፣ እናቶች ሁሉ ሊከበሩ ይገባቸዋል። እስቲ በየቤታችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የሚገኙ አረጋውያንን እንዴት እንደምታከብሯቸው ንገሩኝ?... ጥሩ ብላችኋል። በተናገራችሁት ሁሉ እስማማለሁ።

> **ከአረጋውያን የምናገኘው ትምህርት ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በማንበብ ከምናገኘው ዕውቀት ያልተናነሰ ነው።**

አረጋውያን በወጣትነትና በጎልማሳነት ዕድሜያቸው ለሀገራቸውና ለወገናቸው ጠቃሚ ተግባራትን ያከናወኑና ሰፊ የህይወት ልምድ ያላቸው ናቸው። እነሱን ማክበር ማለት ራሳችንንም ማክበር ማለት ነው። አረጋውያን ቀድመው ሁኔታዎችን ባያመቻቹልን ኖሮ የእኛም ህልውና አይታሰብም ነበር። እነሱን በማክበራችን በብዙ መንገድ ተጠቃሚ እንሆናለን። ተዝቆ ከማያልቀው የህይወት ልምዳቸው ብዙ እንማራለን። ከነሱ የምናገኘው ትምህርት ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በማንበብ ከምናገኘው ዕውቀት ያልተናነሰ ነው። አይደለም እንዴ? እውነት ብላችኋል።

ስለሆነም አረጋውያን ጠቃሚ የማኅበረሰቡ የዕውቀት ምንጮች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል። ታዲያ እነዚህ ዕንቁ የዕድሜ ባለፀጎች መከበር ሊበዛባቸው ነው!? አይደለም እንዴ!? አረጋውያንን የምናከብረው እንዲሁ መከበር ስላለባቸው ብቻ ሳይሆን፣ እነሱን በማክበር ማግኘት የሚገባውን በርካታ ቁምነገሮች ስላሉና የሞራል ግዴታም ስላለብን ነው። ይህም የሚጠቅመው አረጋውያኑን ብቻ ሳይሆን እኛንም ጭምር ነው። ስለዚህ የምንፈልጋቸውን ጠቃሚ ዕውቀቶችና ልምዶች ለመቅሰም አረጋውያን በሚናገሩበት ወቅት በጥሞና መከታተልና ማዳመጥ ይኖርብናል። ካዳመጥናቸው፣ በህይወት ዘመናቸው ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ ሳይሰስቱ ያካፍሉናል። በዚህም በብዙው ተጠቃሚ እንሆናለን።

አረጋውያን በኑሯቸው የተለያዩ የህይወት ውጣውረዶችን አልፈዋል። ደስታና መከራ፣ ማግኘትና ማጣት ተፈራርቀውባቸዋል። ሁሉንም የህይወት ውጣውረዶችን በዘዴና በብልሃት አልፈው ዛሬ ካሉበት ደረጃ ለመድረስ በቅተዋል።

ይህ ልምዳቸው የሚያጋጥሙንን ችግሮች በቀላሉ ተቋቁመን ለማለፍ አቅም ይፈጥርልናል። ጥሩ! እየተከታተላችሁኝ ነው? በሀሳቡ ምን ያህል ትስማማላችሁ? ጥሩ ነው። ውይይታችንን እንቀጥላለን።

አረጋውያን ልምዳቸውን የሚገልፁት በፈሊጣዊ ንግግር፣ በተረትና በምሳሌ ነው። በሚተርኩበት ጊዜ በርጋታ ካዳመጥናቸው ያልተፈቱና ያልተመነዘሩ ቁምነገሮችን ያሳውቁናል። ትኩረት ሰጥተን ካዳመጥናቸውና ከተከታተልናቸው ተፈላጊና «ጠቃሚ ሰው ነኝ» የሚል ስሜት በውስጣቸው ይፈጠራል፤ ስለእኛ የወደፊት ተስፋ ርግጠኛ ይሆናሉ። ስለሆነም ከልምዳቸው ለእኛ ይጠቅማል ያሉትን ሁሉ ሳይደብቁ ይገልፁልናል።

በተጨማሪም አረጋውያን በአካባቢያችን ካሉ በመንገድ ላይ ቅድሚያ በመስጠት ኮፍያችንን ከራሳችን ላይ በማንሳት፣ ከአንገታችን ጎንበስ በማለት ሰላምታ መስጠት፣ ከመቀመጫችን በመነሳት «ነወር» በማለት አክብሮታችንን መግለፅ አለብን። ይህን ስናደርግላቸው በውስጣቸው ደስታ ይፈጠራል፤ በራስ የመተማመን ስሜታቸው ከፍ ይላል። ከዚህ ላይ በማኅበረሰባችን «የሚያድግ ልጅ አይጥላህ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ» የሚለውን አባባል ማስታወስ ያስፈልጋል። ትልቅ ቁምነገር አለው።

በአጠቃላይ አረጋውያንን ማክበር የዕለትተዕለት ተግባራችን ሊሆን ይገባል። ካለፉ በኋላ ልናገኛቸው የማንችላቸውን የዕውቀት ክምችቶች ለወደፊቱ ትውልድ ማስተላለፍ የምንችለው ተገቢውን ክብር በመስጠት ስንከባከባቸውና ከነሱ መማር ስንችል ነው። አይመስላችሁም? ትክክል ናችሁ። ውይይታችን መልካም ነበር፤ በሌላ ጊዜ በሌላ ርዕሰጉዳይ ለመወያየት እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ! አመሰግናለሁ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አረጋውያንን ማክበር የሚያስፈልገው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ወጣቶች ከአረጋውያን ምን ይማራሉ?

ሐ. አረጋውያን ሲናገሩ መከታተልና ማዳመጥ የሚገባን ለምንድን ነው?

መ. አረጋውያን ልምዳቸውን በፈሊጣዊ አነጋገር፣ በተረትና ምሳሌ የሚገልጹት ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. «የሚያድግ ልጅ አይጥላህ፣ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ» የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር በራሳችሁ አባባል ግለጹ።

2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. አረጋውያን በወጣትነትና በጎልማሳነት ዕድሜያቸው ለሀገር ጠቃሚ ተግባር ሠርተዋል።

ለ. ከአረጋውያን ተዝቆ የማያልቅ የህይወት ልምድ እንማራለን።

ሐ. እነዚህ ዕንቁ የዕድሜ ባለጸጋዎች መከበር ይገባቸዋል።

መ. አረጋውያን የተለያዩ የህይወት ውጣውረዶችን አልፈዋል።

ሠ. አረጋውያን ልምዳቸውን የሚገልጹት በፈሊጣዊ ንግግር፣ በተረትና ምሳሌ ነው።

ረ. አረጋውያንን ካዳመጥናቸው ያልተፈቱና ያልተመነዘሩ ቁምነገሮችን ያሳውቁናል።

ሰ. አረጋውያንን ካዳመጥናቸው በህይወት ዘመናቸው ካካበቱት ዕውቀትና ልምድ ሳይሰስቱ ያካፍሉናል።

ሸ. አረጋውያንን በትህትና መቀበልና ማስተናገድ ይጠበቅብናል።

#### ተግባር 2

ምንባቡን መሠረት በማድረግ በ«ሀ» ረድፍ ላሉት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳያቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመፈለግ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በጥሞና | ሀ. ብልሀት |
| 2. በርካታ | ለ. ካካበቱት |
| 3. ተቋቁመን | ሐ. ያልታወቁ |
| 4. ካጠራቀሙት | መ. በትኩረት |
| 5. ያልተፈቱ | ሠ. ከተሞክሯቸው |
| 6. ዘዴ | ረ. ተጋፍጠን |
| 7. ከልምዳቸው | ሰ. ብዙ |


## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና በመዘርዝር ስልት አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር 1

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በምንባቡ መሠረት አሟልታችሁ ባለአንድ አንቀጽ የንግግር ጽሑፍ አዘጋጁ።




#### ተግባር 2

«አረጋውያንን ማክበር ለምን ይጠቅማል?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱ ዋናዋና ሀሳቦች በቢጋር ሠንጠረዥ አስፍራችሁ ሀሳቦቹን በማስፋፋት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን እያረቡ መጻፍ

**ተግባር**

«ጠበቀ» የሚለውን ግስ በተሰጠው ምሣሌ መሠረት በተለያዩ መደቦች እያረባችሁ ጻፉ።

| 1ኛ መደብ | 2ኛ መደብ | 3ኛ መደብ |
|---|---|---|
| አከብሬነበር | አከብረህነበር | አከብሮነበር |
| አከብረንነበር | አከብረሽነበር | አከብራነበር |
| | አከብራችሁነበር | አከብረውነበር |

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### አረጋዊያንን ማክበር

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን «አረጋውያንን ማክበር» በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋናዋና ሀሳቦች በቃል ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

ሀ. «አረጋውያንን ማክበር» የሚለውን ምንባብ 4ኛ፣ 5ኛና 6ኛ አንቀጾችን ድምፅ እያሰማችሁ ከመምህራችሁ ጋር በአንድ ላይ አንብቡ።

ለ. በቡድን በቡድን በመሆን «አረጋውያንን ማክበር» የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሦስት አንቀጾች ሥርዓተነጥቦችንና የሐረግ አከፋፈልን ተከትላችሁ ተራበተራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## ማዳመጥ

## ወላጆችን ማክበር

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ልጆች ወላጆችን ማክበር ያለባቸው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ወላጅን ማክበር የልጆች ግዴታ ነውን? ለምን?

### የማዳመጥ ሂደት

#### ተግባር

«ወላጆችን ማክበር» የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋናዋና ነጥቦችን በመጻፍ በንቃት አዳምጡ።

### አዳምጦ መረዳት

#### ተግባር

የሚከተሉትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ቀበጡ ልጅ «እናቴ ሞታለች» የሚለው ለምን ነበር?

ለ. የቀበጡ ልጅ እናት የደረሰባት አደጋ ምን ነበር? በምን ምክንያት?

ሐ. ቀበጡን ልጅ እናቱ በእሳት እንዳይቃጠል ያዳነችው እንዴት ነው?

መ. ቀበጡ ልጅ እናቱን ይቅርታ የጠየቀው ለምንድን ነው?

ሠ. ከቀበጡ ልጅ ምን ትማራላችሁ?

ረ. ወላጆችን ማክበር የሚገባን ለምንድን ነው?


ሰ. ከምንባቡ ታሪክ ምን ተማራችሁ?

## ሰዋስው

### ጊዜ አመልካቾች

#### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት «ጠረገ» የሚለውን ቃል በተለያየ መደብና ቁጥር በማርባት ጊዜ አመልካቾችን አውጡ።




አመልካች
- ነው
- ነበር

አመልካች
- -ኣል
- ነበር

## ተግባር 2

«ጎበኘ» የሚለውን ቃል በ1ኛ መደብና በ2ኛ መደብ ብዙ ቁጥር በማርባት የጊዜ አመልካች ቅጥያውን ነጥላችሁ አሣዩ

## ማንበብ

### አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ

### ቅድመንባብ

**የቀደመ ዕውቀትን በመጠቀምና ስዕልን በመመልከት የምንባቡን ይዘት መገመት**

#### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀምና ሥዕሉን በመመልከት ስለአካል ጉዳተኝነት የምታውቁትን ያህል ግለጹ።

ለ. አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ሰው በሥራቸው ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

የሚከተሉትን የማንበብ ተግባራት ሥሩ።

ሀ. «አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ» የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያ ሦስት አንቀጾች መምህራችሁን እየተከተላችሁ አንብቡ።

ለ. «አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ» የሚለውን ምንባብ ቃላት ሳትደጋግሙ፣ ፊደል ሳትገድፉ፣ የሐረግ አከፋፈልን ተከትላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ በትክክል አንብቡ።

# አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ



ውድ የስብሰባው ተሳታፊዎች! እንደምን አረፈዳችሁ? ጥሪያችንን አክብራችሁ በሰዓቱ በመገኘታችሁ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ። እ... ስለአቀባበላችሁም በድጋሚ አመሰግናለሁ።

ያው ዛሬ እዚህ የተገናኘነው የአካል ጉዳተኞችን ቀን ለማክበር ሲሆን፣ መሥሪያቤታችሁ ባደረገልኝ ጥሪ መሠረት በመካከላችሁ በመገኘቴ ልዩ ደስታ ይሰማኛል። የመጣሁት ከኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማህበር ነው። አለማየሁ አወቀ እባላለሁ። ዛሬ የምንወያየው «አካልጉዳተኞችን መንከባከብ» በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ነው።

እስኪ በመጀመሪያ ስለአካልጉዳተኝነት የምታውቁትን ንገሩኝ? ጥሩ ነው። ሌሎቻችሁም ተጨማሪ አስተያየት እንድትሰጡ እፈልጋለሁ። አዎ! በተለይ ዓይነስውሩ ሰውዬ የሰጡት መልስ ለሁላችንም ግልጽ ነው። ጥሩ ነው። አዎ! እንግዲህ አካል ጉዳተኝነት የሰዎችን ከውልደት ጀምሮም ሆነ በህመም ወይም በአደጋ ምክንያት የተወሰነ የአካል ክፍላቸውን ማጣት ወይም የተወሰነ ተፈጥሯዊ የሰውነት ሥርዓታቸው መዛባትን ይመለከታል።

እንደምናውቀው አካል ጉዳተኝነት የሰው ልጆች አኗኗር አንዱ ገጽታ ነው። ሰው ነንና በህይወት ዘመናችን ጊዜያዊ ወይም ዘለቄታዊ ጉዳት ሊያጋጥመን ይችላል።

አያድርግብንና አሁን ከዚህ አዳራሽ ስንወጣ አንድ ያላሰብነው አደጋ ደርሶብን በአካላችን ላይ ችግር ቢፈጠር ባልገመትነው ሁኔታ የአካል ጉዳት ሊደርስብን ይችላል። አካል ጉዳተኝነት ስላልፈለግነው የሚቀር ሳይሆን፣ ባጋጣሚ የሚመጣ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። አሁን ግልፅ የሆነ ይመስለኛል? አዎ!

በዓለማቀፍ ደረጃ መረጃዎች እንደሚያስረዱት አንድ ቢሊዮን የሚሆኑት ሰዎች አካል ጉዳተኞች ናቸው። እስቲ ተመልከቱ! ከዚህ አንፃር እንግዲህ ከዚህ ከተሰበሰብነው መካከል ራሳችን ወይም ከቤተሰቦቻችን ወይም ከዘመዶቻችን አንድ አካል ጉዳተኛ ሊኖር/ልትኖር ይችላል/ትችላለች ማለት ነው። አይደለም እንዴ? አዎ! «ስለዚህ እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች እንዴት መርዳትና መንከባከብ አለብን?» የሚለው ጥያቄ የሁላችንንም ምላሽ ይፈልጋል። ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት በመጀመሪያ ያሉባቸው ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ በትክክል መለየት አለብን። እየተከታተላችሁኝ ነው? አዎ! አካል ጉዳተኛ የሆኑት የማኅበረሰብ ክፍሎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑት የበለጠ ማኅበራዊና ምጣኔሀብታዊ ችግሮች ያጋጥማቸዋል። በተለያዩ ማኅበራዊ አመለካከቶች የተነሳ የትምህርት ዕድል የሚያገኙት የተወሰኑት ናቸው። የሥራ ተሳትፏቸውም አናሳ ነው።

> **አካል ጉዳተኝነት ማንኛውም ሰው ሊያጋጥመው የሚችል ተፈጥሯዊም ሆነ ሰውሠራሽ አደጋ ውጤት ነው።**

የአካል ጉዳተኞች የአቅም ውስንነት እንዳለባቸው የሚያምኑት የማኅበረሰብ ክፍሎች ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም። ይህ አመለካከት ግን የተዛባ ነው። የአካል ጉዳተኞች የመማርና የመሥራት እድሉን ካገኙ የአቅም ውስንነት የለባቸውም። ይህንንም በተግባር ያስመሰከሩ በርካቶች ናቸው።

የአካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ያለው የተዛባ ማኅበራዊ አመለካከት የበለጸጉትም ሆነ በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች ችግር ነው። እስቲ በእናንተ አካባቢ ለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት የሆኑ ችግሮችን ዘርዝሩ? ጥሩ ነው! ሀሳቦቻችሁን እኔም እጋራለሁ።

ለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት ከሚሆኑት መካከል እኔ ደግሞ የተወሰኑትን ልጥቀስ፤ የህንጻዎችና የመንገዶች አሠራር፣ የመረጃና የቴክኖሎጂ ተደራሽ ያለመሆን ወዘተ ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍና ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ ለማድረግ «ምን ማድረግ አለብን?» የሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አለበት። የዛሬው ውይይታችን ቁልፍ ጉዳይም እሱ ነው። አሁን አንድ በአንድ እንመልከተው።

አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም የማኅበረሰብ ክፍል የመማር መብት አላቸው። በመሆኑም ትምህርትቤቶችና የመማር ማስተማር ሂደቶች ለአካል ጉዳተኞች የተመቻቹ መሆን ይኖራባቸዋል። ከክፍል ውጭ የህንፃዎች መውጫና መግቢያ፣

በክፍል ውስጥ የመቀመጫ ወንበሮች ለአካል ጉዳተኞች በጣም የተመቹ መሆን አለባቸው። የትምህርት አሰጣጡም ልዩነት እንዳይፈጥር ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች እንደየፍላጎታቸው እገዛ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል። መስማት ለተሳናቸው በጽሑፍ ወይም ሊታይ በሚችል የምልክት ቋንቋ፣ ለዓይነስውር ተማሪዎች ደግሞ መምህራን ወይም ጓደኞቻቸው በማንበብ ሊያግዟቸው ይገባል።

በተለይም ሴት አካል ጉዳተኞች በጾታቸውና በጉዳታቸው ምክንያት ድርብርብ ችግሮች ስላሉባቸው የተለየ እንክብካቤና እገዛ ያስፈልጋቸዋል። በመኖሪያ አካባቢም የሚሠሩ ህንፃዎችና መንገዶች አካል ጉዳተኞችን ከግምት ሊያስገቡ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን አካል ጉዳተኞች ለተጨማሪ ጉዳት ሊዳረጉ ይችላሉ። አይደለም እንዴ? በህንፃ ግንባታ ችግር ምክንያት አደጋ የደረሰባቸው አካል ጉዳተኞች አጋጥሟችሁ አያውቅም? አዎ! ሁላችንም ያጋጥመናል። ስለዚህ እያንዳንዳችን ይህ ችግር እንዳይደርስ የበኩላችንን ድርሻ መወጣት ይኖርብናል። ሀሳቡ ሁላችንንም የሚያስማማ ይመስለኛል፣ ተሳስቻለሁ እንዴ?

> **አካል ጉዳተኞች ሀገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ መረጃዎችን ከሌሎች እኩል ማግኘት ይኖርባቸዋል።**

መረጃን የሚመለከተው ደግሞ ሌላው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። መረጃ ለዕድገት ወሳኝ ነገር መሆኑ አያጠያይቅም። ስለሆነም አካል ጉዳተኞችም ሀገራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ መረጃዎችን ከሌሎች እኩል ማግኘት ይኖርባቸዋል። ስለዚህም መረጃዎች የተለያዩ አካል ጉዳተኞችን መሠረት አድርገው ሊዘጋጁ ይገባል። ግልጽ ነው? እስከአሁን በተነጋገርንበት ላይ ጥያቄ ካላችሁ? ጥሩ።

ሀሳቤን ለማጠቃለል አካል ጉዳተኞች የትምህርት፣ የመሠረተልማትና የመረጃ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት ከሁላችንም ይጠበቃል። በመሆኑም በተሰማሩበት የሥራ መስክም ሆነ በማኅበራዊ ኑሯቸው አካል ጉዳተኞችን ማገዝ፣ መንከባከብና ማክበር ከሁላችንም የሚጠበቅ ሀላፊነት ነው። በውይይታችን ለነበራችሁ ተሳትፎ አመሰግናለሁ። በሌላ ጊዜ እስከምንገናኝ ቀኑን የሰላም ቀን ያድርግልን። ደህና ዋሉ።

(ጌታሁን ወርቁ። *ከሪፖርተር ጋዜጣ* ሰኔ 24 ቀን 2006። ዕትም መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አካል ጉዳተኞች ያሉባቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው?

ለ. ብዙ አካል ጉዳተኞች የትምህርት ዕድል የማያገኙት ለምንድን ነው?

ሐ. ለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት የሆኑትን ችግሮች ዘርዝሩ።

መ. አካል ጉዳተኞች የአቅም ውስንነት አለባቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ሠ. የአካል ጉዳተኞች የመማር መብት በምን በምን መደገፍ አለበት ትላላችሁ?

ረ. የሴት አካል ጉዳተኞች ችግር «ድርብርብ ነው» ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ሰ. ስለ«አካልጉዳተኝነት» ያላችሁን አስተሳሰብ ግለጹ።

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

**ተግባር**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. በህይወት ዘመናችን ጊዜያዊ ወይም ዘለቄታዊ ጉዳት ሊያጋጥመን ይችላል።

ለ. መረጃ ለዕድገት ወሳኝ ነገር መሆኑ አያጠያይቅም።

ሐ. አካል ጉዳተኞች ከማኅበረሰቡ አመለካከት የተነሳ የትምህርት ዕድል የሚያገኙት የተወሰኑ ናቸው።

መ. አካል ጉዳተኞች ለመማርና ለመሥራት ዕድል ካገኙ የአቅም ውስንነት የለባቸውም።

ሠ. የአካል ጉዳተኞችን ችግሮች ለመቅረፍ የመንግሥት ድርሻ ከፍተኛ ነው።

ረ. የዛሬው ውይይታችን ቁልፍ ጉዳይ «የአካል ጉዳተኞችን ችግር ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?» ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ነው።

ሰ. አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ያለው የተዛባ ማኅበራዊ አመለካከት የበለጸጉትም ሆነ በማደግ ላይ ያሉት ሀገሮች ችግር ነው።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የቢጋር ሠንጠረዥን በመጠቀም ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

ቀጥሎ ያለውን የቢጋር ክብ መሠረት በማድረግ ለንግግር የሚሆን ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።




### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን እያረቡ መጻፍ

#### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት «አገኘ» የሚለውን ቃል በተለያየ መደብ፣ ቁጥርና ጾታ በማርባት ጻፉ።

ምሳሌ፡- «ተመኘ» የሚለው ቃል ሲረባ፣

«ተመኝቻለሁ፣ ተመኝተናል፣ ተመኝተሃል፣ ተመኝተሻል፣ ተመኝታችኋል፣ ተመኝቷል፣ ተመኝታለች፣ ተመኝተዋል።» ይሆናል

#### ተግባር 2

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በትክክል በመጠቀም ጻፉ።

# አቀላጥፎ ማንበብ

## አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን «አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ» ከሚለው ምንባብ ውስጥ ለአካል ጉዳተኞች እንቅፋት ናቸው የተባሉትን ነገሮች በማስታወስ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር 1**

በቡድን ሆናችሁ «አካልጉዳተኞችን መንከባከብ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ 5ኛውን አንቀጽ የሥርዓተነጥቦችን አጠቃቀምና የአነጋገር ድምፀት በአግባቡ በመረዳት አንብቡ።

**ተግባር 2**

«አካል ጉዳተኞችን መንከባከብ» የሚለውን ምንባብ ተራበተራ አንብቡ።

# መናገር

### በገለጻ ንግግር ማድረግ

**ተግባር 1**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን ያዘጋጃችሁትን የንግግር ጽሑፍ ሐረግ አከፋፈልን፣ ሥርዓተነጥብ ተከትሎ ማንበብን፣ የድምፅ አገታትን፣ ከፍታንና ዝቅታን ጠብቃችሁ ንግግር አድርጉ።

**ተግባር 2**

የተዘጋጃችሁበትን የንግግር ጽሑፍ በክፍል ውስጥ በንግግር መልክ አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ጊዜ አመልካቾች

ማስታወሻ፡- ጊዜ አንድ ድርጊት ወይም ሁኔታ መቼ እንደተፈጸመ/እንደሚፈጸም ይገልጻል። በግሶች ውስጥ ጊዜን አመልካቾቹ ነው፣ -ነበርና -ኣል ናቸው።

### ተግባር 1

በቃላቱ ውስጥ የሚገኙትን ጊዜ አመልካቾች አውጡ።

ምሳሌ፡-

| ቃል | ጊዜ አመልካች |
| --- | --- |
| ለብሷል | -ኣል |
| ለብሶነበር | -ነበር |

ሀ. ነግሯል

ለ. ነገሮነበር

ሐ. መክሯል

መ. መክሮነበር

ሠ. ወስዷል

ረ. ወስዶነበር

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ይኖር-ብ-አቸው-አል | ይኖርባቸዋል |
| ለ | እየ-ነገር-አችሁ-አት | እየነገራችኋት |
| ሐ | ተማሪ-ዎች-አቸው-ን | ተማሪዎቻቸውን |
| መ | ኃላፊ-ነት-አች-አችን-ን | ኃላፊነቶቻችንን |
| ሠ | ይ-ሰማ-ብ-አቸው-አል | ይሰማባቸዋል |

## ማንበብ

### ኃላፊነት ምንድን ነው?

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስንት ዓይነት ኃላፊነቶች አሉ?

ለ. ኃላፊነትን መወጣት ለምን ይጠቅማል?

ሐ. ኃላፊነትን የመወጣት ዋና ግብ ምንድን ነው?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«ኃላፊነት ምንድን ነው?» የሚለውን ምንባብ የማታውቋቸውን ቃላት እየጻፋችሁና የየአንቀጾችን ሀሳብ እያጠቃለላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ኃላፊነት ምንድን ነው?

ውድ የልማት ቡድን አባላት፣ ጤና ይስጥልኝ! እንደምንሰነበታችሁ? ዛሬ በመካከላችሁ የተገኘሁት ከሲቭል ሰርቪስ ቢሮ ተወክዬ ነው። ዚነት ከድር እባላለሁ። በሲቭል ሰርቪስ ቢሮ የማኅበራዊ ዘርፍ ባለሙያ ነኝ። የዛሬው ስብሰባ ዓላማ «ኃላፊነት ምንድን ነው?» በሚለው ርዕሰጉዳይ ለመወያየት ነው። እስቲ ስለኃላፊነት ምንነት የምታውቁትን ንገሩኝ። በጣም ጥሩ! ሁላችሁም የገለፃችሁት ሀሳብ ትክክል ነው።

ኃላፊነት ማለት በተሰማሩበት ሙያ ድርሻን ውጤታማ በሆነ መንገድ መወጣት ማለት ነው። ኃላፊነትን የመወጣት ዋና ግብ የሀገር ልማትንና ብልጽግናን ማምጣት ነው። እንደዚህ ያለው ዕድገትና ብልጽግና የሚመጣውም በሥራ ነው። በመሆኑም የሥራ ኃላፊነትን መቀበልና ሥራው የሚጠይቀውን ግዴታ በአግባቡ መወጣት የሁላችንም የዜግነት ግዴታ ይሆናል። ኃላፊነትን መቀበል አንድን ተግባር ለማከናወን ግላዊና ማኅበራዊ ግዴታን መወጣት ይጠይቃል። በኃላፊነት ስሜት የግልና የጋራ ደህንነትን በማረጋገጥ ሀገርንና ዜጎችን ከሚጎዳ ከማንኛውም መጥፎ ድርጊት መቆጠብ ይኖርብናል።

የግል ኃላፊነት እያንዳንዳችን በግላችን መወጣት የሚገባንን ኃላፊነት ይመለከታል። የግል ኃላፊነት እያንዳንዳችን እንደየዕድሜያችን፣ እንደየችሎታችን፣ እንደየሥራድርሻችን፣ የምንወጣው ህጋዊና ሞራላዊ ግዴታ ነው። እንደተሰማራንበት የሙያ መስክም ኃላፊነታችን ሊለያይ ይችላል። ሁላችንም ለምሳሌ የሀገራችን ዕድገት ይመለከተናል። ለራሳችን ደህንነት እንደምንጨነቀው ሁሉ የሌሎችም ደህንነት ሊያስጨንቀን ይገባል። ለምሳሌ ሐኪሞች ሙያዊና ሞራላዊ በሆነ ኃላፊነት ሕሙማንን እንደራሳቸው መንከባከብና መርዳት ይኖርባቸዋል። በመማር ማስተማር ሂደትም መምህራን ለተማሪዎቻቸው የትምህርት አቀባበልና ደህንነት አጥብቀው መጨነቅና ኃላፊነት መውሰድ ይኖርባቸዋል።

እናንተም በተሰማራችሁበት ዘርፍ በሙያችሁ እኩል ኃላፊነት አለባችሁ ብል የምትስማሙ ይመስለኛል። ተመልከቱ! በሁሉም ዘርፍ ይህ ይንጸባረቃል። አይደለም እንዴ? ተሳስቻለሁ? በጣም ጥሩ! ትክክል ናችሁ፤ ስለዚህ ሁላችንም የግል ኃላፊነታችንን ካልተወጣን ራሳችንን ከመጉዳት አልፈን ያለንበትን ማኅበረሰብም ሆነ ሀገራችንን ልንጎዳ እንችላለን።

ሰዎች ለጋራ ኑሮ አመቺነት በሚጠቀሙባቸው ጉዳዮች ላይ የሚወስዱት ርምጃ የጋራ ኃላፊነት ይባላል። ለምሳሌ የሀገርን ሉዓላዊነት መጠበቅ፣ የመንግሥትና የሕዝብን ንብረቶች ከብክነትና ከጥፋት መከላከል፣ እኩይ ተግባራትን መዋጋትና የመሳሰሉት ተግባራት ሁሉ የግል ብቻ ሳይሆኑ የጋራ ኃላፊነቶች ናቸው። አሁን ደግሞ እስቲ እናንተ በአካባቢያችሁ የምትወጧቸውን ማኅበራዊ ኃላፊነቶች ንገሩኝ፤ በጣም ጥሩ ነው! ሁላችሁም በተናገራችሁት እስማማለሁ። ለምሳሌ ሁሉም የማኅበረሰብ አባላት በየአካባቢያቸው ሰላምን ለማስፈን መጣር ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህም ምክንያቱ በተለያየ ወቅት የሚከሰቱ ችግሮች ሁሉንም የማኅበረሰብ አባላት የሚመለከቱ መሆናቸው ነው።

እንግዲህ ወደማጠቃለሉ ልምጣ፤ የኃላፊነት ስሜት የዜግነት ድርሻቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች ባህርይ ነው። በመሆኑም ኃላፊነትን መወጣት በቅንነትና በታማኝነት የግልም ሆነ የጋራ ተግባርን በማከናወን የሚገለጽ ስለሆነ እኛም ለተግባራዊነቱ የበኩላችንን መወጣት ይኖርብናል። እስከአሁን በተወያየነው ላይ ጥያቄ አላችሁ? እሺ! ግልጽ ከሆነ ሞቅ ባለ ተሳትፎ ስለተከታተላችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ። የተመደበልኝ ጊዜ ስላበቃ ንግግሬን በዚሁ አጠናቅቃለሁ። በሰላም ሰንብቱ! አመሰግናለሁ።

(ትምህርት ሚኒስቴር። 2003። *ሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት 7ኛ ክፍል የተማሪ መጽሐፍ፣* ገጽ 68-69 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ምንባቡ የተጻፈበትን ዋና ዓላማ ለይታችሁ ምክንያቱን ጻፉ።

ለ. በ1ኛው ሳምንት «አረጋውያንን ማክበር»፣ በ2ኛው ሳምንት «የአካልጉዳተኞችን መንከባከብ»፣ በዛሬው ዕለት ደግሞ «ኃላፊነት ምንድን ነው?» የሚሉ ምንባቦችን አንብባችኋል። ሦስቱ ምንባቦች ከማኅበራዊ እሴት አንጻር ያላቸውን ተመሳስሎ በጽሑፍ ግለጹ።

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

## ቃላትን በዐውድ መጠቀምና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መካከል ተገቢ የሆኑትን በመምረጥ ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ታሪክ | ሞታለች | የተጨማደደ |
| የተለበለበ | ይገረማሉ | ቀልቤን |
| ሽፍኜ | ቀበጥ | ወደውጪ |

ሀ. ዛሬ የምነግራችሁ ተረት ሳይሆን እውነተኛ ________ ነው።

ለ. አንድ ________ ልጅ የነበራት አንዲት እናት ነበረች።

ሐ. እናቲቱ ፊቷ በእሳት ________ ነበር።

መ. ሴትዮዋን የሚያዩዋት ሁሉ ________።

ሠ. ልጅየው በእናቱ________ና የጠቆረ ፊት ያፍር ነበር።

ረ. ልጅየው ለጓደኞቹ እናቴ ________፤ ለሌሎች ደግሞ እናቴ ________ ሀገር ሄዳለች እያለ ይዋሽ ነበር።

ሰ. እናቱ «አንተን ለማዳን በእሳት መካከል ________ ስቼ ገብቼ ነበር አለችው»

ሸ. «አንተን በብርድልብስ ________ አምላኬን እየተማፀንኩ ይገፍሀ ወጣሁ» አለችው።

## ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ከ«ለ» ረድፍ ተቃራኒ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ጉዳት | ሀ. ቀዝቃዛ |
| 2. የግል | ለ. የጋራ |
| 3. ጥፋት | ሐ. ጥቅም |
| 4. እኩይ | መ. ሰናይ |
| 5. ቅንነት | ሠ. ልማት |
| 6. ሙቅ | ረ. ክፋት |
| | ሰ. ሰላም |


## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና በመዘርዝር ስልት የንግግር ጽሑፍ ማዘጋጀት

## ተግባር

ሀ. የሚከተለውን የቢጋር ክብ መሠረት በማድረግ ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን የያዘ ለንግግር የሚሆን ጽሑፍ አዘጋጁ።




ለ. የጻፋችሁትን ጽሑፍ ከልሳችሁ በማስተካከል ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን በትክክል መጻፍ

**ተግባር 1**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በማዳመጥ በትክክል ጻፉ።

**ተግባር 2**

«ዘፈነ» የሚለውን ግስ በተለያዩ ርባታዎች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በማዳመጥ በትክክል ጻፉ።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ኃላፊነት ምንድን ነው?

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ3ኛው ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን «ኃላፊነት ምንድን ነው?» በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ በማስታወስ የግልና የጋራ ኃላፊነቶችን አንድነትና ልዩነት ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር 1

«ኃላፊነት ምንድን ነው?» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ አራተኛውን አንቀጽ ንግግራዊ ድምጸቱን ጠብቃችሁ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

### ተግባር 2

«ኃላፊነት ምንድን ነው?» የሚለውን ምንባብ በጥንድ በጥንድ እየሆናችሁ ንግግራዊ ድምጸቱን ጠብቃችሁ ተራበተራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

## መናገር

### የንግግር ጽሑፍ በማዘጋጀት መናገር

### ተግባር

ተማሪዎች በትምህርትቤት የግልና የጋራ ኃላፊነታቸውን እንዴት መወጣት እንዳለባቸው የሚገልጽ ንግግር በጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ንግግራዊ ድምፀቱን ጠብቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## ስዋስው

### ጊዜ አመልካቾች

### ተግባር 1

በሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ውስጥ ጊዜ አመልካች ቅርጸችን አውጡ።

ሀ. እየመከረነው

ሐ. መከሯል

ለ. እየመከረነበር

መ. መክሮነበር

### ተግባር 2

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች፣ በተሰመረባቸው ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ጊዜ አመልካች ቅርጾች አውጥታችሁ አሣዩ።

ሀ. መሀመድ ሁለት መጻሕፍት <u>ገዝቷል</u>።

ለ. አሊማ ጥሩ ውጤት አስመዝግባ ወደ9ኛ ክፍል <u>አልፋነበር</u>።

ሐ. መሠረት ወደጎንደር <u>እየሄደችነው</u>።

መ. ሥራ የሚጠይቀውን ሥነምግባር መጠበቅ የሠራተኞች ኃላፊነት <u>ይሆናል</u>።

ሠ. ሀኪሞች በሽተኞችን መንከባከብና መርዳት <u>ይኖርባቸዋል</u>።

ረ. ሥራን በጋራ መሥራት <u>እየተለመደነው</u>።

ሰ. እኔ ወደትምህርትቤት ስመጣ ዝናብ <u>እየዘነበነበር</u>።



# ባህላዊ ግጥሞች

ምዕራፍ 4

## ባህላዊ ግጥም

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

### የቃላት ጥናት

#### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ፍላጎት-ኣቸው-ን | ፍላጎታቸውን |
| ለ | መሠረት-ኡ-ኣ | መሠረቷ |
| ሐ | ይገልጽ-ኡ-ብ-ኣቸው-ኣል | ይገልጹባቸዋል |
| መ | ጊዜ-ዎች-ሽ | ጊዜዎችሽ |
| ሠ | አስ-መሰለ-ች-ው | አስመሰለችው |
| ረ | ይ-ሠራ-ው-ኣል | ይሠራዋል |
| ሰ | አፍ-ኡ-ኣ | አፏ |
| ሸ | መግለጫ-ዎች | መግለጫዎች |
| ቀ | ምኞት-ኣቸው-ን | ምኞታቸውን |
| በ | አስ-ፈተለ-ች-ው | አስፈተለችው |
| ተ | ደረት-ኡ-ኣ | ደረቷ |
| ቸ | ወንድም-ኦች-ሽ | ወንድሞችሽ |
| ኀ | እንግዳ-ይት-ኡ | እንግዳይቱ |

# ማንበብ

## ባህላዊ ግጥሞች


### ቅድመንባብ

### ስዕልን በመመልከት ምንባብን መገመት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅደመንባብ ተግባራት ሥሩ።

ሀ. የቀደመ ዕውቀታችሁን መነሻ በማድረግ የሚከተለውን የቢጋር ክብ አሟሉ።




ለ. «ባህላዊ ግጥሞች» በሚለው ርዕስ ሥር ያለውን ሥዕል በትኩረት ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

ሐ. «ባህላዊ ግጥሞች» በሚለው ርዕስና ከስሩ ባለው ሥዕል መካከል ያለው ዝምድና ምን ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የማንበብ ተግባራት ሥሩ።

ሀ. መምህራችሁን እየተከተላችሁ የእርሻና የሙገሳ ግጥሞችን የሐረግ አከፋፈልን ተከትላችሁ፣ ዜማቸውንና ድምጸታቸውን ጠብቃችሁ አንብቡ።

ለ. ጥንድ ጥንድ በመሆን አንዳችሁ ስታነቡ ሌሎቻችሁ እያዳመጣችሁ የሐረግ አከፋፈልን፣ ዜማንና ድምጸትን መጠበቃችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ።

ምሳሌ:-

ሀ. ሰው የማያውቅ ሰው/ክፉ ሰው ተፈጥሮ፣
ስሙን ሞት የሚሉት/የማይሰጥ ቀጠሮ።

ለ. የኛ ሙሽራ/ሥሪ መደብ፣
ከእንግዷህ ቀረ/መደባደብ።

**ማስታወሻ**

ግጥም የሚነበበው በመጀመሪያው ሐረግ መጨረሻና በሁለተኛው ሐረግ መጀመሪያ ላይ መጠነኛ ጊዜ ወስዶ ቆም በማለት፣ በስንኙ መጨረሻ ደግሞ የበለጠ ጊዜ ወስዶ ቆም በማለት ነው። ከላይ በቀረበው ምሳሌ የመጀመሪያው ሐረግና የሁለተኛው ሐረግ መለያ ቦታ በእዝባር ምልክት ተከፍሏል። የሐረጎቹ አከፋፈልም እንደግጥሞቹ ዓይነት ይለያያል። በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ የሀዘን ግጥም ሐረጎች ረጃጅም ናቸው። በመሆኑም ሲዜሙ ጊዜ የመውሰድ፣ ረጋ የማለት፣ የሀዘን ድባብ (ስሜት) የመፍጠር ባህርይ አላቸው። ባንፃሩ የሠርግ ግጥም ሐረጎች አጠር ያሉና ሲዜሙ ጊዜ የማይወስዱ ናቸው። በመሆኑም የፍጥነትና የደስታ ድባብ የመፍጠር ባህርይ አላቸው።

## ባህላዊ ግጥሞች



ባህላዊ ግጥሞች የተለያዩ አጋጣሚዎችን መሠረት አድርገው የሚገጠሙ፣ የማኅበረሰብን ልዩ ልዩ የህይወት መልኮች የሚያሳዩ የጠንካራ ስሜት መግለጫዎች ናቸው። ማኅበረሰቦች እንደባህላቸውና የአኗኗር ስልታቸው ደስታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ ምኞታቸውንና ፍላጎታቸውን ይገልጹባቸዋል። ከባህላዊ ግጥሞች መካከል የሀዘን፣ የሠርግ፣ የእርሻና የሙገሳ ለአብነት ይጠቀሳሉ።

## የሀዘን ቃላዊ ግጥሞች

ሀ. ሰው የማያውቅ ሰው ክፉ ሰው ተፈጥሮ፣
ስሙን ሞት የሚሉት የማይሰጥ ቀጠሮ፣
ሰው ነው ያልነውን ሰው ወሰደው ዘንድሮ።

ለ. ምነው እኔ በሞትኩ ድሃው ወንድምሽ፣
የምትሰጪበት የምታበይበት ከሚፈርስ ቤትሽ።

ሐ. ልላክልሽ እንዴ መቀስና ሚዶ፣
አልተጫነሽ እንደሁ አፈሩ ተንዶ።

መ. አንተ አለኸኝ ብዬ ስመካ ስመካ፣
አወይ የሰው ነገር ሞተህ ነወይ ለካ።

ሠ. ሲሠራው ዋለና ሲያንፀው ሲያንፀው፣
እንደመፋቂያ እንጨት ከመንገድ ቆረጠው።

## የሠርግ ቃላዊ ግጥሞች

ሀ. ሙሽሪት ለምዳለች፣ (2 ጊዜ ይዜም)
እንዝርቱን፣ ደጋኑን ላኩልኝ ብላለች።

ለ. የኛ ሙሽራ ሥሪ መደብ፣ (2 ጊዜ ይደገም)
ከእንግዲህ ቀረ መደባደብ።

ሐ. እንዳላይሽ እንዳላይሽ፣
ወርቁን ጋረዱት ሚዜዎችሽ።

መ. ጡረው ጡረው አማጭህን፣ (2 ጊዜ ይደገም)
ከዚች ቆንጆ ያጋባህን።

ሠ. የኛ ሙሽራ ሹራብ ሠሪ፣
ወሰዳት አስተማሪ። (2 ጊዜ ይደገም)

## የእርሻ ቃላዊ ግጥሞች

ሀ. አሁን ማን ያውቃል የአርሶአደርን ለዛ፣
አሁን ማን ያውቃል የበሬን ለዛ፣
እህል ካልቀመሱ ከንፈርም አይወዛ።

ለ. ማረስ ነው እንጂ የጨባውን ሥር፣
ማረስ ነው እንጂ የግራሩን ሥር፣
ሥርቆት ምንድነው ውሻ ይመስል።

ሐ. ማረስ ነው እንጂ እርፍን ነቅንቆ፣
ራብ ክፉ ነው ይገላል አንቆ።

መ. በሬው ቀና በል ከጥጉ ድረስ፣
አርሶ ያበላ አለው የደስደስ።

ሠ. ያርሳል ያሳርሳል ያወጣል እዳሪ፣
አይላትም ሚስቱን ቆጥበሽ እደሪ።

## የሙገሳ ቃላዊ ግጥሞች

ሀ. የኔማ ጌታ የሰጠኝ ሙክት፣
አንድ ዓመት ሞላኝ እሱን ሳነክት።

ለ. የኔማ እመቤት የፈተለችው፣
የሸረሪት ድር አስመሰለችው።

ሐ. አምላክ እሷን ሠራ ተጠቦ ተጨንቆ፣
አንገቷ የሚመስለው የእንግሊዝ ብርጭቆ።

መ. የእኔ ሴት ወይዘሮ የኔ ስመ መልካም፣
በእጇ ሥራን እንጂ በአፏ ሰው አትነካም።

ሠ. በራፉም ይከፈት ሁሉም ይሰናዳ፣
ልክ የለውም አሉ ለዚህ ቤት እንግዳ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር1

የግጥም ቃላት አጠቃቀም ከዝርው ጽሑፍ ቃላት አጠቃቀም በምን በምን እንደሚለይ ግለጹ።

ምሳሌ፡-

የግጥም ቃላት አጠቃቀም ከዝርው ጽሑፍ አጠቃቀም የሚለዩት ረቂቁን ነገር አግዝፈውና ተጨባጭ አድርገው በማቅረብ ባህርያቸው ነው።


ለምሳሌ፡- ሰው የማያውቅ ሰው ክፉ ሰው ተፈጥሮ፣
ስሙን ሞት የሚሉት የማይሰጥ ቀጠሮ።

በሚሉት ስንኞች ውስጥ ረቂቅ የሆነው ሞት በሰው ተወክሎ ገዝፎ ቀርቧል።

## ተግባር 2

በፊደል ተወክለው የቀረቡትን ስንኞች መሠረት በማድረግ የሀዘን፣ የሠርግ፣ የእርሻና የሙገሳ ቃላዊ ግጥሞችን አንድነትና ልዩነት አስረዱ። የግጥሞቹን አንድነትና ልዩነት ለማወዳደርና ለማነፃፀር «ዋይ» ቻርትን መጠቀም ይቻላል።

ምሳሌ፡- የሀዘን ቃላዊ ግጥም «ሀ»ና የሠርግ ቃላዊ ግጥም «ሀ»




ሀ. የሀዘን ቃላዊ ግጥም «ለ»ና የሠርግ ቃላዊ ግጥም «ለ»

ለ. የእርሻ ቃላዊ ግጥም «ሀ»ና የሙገሳ ቃላዊ ግጥም «ለ»

ሐ. የእርሻ ቃላዊ ግጥም «ሀ» የሀዘን ቃላዊ ግጥም «ሀ»

# ቃላት

## ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር

«ባህላዊ ግጥሞች» በሚለው ምንባብ መሠረት የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት ዓውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ ግለጹ።

ምሳሌ፡-

ሰው የማያወቅ ሰው ክፉ ሰው ተፈጥሮ፣

ስሙን ሞት የሚሉት የማይሰጥ ቀጠሮ።

በግጥሙ የተሠመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ «ሞት» ማለት ነው።

ሀ. ሰው ነው ያልነውን ሰው ወሰደው ዘንድሮ።

ለ. የምትሰጪበት የምታበይበት ከሚፈርስ ቤትሽ።

ሐ. አልተጫነሽ እንደሁ አፈሩ ተንዶ።

መ. አንተ አለሽኝ ብዬ ስመካ ስመካ፣

ሠ. እንደመፋቂያ እንጨት ከመንገድ ቆረጠው።

ረ. ከእንግዲህ ቀረ መደባደብ።

ሰ. ያርሳል ያርሳል ያወጣል እዳሪ፣

ሸ. በእጇ ሥራን እንጂ በአፏ ሰው አትነካም።

ቀ. ሰው ነው ያልነውን ሰው ወሰደው ዘንድሮ።

በ. ዝንብ አይከለክል ራብ አይከላ።

ተ. ማረስ ነው እንጂ የጨባውን ሥር፣

ቸ. ማረስ ነው እንጂ እርፍን ነቅንቆ፣

## መጻፍ

### ቃላዊ ግጥም መጻፍ

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ግጥሞች ሀሳብ፣ በሁለት ወይም በሦስት ዓረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ጻፉ።

ሀ. ማረስ ነው እንጂ የጨባውን ሥር፣
ማረስ ነው እንጂ የግራሩን ሥር፣
ሥርቆት ምንድን ነው ሌባ ይመስል።

ለ. ሰው የማያውቅ ሰው ክፉ ሰው ተፈጥሮ፣
ስሙን ሞት የሚሉት የማይሰጥ ቀጠሮ፣
ሰው ነው ያልነውን ሰው ወሰደው ዘንድሮ።

#### ተግባር 2

የምትመርጡትን የቃላዊ ግጥም ዓይነት ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቃችሁ ጻፉ።

#### ተግባር 3

የሀዘንና የሠርግ ቃላዊ ግጥሞች (ከእያንዳንዱ ሁለት ሁለት) አሰባስባችሁ ይዘታቸውን በመተንተን አጭር ጽሑፍ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላዊ ግጥሞችን አዳምጦ መጻፍ

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ግጥሞች አዳምጣችሁ ሐረግ በሐረግ ፊደል ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ባህላዊ ግጥሞች

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን «ባህላዊ ግጥሞች» በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን የቃላዊ ግጥሞች ምንባብ በማስታወስ የሀዘንና የሠርግ ቃላዊ ግጥሞችን አንድነትና ልዩነት በቃላችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

#### ተግባር 1

በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን «የሀዘን ቃላዊ ግጥሞች» ከሚለው ሥር በ«ሀ» የተወከሉትን ስንኞች ጽሑፉን ሳትመለከቱ በቃላችሁ በሉ።

#### ተግባር 2

«ባህላዊ ግጥሞች» በሚል ርዕስ ሥር የቀረቡትን ግጥሞች የሐረግ አከፋፈልን ተከትላችሁና ዜማቸውን ጠብቃችሁ ተራበተራ አንብቡ።

## ማዳመጥ

### ባህላዊ ግጥሞች

### ቅድመማዳመጥ

### ግጥም አዳምጦ በቃል ማለት

#### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የፉከራና የቀረርቶ ግጥም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? አንድ ግጥም በቃላችሁ በሉ።

ለ. የአጨዳና የውቂያ ግጥምስ ታውቃላችሁ? አንድ ግጥም በቃላችሁ በሉ።

## የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

«ባህላዊ ግጥሞች» በሚል ርዕስ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን የፉከራ፣ የቀረርቶ፣ የአጨዳና የውቂያ ቃላዊ ግጥሞች የማታውቋቸውን ቃላት በንቃት እያዳመጣችሁ ጻፉ።

## አዳምጦ መረዳት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ግጥሞቹን ስታዳምጡ በፉከራና በቀረርቶ ግጥም መካከል ምን ልዩነት አስተዋላችሁ?

ለ. የሚከተሉት ስንኞች የሚያስተላልፉትን መልዕክት በአጭሩ በቃላችሁ ተናገሩ።

ዛሬ ማጭዴ ተበሳጭታለች፣

በጧት ተነስታ ጤፍ ትበላለች።

# ሰዋስው

## ዓረፍተነገሮችን ወደጥገኛ ሐረግ መለወጥ

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ግሶቻቸው እንዳይሠሩ በማድረግ ወደጥገኛ ሐረግ ለውጧቸው።

ምሳሌ፡-

| ዓረፍተነገር | ጥገኛ ሐረግ |
|---|---|
| ዙፋን ቀሚስ ለበሰች። | ዙፋን ቀሚስ ስትለብስ |

ሀ. በራፍ ይከፈት።

ለ. ምድር ተቆጣች።

ሐ. በአፏ ሰው ነካች።

መ. ክፉ ሰው ተፈጠረ።

ሠ. እንደመፋቂያ እንጨት ከመንገድ ቆረጡት።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥገኛ ሐረጎች ከተራ ዓረፍተነገር ጋር እያይዛችሁ የተስፋፉ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

ምሳሌ፡-

| <u>ጥገኛ ሐረግ</u> | <u>ዓረፍተነገር</u> | <u>የተስፋፋ ዓረፍተነገር</u> |
|---|---|---|
| ልጆች ሲያገቡ | ወላጆች ይደሰታሉ። | ልጆች ሲያገቡ ወላጆች ይደሰታሉ። |

| ጥገኛ ሐረግ | ዓረፍተነገር |
|---|---|
| ሀ. መሠረት ስትመጣ | ክንፈ መጽሐፉን ይሰጣት። |
| ለ. አልማዝ ሎሚ ስትጥል | ሀና አነሳችው። |
| ሐ. አርሶአደሮች በፍጥነት ስላጨዱ | አርሶአደርዎቹ ሥራቸውን በወቅቱ አጠናቀቁ። |
| መ. የትምህርትቤቱ ርዕሰ መምህር ሲመክሩ | ተማሪዎቹ መልዕክቱን በደንብ አዳመጡ። |
| ሠ. ቾኔ ምሣውን እንደበላ | ቾኔ ወደኳስ ጨዋታ ሄደ። |

## ተግባር 3

ጥገኛ ሐረግን ከዓረፍተነገር ጋር በማጣመር የተስፋፉ አምስት ዓረፍተነገሮችን በደብተራችሁ ጻፉ።

## ማንበብ

### የግጥም ቃላት

## ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን በመጠቀም ለቃላት ፍቺ መስጠት

#### ተግባር

የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላት ፍቺ ስጡ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ስንኝ | ሐ. አንጓ | ሠ. ምት | ሰ. ምናባዊ |
| ለ. ሐረግ | መ. ዜማ | ረ. ምጣኔ | ሸ. ቁጥብነት |

## የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

«የግጥም ቃላት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሐሳቦችን ርስበርስ በማስተሳሰር፣ ራስን በመጠየቅና በማጠቃለል ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ። በየመካከሉ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ የማንበብ ሂደት ጥያቄዎች መልስ እየሰጣችሁ ንባባችሁን ቀጥሉ።

### የግጥም ቃላት

በአማርኛ ስለግጥም ምንነት አንድ ወጥ ብያኔ ያለ አይመስልም። ግጥም ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ በመሆኑ የየዘመኑ ፍልስፍናና የባለሙያዎች አስተያየት ልዩነት ለብያኔው ወጥ አለመሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል። ግጥም ገጣሚዎች ምርጥ ቃላትን በመምረጥና ተገቢ በሆነ ቅደምተከተል በማዋቀር፣ በምናባቸው የፈጠሩትን ጥልቅ ስሜትና ሀሳብ የሚገልጹበት የፈጠራ ጥበብ ነው።

በአማርኛ ግጥም ውስጥ ተዘውታሪና መሠረታዊ የግጥም ቃላት አሉ። ስንኝ፣ ሐረግ፣ ምጣኔ፣ ምት፣ ዜማና አንጓ የተሰኙትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ስንኝ በአማርኛ ግጥም ከሚዘወተሩ የግጥም አላባዎች አንዱ ነው። ግጥም በተመጠኑና የተወሰነ ልክ ባላቸው መስመሮች የሚቀመር ሲሆን እያንዳንዱ መስመር ስንኝ ይባላል። ለምሳሌ:- ቀጥሎ የቀረበው ባለሁለት ስንኝ ግጥም ነው።

ስህተት ነው መሰለኝ ሰበቡን መሻት፣
«ለምንድነው» ማለት ለምን ምክንያት።

ስንኝ በሐረጋት ይዋቀራል። ሐረግም በአንድ ትንፋሽ የሚነበብና የተወሰኑ ቀለማትን የያዘ የስንኝ ክፋይ ነው። ከላይ የቀረበውን ግጥም የመጀመሪያውን ስንኝ ስናነብ የመጀመሪያው ቆምታ ወይም ረፍት የምናደርገው «ስህተት ነው መሰለኝ» የሚለውን ሐረግ በአንድ ትንፋሽ አንብበን ጨርሰን ነው። ስለሆነም «ስህተት ነው መሰለኝ» የሚለው አንድ ሐረግ ይሆናል ማለት ነው። ሁለተኛውን ስንኝ ስናነብ ደግሞ «ለምንድነው ማለት» የሚለው ላይ ቆምታ ወይም ረፍት በማድረግ ሐረጉን እንከፍላለን። በዚህም መሠረት ሐረጉን የከፈልነው ቃላቱን በመቁጠር ሳይሆን በምናነብበት ጊዜ በሚኖረን ቆምታ መሆኑን ማጤን ይገባል።

ግጥም የሚጻፈው ለስሜታችን እንዲደመጠንና ምሥል እንዲፈጥርልን ነው። ለዚህም ሲባል በግጥም ውስጥ ያሉት ሐረጋትና ስንኞች መመጠን አለባቸው። ምጣኔ የሐረጋትና የቀለማት መጠን የሚወሰንበት ልክ ሲሆን፣ ይህም ግጥሙ ምት እንዲኖረው ያደርጋል። ምት የሚመነጨው ከምጣኔው ሲሆን፣ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ቀለማትን መጥራት ምት ይፈጥራል። ስለዚህ የግጥም ስንኞች ይርዘሙም ይጠሩም፣ የአሰነኛኘት ስልቱም ይለያይ የግጥሙ ምጣኔና ምት የተስተካከለ ከሆነ ዜማ ይኖረዋል። ዜማ ተለጣጣቂነት ያላቸው የቃላት ቅንብሮች የሚያስገኙት ሥርዓታዊ የድምፅ አወራረድ ወይም ፍሰት ነው። የተሰተካከለ ምጣኔና ምት በሐረጉ ውስጥ ሲኖር ዜማ ይፈጥራል። ምጣኔ ለምቱ መኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ምጣኔ ከተዛባ ምቱ ይዛባል፤ ምቱ ከተዛባም ዜማው ይዛባል። በመሆኑም ሦስቱም (ምጣኔ፣ ምትና ዜማ) ለግጥሙ ጥራት ጠቀሜታቸው የጎላ ነው።

**ምጣኔ ለምት መኖር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው። ምጣኔ ከተዛባ ምቱ ይዛባል።**

ሌላው የግጥም አካል አንጓ ነው። አንጓ በግጥም ውስጥ ስለአንድ ሀሳብ በሚገልጹ ስንኞች ይዋቀራል። ስለሆነም የአንጓ ዋና መለያ የሀሳብ አንድነት ነው። በአንድ አንጓ ውስጥ የሚኖሩትን የስንኞች ብዛት የሚወስነው ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት በመሆኑ አንድ አንጓ ይህን ያህል ስንኝ ይይዛል ማለት አይቻልም። የዚህም ምክንያቱ አንጓ በሀሳብ አንድነት እንጂ በስንኝ ብዛት ስለማይወሰን ነው። አስረጂ እንዲሆን ቀጥሎ ያለውን ግጥም እንመልከት፡-

ለክንዴ አምባር አልል፣ ወለባ ለፀጉሬ፣
ማርዳ ድሪ ለጌጥ፣ አልቦ አልሻም ለግሬ፣
አልቻለም ደሞዜ እቁቤን ጨምሮ፣
አምናን እገዛበት ቀርቶብኝ ዘንድሮ።
ጣሉብኝ እርጥባን ምንተ... ስለ ስለት፣
በዋዛፈዛዛ ያሳለፍኩትን ቀን መልሼ ልግዛበት።

አይበርድም ነዲዱ ፍሙ እንኳ ቢከስል፣

እዩት እንደራቀ የባከነ ጊዜ ምን አለ 'ሚያቃጥል።

(ከአረጋሽ ሠይፉ፣ ርጥባን ከሚለው ርዕስ የተወሰደ)

ይህ ግጥም በስምንት ስንኞች የተዋቀረ ነው። ግጥሙ ሁለት ተቀራራቢ ግን የተለያዩ ሀሳቦችን በመያዙ ሁለት አንጓ አለው ማለት ይቻላል። በዚህ ግጥም የመጀመሪያ ሁለት ስንኞች፣ ሶስተኛውና አራተኛው ስንኞች በተመሳሳይ ፊደል ጨርሰዋል። እነዚህ ስንኞችም እኩል ጊዜ ስለሚወስዱ ግጥሙ ዜማ እንዲኖረው አድርገዋል። በሁለተኛው አንጓም የዚሁ ዓይነት አሰላለፍ ይታያል።

በአጠቃላይ የእነዚህ ሥነግጥማዊ ቃላት ለግጥም ኪነጥበባዊ ውበትን በመስጠት ግጥሙን ሳቢና ማራኪ ያደርጉታል።

(ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን፣* ከገጽ73-83 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በምትና በዜማ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለጹ።

ለ. በሐረግና በስንኝ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. አንጓ በስንኝ ብዛት የማይወሰነው ለምንድን ነው?

መ. በግጥም ውስጥ ሐረግ በቃላት ብዛት የማይወሰነው ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. ግጥም ዜማ ሰበረ የሚባለው መቼ ነው?

ረ. በግጥም ውስጥ ምጣኔ ለምት አስፈላጊ ነው የሚባለው ለምን ይመስላችኋል?

ሰ. «የግጥም ቃላት» ከሚለው ምንባብ 5ኛውን አንቀጽ በራሳችሁ አገላለጽ አሳጥራችሁ ጻፉ።

## 5ኛ ቀን

# ቃላት

## የግጥም ቃላትን ከማብራሪያቸው ጋር ማዛመድ

### ተግባር

በ«ሀ» ረድፍ ለሚገኙ የግጥም ቃላት ትክክለኛ ማብራሪያቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ሐረግ | ሀ. በግጥም ውስጥ ስለአንድ ሐሳብ የሚገልጹ የስንኞች ስብስብ |
| 2. ምጣኔ | ለ. በዓይነህሊናና በእዝነልቦና አግዝፎ ማየት፣ መስማት፣ መረዳት፣ መግለጽ |
| 3. ምት | ሐ. በአንድ ትንፋሽ የሚነበብና የተወሰኑ ቀለማትን ያካተተ የቃላት ስብስብ |
| 4. ዜማ | መ. አንድ የግጥም መስመር |
| 5. አንጓ | ሠ. ተለጣጣቂነት ያላቸው ቃላት ቅንብሮች የሚያስገኙት ሥርዓታዊ የድምፅ አወራረድ ወይም ፍሰት |
| 6. ስንኝ | ረ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የተወሰኑ ቀለማትን መጥራት |
| 7. ምናባዊ | ሰ የሐረግና የቀለማት መጠን የሚወሰንበት ልክ |

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## ቃላዊ ግጥም መጻፍ

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በመረጣችሁት የባህላዊ ግጥም ዓይነት የሐረግ ምጣኔው የተጠበቀ፣ ምትና ዜማው የተስተካከለ አንድ አጭር ግጥም በቡድን ጻፉ።

ለ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ግብረመልስ መሠረት የጻፋችሁትን ግጥም አርማችሁና አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሐ. በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በሚከተለው ግጥም በየስንኞቹ ያሉትን ሐረጎች ከፋፍላችሁ አሳዩ፤ ለአከፋፈላችሁ ምክንያት ስጡ።

ምሳሌ፡-

አሮጌውን ማሳ/ የሚያረገው አዲስ፣

ማርከሻው አርሶአደር/ የስራው መሐንዲስ።

(ሐረጎቹ የተከፈሉት በአንድ ትንፋሽ የሚነበቡትን ቃላት አንድ ላይ በማድረግ ነው።)

አንድ ቀን ብረት ድስት ሸክላ ድስትን አለው፣

እኔን ነው በሁሉም መልክህ የሚመስለው።

ወንድሜ ነህ እኮ ባታውቀው ነው እንጂ፣

ከዛሬ ጀምሮ እንሁን ወዳጅ።

እኔን እንደመቅረብ መሸሽህ ለምን ነው?

አካሌ አካላትህ የኔ ቤት ያንተም ነው።

አሁንም በል ተነስ የእኛ ፍቅር ይጥና፣

ሸርሸር እያልን እንናፈስና።

መፋቀራችንን ይይልን ሰው ሁሉ፣

የማንተዋወቅ ለምን ነው መምሰሉ።

አጥቂ ቢመጣብህ ዘሎ የሚማታ፣

እኔ እሆንሃለሁ ሀይለኛ መከታ።

ለፀሐይ ላቧራው እየሆንኩህ ድንኳን፣

እደግፍሀለሁ ቢያነቅፍህ እንኳን።

(ከበደ ሚካኤል። 1999። *ተረትና ምሳሌ ፩ኛ መጽሐፍ፣* 2ኛ እትም ገጽ 7፣ በከፊል የተወሰደ)

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ቃላትንና ሐረጋትን አዳምጦ በትክክል መጻፍ

### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላትና ሐረጋት አዳምጣችሁ የፊደላትን ቅርጽ ሳትቀይሩና ፊደል ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

## 6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የግጥም ቃላት

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ካነበባችሁት «የግጥም ቃላት» ከሚለው ምንባብ ውስጥ የምታስታውሷቸውን ቁልፍ የግጥም ቃላት ጥቀሱ።

ለ. የጠቀሳችኋቸውን የግጥም ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

«የግጥም ቃላት» የሚለውን ምንባብ በሐረግና በዓረፍተነገር መጨረሻ ንባባችሁን እየገታችሁ፣ ሥርዓተነጥቦችንና የጽሑፉን ድምጸት ጠብቃችሁ ድምፅ በማሰማት በፍጥነት አንብቡ።

# መናገር

## ድምጸትን ጠብቆ ቃላዊ ግጥሞችን ማለት (መናገር)

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላዊ ግጥሞች በቃላችሁ አጥንታችሁና ድምጸታቸውን ጠብቃችሁ ሐረግ በሐረግ በሉ (ተናገሩ)።

ሀ. አረምን ካረሙ ከሥሩ ነቅሎ ነው፣

ከቆረጡትማ ያው መተካቱ ነው።

ለ. ኧረ ተይ ዝንጀሮ ግፍ አትናገሪ፣

አሁን ትገኛለሽ ዐውድማ ስትጭሪ።

ሐ. በርዬ አንተን አንተን ጎንዬ አንተን አንተን፣

እንጀራህን እንጂ አያሳየኝ ሞትክን።

መ. ዱብ ዱብ ይላል እንደበረዶ፣

በልጅነቱ በረሃ ለምዶ።

ሠ. የጎበዝ ወዳጅ ታስታውቃለች፣

ከመሃል ገብታ በለው ትላለች።

## ሰዋስው

### በመሙያነት የገቡ ስማዊ ሐረጎችን መለየትና መጠቀም

#### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ በመሙያነት የገቡትን ስማዊ ሐረጎች አውጥታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ምት፣ ዜማና አንጓ የግጥም ቃላት ናቸው።

በዚህ ዓረፍተነገር «የግጥም ቃላት» የሚለው ስማዊ ሐረግ፣ «ናቸው» ለሚለው የመሆን ግስ «መሙያ» ነው።

ሀ. ሥነግጥም የፈጠራ ጥበብ ነው።

ለ. ምትና ዜማ ትልቅ ጥቅም አላቸው።

ሐ. ስንኝና ሐረግ የግጥም አላባዎች ናቸው።

መ. ሐረግ የስንኝ ግማሽ አካል ነው።

ሠ. ሥነግጥም የሥነጽሑፍ ዘርፍ ነው።

#### ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረቡትን ስማዊ ሐረጎች በመሙያነት በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፡- ግጥም <u>ረጅም ዕድሜ</u> አለው። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ስማዊ ሐረግ የመሆን ግሱ መሙያ ነው።

ሀ. ጥሩ ግጥም

ለ. ረጅም ሐረግ

ሐ. አዋቂ ልጅ

መ. የጽጌረዳ አበባ

ሠ. ቆንጆ ልጅ

ረ. ግሩም ዝንጀሮ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | መልዕክት-ኦች-ኡ-ን | መልዕክቶቹን |
| ለ | መ-ሥራት-ኣቸው-ን | መሥራታቸውን |
| ሐ | እየ-አማረ-ብ-ኣቸው | እያማረባቸው |
| መ | በሬ-ዎች-ኣቸው-ን | በሬዎቻቸውን |
| ሠ | ኑር-ኡ-ኣቸው-ን | ኑሯቸውን |
| ረ | ጠንካራ-ዎች-ኡ | ጠንካራዎቹ |

## ማንበብ

## የግጥም ጭብጥ ትንተና

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ግጥም ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. የግጥም ጭብጥ መተንተን ሲባልስ ምን ማለት ነው?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«የግጥም ጭብጥ ትንተና» የሚለውን ምንባብ፣ የማታውቋቸውን ቃላት እየመዘገባችሁ፣ የአንቀጹን ሐሳብ እያጠቃለላችሁና ያልገባችሁን እንደገና እየከለሳችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ። መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች መልስ እየሰጣችሁ ንባባችሁን ቀጥሉ።

## የግጥም ጭብጥ ትንተና

ግጥም የሚገለጸውን ሀሳብ ለአንባቢዎች ወይም ለአድማጮች በጉልህ እንዲታያቸውና እንዲሰማቸው አድርጎ ያቀርባል። የመግለፅና ምሥል የመፍጠር ኃይል ያላቸው ጠንካራ ቃላት በግጥም ውስጥ ይገኛሉ። ቃላቱ ሀሳብን አምቀው የመያዝ ኃይል ስላላቸውም የሚገልጹት ሀሳብ አይረሴነት አለው።

ግጥም ለስሜት ተብሎ ስለሚጻፍ የአድማጮችን ወይም የአንባቢዎችን ፍላጎት ያነሳሳል። በግጥም የሚገለፀው ሀሳብ ለስሜት ቅርበት አለው። ለዚህም ትልቁን ሚና የሚጫወቱት የግጥሙ ምርጥ ቃላት ናቸው። የግጥም ቃላት ተራ ሳይሆኑ ላቅ ያሉና ምርጥ በመሆናቸው በነዚህ ጠንካራ ቃላት የሚገለፁት ሀሳቦች ግጥሙን ሳቢና ማራኪ ያደርጉታል።

ገጣሚዎች ግጥምን የሚጽፉት ለግጥምነቱ ብቻ ብለው ሳይሆን አንድ ጠንካራ መልዕክት ለማስተላለፍ ነው። ያዩትን፣ የሰሙትን፣ ያጋጠማቸውንና በምናባቸው የፈጠሩትን ሀሳብ መሠረት አድርገው ይገጥማሉ። እነሱ የተሰማቸውን ሌሎችም እንዲሰማቸው ይጥራሉ። ለዚህም ቃላትን መርጠው ግጥሙን ያዋቅራሉ። ግጥም ቁጥብ በመሆኑ ከዝርው ጽሑፍ ይልቅ በተወሰኑ ቃላት ብዙ መልዕክቶችን ያስተላልፋል። በመሆኑም የአንድን ግጥም ጭብጥ ለመረዳት የገጣሚዎችን የአገጣጠም ስልት፣ ማኅበራዊ ዳራቸውንና የቃላት ምርጫቸውን በትኩረት ማየትና መረዳት ያስፈልጋል። ቀጥሎ የቀረቡትን ባለሁለት ስንኝ ቃላዊ ግጥሞች በምሳሌነት ወስደን እንመልከት።

በጎምላላ በሬ ግፋ ሲል ግፋ ሲል፣
ቆርቆሮ ቤት ሠራ ፋኖስ የሚመስል።

የቃላዊ ግጥሙን ጭብጥ ለመረዳት መታየት ያለባቸው ነጥቦች አሉ። ገጣሚው ማን ነው/ናት? መቼ ገጠመው/ገጠመችው? ምን አለ/አለች? የሚሉትን ማጤን ያስፈልጋል። ይህ ግጥም የሚገጠመው አርሶአደሮች በእርሻ ሥራ ወቅት ራሳቸውን ለማነቃቃት፣ ለማበረታትና ድካም እንዳይሰማቸው ለማድረግ ነው። የእርሻ ሥራ ሲነሳ በሬንና አርሶአደርን ነጥሎ ማየት አይቻልም። በሬው ጉልበታምና ጠንካራ በመሆኑ በርትቶ በማረሱ አርሶአደሮች ጥሩ ምርት አግኝተው ኑሯቸውን አሻሽለው ቆርቆሮ ቤት መሥራታቸውን ያመለክታል። የቆርቆሮውን ደረጃ ከፍ ለማድረግም ብርሃን ሰጪ ከሆነው ከፋኖስ ጋር በማወዳደር ሀሳቡን አጉልቶታል።

የመስቀል ጌታ ይጠምዳል ማልዶ፣
በረጅም ዋንጫ መቀልጠም ለምዶ።

አርሶአደሮች ለበሬዎቻቸው የተለያዩ መጠሪያዎች ያወጣሉ። በዚህ ግጥም «መስቀል» የተባለው «በሬ» ሲሆን «ጌታ» የተባለው ደግሞ «የበሬው ባለሀብት» ነው። የበሬው ባለቤቶች በጠዋት በመነሳት ወደእርሻ የሚሄዱ ጠንካራ አርሶአደሮች

ናቸው። ጠንክረው በመሥራታቸውም በቤታቸው ጠላና ምግብ እንደተፈለገ ይገኛል። የግጥሙ መልዕክትም ጠንክሮ በመሥራት የተፈለገውን መብላትም ሆነ መጠጣት እንደሚቻል የሚገልጽ ነው።

ጠንካራዎቹ አርሶአደሮች እንደሚሞገሱ ሁሉ ደካሞችም በስንፍናቸው ይንኳሰሳሉ። የሚከተለው ግጥም ይህን ይገልፃል።

እነነጭ ለባሽ እነጣተ ለምለም፣

እቤታቸው ሲኬድ የሚቀመስ የለም።

የግብርና ሥራ ከአቧራና ከጭቃ ጋር ያውላል፤ በመሆኑም ጠንካራ አርሶአደሮች በሥራ ወቅት የሚጨነቁት ለሥራቸው እንጂ ለአለባበሳቸው አይደለም። ምክንያቱም ከልፋት በኋላ የሚያገኙት ውጤት ደስታን ይፈጥርላቸዋልና። ነገርግን በግጥሙ እንደተገለጸው እየተወለወሉና የጸዳ እየለበሱ እጅን እያለሰለሱ ቢታዩ የሚላስ የሚቀመስ በማጣት ለችግር ይጋለጣሉ። ስለዚህ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጠንክሮ በመሥራት መበልጸግ መቻልን ነው። ግጥሞቹ ጠንካራ አርሶአደሮችን በማበረታታት የበለጠ እንዲሠሩ፣ ሰነፎች ደግሞ ከስንፍናቸው እንዲላቀቁ ያስተምራሉ።

በአጠቃላይ የምናነበውን ግጥም ጭብጥ ለመረዳት ግጥሙን ደጋግሞና ትኩረት ሰጥቶ ማንበብ ይጠቅማል። በንባብ ወቅትም የገጣሚዎችን የቃላት ምርጫ፣ የአጻጻፍ ስልትና የሐረግ አወቃቀር ማጤን ይገባል።

(ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን፣* ከገጽ 73-83 ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

በ«ሀ» ረድፍ ለሚገኙት መግለጫዎች የሚስማማቸውን ቃላት ወይም ሐረጋት ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ቁጥብ ነው። ለአድማጮች ሀሳቡ በጉልህ እንዲሰማቸው ያደርጋል። በተወሰኑ ቃላት ብዙ መልዕክቶች ያስተላልፋል። | ሀ. ገጣሚዎች |
| 2. ያዩትን፣ የሰሙትንና የገጠማቸውን ሌሎች እንዲሰማቸው ያደርጋሉ። | ለ. የግጥም ቃላት |
| 3. ተራ ሳይሆኑ ላቅ ያሉና ምርጥ ናቸው። ሀሳብን አምቀው የመያዝ ኃይል አላቸው። የመግለፅና ምሥል የመፍጠር ኃይል አላቸው። | ሐ ግጥም |

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

1. የቃላዊ ግጥምን ጭብጥ ለመረዳት መታየት ያለባቸው ነጥቦች ምን ምን ናቸው?
2. የሚከተሉትን ቃላዊ ግጥሞች ጭብጥ በጽሑፍ ግለጹ።

   ሀ. በሬ አይደለም ወይ ያቀናው ቤቱን፣ እንኳን ጥሬውን ይብላው ዱቄቱን።

   ለ. ወይኖ ቀና በል ጃሪ ተራመድ፣ ራስ ካልቻሉ አይወድም ዘመድ።

   ሐ. የፊተለች እንደሁ አስመስላ ጭራ፣ የጋገረች እንደሁ አስመስላ ሞራ፣ ማን ይወዳደራል ከዚያች ቆንጆ ጋራ።

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ፍቺ መስጠት፣ የግጥም ቁልፍ ቃላትን መለየት

## ተግባር 1

«የግጥም ጭብጥ ትንተና» በሚለው ምንባብ መሠረት ከዚህ ቀጥሎ በዓረፍተነገሮቹ የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ግለጹ።

ሀ. የግጥም ቃላት ሀሳብን <u>አምቀው</u> የመያዝ ኃይል አላቸው።

ለ. ግጥም የአንባቢዎችን ፍላጎት <u>ያነሳሳል</u>።

ሐ. የግጥም ቃላት ተራ ሳይሆኑ <u>ላቅ ያሉ</u> ናቸው።

መ. የግጥም ቃላት ለስሜት <u>ቅርበት</u> አላቸው።

ሠ. በግጥም ውስጥ የመግለጽና <u>ምሥል</u> የመፍጠር <u>ኃይል</u> ያላቸው ቃላት ይገኛሉ።

## ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት መልሱ።

ሀገሬ ድምፅሽን ቀርቤ እንዳልሰማ፣
አላጥፍ አልጠቀልል መሬት አይደል ሸማ።
ክል እያለ መጥቶ የዝማሬሽ ቃና፣
ያማልለኝ ገባ ያዘናጋኝ ገባ ከሩቁ ሆነና።

ሀ. ግጥሙ ስንት ስንኞች አለው?

ለ. በግጥሙ ውስጥ ስንት ሐረጎች አሉ?

ሐ. የግጥሙን የመጨረሻ ስንኝ ሐረጎች ከፋፍላችሁ አሳዩ።

መ. ግጥሙ ዜማ ይሰብራል? የሚሰብር ከሆነ የትኛው ሐረግ ላይ ነው የሚሰብረው?

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ቃላዊ ግጥም መጻፍ

#### ተግባር 1

ከሀዘን፣ ከሠርግና ከሙገሳ የቃላዊ ግጥም አይነቶች አንዱን መርጣችሁ ሦስት ባለመንቶ (ባለሁለት) ስንኝ ግጥሞች ጻፉ።

#### ተግባር 2

በተግባር «1» የጻፋችኋቸውን ቃላዊ ግጥሞች የሐረግ ምጣኔያቸውን፣ ምታቸውን፣ የስንኞችን ቤት ዓመታትና ዜማ በማረጋገጥ ከልሳችሁ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላዊ ግጥሞችን አዳምጦ መጻፍ

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላዊ ግጥሞች አዳምጣችሁ የሐረግ አከፋፈላቸውንና የፊደል አሰዳደራቸውን ጠብቃችሁ በትክክል ጻፉ።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የግጥም ጭብጥ ትንተና

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

በተግባር «1» የቀረበው ቀን «የግጥም ጭብጥ ትንተና» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሷቸውን ዋናዋና ነጥቦች በቃላችሁ ተናገሩ።

## ማንበብ

### ተግባር

«የግጥም ጭብጥ ትንተና» የሚለውን ምንባብ የጽሑፉን ድምጸትና ሥርዓተነጥብ ጠብቃችሁ አንቀጽ በአንቀጽ እየተቀያየራችሁ ተራበተራ አንብቡ።

## መናገር

### ግጥሞችን በቃል መናገር

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ግጥሞች የሐረግ አከፋፈላቸውን ተከትላችሁና ዜማቸውን ጠብቃችሁ ተራበተራ በቃላችሁ በሉ (ተናገሩ)።

ሀ. አባሮ ገዳይ ቆንጥር ለቆንጥር፣
ትንሽ ለነፍሱ የማይጠረጥር።

ለ. ከረጅም ዛፍ ላይ ታርፋለች ገዴ፣
አሻግሮ ገዳይ በረጅም ጓንዴ።

ሐ. ኸረ ማረስ ማለት ጎድጓዳ ማሳነው፣
ኸረ መጥመድ ማለት የላም ልጅ በሬ ነው፣
ኸረ መጫን ማለት ዋርዳ በቅሎ ነው።
ከዚህ በተረፈ ውሽልሽል ኑሮ ነው።

### ተግባር 2

በተግባር «1» የቀረቡት ግጥሞች የሚያስተላልፉትን ሀሳብ በቡድን ተወያይታችሁ በተወካዮቻችሁ አማካይነት ለክፍላችሁ ተማሪዎች በቃላችሁ አቅርቡ።

## ሰዋስው

### ጥገኛ ሐረጎችን ከነጠላ ዓረፍተነገር ጋር በማያያዝ ዓረፍተነገር ማስፋፋት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥገኛ ሐረጎች ከነጠላ ዓረፍተነገር ጋር አያይዛችሁና አስፋፍታችሁ ጻፉ።

| ጥገኛ ሐረጎች | ተራ ዓረፍተነገሮች |
|---|---|
| ሀ. የግጥም ቃላት ጠንካራ ምሥል ስለሚፈጥሩ | የግጥም ቃላት ሀሳብን በጉልህ ያቀርባሉ። |
| ለ. ግጥም ለስሜት ስለሚጻፍ | ግጥም የአንባቢን ፍላጎት ያነሳሳል። |
| ሐ. የግጥም ቃላት ምርጥና ጠንካራ ስለሆኑ | የግጥም ቃላት ሀሳቡን ማራኪ ያደርጉታል። |
| መ.ግጥም ቁጥብ ስለሆነ | ግጥም በጥቂት ቃላት ብዙ መልዕክት ያስተላልፋል። |
| ሠ. ግጥም በአጭር ስንኝ ስለሚጻፍ | ግጥም በጥቂት ቃለት ሰፊ ሀሳብ ያስተላልፋል። |

## ተግባር 2

ስማዊ ሐረጎችን በመሙያነት በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን አሟልታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

ጥያቄ፡- ካሰች ____________ ነበረች።

መልስ፡- ካሰች ፈጣን ሯጭ ነበረች።

ሀ. ሁለቱ ልጆች ____________ ናቸው።

ለ. አስቴር ____________ ናት።

ሐ. አስቻለው ____________ ነው።

መ. አንተ ____________ ነህ።

ሠ. አንቺ ____________ ነሽ።

ምዕራፍ 5

# ሥነሕዝብ

የውልደት ምጣኔ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ምጣኔሀብት-ያዊ | ምጣኔሀብትያዊ |
| ለ | ሕጻን-ኣት | ሕጻናት |
| ሐ | ሥነ-ሕዝብ | ሥነሕዝብ |
| ሠ | ተወሰን-ኡ | ተወሰኑ |
| ረ | ህብረተሰብ-ኦች-ን | ህብረተሰቦችን |
| ሰ | ቀመር-ኡ-ን | ቀመሩን |
| ሸ | መቆጣጠር-ኢ-ያ-ዎች-ኡ-ን | መቆጣጠሪያዎቹን |

## ማንበብ

## የውልደት ምጣኔ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ጽንሰሀሳብ በቃላችሁ ተናገሩ።

ሀ. ምጣኔ

ለ. የውልደት ምጣኔ

ሐ. ግርድፍ የውልደት ምጣኔ

መ. መገመት

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

ሀ. «የውልደት ምጣኔ» በሚለው ምንባብ ውስጥ ያለውን ሠንጠረዥ መምህራችሁን እየተከተላችሁ ሁለት ጊዜ አንብቡ።

ለ. የምንባቡን የመጨረሻ ሦስት አንቀጾች መምህራችሁን እየተከተላችሁ አንብቡ።

ሐ. «የውልደት ምጣኔ» የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሠረት ተራበተራ አንብቡ።

## የውልደት ምጣኔ

የውልደት ምጣኔ እናቶች ፀንሰው የሚወልዷቸውን የሕጻናት መጠን ያመለክታል። የሕዝብ አኗኗር ዘይቤ፣ ባህልና የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን የሚያሳይ የሥነሕዝብ መለኪያ በመሆን ያገለግላል። የሰዎች የአኗኗር ዘይቤ በተለያየ ቁጥር የቤተሰብ ምጣኔ ለመጠቀም የሚኖራቸውም ፍላጎት ይለያያል። የተወሰኑ ወላጆች ወሊድን የመቆጣጠር ፍላጎትና ውሳኔ የመስጠት ጥንካሬ መላላት የውልደት ምጣኔን ከፍ ያደርጋል። ሌሎችም እንዲሁ ለመውለድ ካላቸው ጉጉት የተነሳ በተከታታይ ይወልዳሉ። ይህም በራሱ የውልደት ምጣኔውን መጨመሩ አይቀርም።

የሕዝብ የመውለድ አቅም (የሥነተዋልዶ መጠን) የተለያዩ ማኀበራዊ፣ ባህላዊና ምጣኔሀብታዊ ምክንያቶች ውጤት ነው። የሕዝብን የውልደት መጠን በተለያዩ የውልደት መለኪያዎች መለካት ይቻላል። ዋና ዋናዎቹ የውልደት መለኪያዎች ግርድፍ፣ አጠቃላይ ዕድሜን ያማከለና አማካይ የውልደት ምጣኔ ናቸው።

ግርድፍ የውልደት ምጣኔ በአብዛኛው የተለመደ የውልደት ልኬት ሲሆን፣ ባንድ አካባቢ በዓመቱ አማካይ ከሚኖረው አጠቃላይ ሕዝብ በህይወት የተወለዱ ሕጻናትን ቁጥር ያሳያል። በአንድ ዓመት አጠቃላይ በህይወት የተወለዱ የሕጻናት ቁጥር

በአገሪቱ ወይም በአንድ አካባቢ ላሉ አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር በማካፈል የሚገኝ ሲሆን፣ ውጤቱም ከ1000 ሰዎች የተወለዱ ሕጻናትን ቁጥር ይገልፃል። የዚህም ቀመር የሚከተለውን ይመስላል።

$$\text{ግርድፍ የውልደት ምጣኔ} = \frac{\text{በዓመቱ በህይወት የተወለዱ ሕጻናት ቁጥር}}{\text{በዓመቱ ያለው አጠቃላይ ሕዝብ አማካይ}} \times 1000$$

አጠቃላይ የውልደት ምጣኔ አካፋዩ አጠቃላዩ የሕዝብ ቁጥር ሳይሆን መውለድ የሚችሉ ሴቶች ቁጥርን መነሻ በማድረግ የሚሰላ ነው። በመሆኑም ከግርድፍ የውልደት መጠን የተሻለ የውልደት መለኪያ ነው። ስሌቱ መውለድ ከሚችሉ 1000 ሴቶች መካከል የተወለዱ ሕጻናትን ቁጥር ያሳያል። ይህም ቀጥሎ ባለው ቀመር ይገለጻል።

$$\text{አጠቃላይ የውልደት ምጣኔ} = \frac{\text{በዓመቱ በህይወት የተወለዱ ሕጻናት ቁጥር}}{\text{በዓመቱ መውለድ የሚችሉ እናቶች ቁጥር (ከ15-49 ዓመት)}} \times 1000$$

በዚህ ስሌት መሠረት ባንድ ሀገር ወይም አካባቢ ከ15-49 ዓመት ከሚገኙት 1000 እናቶች መካከል ምን ያህል ሕጻናት በህይወት እንደተወለዱ መረዳት ይቻላል። ስሌቱ መውለድ የሚችሉ እናቶችን ከግምት ያስገባ በመሆኑ የውልደት መጠንን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ያስችላል።

ዕድሜን ያማከለ የውልደት ምጣኔ መለኪያ ደግሞ መውለድ በሚችሉ በተወሰነ ዕድሜ ክልል ካሉ እናቶች የተወለዱ ሕጻናትን ቁጥር በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ካሉ ሁሉም ሴቶች ጋር በማነጻጸር ይታወቃል። ስሌቱ በተለያየ የዕድሜ ክልል ከሚገኙና መውለድ ከሚችሉ እናቶች በህይወት የተወለዱ ሕጻናትን ቁጥር በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ከሚገኙ 1000 ሴቶች ጋር በማነጻጸር ይገኛል። ቀመሩም የሚከተለው ነው።

$$\text{ዕድሜን ያማካለ የውልደት ምጣኔ} = \frac{\text{በተወሰነ የዕድሜ ክልል ካሉ እናቶች የተወለዱ ሕጻናት ቁጥር}}{\text{በተመሳሳይ ዕድሜ ክልል ያሉ ሴቶች ብዛት}} \times 1000$$

በዚህ ዘዴ በየትኛው የዕድሜ ክልል ያሉ ሴቶች የበለጠ መውለድ እንደሚችሉ ይታወቃል። ዘዴው የተሻለ ገላጭና ከፍተኛ የውልደት መጠን ያለበትን የዕድሜ ክልል ያሳያል።

አማካይ የተዋልዶ ምጣኔ እናት በህይወት ዘመኗ በአማካይ የምትወልዳቸውን የሕጻናት መጠን ይጠቁማል። አንዲት እናት፣ ልጅ ልትወልድ በምትችልባቸው

ዓመታት ሁሉ ብትወልድ ምን ያህል ልጆች እንደምትወልድ ያሳያል። በዚህ ስሌት በተለያየ የዕድሜ ክልል ላይ ያሉ ሴቶችን የመውለድ መጠን እንደሚከተለው ማነጻጸር ይቻላል።

ዕድሜን ያማከለ የውልደት ምጣኔ

| የእናቶች ዕድሜ | የሴቶች ቁጥር | በእያንዳንዱ የዕድሜ ክልል የተወለዱ ሕጻናት | የውልደት ምጣኔ |
|---|---|---|---|
| 15-19 | 258,600 | 8,504 | 32.9 |
| 20-24 | 265,320 | 30,600 | ? |
| 25-29 | 242,580 | 15,450 | ? |
| 30-34 | 219,800 | 19,200 | ? |
| 35-39 | 150,230 | 12,100 | ? |
| 40-44 | 906,000 | 34,500 | ? |
| 45-49 | 72,000 | 104 | ? |

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የሥነሕዝብን መሠረተ ሀሳብ ግለጹ።

ለ. በግርድፍ የውልደት ምጣኔና በአጠቃላይ የውልደት ምጣኔ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. ከአጠቃላይ የውልደት ምጣኔና ዕድሜን ካማከለ የውልደት ምጣኔ የትኛው የተሻለ ይመስላችኋል? ለምን?

መ. ከ25-29 ዕድሜ ያላቸው እናቶች የውልደት ምጣኔ ስንት ነው? እንዴት ይታወቃል?

ሠ. በየትኛው የዕድሜ ክልል የሚገኙ እናቶች ናቸው ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ ያላቸው? ለምን?

ረ. ከሠንጠረዡ እንደሚታየው ከ45-49 የዕድሜ ክልል ከሚገኙ እናቶች የተወለዱ ሕጻናት ቁጥር ከሁሉም የዕድሜ ክልሎች ያነሰ ነው። ይህ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላት በተለያዩ ቅርጾች መጻፍ፣ ፍቺ መስጠትና በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ጻፉ፡

ምሳሌ፡- ውልደት

ወለደች ወላድ መውለድ መውለጃ አወላለድ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ምጣኔ | ለ. ልኬት | ሐ. ፅንሰት | መ. ቀመር |

### ተግባር 2

ከላይ በተግባር «1» በተለያዩ ቅርጾች የጻፋችኋቸውን ቃላት ያላቸውን መጠነኛ የፍቺ ልዩነት በጽሑፍ ግለጹ።

ምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ወለደች | ነፍሰጡር የነበረችው እናት ተገላገለች፣ ልጅ ወለደች |
| ወላድ | መውለድ የምትችል ሴት |
| መውለድ | የመውለድ ድርጊት መጠሪያ |
| መውለጃ | የመውለድ ድርጊት የሚካሄድበት ቦታ ወይም ጊዜ |
| አወላለድ | የመውለድ ድርጊት ሂደት ባህርይ |

### ተግባር 3

በተግባር «1» የጻፋችኋቸውን የተለያዩ የቃላት ቅርጾች የፍቺ ልዩነቶች በዓረፍተነገር አሳዩ።

ምሳሌ፡-

ሀ. ይፍቱ ቆንጆ ሴት ልጅ <u>ወለደች።</u>

ለ. <u>ለወላድ</u> ሴቶች እንክብካቤ ማድረግ ይገባል።

ሐ. አንዲት እናት <u>መውለድ</u> የምትችለው ጤነኛ ስትሆን ነው።

መ. ሆስፒታሎች <u>የመውለጃ</u> ክፍሎችን በንጽህና መያዝ ይገባቸዋል።

ሠ. የእናቶች <u>አወላለድ</u> በሆስፒታልና በግል መኖሪያቤት ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በማነጻጸር ስልት አንቀጽ መጻፍ

#### ተግባር 1

በግርድፍና በአጠቃላይ የውልደት ምጣኔ መለኪያዎች መካከል ያለውን ልዩነት በማነጻጸር ሁለት አንቀጾች ጻፉ።

#### ተግባር 2

«የውልደት ምጣኔ» በሚለው ምንባብ ውስጥ በሚገኘው ሠንጠረዥ «የውልደት ምጣኔ» በሚለው ሥር በጥያቄ ምልክት የታለፉትን ውጤቶች በቀመሩ መሠረት አስልታችሁ ካሟላችሁ በኋላ በማነጻጸር ሁለት አንቀጽ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ውስብስብ ቃላትን አዳምጦ መጻፍ

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በትክክል በማዳመጥ ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የውልደት ምጣኔ

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «የውልደት ምጣኔ» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ ስንት የቀመር ዓይነቶች ታስታውሳላችሁ? በስም ጥቀሱ።

ለ. ዝቅተኛ የውልደት ምጣኔ የታየው በየትኛው የእናቶች የዕድሜ ክልል ነበር? ለምን ይመስላችኋል?

## ማንበብ

### ተግባር

ሀ. «የውልደት ምጣኔ» ከሚለው ምንባብ ውስጥ ሦንጠረዡንና የተለያዩ ቀመሮች መምህራችሁን እየተከተላችሁ በፍጥነት አንብቡ።

ለ. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ ሠንጠረዡንና ቀመሮቹን በፍጥነት አንብቡ።

ሐ. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ «የውልደት ምጣኔ» የሚለውን ምንባብ ተራበተራ በፍጥነት አንብቡ።

## ማዳመጥ

# ወላጆችና ... የሕዝብ ቁጥር ዕድገት

## ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. የሕዝብን ቁጥር ዕድገት መጠን ከፍ የሚያደርጉት ምን ምን ነገሮች ይመስሏችኋል? ለምን?

ሐ. የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ እናቶችን ስለማስተማር ጠቀሜታ የምታውቁትን ተናገሩ።

## የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

«ወላጆችና... የሕዝብ ቁጥር ዕድገት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በንቃት እያዳመጣችሁ ቁልፍ ቃላትንና ሐረጋትን በመለየት በደብተራችሁ ጻፉ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

በ«ሀ» ሥር የቀረቡትን ሀሳቦች በ«ለ» ሥር ከቀረቡት ሀሳቦች ጋር በፍቺ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. በለጋ ዕድሜ መውለድ | ሀ. ልጅ መውለድ የፈጣሪ ጸጋ ነው። |
| 2. ማኅበራዊ አመለካከት | ለ. ያለዕድሜ ጋብቻ። |
| 3. ሀይማኖታዊ አመለካከት | ሐ. ልጅ መውለድን እንደጸጋ መቁጠር። |
| 4. የውልደት መጠን | መ. ያልተዛባ የቤተሰብ ምጣኔ ግንዛቤ |
| 5. የእናቶች መማር | ሠ. እናቶች የሚወልዷቸው የሕጻናት ብዛት |

### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «ሴቶችን ማስተማር ማኅበረሰብን ማስተማር ነው» የሚለውን አባባል አብራሩ።

ለ. ልጆችን መጥኖ ስለመውለድ ጠቀሜታ ግለጹ።

## ሰዋስው

### ነጠላ ዓረፍተነገሮችን በማቀናጀት ድርብ ዓረፍተነገር መመሥረት

ማስታወሻ

በወደረኛ መስተጻምር የተያያዙ ከሁለት በላይ ራሳቸውን የቻሉ ዓረፍተነገሮች ያለው ዓረፍተነገር ድርብ ዓረፍተነገር ይባላል።

ምሳሌ:- ምህረት መጣች። ምህረት ወደቤቷ ሄደች። } ምህረት መጣችና ወደቤቷ ሄደች።

(ዳኛቸው። 1988፤102)

## ተግባር

የሚከተሉትን ነጠላ ዓረፍተነገሮች በማቀናጀት ድርብ ዓረፍተነገር መሥርቱ።
ምሳሌ፡-

ሀ. 1. የእያንዳንዱ ቤተሰብ ቁጥር ጨምሯል።

2. የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ማደጉ አይቀርም።

ድርብ ዓረፍተነገር፡-

የእያንዳንዱ ቤተሰብ ቁጥር ጨምሯል፤ ስለዚህ የሕዝብ ቁጥር በፍጥነት ማደጉ አይቀርም።

ለ. 1. በንግድ ሥራ በመሰማራት አትራፊ ሁኚ።

2. በርትተሽ በመማር ኑሮሽን ለውጪ።

ድርብ ዓረፍተነገር፡-

በርትተሽ በመማር ኑሮሽን ለውጪ ወይም በንግድ ሥራ በመሰማራት አትራፊ ሁኚ።

ሀ. 1. ያላቻ ጋብቻ ሴቶችን ለማኅበራዊ ችግር ያጋልጣል።

2. ያላቻ ጋብቻ ሴቶችን ለጤና ችግር ያጋልጣል።

ለ. 1. አንዳንድ ቤተሰቦች ወሊድን የመቆጣጠር ፍላጎት የላቸውም።

2. የቤተሰብ ምጣኔን ለመተግበር ያስቸግራሉ።

ሐ. 1. የተማሩ እናቶች ልጆችን አራርቀው ይወልዳሉ።

2. የተማሩ እናቶችን ስለቤተሰብ ምጣኔ ማስተማር ከባድ አይሆንም።

መ. 1. የተማሩ ወላጆች ያላቻ ጋብቻን ይከላከላሉ።

2. የተማሩ ወላጆች ልጆችን መጥነው ይወልዳሉ።

ሠ. 1. ወላጆች ይመጣሉ።

2. መውለጃ ክፍሉን ለወላዶች እናዘጋጅላቸው።

## ማንበብ

### የሞት ምጣኔ

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም፣ የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ስለሞት ምጣኔ» አንብባችሁ ወይም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. የሞት መጠን ሊለካ የሚችል ይመስላችኋል? እንዴት?

ሐ. ውልደትና ሞት ከሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ምን ግንኙነት እንዳላቸው የምታውቁትን ተናገሩ።

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«የሞት ምጣኔ» የሚለውን ምንባብ፣ የማታውቋቸውን ቃላትና ሐረጋት እየጻፋችሁና ሀሳቡን እየተረዳችሁ በየግላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ። ሦስት ሦስት አንቀጾች አንብባችሁ ስትጨርሱ በማታውቋቸው ቃላትና ሐረጋት ላይ በጥንድ እየተወያያችሁ ንባባችሁን ቀጥሉ።

### የሞት ምጣኔ

የሞት ምጣኔ የሞት መከሰትን የሚያሳይና የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን የሚወሰን የሥነሕዝብ ጽንሰሀሳብ ነው። ሞት በተለያዩ ምክንያቶች ይከሰታል። ከምክንያቶቹ መካከል ጦርነትንና ፍልሰትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ጦርነት የሀገርን ሰላም በማደፍረስ ሰዎችን ከቤት ንብረታቸው ያፈናቅላል፣ ህይወትን ያሳጣል። በተለይ ሕጻናትና ሴቶች ግንባር ቀደም ተጠቂ በመሆናቸው አካባቢያቸውን ትተው ይሰደዳሉ። በሄዱበት አካባቢም የጤና፣ የምግብና የውኃ አቅርቦት በተሟላ መልኩ ስለማያገኙ ለበሽታና ለሞት ይዳረጋሉ። በአጠቃላይ በጦርነት ቀጣና ውስጥ የሚገኙ ህዝቦች ሞትና ፍልሰት ያጋጥማቸዋል።

ፍልሰት በራሱ ለሰዎች ሞት ምክንያት ይሆናል። በአለንበት ግሎባላይዜሽን (ሉአላዊነት) ዘመን ዓለም ወደአንድ መንደር እየተለወጠች በመምጣቷ ከሀገር


ወደሀገር የሚደረገው ፍልሰት ጨምሯል። የታዳጊ ሀገር ዜጎች የተሻለ ክፍያ ፍለጋ ከሀገራቸው ይወጣሉ። ፍልሰቱ በአብዛኛው በህገወጥ መንገድ ስለሚካሄድ ሰዎች በየበርሃው በየባህሩና በየውቅያኖሱ ይሞታሉ፤ ዕድል ቀንቷቸው መሄድ ወደሚፈልጉት ሀገር የደረሱትም በአሠሪዎቻቸው የተለያዩ ግፎችና በደሎች ይፈጸምባቸዋል፤ ለሞትም ሊዳረጉ ይችላሉ። እነዚህና ሌሎችም ተዳምረው የሞት መጠንን ከፍ ያደርጉታል።

የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን ለመወሰን የውልደት ምጣኔ ብቻ ሳይሆን የሞት ምጣኔም ከግምት መግባት አለበት። እንደውልደት ምጣኔ ሁሉ የሞት ምጣኔንም የተለያዩ መለኪያዎችን በመጠቀም ማስላት ይቻላል። ከነዚህም መካከል ግርድፍ የሞት ምጣኔ ይጠቀሳል። ግርድፍ የሞት ምጣኔ በአንድ አካባቢ በተወሰነ ጊዜ በዓመት ውስጥ የሞቱ አጠቃላይ ሰዎች በዓመቱ አማካይ ካለው አጠቃላይ ሕዝብ ጋር ሲነፃፀር ያለውን ውጤት በ1000ኛ የሚያሳይ ነው። ይህም በአብዛኛው የተለመደ ስሌት ሲሆን ከ1000 ሰዎች መካከል የሞቱትን ሰዎች መጠን ያሳያል። ነገርግን በአንድ ሀገር ያለውን የሞት ቁጥር በትክክል ሊያሳይ አይችልም። ምክንያቱም በተለያዩ የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎች ተመሳሳይ የሞት ምጣኔ የሌላቸው በመሆኑ ነው።

$$\text{ግርድፍ የሞት ምጣኔ} = \frac{\text{በየዓመቱ የሞቱ ሰዎች ቁጥር}}{\text{በዓመቱ አማካይ ያለው አጠቃላይ ሕዝብ}} \text{X1000}$$

| የሞት ምጣኔ በኢትዮጵያ | |
|---|---|
| ዓ.ም.(እ.አ.አ.) | መጠን |
| 2000 | 17.63 |
| 2001 | 17.84 |
| 2002 | 18.04 |
| 2003 | 20.17 |
| 2004 | 20.36 |
| 2005 | 15.06 |
| 2006 | 14.86 |
| 2007 | 14.67 |
| 2008 | 11.83 |
| 2009 | 11.55 |
| 2010 | 11.29 |
| 2011 | 11.04 |

| | |
|---|---|
| 2012 | 10.79 |




ግርድፍ የሞት ምጣኔ ስሌት ከፍተኛ የሞት መጠን የሚታይበትን የዕድሜ ክልል የማያሳይ በመሆኑ ዕድሜን መሠረት ያደረገ የሞት መጠን ልኬት አስፈላጊ ይሆናል። የሞት መጠን በሕጻንነት ዕድሜ ከፍተኛ ይሆንና በአማካይ ዕድሜ ላይ ሲቀንስ በእርጅና ዕድሜ በሚገኙ ሰዎች እየጨመረ ይመጣል።

ዕድሜን መሠረት ያደረገ የሞት መጠን ልኬትም በተለያዩ የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ ሰዎችን የሞት መጠን በትክክል ሊያሳይ የሚችል ቀመር ነው። ስሌቱ በተወሰነ የዕድሜ ክልል የሞቱ ሰዎች ቁጥርን በተመሳሳይ  የዕድሜ ክልል ከሚገኙ ጠቅላላ ህዝቦች በማነፃፀር የሚገኝ ነው።

$$\text{ዕድሜን መሠረት ያደረገ የሞት ምጣኔ} = \frac{\text{በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሞቱ ሰዎች ቁጥር}}{\text{በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ አጠቃላይ ሕዝብ}} \text{X1000}$$

ብዙውን ጊዜ የሞት መጠን በዕድሜ ገደብ የሚሰላው በየአምስት ዓመታት ልዩነት ነው። ይህ የሞት ስሌት በጾታ፣ ለሞት ምክንያት በሆኑ ምክንያቶች፣ በሥራ ዘርፍ በመከፋፈል የሞት መጠንን ለማወቅ የሚያስችል በመሆኑ የበለጠ ገላጭና ተመራጭ ዘዴ ነው።

ለምሳሌ፣ በአንድ ወረዳ በ2006፣ ከ25-29 ዓመት ዕድሜ ካላቸው 29,894 ከሚሆኑ ሰዎች መካከል 182 የሚሆኑት ሰዎች በሞት ተለይተዋል እንበል። በዚህ የዕድሜ ክልል የሞት ምጣኔው እንደሚከተለው ይሰላል።

$$\text{ዕድሜን መሠረት ያደረገ የሞት ምጣኔ} = \frac{182}{29894} \times 1000 = 6.088$$

ይህም ውጤት ሲተረጎም በእያንዳንዱ 1000 ከሚሆኑ ከ25-29 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ሰዎች መካከል 6.088 ይሞታሉ ማለት ይሆናል።


በአጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ከሁለቱ የሥነሕዝብ የለውጥ ምክንያቶች ጋር በቀጥታ ይቆራኛል። ከፍተኛ የውልደት ምጣኔ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ያስከትላል። ከፍተኛ የሞት ምጣኔም የሕዝብ ቁጥርን ይቀንሳል። ነገርግን ሁለቱ ክስተቶች በአንድ ላይ ስለሚከሰቱ የሕዝብ ቁጥር እድገቱ የሁለቱ ንፅፅር ውጤት ይሆናል። ይሁን እንጂ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን ለመግታት ሁለቱን ማጣጣም መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ከፍተኛ የሞት መጠን በራሱ ማኅበራዊ ችግር ሊሆን ስለሚችል ነው። በመሆኑም የውልደት መጠንን በመቀነስ የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን ማመጣጠን የተሻለ መንገድ ይሆናል።

## አንብቦ መረዳት

«የሞት ምጣኔ» በሚለው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ተግባራት ሥሩ።

### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት ግርድፍ የሞት ምጣኔንና ዕድሜን መሠረት ያደረገ የሞት ምጣኔን በማወዳደርና በማነጻጸር የሚያሟይ የቢጋር ክብ አዘጋጅታችሁ አሟሉ።




### ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የታዳጊ ሀገር ዜጎች የሚፈልሱት በምን በምን ምክንያት ነው? በሚፈልሱበት ጊዜ ምን ምን ችግሮች ያጋጥሟቸዋል?

ለ. በምንባቡ ውስጥ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሞት ምጣኔ የታየባቸው ሁለት ዓመታት የትኞቹ ናቸው? ዝቅተኛ የሞት ምጣኔ የታየበት ዓመትስ የትኛው ነው?

ሐ. ጦርነትና ፍልሰት ለሞት ምክንያት በመሆን ረገድ ያላቸው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን ከተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር ማዛመድ

#### ተግባር 1

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
| --- | --- |
| 1. ግንባርቀደም | ሀ. ተጨምረው |
| 2. ተጠቂ | ለ. መፈናቀል |
| 3. ይዳረጋሉ | ሐ. ሰፈር |
| 4. ቀጣና | መ. ተጎጂ |
| 5. ግፍ | ሠ. ተፈላጊ |
| 6. ፍልሰት | ረ. ሲወዳደር |
| 7. ተመራጭ | ሰ. አካባቢ |
| 8. ሲነጻጸር | ሸ. ይጋለጣሉ |
| 9. መንደር | ቀ. መጀመሪያ |
| 10. ተዳምረው | በ. በደል |

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በዓረፍተነገር ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ በማስገባት ዓረፍተነገሩን አሟልታችሁ ጻፉ።

| | | |
| --- | --- | --- |
| ግርድፍ | በአምስት | የሞት |
| ቀጣና | መለኪያዎች | |

ሀ. የሞት ምጣኔ ______ መከሰትን ያሳያል።

ለ. በጦርነት ______ ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦች ሞትና ፍልሰት ያጋጥማቸዋል።

ሐ. እንደውልደት ምጣኔ ሁሉ የሞት ምጣኔንም የተለያዩ ______ በመጠቀም ማስላት ይቻላል።

መ. ______ የሞት ምጣኔ ስሌት ከፍተኛ የሞት መጠን የሚታይበት የዕድሜ ክልል አያሳይም።

ሠ. ብዙ ጊዜ የሞት መጠን በዕድሜ ገደብ የሚሰላው ______ ዓመት ነው።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

ሀ. ጦርነትንና ፍልሰትን በሚመለከት ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

ለ. መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የመጀመሪያ ረቂቅ ጽሑፋችሁን አርማችሁና አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉ፡፡

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አስተካክሎ ዓረፍተነገሮችን በትክክል መጻፍ

#### ተግባር 1

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በትክክል አጻምጣችሁ ጻፉ።

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን የአወቃቀር ችግር ያለባቸውን ዓረፍተነገሮች በማስተካከልና ሥርዓተነጥቦችን በማሟላት ፊደል ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

ምሳሌ፡-

| ያልተስተካከለ ዓረፍተነገር | የተስተካከለ ዓረፍተነገር |
|---|---|
| ፈረደ ነው ተማሪ ጎበዝ? | ፈረደ ጎበዝ ተማሪ ነው? |

ሀ. ምጣኔ የሞት መለኪያ ምን አለው?

ለ. ይሆናሉ ስደት ለሞት ጦርነት ምክንያት ረሀብ

ሐ. ሌላው ነው ምክንያት ፍልሰት የሚሆነው ለሞት

6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የሞት ምጣኔ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት የመጀመሪያ ክፍለጊዜ «የሞት ምጣኔ» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሷቸውን ነጥቦች በቃላችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር**

ሀ. «የሞት ምጣኔ» የሚለውን ምንባብ የመጀመሪያ ሦስት አንቀጾች መምህራችሁን እየተከተላችሁ፣ የሐረጋት አከፋፈሎችንና ሥርዓተነጥቦችን ጠብቃችሁ በፍጥነት አንብቡ።

ለ. ጥንድ ጥንድ በመሆን «የሞት ምጣኔ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተራበተራ የሐረጋት አከፋፈሎችንና ሥርዓተነጥቦችን ጠብቃችሁ በፍጥነት አንብቡ።

# መናገር

## ቃለመጠይቅ በማዘጋጀት ንግግር ማቅረብ

ማስታወሻ

ቃለመጠይቅ ስታዘጋጁና ስታቀርቡ፣ የቡድኑ አባላት በሙሉ የሥራ ድርሻ ቢኖራቸው መልካም ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ነጥቦች እንደመመሪያ መጠቀም ይቻላል።

1. አንዷ/ዱ ተማሪ ለቃለመጠይቅ የሚሆኑ ጥያቄዎች ታዘጋጅ/ያዘጋጅ።
2. አንዷ/ዱ ተማሪ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በማየት አርማ/አርሞ ታስተካክል/ያስተካክል።
3. ሌላዋ/ው እንደጋዜጠኛ ጠያቂ ትሁን/ይሁን።
4. ሌላዋ/ው ተጠያቂ በመሆን መልስ ትስጥ/ይስጥ።
5. ሌላዋ/ው ፎቶ የማንሳት ወይም ቪዲዮ የመቅረጽ ድርጊት በማስመሰል ትፈጽም/ይፈጽም።

## ተግባር

በቡድን በመደራጀት የሞት ምጣኔ ከውልደት ምጣኔና ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው ለማወቅ የሚያስችል የቃለመጠይቅ ናሙና በማዘጋጀት ርስበርስ ተጠያየቁ።

# ሰዋስው

## መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም ዓረፍተነገር መመሥረት

## ተግባር

*መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም፣ መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮችን ጻፉ።*

ምሳሌ፡-

ሴቶች ግንባርቀደም የጦርነት ተጠቂዎች ናቸው።

1. ግንባርቀደም የጦርነት ተጠቂዎች እነማን ናቸው?
2. ሴቶች እንዴት ግንባርቀደም የጦርነት ተጠቂ ሆኑ?
3. ሴቶች ለምን ግንባርቀደም የጦርነት ተጠቂ ሆኑ?
4. ሴቶች ግንባርቀደም ተጠቂ የሆኑት በምንድን ነው?

ሀ. ፍልሰት ከሕዝብ ቁጥር ጋር ግንኙነት አለው።

ለ. የውልደት ምጣኔ ከሕዝብ ቁጥር መቀነስ ጋር ግንኙነት አለው።

ሐ. በጦርነት ቀጣና ውስጥ የሚገኙ ህዝቦች ሞትና ፍልሰት ያጋጥማቸዋል።

መ. በጦርነት ምክንያት ብዙ ሰዎች ይፈናቀላሉ።

ሠ. የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን ለመወሰን የውልደት ምጣኔንና የሞት ምጣኔን መለካት ያስፈልጋል።

# 3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

# የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ምጣኔ-ሀብት-ኣዊ | ምጣኔሀብታዊ |
| ለ | ደረሰ-ኡ-ብ-ኧት | ደረሱበት |
| ሐ | እየ-ጨፈጨፍ-ኡ | እየጨፈጨፉ |
| መ | ተፈጥሮ-ኣዊ | ተፈጥሯዊ |
| ሠ | ተ-ጠቃሚ-ነት | ተጠቃሚነት |
| ረ | እንግሊዝ-ኣዊ-ው | እንግሊዛዊው |
| ሰ | ለም-ነት-ኡ-ኣ-ን | ለምነቷን |
| ሸ | ኣ-በልጽግ-አ | አበልጽጎ |

## ማንበብ

**የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ**

### ቅድመንባብ

**የቀደመ ዕውቀትን በመጠቀም ለቃላት ፍቺ መስጠት**

**ተግባር**

የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ በቃላችሁ ተናገሩ።

ሀ. መስተጋብር

ለ. እየጨፈጨፉ

ሐ. እየመነጠሩ

መ. ጥግግት

ሠ. መራቆት

ረ. ብክለት

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር 1

«የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሁለተኛ አንቀጽ ከመምህራችሁ ጋር በጋራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡና የአንቀጹን ሀሳብ ባጭሩ ተናገሩ።

### ተግባር 2

ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ «የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ» የሚለውን ምንባብ የአንቀጾቹን ዋና መልዕክት ቆም በማለት በአዕምሯችሁ እያጠቃለላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ

የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ምጣኔሀብታዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች ውጤት ነው። የሕዝብ ቁጥር በልማት ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው። ጉልበትንና ዕውቀትን በማስተባበር የተፈጥሮ ሀብቶችን በመጠቀም ልማትን ያረጋግጣል። ልማትም የሕዝብን ተጠቃሚነት ያሰፋል። የህዝቦች የኑሮ ደረጃና ዕድገት በልማት መጠን ይወሰናል። በሌላ በኩልም ደግሞ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በሀገር ሀብት ላይ ጫና ስለሚፈጥር አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ከዚህም ሕዝብና ልማት ተነጣጥለው የማይታዩ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። ስለሆነም የሕዝብንና የልማትን መስተጋብር ማጣጣም ይገባል።

በሥነሕዝብ ጥናት «የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ልማትን ያፋጥናል ወይስ ያጓትታል?» የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ጉዳይ ነው። ይህንንም በተመለከተ አሉታዊና አዎንታዊ አስተሳሰቦች አሉ። ከአሉታዊ አስተሳሰቦች መካከል የእንግሊዛዊው «የማልተስ» አስተሳሰብ ይጠቀሳል። ማልተስ ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ይከራከራል። የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በታዳጊ ሀገሮች ማኅበራዊ፣ ምጣኔሀብታዊና የአስተሳሰብ ችግሮች እያስከተለ መሆኑንም ያስተጋባል። በምግብ አቅርቦትና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጫና በመፍጠር ረሀብና ድህነት ያስፋፋል በማለት ይከራከራል። በመሆኑም ፈጣን ዕድገትን ለማምጣት የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን መወሰን አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ይጠቁማል።

ከማልተስ በተቃራኒ «የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለምጣኔሀብታዊ ዕድገት ጠቃሚ ነው» የሚል አስተሳሰብ አለ። ይህም ለምጣኔሀብታዊ ዕድገት ወሳኙ ሕዝብ ስለመሆኑ ይገልጻል። ይህን አስተሳሰብ የሚደግፉት ሊቃውንት «የሕዝብ ቁጥር ማደግ የዕውቀት አማራጮች እንዲሰፉ በማድረግ አሁን የሰው ልጆች የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ አመላካች ይሆናል» በማለት ይከራከራሉ።

በርግጥም የሰው ኃይል ለአገር ምጣኔሀብታዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው የሚካድ አይደለም። ማኅበራዊና ምጣኔሀብታዊ ዕድገት እንዲሁም አጠቃላይ ልማት

ሲታሰብ ሕዝብ መታሰቡ አይቀርም። የምጣኔሀብት ዕድገት የሚወሰነው ሀዝቦች የሀገር ሀብትን ጠቃሚ በሆነ መልኩ መለወጥ ሲችሉ ነው። ብዙ ሕዝብ ባለበት በምርት ተግባር ላይ ሊሰማራ የሚችል ብዙ የሰው ኃይል ይኖራል። የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ብዙ አምራች ኃይልን ያካተተ ሲሆንና በቂ ዕውቀትና ክህሎት ሲኖረው ለሀገር ዕድገትና ልማት ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል። በተለይም በማኅበረሰቡ ውስጥ የሰለጠኑ ሰዎች ቁጥር በርካታ ሲሆን የምጣኔሀብታዊ ዕድገት ይፋጠናል። ልማት በሰዎች ህይወት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ሁሉ ሰዎችም በልማት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።

ምንም እንኳን ሕዝብ በልማት ሥራ ከፍተኛ ድርሻ ቢኖረውም በሀገር ውስጥ ካሉት ተፈጥሯዊ ሀብቶች ጋር መጣጣም ይኖርበታል። ከተፈጥሯዊ ሀብቶች መካከል መሬት በዋናነት ትጠቀሳለች። ሰዎች መሬትን እንድትለማም ሆነ እንድትራቆት ሊያደርጉ ይችላሉ። የሰዎች በጥግግት መኖር አካባቢን ያራቁታል። ሰዎች ለመኖሪያና ለተለያዩ ተግባራት ደኖችን እየመነጠሩና እየጨፈጨፉ የአካባቢ መራቆትን ያስከትላሉ። በዚህም የአየር ብክለት ይከሰታል። መሬትም የተፈጥሮ ለምነቷን ስለምታጣ ምርት ይቀንሳል፤ ድህነትም ይስፋፋል። ይህ እንዳይሆን በየጊዜው የሕዝብ ቆጠራ በማከናወን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለውጡን መከታተል ይገባል። በዚህ መነሻነትም የሕዝብ እድገቱን ለመወሰን ለማኅበረሰቡ ስለቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት መስጠት ይገባል። በተለይም «ልጅ ሀብት ነው» በሚል አጉል ባህል በመገፋፋት ብዙ ልጆችን የሚወልዱ ወላጆችን ማስተማር ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በአጠቃላይ ምጣኔሀብታዊ ዕድገት እንዲኖር ሀብት ያስፈልጋል። ሕዝብ ደግሞ በራሱ ሀብት ነው። የሕዝብ ቁጥር መቀነስ የተፈጥሮ ሀብቶችን አበልጽጎ ለመጠቀም የሚያስችል ሰብዓዊ ሀብት እጥረትን ይፈጥራል። በአንጻሩ ደግሞ የሀገር ምጣኔ ሀብት ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የሕዝብ ቁጥር ሲኖር የህዝቡን የኑሮ ደረጃ በመቀነስ የምግብ አቅርቦት ችግር ያስከትላል። ስለዚህ የሀገርን ዕድገት ለማፋጠን የተመጣጠነ የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን በማምጣት ዜጎችን የልማት ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. በቡድን ሆናችሁ በሚከተሉት ሁለት ሀሳቦች ላይ በመወያየት የተስማማችሁበትን ሀሳብ በተወካያችሁ አማካይነት ክፍል ውስጥ አቅርቡ።

   ሀ. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በልማት ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው?

   ለ. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በሀገር ሀብት ላይ ጫና ስለሚፈጥር አሉታዊ ተጽዕኖ አለው»

2. «የሕዝብንና የልማትን መስተጋብር ማጣጣም ይገባል» ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን ከተመሳሳይና ከተቃራኒ ፍቾቻቸው ጋር ማዛመድ

**ተግባር 1**

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቾቻቸውን ከ«ለ» ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አመላካች | ሀ. ፈጻሚ |
| 2. ጠቀሜታ | ለ. አመለካከት |
| 3. መጨረስ | ሐ. ድርሻ |
| 4. አስተሳሰብ | መ. መፍጀት |
| 5. ያጓትታል | ሠ. ጠቋሚ |
| 6. መገፋፋት | ረ. መነሳሳት |
| 7. ሲታሰብ | ሰ. አገልግሎት |
| 8. ሊሰማራ | ሸ. ሲታወስ |
| 9. ሚና | ቀ ያዘገያል |
| 10. አድራጊ | በ. ሊውል |
| | ተ. እድገት |
| | ቸ. ብክለት |

## ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላት በ«ለ» ረድፍ ካሉት ተቃራኒ ፍቺዎች በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አሉታዊ | ሀ. ያጓትታል |
| 2. መጠጋጋት | ለ. ጥፋት |
| 3. ተጠቃሚ | ሐ. አዎንታዊ |
| 4. ያፋጥናል | መ. ተጎጂ |
| 5. ልማት | ሠ. መራራቅ |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ሀሳብን በቢጋር ሠንጠረዥ በማደራጀት ድርሰት መጻፍ

## ተግባር

ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው የቢጋር ሠንጠረዥ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች መሠረት በማድረግ ሦስት አንቀጽ ያለው ድርሰት ጻፉ።

## የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ልማትን ያፋጥናል ወይስ ያጓትታል?

### አሉታዊ አስተሳሰቦች

- ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በምጣኔ ሀብት ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው።
- ማኅበራዊና ምጣኔሀብታዊ ችግር ያስከትላል
- በምግብ አቅርቦትና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጫና በመፍጠር ረሀብና ድህነት ያስፋፋል፣
- ስለዚህ የሕዝብ ቁጥር ዕድገትን መወሰን አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው።

### አዎንታዊ አስተሳሰቦች

- የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለምጣኔሀብታዊ ዕድገት ጠቃሚ ነው።
- የዕውቀት አማራጮች እንዲስፋፉ በማድረግ ዕድገትን ያፋጥናል።
- የሀገር ሀብትን ጠቃሚ በሆነ መልክ ይለውጣል
- ብዙ አምራች ኃይል እንዲኖር ያደርጋል።
- ለምጣኔሀብታዊ ዕድገት ወሳኙ ሕዝብ ነው።

### ማጠቃለያ

- ልማት በሰዎች ህይወት ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ሁሉ ሰዎችም በልማት ሂደት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራሉ።
- የሕዝብ ቁጥር መቀነስ የተፈጥሮ ሀብቶችን አበልፅጎ ለመጠቀም የሚያስችል ሰበአዊ ሀብት እጥረት ይፈጥራል። በአንፃሩ ደግሞ የሕዝብ ቁጥር መጨመር የምግብ አቅርቦት ችግር ያስከትላል።
- በመሆኑም ሕዝብ በልማት ሥራ ከፍተኛ ድርሻ ቢኖረውም በሀገር ውስጥ ካሉት ተፈጥሯዊ ሀብቶች ጋር መጣጣም ይኖርበታል

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አስተካክሎ ዓረፍተነገር መጻፍ

**ተግባር**

ቀጥሎ ተዘበራርቀው የቀረቡትን ቃላት ቅደምተከተል በማስተካከል ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ሀ. መካከል ሀብቶች በዋነኛነት ከተፈጥሯዊ መሬት ትጠቀሳለች

ለ. ሀብት ያስፈልጋል በአጠቃላይ ምጣኔ እንዲኖር ሀብታዊ ዕድገት

ሐ. እየመነጠሩና እየጨፈጨፉ ሰዎች ደኖችን የአካባቢ ያስከትላሉ መራቆትን

መ. የሕዝብ በልማት ከፍተኛ ውስጥ ቁጥር አለው ሚና

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ልማትን ያፋጥናል ወይስ ያጓትታል? ከሚለው ሀሳብ የምታስታውሱትን በቃላችሁ ተናገሩ።

### ማንበብ

**ተግባር 1**

«የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ ደቂቃ በመያዝ በፍጥነት አንብቡ።

(አንብቦ ለመጨረስ የወሰደባችሁን ጊዜ ከጓደኞቻችሁ ጋር በማወዳደር ርስበርስ ተነጋገሩ።)

**ተግባር 2**

«የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምጣኔሀብታዊ አንድምታ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ እያሰማችሁ ደቂቃ በመያዝ በፍጥነት አንብቡ። (ድምፅ እያሰማችሁ ስታነቡ የወሰደባችሁን ጊዜ ድምፅ ሳታሰሙ ስታነቡ ከወሰደባችሁ ጊዜ ጋር አነጻጽሩ።)

## መናገር

### ሀሳብን በመደገፍ መከራከር

**ማስታወሻ**

ክርክር በሚካሄድበት ጊዜ ሊታወሱ የሚገቡ ነጥቦች፡-

1. የሚከራከሩበትን ነጥብ ርዕስ በቅድሚያ ማወቅ፣
2. ቀድሞ የመከራከሪያ ሀሳቦችን ማዘጋጀት፣
3. ሀሳቦች ሲዘጋጁና ክርክር ሲካሄድ ማስታወሻ መያዝ፣
4. ከርዕሱ አለመውጣት፣
5. የተመደበውን የመከራከሪያ ጊዜ ማክበር፣
6. የተከራካሪን ሀሳብ እንጂ ተከራካሪን አለመንቀፍ፣
7. ተራ በመጠበቅ መከራከር፣
8. የክርክር ዳኛውን ውሳኔ መቀበል።

**ተግባር**

በሁለት ቡድን በመከፈል አንዱ ቡድን «የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ልማትን ያፋጥናል» የሚል ሀሳብ በመደገፍ ሌላው ቡድን «የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ልማትን ያጓትታል» የሚል ሀሳብ በመደገፍ ክርክር አካሂዱ።

## ሰዋስው

### ዓረፍተነገሮችን በዓይነት መመደብ

**ተግባር 1**

የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች፣ ድርብ ዓረፍተነገር ከሆኑ «ድርብ» መጠይቃዊ ዓረፍተነገር ከሆኑ «መጠይቃዊ፣» ሁለቱንም ካልሆኑ «ሌላ» ብላችሁ ጻፉ። ለመልሳችሁ ምክንያት ስጡ።

ሀ. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለልማት አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ለ. ሰዎች ተጠጋግተው ሲኖሩ፣ ደኖችን ያወድማሉ።

ሐ. የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ልማትን ያፋጥናል?

መ. የህዝቦች የኑሮ ደረጃ በልማት መጠን ይወሰናል።

ሠ. የሕዝብን ቁጥር እንዴት ለልማት ማዋል ይቻላል?

ረ. ሕዝብ በራሱ ሀብት ነውና የሕዝብ ቁጥር መጨመር የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማበልጸግ ያስችላል።

ሰ. ሕዝብ ለልማት ሥራ ከፍተኛ ድርሻ ቢኖረውም፣ ቁጥሩ ከተፈጥሮ ሀብቶች ጋር መጣጣም አለበት።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ሐተታዊ ዓረፍተነገሮች ወደ መጠይቃዊ ዓረፍተነገር ቀይራችሁ ጻፉ።

ሀ. ሰዎች መሬትን እንድትለማ ማድረግ ይችላሉ።

ለ. የሰው ኃይል ለአገር ምጣኔሀብታዊ ዕድገት አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ሐ. የሰለጠኑ ሰዎች ቁጥር በርካታ መሆን ለህብረተሰብ ዕድገት አስተዋጽኦ አለው።



በርሃማነት

ምዕራፍ 6

የደን ውድመት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላት በምሳሌው መሠረት ካነበባችሁ በኋላ እንደገና አጣምራችሁ በመጻፍ አንብቡ።

ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| • እየ-ጨመሩ<br>• አመለከቱ-ኣቸው<br>• እየ-ተመናመነ | → | • እየጨመሩ<br>• አመለከቷቸው<br>• እየተመናመነ |

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሽማግሌ-ዎች-ኣችን<br>ለ. መታረስ-ኣቸው-ን<br>ሐ. ኡ-ድንቅ-ኧው-ል-ኣት-ኣል<br>መ. ት-ነግር-ኧኝ-ኣል-ኧህ<br>ሠ. አውርጻ-ብ-ን-ኣል-ኧች<br>ረ. አብልተው-ኣቸው-ኣል | → | |

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ደጋግማችሁ አንብቡ።

| | | |
|---|---|---|
| እንዲያንገብብ | በገዛ እጃችን | በመታረሳቸው |
| ሕፃኖቻችን | ግርም ይለኛል | ከጓደኞቻቸው |
| ዕድሚያቸውም | ሲጨፈጨፍ | እስከሚመጡ |
| በጉርምስና | የሚቆጨኝን | አዕዋፍ |
| ታስታውሳለህ | ሰማይጠቀስ | አመለከቷቸው |
| | | ትነግረኛለህ |

# ማንበብ

## የደን ውድመት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

## ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን ተጠቅማችሁ መልሱ።

ሀ. የምንባቡን ርዕስና ሥዕሉን በመመልከት የምንባቡ መልዕክት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

ለ. ደን ጠባቂ አለው ወይስ የለውም? ለምን?

ሐ. ደኖችን መጠበቅ ያለበት ማነው ትላላችሁ? ደኖችን የሚያወድመውስ ማነው? ለምን ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

## ተግባር

«የደን ውድመት» የሚለውን ምንባብ ሀሳቦችን በድርጊትና በጊዜ ቅደምተከተል በመረዳት ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

# የደን ውድመት



የረፍት ቀን በመሆኑ አቶ አሰፋ ዛሬ ወደእርሻ ሥራቸው አልሄዱም። የተጣሉ ሰዎችን ለማስታረቅ ከጓደኞቻቸው ጋር ቀጠሮ ይዘዋል። ጓደኞቻቸው እስከሚመጡ ከቤታቸው ፊትለፊት ካለች ጉቶ ላይ ቁጭ ብለው ይጠባበቃሉ። አሻግረው የተወሰኑ ዛፎችን ሲመለከቱ የቀድሞ ትዝታቸው ተቀሰቀሰ።

የዛሬ 50 ዓመት ገደማ በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር አነስተኛ ስለነበረ ጎጆዎች ራቅ ራቅ ብለው ነበር የተሠሩት። አቶ አሰፋ ገና የሰባትና የስምንት ዓመት ልጅ ሆነው፣ አባታቸው ወደጫካው ይዘዋቸው በመሄድ ኮሽም፣ አጋም፣ ቀጋና ሾላ እየለቀሙ ያበሏቸው ነበር። በጉርምስና ዕድሜያቸውም ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ጥቅጥቅ ያለውን ጫካና የሚሰሙትን የአዕዋፍና የእንስሳት ድምፅ ያደንቁ ነበር።

ከጊዜ በኋላ ግን በአካባቢው የሰዎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ የእርሻ መሬት ተስፋፉ፣ ተዳፋት መሬቶች ሳይቀሩ ታረሱ፣ ለማገዶ፣ ለቤት መሥሪያና ለመሳሰሉት ተግባራት ጫካው በመጨፍጨፉና በመመናመኑ በማራኪ ዜማቸው ያስደስቱ የነበሩት አዕዋፍ አካባቢውን ለቀው ተሰደዱ። ተዳፋት መሬቶች ስለታረሱ በአነስተኛ ዝናብ እንኳ መሬቱ በመሸርሸሩ፣ ለምነቱ እየቀነሰ መጣ። ወይዘሮ ፋጡማ በድንገት ከቦታው በመድረስ አቶ አሰፋን ከሰጠሙበት የዱሮ ትዝታቸው አባነናቸው።



አቶ አሰፋም ከተቀመጡበት በመነሳት ከወይዘሮ ፋጡማ ጋር ሰላምታ ተለዋውጠው ሌላው ጓደኛቸው እስኪመጡ አረፍ እንዲሉ መቀመጫ አመለከቷቸው። ወይዘሮ ፋጡማ «ምነው ደህና አይደለህም እንዴ? የተከዘክ ትመስላለህ» በማለት ጠየቋቸው። አቶ አሰፋም «የሰፈራችን የቤት ብዛትና የማዶው ጫካ መመናመን እየገረመኝ ነው እንጂ» አሏቸው። ወይዘሮ ፋጡማ «ይህንማ ምኑን ትነግረኛለህ፤ በገዛ እጃችን ያደረግነውን። በየጊዜው አባቶቻችን የመከሩንን አልሰማ ብለን አካባቢውን ምድረበዳ አደረግነው። በተለይ ያ ወጣት የግብርና ልማት ሠራተኛ ታስታውሳለህ? «ደን ሲጨፈጨፍ ዝናብ ይጠፋል፤ መሬትም ለምነቷን ታጣለች፤ የዘሩት ምርት ይቀንሳል፤ ብሎም ድህነት ይከሰታል» እያለ በየጊዜው ነግሮናል።

«ዱሮ መንገድ ስንሄድ ጥላጥላውን ስለምንጓዝ ድካም አይሰማንም ነበር። አሁን ግን ደኑ ሁሉ በመውደሙ ፀሐይ ያለ የሌለ ኃይሏን ታወርድብናለች። እኔማ ያ የወትሮው ቀያችን ወደበርሃማነት ተለውጦ ሳየው ግርም ይለኛል። በየጊዜው ይጥል የነበረው ዝናብ በመቀነሱም ድርቅ ስንት ጊዜ እንዳጠቃን ታስታውሳለህ?»

«እኔማ የሚቆጨኝ እዚያ ዐውድማ ዙሪያ ይከመር የነበረው ሰማይጠቀስ ክምር ነው። ዛሬ ያ ሁሉ ቀርቶ ድህነት በላያችን ላይ እንዲያንዣብብን አደረግነው። በየጊዜው ሕጻናትና ሽማግሌዎች በበሽታ ይጠቃሉ። ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎች እኛው ነን። በመሆኑም ይህን አካባቢ ወደቀድሞ ይዞታው የመመለስ ኃላፊነት አለብን» እያሉ ሲነጋገሩ፣ ለሽምግልና አብረው የሚሄዱት ጓደኛቸው በመምጣታቸው ተያይዘው ሄዱ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በምንባቡ የመጨረሻ አንቀጽ «ይህን አካባቢ ወደቀድሞ ይዞታው የመመለስ ኃላፊነት አለብን» በሚል የተገለጸውን ሀሳብ አብራርታችሁ ግለጹ።

ለ. የአቶ አሰፋን የቀድሞ ትዝታ የቀሰቀሰው ምንድን ነው? ለምን?

ሐ. አቶ አሰፋ በአዕምሯቸው የሚያብሰለስሉት ነገር ምንድን ነው?

መ. አቶ አሰፋን በአሁን ሰዓት እያስገረማቸው ያለው ነገር ምንድን ነው?

ሠ. ከምንባቡ በአራተኛው አንቀጽ «በገዛ እጃችን ያደረግነውን...» የሚለውን አገላለጽ በራሳችሁ አባባል ተናገሩ።

ረ. ሰዎች በአሁኑ ዘመን መንገድ ሲሄዱ ከድሮው ዘመን የበለጠ ድካም የሚሰማቸው ለምንድን ነው?

ሰ. በምንባቡ ውስጥ በሚገኙት ሁለት ሥዕሎች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለጹ።

ሸ. ተጻፉት መሬቶች ሳይቀሩ እንዲታረሱ የተደረገው ለምን ይመስላችኋል?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ዐውድ መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተቀሰቀሰ (አንቀጽ «1»)

ለ. ገደማ (አንቀጽ «2»)

ሐ. ተጻፉት (አንቀጽ «3»)

መ. ዐውድማ (አንቀጽ «6»)

ሠ. ጥቅጥቅ ያለውን (አንቀጽ «2»)

ረ. መሸርሸር (አንቀጽ «3»)

ሰ. ጥላጥላውን (አንቀጽ «5»)

ሸ. ቀያችን (አንቀጽ «5»)

ቀ. በመውደሙ (አንቀጽ «5»)

በ. በመመናመኑ (አንቀጽ «3»)

## ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተሰደዱ (አንቀጽ «3»)

ለ. ይጠቃሉ (አንቀጽ «6»)

ሐ. ሰማይጠቀስ (አንቀጽ «6»)

መ. ለሽምግልና (አንቀጽ «6»)

ሠ. ምድረበዳ (አንቀጽ «4»)

ረ. አልሰማ ብለን (አንቀጽ «4»)

ሰ. ሲጨፈጨፍ (አንቀጽ «4»)

ሸ. የተጣሉ ሰዎች (አንቀጽ «1»)


ቀ. ተስፋፉ (አንቀጽ «3»)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### መግቢያ፣ ዋና አካልና ማጠቃለያ ያለው ድርሰት መጻፍ

«የደኖች መመናመን» በሚል ርዕስ መግቢያ፣ ዋና አካልና ማጠቃለያ ያለው ድርሰት በትረካ ስልት ለመጻፍ የሚያስችል ቢጋር አዘጋጁ።



## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አጻምጦ በትክክል መጻፍ

**ተግባር 1**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላትና ሐረጋት አጻምጣችሁ ፊደል ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የደን ውድመት

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«የደን ውድመት» የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የማንበብ ፍጥነታችሁን ለክታችሁ ታውቃላችሁ?

ለ. በደቂቃ ስንት ቃላት ታነባላችሁ?

### ማንበብ

**ተግባር**

ሀ. «የደን ውድመት» ከሚለው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን አራት አንቀጾች ከመምህራችሁ ጋር በጋራ አንብቡ።

ለ. በቡድን በቡድን በመሆን «የደን ውድመት» የሚለውን ምንባብ በየተራ አንዳችሁ ስታነቡ ሌሎቻችሁ ሰዓት እየያዛችሁ አንብቡ።

## ማዳመጥ

### ቁጭት

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ

ሀ. በህይወታችሁ «የሚያስቆጭ» ነገር አጋጥሟችሁ ያውቃል? መቼ?

ለ. ዛሬ የምታዳምጡት ምንባብ ርዕስ «ቁጭት» የሚል ነው። ርዕሱን መነሻ በማድረግ ምንባቡ ስለምን እንደሚናገር ግምታችሁን ተናገሩ።

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

መምህራችሁ «ቁጭት» በሚል ርዕስ የተጻፈ ምንባብ ሲያነቡላችሁ፣ ዋናዋና ሀሳቦችን በጊዜና በድርጊት ቅደምተከተል እያደራጃችሁ በመረዳት አዳምጡ።

### አዳምጦ መረዳት

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በየአካባቢው ደኖች ሲጨፈጨፉ እያዩ ሰዎች በዝምታ ማለፋቸው ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ. ደኖችን ከጉዳት ወይም ከመጨፍጨፍ ለመታደግ ከአካባቢው ማኅበረሰብ የሚጠበቀው ምን ይመስላችኋል? ለምን?

ሐ. የደን ጥበቃንና እንክብካቤን በተመለከተ ወደፊት ምን ማድረግ የምትችሉ ይመስላችኋል? እንዴት?

## ሰዋስው

### ዓረፍተነገሮችን ወደአሉታዊና መጠይቃዊ ቅርፅ መቀየር

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በምሳሌው መሠረት ወደአሉታዊና ወደመጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች ለውጣችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

ትህትና ከዛፍ ሥር ቆማለች።

- ትህትና ከዛፍ ሥር አልቆመችም።
- ትህትና ለምን ከዛፍ ሥር አልቆመችም?
- ትህትና ከዛፍ ሥር ለምን ቆመች?

ሀ. ችግኝ በመትከል ብቻ ደንን መንከባከብ ይቻላል።

ለ. የሰዎች ቁጥር በመጨመሩ ምክንያት ብቻ ደኖች ይወድማሉ።

ሐ. ከመንደሩ በቅርብ ርቀት ጫካ አለ።

መ. እልፍነሽ ጥሩ ውጤት አስመዝግባለች።

#### ተግባር 2

አምስት አዎንታዊ ዓረፍተነገሮች ጽፋችሁ ወደአሉታዊና መጠይቃዊ ዓርፈተነገር በመቀየር ጻፉ።

## ማንበብ

### ችግኝ በመትከል አካባቢን መታደግ

### ቅድመንባብ

#### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም መልሱ።

ሀ. የተራቆቱ ደኖችን እንዴት መተካት የሚቻል ይመስላችኋል?

ለ. ችግኝ ተክላችሁ ታውቃላችሁ? ሰዎች ችግኝ ሲተክሉ በውስጣቸው ምን ዓይነት ተስፋ የሚሰንቁ ይመስላችኋል?

ሐ. በበጋ ወቅት የጠወለጉ ወይም የደረቁ ችግኞች ዓይታችሁ ታውቃላችሁ? ስታዩአቸው ምን ይሰማችኋል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ሀ. የምንባቡን የመጀመሪያ ሁለት አንቀጾች በየግላችሁ ካነበባችሁ በኋላ፣ አርሶአደሮች ስለገጠማቸው ችግርና ስለመፍትሔ ሃሳቦች በአዕምሯችሁ አሰላስሉ። የአንቀጾችን ሀሳቦች እያጠቃለላችሁ፣ ያልተረዳችሁት ሀሳብ ሲኖር ደጋግማችሁ እያነበባችሁ፣ ቀሪዎቹን አንቀጾች ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

# ችግኝ በመትከል አካባቢን መታደግ



በአዲስ አበባ የገጠር ተራራማ ክፍል የሚኖሩ ማህበረሠቦች አካባቢያቸው ለረጅም ጊዜ በመታረሱና ለምነቱ በመቀነሱ ምክንያት ምርት አልሰጥ ስላላቸው አርሶአደሮች ተቸግረዋል። የዘሩት እህል አልፎአልፎ በሚጥለው ዝናብ በጐርፍ ይወሰድባቸዋል። በበጋ ወቅት እንስሶቻቸው የሚጠጡት ውኃ አያገኙም። የሙቀት መጠኑም ከለመዱት የተለየ ሆኖባቸዋል። በአካባቢያቸው የሚገኘው የምንጭ የጉድጓድ ውኃ መጠኑ እየቀነሰ መጥቷል። የመንደሩ ሰዎች ውኃ ለመቅዳት በማለዳ ሂደው የሚመለሱት ቀትር ላይ ነው።

መሬት ለምነቷን ስላጣች ምርት ቀንሷል፤ ውኃ ጠፍቷል። በአጠቃላይ የኗሪዎቹ ችግሮች ከዕለት ወደዕለት እየተበራከቱ ናቸው። ኗሪዎቹ ግን የችግሮቹን ምንጭ ማወቅ አልቻሉም። እንዲሁ ፈጣሪያቸውን እያማረሩ ይኖራሉ።

ይህ ጉዳይ የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ባለሙያ የሆነችውን ዘቢደሩን እያሳሰባት መጣ። አንድ ቀን የአካባቢውን ኗሪዎች ለማወያየት ስብስባ ጠራች። ኗሪዎቹ የስብሰባውን ሰዓት አክብረው ተገኙ። ባለሙያዋ የመወያያው ርዕሰጉዳይ የአካባቢ ልማት መሆኑን አስተዋወቀች።

ከዚያም ንግግሯን እንዲህ በማለት ጀመረች። «እንደምታዩት በአካባቢው የሚታይ ሳርም ሆነ ቅጠል የለም። የአንዳንድ አርሷደሮች ከብቶች የሚግጡት ሳር የለም።

የመጠጥ ውኃ እንደልባችን ማግኘት አልቻልንም። በአጠቃላይ የአካባቢው የዱሮ ልምላሜ አሁን የለም። የችግሩ ፈጣሪዎች እኛው ራሳችን ስለሆንን መፍትሔውንም ራሳችን መፈለግ አለብን። ስለዚህ አካባቢውን ወደነበረበት ይዞታ ለመመለስ የራሳችንን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል» በማለት ገለጸች። ተሰብሳቢዎችም የየራሳቸውን ሀሳብ አንጸባረቁ። ሀሳባቸውን ከተለዋወጡ በኋላ የመጀመሪያ ሥራቸው በዝናብ እየታጠበ የሚጠረገውን አፈር ሰብስቦ ለመያዝና ርጥበትን ጠብቆ ለማቆየት ችግኝ አፍልቶ መትከል እንዳለበት ተስማሙ። በዚህ ሥራም ሁሉም የማኅበረሰብ አባላት መሳተፍ እንዳለባቸው ተነጋገሩ። በመጨረሻም ሥራውን ለመጀመር ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ።

በቀጠሮው ቀን ዕድሜያቸው ለሥራ የደረሰ ሁሉ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ እንደአካፋ፣ ዶማ ወዘተ ያሉትን መሣሪያዎች ይዘው በቦታው ተገኙ። በመጀመሪያ ምን አይነት ችግኝ ማፍላት እንዳለባቸው ከባለሙያዋ እንደየ አካባቢው አየር ንብረት ትምህርት ወሠዱ። ለችግኝ ማፍያ የሚሆን ቦታና መደብ አዘጋጁ ችንኙን ዘሩ በአቅራቢያው ያለችውን የምንጭ ውሃ እንዳይደርቅ በጥልቀት ቆፈሩና ካብ ካቡ በተራም ችግኙን መንከባከብ እንዳለባቸው ተመካከሩ ይህንን በማድረጋቸው የመንፈስ ብርታት አገኙ። በዚህ ተግባር ላይ ሁሉም የማህበረሠብ ክፍል አካል ጉዳተኛ ሳይቀሩ እንደ አቅማቸው ተሳተፉበት በተራራው ላይም የጉርፍ ውሃ ወርዶ እንዳይሄድ አልፎ አልፎ የውሃ ማቆርያ ጉድጓዶችን አዘጋጁ ይህንን ሁሉ አደረገው የችግኝ መንከባከብ ተግባርና ሃላፊነት ተከፋፍለው ተለያዩ።

ችግኝ ተከላው ከመካሄዱ ቀደም ብሎ የተወሰኑት ኗሪዎች ለችግኝ መትከያ ጉድጓድ ቆፈሩ። በቀጠሯቸው መሠረት ክረምት በገባ በሁለተኛ ሳምንት ለኗሪዎቹ በጥሩንባ ጥሪ ተላለፈ። በስምምነታቸው መሠረት በመጀመሪያ ሁሉም ኗሪዎች ከችግኝ ጣቢያው የሚችሉትን ያህል ችግኝ በመያዝ ወደተራራው አመሩ። ከተራራው ላይ እንደደረሱም በአስተባባሪዎች አማካይነት የሥራ ክፍፍል አደረጉ። የተወሰኑት ችግኝ ሲያቀርቡ ሌሎቹ ተቆፍሮ በተዘጋጀው ጉድጓድ ውስጥ ችግኝ መትከል ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ ተረዳድተው ያለምንም ድካም የተለያዩ ችግኞችን ተከሉ። በመጨረሻው ቀን የችግኝ ተከላው ሥራ እንደተጠናቀቀ ለአጭር ጊዜ በመወያየት «ችግኝና ሕጻን እንክብካቤን ይወዳል» በሚለው አባባል መሠረት ተራ ገብተው ችግኞችን ለመንከባከብ ወሰኑ።

ችግር አስተምሯቸዋልና ሁሉም የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት አደረጉ። በአካባቢው የሚገኙ እንስሳትም ወደችግኙ እንዳይሄዱ ለማድረግ እንዲሁም ጭፍጨፋ እንዳይካሄድ የመተዳደሪያ ደንብ አወጡ።

የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ባለሙያዋ ችግኞቹ ከተተከሉ በኋላ ክትትል ማድረጓን አላቋረጠችም። በየወሩ ከተተከሉት ችግኞች መካከል ምን ያህሉ እንደደረቁ ከባልደረቦቿ ጋር በመሆን በመቁጠር እንደሚከተለው በሠንጠረዥ አስፈረች።

| የተተከሉ ችግኞች | | የችግኞች ሁኔታ በወራት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከኅሐሴ-ህዳር | | ከታህሳስ-የካቲት | | ከመጋቢት-ሰኔ | |
| ዓይነት | ብዛት | የደረቁ | የፀደቁ | የደረቁ | የፀደቁ | የደረቁ | የፀደቁ |
| ፅድ | 29,300 | ? | 29,119 | 80 | ? | 112 | ? |
| ወይራ | 11,500 | 100 | ? | 85 | 11,515 | ? | 11,253 |
| ዋንዛ | 6,100 | ? | 5,895 | 74 | ? | 90 | 5,731 |
| ግራር | 9,400 | 135 | 9,265 | 142 | 9,125 | 85 | ? |
| ድምር | 56,300 | ? | 55,679 | 224 | ? | 349 | ? |

በዚህም መሠረት ጫካው ጥብቅ ሆነ። አሁን አካባቢው ለምቶ ለዓይን ማረፊያ ሆኗል። በአካባቢው ይከሰት የነበረው ጐርፍ ቀንሷል። አፈሩም ለምነቱን ጨምሯል። ውኃም እንደልብ ማግኘት ተችሏል። እንስሳትም ከቤት እየዋሉ የሚዘጋጅላቸውን መኖ እንደልብ ማግኘት ችለዋል። የአካባቢው ነሪዎችም የእርከን ሥራንና የችግኝ ተከላን ጥቅም በመረዳት በየጓሯቸውና በየእርሻቸው ተግባራዊ እያደረጉት ይገኛሉ።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የነሪዎቹ ችግሮች እየተበራከቱ የሄዱት ለምን ይመስላችኋል?

ለ. «የመንደሩ ሰዎች ውኃ ለመቅዳት በማለዳ ሄደው የሚመለሱት ቀትር ላይ ነው» የሚለውን ዓረፍተነገር ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ አብራሩ።

ሐ. የሰዎቹ ፈጣሪያቸውን ማማረር ተገቢ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

መ. በመጀመሪያዎቹ ሁለት አንቀጾችና ከነሱ ቀጥሎ በቀረቡት አንቀጾች መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

ሠ. አርሶአደሮቹ ችግኝ ማፍላት ሠርተው እንደጨረሱ ችግኝ መትከል ያልጀመሩት ለምን ይመስላችኋል?

ረ. በምንባቡ ውስጥ በሚገኘው ሠንጠረዥ በጥያቄ ምልክት የታለፉትን መረጃዎች በትክክል አሟሉ።

ሰ. በምንባቡ ውስጥ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ሁሉም የተተከሉት ችግኞች ያልጸደቁት ለምን ይመስላችኋል?

ሸ. በምንባቡ ውስጥ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ችግኞች የደረቁት በየትኞቹ ወራት ነው? ለምን ይመስላችኋል?

## 5ኛ ቀን

# ቃላት

## ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቺ ሥጡ።

ሀ. ይወሰድባቸዋል (አንቀጽ «1»)
ለ. የሚግጡት (አንቀጽ «4»)
ሐ. እየተበራከቱ (አንቀጽ «2»)
መ. የችግሮች ምንጭ (አንቀጽ «2»)
ሠ. የመንፈስ ብርታት (አንቀጽ «5»)
ረ. እንደየአቅማቸው (አንቀጽ «5»)
ሰ. የውሃ ማቆሪያ (አንቀጽ «5»)
ሸ. ችግኝ ማፍላት (አንቀጽ «5»)

### ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን በዐውዱ መሠረት በ «ለ» ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ጫካ | ሀ. ዛፍ |
| 2. ጥብቅ | ለ. ምሽት |
| 3. ለምቶ | ሐ. ወድሞ |
| 4. ማለዳ | መ. በጋራ |
| 5. ችግኝ | ሠ. ምድረበዳ |
| 6. መከፋፈል | ረ. ልቅ |
| | ሰ. መትከል |

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## በትረካ ስልት መጻፍ

### ተግባር

በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን ድርሰት መጻፍ በሚለው ተግባር በቢጋር ሠንጠረዥ ያሰፈራችኋቸውን የመግቢያ፣ የዋናአካልና የማጠቃለያ ሀሳቦች በማስፋፋት «የደኖች መመናመን» የሚል ድርሰት ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተነገሮችን አዳምጦ መጻፍ

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተነገሮች አዳምጣችሁ በትክክል ጻፉ።

## 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ችግኝ በመትከል አካባቢን መታደግ

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

«ችግኝ በመትከል አካባቢን መታደግ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. "የደን ውድመት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ስታነቡ በደቂቃ ስንት ቃላት አንብባችሁ ነበር? በዛሬው ዕለት ስታነቡ ፍጥነታችሁን የምትጨምሩ ይመስላችኋል? እንዴት?

ለ. «ችግኝ በመትከል አካባቢን መታደግ» በሚለው ምንባብ ውስጥ በሚገኘው ሠንጠረዥ የምታስተውሏቸውን መረጃዎች ተናገሩ።


### ማንበብ

#### ተግባር

ሀ. «ችግኝ በመትከል አካባቢን መታደግ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከመምህራችሁ ጋር ድምፅ እያሰማችሁ አንድ ጊዜ አንብቡ።

ለ. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ የቀረበውን የንባብ ፍጥነት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ በደብተራችሁ በማዘጋጀት ፍጥነታችሁን እየመዘገባችሁ ተራበተራ አንብቡ።

የንባብ ፍጥነት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ




ሐ.«ችግኝ በመትከል አካባቢን መታደግ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ፍጥነታችሁን በንባብ ፍጥነት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ እየመዘገባችሁ ቢያንስ አምስት ጊዜ አንብቡ።

## መናገር

### ንግግርን በምክንያት ማቅረብ

#### ተግባር

የወደሙ ደኖችን እንዴት መተካት ይቻላል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ምክንያታዊ ንግግር አቅርቡ።

## ሰዋስው

### መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮችን መመሥረት

#### ተግባር 1

ቢጋሩን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በምሳሌው መሠረት ስድስት መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

- መቼ
- ለምን
- እንዴት
- ከማንጋር
- በምን

?

ማርታ መጣች

ሀ. ማርታ መጣች?
ለ. ማርታ መቼ መጣች?
ሐ. ማርታ ለምን መጣች?
መ. ማርታ እንዴት መጣች?
ሠ. ማርታ ከማን ጋር መጣች?
ረ. ማርታ በምን መጣች?

- መቼ
- ለምን
- እንዴት
- ከማንጋር
- በምን

?

ሙስጠፋ ሄደ

ሀ. ____________________
ለ. ____________________
ሐ. ____________________
መ. ____________________
ሠ. ____________________
ረ. ____________________

## ተግባር 2

በምሳሌው መሠረት ቅርፃቸውን እየለወጣችሁ አዳዲስ ቃላት መሥርቱ።

ደረበ
መከረ
ፈለገ
→
ደራረበ
መካከረ
ፈላለገ
→
ተደራረበ
ተመካከረ
ተፈላለገ
→
አደራረበ
አመካከረ
አፈላለገ

ሀ. ቀደመ　　ለ. በለጠ　　ሐ. ጠበቀ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ፓርክ-ኡ-ን | ፓርኩን |
| ለ | ቤተሰብ-ኦች-አቸው | ቤተሰቦቻቸው። |
| ሐ | ብ-ት-አከራይ-ኧኝ | ብታከራየኝ |
| መ | ቅርንጫፍ-ኦች-አቸው | ቅርንጫፎቻቸው |
| ሠ | አንድ-አንድ-ኦች-ኡ | አንዳንዶቹ |
| ረ | ሰማ-ህ-ኧኝ | ሰማኸኝ |
| ሸ | እ-ሠራ-ብ-ኧት-አል-ኧሁ | እሠራበታለሁ |
| ሰ | ል-ይ-አስተናግድ-ኡ | ሊያስተናግዱ |

## ማንበብ

### የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ

### ቅድመንባብ

#### ከርዕሱ በመነሳት ምንባብን መገመት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን ተጠቅማችሁ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ» የሚለውን ርዕስ መነሻ በማድረግ ይዘቱ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

ለ. በሰውሠራሽና በተፈጥሯዊ አካባቢዎች መካከል ያለውን ልዩነት ተናገሩ።

ሐ. ገቢ በማስገኘት ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ አገልግሎቶችስ በአካባቢያችሁ ይገኛሉ? የሚጠበቀውን ያህል በሥራ ላይ ውለዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ሀ. «የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የማታውቋቸውን ቃላት እየመዘገባችሁ በየግላችሁ አንድ ጊዜ አንብቡ።

ለ. እያንዳንዱን አንቀጽ አንብባችሁ ስትጨርሱ መረዳታችሁን ከሚከተሉት ጥያቄዎች አንጻር በመፈተሽ አረጋግጡ።

**አንብቦ መረዳትን መፈተሻ ጥያቄዎች**

- የአንቀጹ ቁልፍ ቃላት/ሐረጋት የትኞቹ ናቸው? ፍቻቸው ምንድን ነው?
- የአንቀጹ ሀሳብ ገብቶኛል? እንዴት ማረጋገጥ እችላለሁ?
- አንቀጹን በማንበቤ የተማርኩት ቁምነገር ምንድን ነው?
- አንቀጹን እንደገና ማንበብ አለብኝ? ለምን?

### የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ

ከከተማው አቅራቢያ የሚገኝ ዳገታማ ቦታ ነው። በውስጡ የተለያዩ ዛፎችንና ተክሎችን ይዟል። አንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች በድብቅ እየሄዱ የማገዶ እንጨት ይለቅሙበታል። በንፋስ የሚወዳደቁ ዛፎችን በማቃናት ከጉዳት ለመከላከል ጥረት ባለመደረጉ ለሌባ ሲሳይ ሆነዋል። በጫካው መሃል ለመሃል አቋርጦ የሚፈስ መጠነኛ ወንዝ አለ። ነገርግን በንጽህና ባለመያዙ በቅጠላቅጠል ርግፍጋፊ ተበላሽቷል።

አካባቢው ምንም እንኳ በተፈጥሮ ሃብት የታደለ ቢሆንም አቶ እጅጉ አልፎአልፎ ወደስፍራው ሲሄድ ከመደሰትና ከመዝናናት ይልቅ ተከፍቶና ተበሳጭቶ ይመለሳል። አንድ ቀን አቶ እጅጉ ይህን ጫካ ጨፍጭፎ ለመሸጥ አሰበ። ይህንንም ለልብ ጓደኛው ለአቶ ዲባባ አማከረው። ጓደኛውም ምንም ዓይነት ሀሳብ ከማቅረቡ በፊት ቦታውን ለመመልከት ፈለገ። በዚህም ተስማምተው ቀጠሮ ያዙ።

በቀጠሮው ቀን ሁለቱም በቦታው ተገኙ። ጫካው ያለበት የቦታው አቀማመጥ ከተማውን ከርቀት ለመመልከት ያስችላል። በውስጡ የተለያዩ የተፈጥሮ ዛፎች አሉት። ዛፎቹ በዓይነት የተለያዩ ናቸው። አንዳንዶቹ ዕድሜ ጠገብ በመሆናቸው ቅርንጫፎቻቸው ሰፍተው ለጥላነት ያገለግላሉ። በተለይም የወንዙ አወራረድ አመቺ ነው። ሆኖም የወንዙ የውኃ ክፍል ጥቅም እንዲሰጥ ሆኖ አልተዘጋጀም። በአጠቃላይ ቦታው ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጥ የቆየ ነው።

ተዘዋውረው ከተመለከቱ በኋላ አቶ ዲባባ «ሰማኸኝ ጓዴ! ለጊዜያዊ ጥቅም ብለህ እነዚህ ዛፎች መቆረጥ መጨፍጨፍ የለባቸውም። ቦታውን ከመጨፍጨፍ ይልቅ

ለአካባቢው ማኅበረሰብ የሚጠቅም ሥራ እሠራበታለሁ፣ ሁለታችንም በሚገኘው ገቢ ተጠቃሚ እንሆናለን» በማለት ገለጸለት። አቶ እጅጉም በሀሳቡ ተስማማ።

አቶ ዲባባ በስምምነታቸው መሠረት ጋራ ቦታውን ለማስተካከል ወሰኑ። በመጀመሪያ የወዳደቁ ዛፎችን አስነሱ። ከዚያም በወንዙ ውስጥ ያለውን ቆሻሻና አፈር እንዲጠረግ አደረጉ። በመቀጠልም ወንዙን በመጠቀም የተለያዩ አበባዎችን፣ ዓይን የሚማርኩ የአትክልት ዓይነቶችንና ዛፎችን ተከሉ። በተወሰነ ቦታ ላይ ሰውሠራሽ ሀይቅ በማዘጋጀት የተለያዩ የዓሳ ዝርያዎችን አስገቡ። በተወሰነው የደኑ ክፍልም የጎብኝዎችን ዓይን ሊስቡ የሚችሉ የዱር እንስሳት በማምጣት ለቦታው ልዩ ውበትን አላበሱት። በአጠቃላይ የቦታውን የቀድሞ ሁኔታ በማሻሻል ጥሩ መስህብነት ያለው ቦታ አደረጉት። ለመዝናኛ የሚሆኑ ጎጆዎችን ሠርተው እንደጨረሱ የመገልገያ ቁሳቁሶችን አሟሉ። በመዝናኛ ቦታውም ሊያስተናግዱ የሚችሉ ሠራተኞችን በመቅጠር ለሌሎች የሥራ ዕድል ፈጠሩ።

በመቀጠል የመዝናኛ ፓርኩን ለማስመረቅ ቅድመዝግጅት ተደረገ። ለአካባቢው ኗሪዎች የጥሪ ደብዳቤ ተሠራጨ። ምረቃውም ለእንግዶች አመች ቢሆንም እሁድ ቀን እንዲሆን ተወሰነ።

በዚሁ ቀን ዋናው የክብር እንግዳው ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን በሰዓቱ ተገኙ። ከቦታው ሲደርሱ ያዩትን ሁሉ ማመን አቃታቸው። ተዘዋውረው ሲመለከቱ በጣም ተገረሙ። የተጠሩት እንግዶች ቀስበቀስ በቦታው ተገኙ። ግብዣው እየተካሄደ የቦታው ባለቤት አቶ እጅጉ በእቅዱ መሠረት ንግግር እንዲያደርጉ ተጋበዙ።

አቶ እጅጉ «ይህ ስፍራ በኔ ይዞታ ሥር ሆኖ ምንም ዓይነት እንክብካቤና መሻሻል ሳይደረግበት የኖረ ነው። አሁን ግን በጓደኛዬ ብርታት ለቦታው ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጎለት ለዚህ ደረጃ በቅቷል። የእኔ ዓይን ያላየውን በጓደኛዬ ዓይን በማየቱ ደስተኛ ሆኛለሁ» በማለት ንግግራቸውን ሲጨርሱ ሌሎቹ እንግዶች በጭብጨባ አጀቧቸው። በዕለቱ የነበረው ጨዋታና ዝግጅት በጣም የሚያምር ነበር።

ፓርኩ ሳቢና ማራኪ ሆኖ በመዘጋጀቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ በመዝናኛነት ይጠቀምበታል። ከአቅራቢያው ከተማም ሆነ ከዙሪያው የሚመጡ ሙሽሮች ይዝናኑበታል። ሕጻናት በቦታው በመገኘት ይቦርቁበታል። የዱር እንስሳትና በውኃ ውስጥ ያሉት ዓሳዎች ለአካባቢው ልዩ ውበት አጎናጽፈውታል። ከፓርኩ የሚገኘው ገቢም ለሰዎቹ የመተዳደሪያ ምንጭ ሆኗል።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች «የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብ» በሚለው ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ጸሐፊው/ዋ አቶ እጅጉን «አንተ» ሲላቸው ከቆየ በኋላ በስብሰባ ቦታው አንቱ ያላቸው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. አንቀጽ አንድ ውስጥ «በንፋስ የሚወድቁት ዛፎች… ለሌባ ሲሳይ ሆነዋል» የሚለውን አገላለጽ አብራሩ።

ሐ. አንቀጽ ስምንት ውስጥ «የእኔ ዓይን ያላየውን በጓደኛዬ ዓይን በማየቴ ደስተኛ ሆኛለሁ» የሚለውን አገላለጽ ሰፋ አድርጋችሁ አብራሩ።

መ. አቶ እጅጉን ያስከፋቸው ነገር ምንድን ነው?

ሠ. ተፈጥሯዊ አካባቢዎችን መንከባከብ ለምን ይጠቅማል?

ረ. ከአቶ እጅጉ ንግግር ምን ዓይነት ቁምነገር መማር የሚቻል ይመስላችኋል?

ሰ. በአንደኛው አንቀጽና በሶስተኛው አንቀጽ መካከል ያለውን ተመሳስሎ ግለጹ።

ሸ. አቶ እጅጉና አቶ ዲባባ በሀሳብ ባይስማሙ ኖሮ የአካባቢው ዕጣ ፈንታ ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

ቀ. የምንባቡን ዋና መልዕክት «ችግርን፣ መፍትሔንና ውጤት» በሚገልጹ ሦስት ዓረፍተነገሮች አሳጥራችሁ ከጻፋችሁ በኋላ በቃል ተናገሩ።

# 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን በፊደል ተራ መዘርዘርና ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ በተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተኩ።

| | | |
|---|---|---|
| አጠገብ | ትንንሽ የሣርቤቶች | ይገለገሉበታል |
| አፈሳሰስ | ዕቃዎች | ተፈጥሯዊ ያልሆነ |
| የሚገረሰሱ | መጠቀሚያ | ረጅም ጊዜ የቆዩ |

ሀ. በንፋስ የሚወድቁ ዛፎችን በማቃናት ከጉዳት ለመከላከል ጥረት ባለመደረጉ ለሌባ ሲሣይ ሆነዋል።

ለ. የወንዙ አወራረድ አመቺ ነው።

ሐ. ለመዝናኛ ቦታው የሚሆኑ ጎጆዎችን ሠርቶ እንደጨረሰ የመገልገያ ቁሳቁሶችን አሟላ።

መ. ፓርኩ ሳቢና ማራኪ ሆኖ በመዘጋጀቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ በመዝናኛነት ይጠቀሙበታል።

ሠ. በከተማው አቅራቢያ የሚገኝ ዳገታማ ቦታ አለ።

ረ. በተወሰነ ቦታ ላይ ሰውሠራሽ ሀይቅ በማዘጋጀት የተለያዩ የአሳ ዝርያዎችን አስገቡ።

ሰ. አንዳንዶቹ ዕድሜ ጠገብ በመሆናቸው ቅርንጫፎቻቸው ሰፍተው በጥላነት ያገለግላሉ።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት በፊደል ተራ ቅደምተከተላቸው አስተካክላችሁ ከጻፋችሁ በኋላ በምንባቡ መሠረት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ስጡ።

ምሳሌ፡-

በ«ሀ ለ ሐ ... የፊደል ተራ ቅደምተከተል መሠረት ከሚከተሉት ቃላት በመጀመሪያ የሚጻፈው «ርግፍጋፊ» የሚለው ቃል ሲሆን ዐውዳዊ ፍቹ ውድቅዳቂ ማለት ነው። ፍችውን ለማግኘት የረዱት ከቃሉ በፊትና በኋላ የሚገኙት በቅጠላቅጠል... ተበላሽቷል» የሚሉት ናቸው።

ሀ. ርግፍጋፊ (አንቀጽ «1»)

ለ. ተበሳጭቶ (አንቀጽ «2»)

ሐ. ጊዜያዊ (አንቀጽ «4»)

መ. ማስተካከል (አንቀጽ «5»)

ሠ. አስገባ (አንቀጽ «5»)

ረ. አላበሰው (አንቀጽ «5»)

ሰ. ተገረሙ (አንቀጽ «7»)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ድርሰትን ከልሶ መጻፍ

## ተግባር

በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን «የደኖች መመናመን» በሚል ርዕስ የጻፋችሁትን ድርሰት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን መስፈርቶች በመጠቀም አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉ።

**የድርሰት መገምገሚያ (ማረሚያ) መስፈርቶች**

ሀ. ርዕስ ጠብቆ መጻፍ።

ለ. የአንቀጹን ዋና ሀሳብ በግልጽ ማሳየት።

ሐ. ዋናውን ሀሳብ በተገቢው መዘርዝሮች መግለጽ።

መ. ሀሳብን ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ማደራጀት።

ሠ. ቃላትን በአግባቡ መጠቀም።

ረ. አንባቢዎች ሊረዷቸው የሚችሏቸው ዓረፍተነገሮች መጠቀም።

ሰ. የተሟላ ዓረፍተነገር መጠቀም።

ሸ. ባለቤትና ማሳሪያ አንቀጽ ያለው ዓረፍተነገር መጠቀም።

ቀ. ተገቢ ሥርዓተነጥብን በተገቢው ቦታ መጠቀም።

በ. የሀሳብ አንድነትና ግጥምጥምነት ያላቸው አንቀጾች ማዋቀር።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀም

ከሚከተሉት ሥርዓተነጥቦች መካከል ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ በአንቀጹ ውስጥ ያሉትን ቁጥሮች ተኩ።

| « | » | ፤ | / |
|---|---|---|---|

የደን ትርጉም 1 በኢትዮጵያ ህግ ስለደን ልማት 2 ጥበቃና አጠቃቀም በወጣው አዋጅ ቁጥር 542 _3 1996 የቃላት ትርጓሜ ክፍል በአንቀጽ 23 መሠረት 4 ደን 4 ማለት በተፈጥሮ የበቀሉ ወይም ተተክለው የለሙ በአብዛኛው ዛፎችና ሌሎች የእንጨትነት ፀባይ ያላቸው ተክሎች የሚገኙበት የዕፅዋት ክምችት በሚል ተገልጿል። 5 ዛፍ 5 የሚለው ቃል ደግሞ በዓይነት 6 በዕድሜውና በመጠኑ ሳይለይ የእንጨትነት ፀባይ ያለው ተክል ሲሆን ቀርከሀ 7 ሸመል 7 ዘንባባና ሚኒስቴር መሥሪያቤቱ ዛፍ ብሎ የሚሰይመውን ተክል ይጨምራል በሚል ተተርጉሟል።

(ፊሊጶስ አይናለም። 2006። *የደን ልማትና ጥበቃ ለምንና በማን?* ቁ 199፣ ጥር 10፣ ገፅ 22 የተወሰደ።)

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ3ኛ ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን «የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ ከመጀመሪያውና ከመጨረሻው አንቀጽ የምታስታውሷቸውን ቁልፍ ሀሳቦች ተናገሩ።

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ሀ. «የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ለአንድ ደቂቃ ያህል ካነበባችሁ በኋላ ደቂቃው ሲሞላ ቆምብላችሁ ያነበባችኋቸውን ቃላት ቁጠሩና በ2ኛ ሳምንት፣ በ6ኛው ቀን በተጠቀማችሁበት የፍጥነት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ ላይ አስፍሩ።

ለ. ምንባቡን እንደገና ለአንድ ደቂቃ ያህል በፍጥነት አንብቡና ያነበባችኋቸውን ቃላት በፍጥነት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ ላይ መዝግቡ።


ሐ. የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን የንባብ ፍጥነታችሁን አወዳድሩ። በስንት ደቂቃ ይበላለጣል?

## መናገር

### በችግርና በመፍትሔ አወቃቀር ስልት መናገር

**ተግባር**

በሚከተለው የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም «የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ዋናዋና ተግባራት» በሚል ርዕስ ንግግር አቅርቡ።



# ሰዋስው

## አዎንታዊ ዓረፍተነገሮችን ወደአሉታዊ መለወጥና መጠይቃዊ ዓረፍተነገር መለወጥ

### ተግባር 1

የሚከተሉትን በአዎንታዊ የተጻፉ ዓረፍተነገሮች ወደአሉታዊ ለውጣችሁ ጻፉ።

ሀ. በተወሰነ ቦታ ላይ ሰውሠራሽ ሀይቅ በማዘጋጀት የአሳ ዝርያዎች አስገባ።

ለ. አቶ ዲባባ በውለታቸው መሠረት ቦታውን ተረከቡ።

ሐ. ፓርኩን የአካባቢው ማኅበረሰብ በመዝናኛነት ይጠቀምበታል።

መ. በምረቃው ቀን የክብር እንግዳው ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን በሰዓቱ ተገኝተዋል።

ሠ. በንፋስ የወደቁ ዛፎችን አቃንቶ ወደነበሩበት ለመመለስ ጥረት ተደርጓል።

### ተግባር 2

መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም መጠይቃዊ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡- የክብር እንግዳው <u>መቼ</u> ተገኙ?

- መቼ
- ለምን
- እንዴት
- ከማን ጋር
- የት
- በምን ምክንያት

?

የክብር እንግዳው ______ ተገኙ

ሀ. ______________________

ለ. ______________________

ሐ. ______________________

መ. ______________________

ሠ. ______________________

ረ. ______________________



# ምዕራፍ 7 የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ግንዛቤ-ያቸው-ን | ግንዛቤያቸውን |
| ለ | ሱቅ-በ-ደረት-ኤ-ነት | ሱቅበደረቴነት |
| ሐ | አሳሳቢ-ነት-ኡ-ን | አሳሳቢነቱን |
| መ | ቁስ-ኣ-ቁስ-ኦች | ቁሳቁሶች |
| ሠ | ህገ-መንግሥት-ኡ-ም | ህገመንግሥቱም |

**ተግባር 2**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በፍጥነት ደጋግማችሁ አንብቡ።

| | |
|---|---|
| ኮንቬንሽን | በማይፈቅድላቸው |
| ዕድሜያቸው | አስገዳጅነት |
| በሚደርስባቸው | እንዲጫወቱ |
| ከትምህርታቸው | እንዲንከባከቡ |
| ሳይፈነጥዙ | ይጠበቅባቸዋል |
| በሚሠሯቸው | አጽድቋል |
| ለአዕምሮ | የቤተሰቦቻቸውን |

## ማንበብ

## የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀት መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስለሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ሰምታችሁ ወይም አንብባችሁ ታውቃላችሁ? የምታስታውሱትን ተናገሩ።

ለ. ሕጻናት መሥራት ያለባቸውና የሌለባቸው ሥራዎች ምን ምን ይመስሏችኋል? ለምን?


ሐ. ሕጻናት ከአቅም በላይ የሆኑ ሥራዎችን እንዲሠሩ የሚገደዱባቸው ምክንያቶች ምንምን ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት


**ተግባር**

«የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የማታውቋቸውን ቃላት እየመዘገባችሁና ያልተረዳችኋቸውን አንቀጾች እየደጋገማችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ







በአሁኑ ዘመን አሳሳቢ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል አንደኛው የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ነው። ብዝበዛው በተለያየ መልክና መንገድ የሚፈጸም በመሆኑ አሳሳቢነቱን ከፍ ያደርገዋል። የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ የብዙ ሀገሮች ችግር ቢሆንም በታዳጊ ሀገራት ችግሩ ከባድ ነው። በአፍሪካ በተለይም ከሰሀራ በታች ባሉ ሀገሮች ደግሞ ችግሩ የበለጠ የከፋ ነው። ኢትዮጵያም የችግሩ ተጠቂ ናት።

በርካታ ሕጻናት በቤት ውስጥ በሚደርሱባቸው ጫናዎች ተገፋፍተውና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮ ለመደጎም ሲሉ በሚሠሯቸው ሥራዎች ለጉልበት ብዝበዛ ይጋለጣሉ። ብዙውን ጊዜ በወላጅ አስገዳጅነት ብሎም በህገወጥ መንገድ ሰዎችን በሚያዘዋውሩ አካላትና ግለሰቦች ለአስከፊ የጉልበት ብዝበዛ የሚጋለጡ ሕጻናት ቁጥር ቀላል አይደለም። በነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ዕድሜያቸው ለሥራ ያልደረሰና፣ አካላቸው ያልዳበረ ሕጻናት ለችግሩ ተጋላጭ ናቸው።

ሕጻናትን ከትምህርት በማሰናከል አእምሮአዊ እድገታቸውን በሚጎዱ ሥራዎች ላይ ማሰማራት የተለመደ ነው። በርካታ ሕጻናት ዕድሜያቸው በማይፈቅድላቸው ተግባራት ውኃ በመቅዳት፣ እንጨት በመልቀም፣ ከብት በመጠበቅ ወዘተ… ሥራዎች ይሰማራሉ። ሌሎች ደግሞ በእርሻ ሥራ፣ በቤት ውስጥ አገልግሎትና በመሳሰሉት ተግባራት ተሰማርተው ቤተሰባቸውን ይረዳሉ። ዕድሜያቸው በማይፈቅደው ሥራ በመሰማራታቸውም አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ እድገታቸው በጣም ይጎዳል።

በከተሞች በጫማ ጠራጊነት፣ በመኪና አጣቢነት፣ በተሸካሚነት፣ በሱቅ በደረቴነት፣ በሎተሪ አዟሪነት፣ በታክሲ ረዳትነት፣ የተሰማሩ ሕጻናት በርካታ ናቸው። በቤት ሠራተኛነት፣ በልጅ አሳዳጊነትና፣ በተላላኪነት ሥራ የተሰማሩትም ቁጥራቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በተለይ በልጅ አሳዳጊነት የሚቀጠሩ ሕጻናት ከፍተኛ ጥንቃቄ በሚጠይቁ ተግባራት ተሰማርተው እንዲይዙ፣ እንዲንከባከቡና

እንዲያጫውቱ ኃላፊነት ይጣልባቸዋል። እነሱ የጨዋታ ፍቅራቸውን ተነጥቀው በጊዜያቸው ሳይፈነጥዙ ሌሎችን እንዲያጫውቱ ይገደዳሉ። ከመንከባከብ በተጨማሪም የሕፃናቱን ልብሶች፣ መመገቢያና መጸዳጃ ቁሳቁሶች እንዲያጸዱ፣ እንዲሁም የቤት ውስጥ ሥራዎችን እንዲሠሩ ይደረጋሉ። እነዚህንና የመሣሰሉትን ከባድ ሥራዎች ቀን ተሌት ስለሚሠሩ በእንቅልፍና በዕረፍት እጦት የሚሰቃዩት በርካታ ናቸው።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሁሉም ሀገራት ችግር የሆነውን የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል የሕጻናት መብት ኮንቬንሽንን አጽድቋል። ኢትዮጵያም እ.ኤ.አ. 1991 ይህንን ኮንቬንሽን ፈርማለች። ኮንቬንሽኑ በአንቀጽ «32» ሕጻናትን አደገኛ በሆነ ሥራ ላይ ማሰማራት፣ ከትምህርታቸው ማሰናከል፣ ለጤንነታቸው፣ ለአካል፣ ለአእምሮ፣ ለመንፈሳዊ፣ ለሞራላዊና ማኅበራዊ እድገታቸው እንቅፋት የሚሆኑ ሥራዎችን ማሠራት የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ እንደሚባል ይደነግጋል። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥትም በአንቀጽ «36» «ሕጻናት ጉልበትን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርታቸው፣ በጤናቸውና በደህንነታቸው ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ሥራዎች የመጠበቅ መብት እንዳላቸው ደንግጓል። ይህም በኢትዮጵያ ሕጻናትን ከጉልበት ብዝበዛ መታደግ ትኩረት እንደተሰጠው ያሳያል።

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት ከቤታችን ጀምሮ የሚፈፀሙት የሕጻናት መብት ጥሰቶች እጅግ በርካታና የከፉ በመሆናቸው ችግሮቹን ለመቅረፍ ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል። የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ለማስቀረት አንደኛውና የመጀመሪያው መፍትሔ ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች ትምህርት መስጠት ነው። ወላጆች፣ አሳዳጊዎችና አሠሪዎች ከከተማ እስከገጠር ስለሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ትኩረት ሠጥተው ግንዛቤያቸውን ማስፋት አለባቸው።

(የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን። 1999። *ዓለማቀፍ የሰብዓዊ መብት ሠነዶች (የአማርኛ ትርጉም)* ለምንባብ እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በተመለከተ ኢትዮጵያና እንግሊዝ ሲነጻጸሩ በእንግሊዝ ሀገር ያለው የከፋ ነው» በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

ለ. በሁሉም ታዳጊ ሀገሮች ያለው የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ተመሳሳይ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

ሐ. የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን ህግ በመደንገግ ብቻ ማስቀረት የሚቻል ይመስላችኋል? ለምን?

መ. የሕጻናትን ጉልበት ብዝበዛ ለማስወገድ ሕጻናት ምንም ዓይነት ሥራ መሥራት የለባቸውም ትላላችሁ?

ሠ. የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በተመለከተ ወላጆች ራሳቸው ምክንያት ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?

## 2ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ መስጠትና በዐውድ መጠቀም

#### ተግባር 1


በ«ሀ» ረድፍ ለሚገኙት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን በ«ለ» ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. መጠበቅ | ሀ. የተሻለ |
| 2. የከፋ | ለ. ማስቀጠል |
| 3. ተጠቂ | ሐ. ተከፋ |
| 4. ደንግጓል | መ. ተጠቃሚ |
| 5. ማሰናከል | ሠ. ሽሯል |
| 6. ህገወጥ | ረ. መጋለጥ |
| 7. ፊነጠዘ | ሰ. ህገኛ |
| | ሸ. መልቀቅ |


#### ተግባር 2

የሚከተሉትን የቢጋር ሠንጠረዦች በተሰጡት ምሳሌዎች መሠረት በትክክለኛ ቃላት አሟሉ።

1.




2.




## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች ድርሰት መጻፍ

**ተግባር**

ሀ. በሚከተለው የቢጋር ሠንጠረዥ «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ዓይነቶች» በሚል ርዕስ በዋናና መዘርዝር ስልት ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችሉ ሀሳቦችን አስፍሩ።

ርዕስ

መግቢያ

| የአንቀጽ 1 ዋና ሀሳብ | የአንቀጽ 2 ዋና ሀሳብ |
|---|---|
| ዝርዝር ሀሳቦች ______ | ዝርዝር ሀሳቦች ______ |
| ______ | ______ |
| ______ | ______ |

| የአንቀጽ 3 ዋና ሀሳብ | የአንቀጽ 4 ዋና ሀሳብ |
|---|---|
| ዝርዝር ሀሳቦች ______ | ዝርዝር ሀሳቦች ______ |
| ______ | ______ |
| ______ | ______ |

ማጠቃለያ

ለ. በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች ስልት ድርሰት ለመጻፍ በቢጋር ሠንጠረዥ ያደራጃችኋቸውን ሀሳቦች በመከለስ አስተካክላችሁ ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም መጻፍ

**ተግባር**

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ተገቢውን ሥርዓተነጥብ አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. ሕጻናት በማንኛውም ሥራ እንዳይቀጠሩ ተደንግጓል ነገርግን ከአቅማቸው በላይ ሥራ ሲሠሩ ይታያሉ

ለ. ሕፃኑ ሲደበደብ የት ነበርሽ

ሐ. የልጅ ባህርይ እንዳሳዳጊው ነው ይላሉ ወሮ ሮማን

መ. ወይንሸት አልማዝ መሀመድ ቢያድግልኝና አስቴር ስለሕጻናት መብት ተወያዩ

ሠ. የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ይቁም

ረ. የሽመና ሥራ ሽክም የታክሲ ረዳትነት የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ የሚካሄድባቸው የሥራ ዘርፎች ናቸው

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

ሀ. «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሷቸውን ፍሬ ሀሳቦች ተናገሩ።

ለ. በምዕራፍ ስድስት የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ፍጥነታችሁን መመዝገባችሁን ታስታውሳላችሁ። ፍጥነታችሁን በማነጻጸር ማን ፈጣን አንባቢ እንደነበር አስተያዩ።

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ» የሚለውን ምንባብ በቡድን ሆናችሁ ተራበተራ ለአንድ ደቂቃ ያህል ድምፅ እያሰማችሁ በማንበብ የፍጥነት ደረጃ አውጡ።

## ማዳመጥ

# የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምክንያቶች

### ቅድመማዳመጥ

### ርዕስን ተመርኩዞ የምንባብ ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ዛሬ የምታዳምጡት ምንባብ ርዕስ «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምክንያቶች» የሚል ነው። ከምንባቡ ርዕስ ተነስታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. ቤተሰቦቻችሁን በሥራ ታግዛላችሁ? በአካባቢያችሁ የሚኖሩ ሕጻናት ምን ምን ሥራ ይሠራሉ?

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

መምህራችሁ «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምክንያቶች» በሚል ርዕስ ምንባብ ያነቡላችኋል፤ ዋናዋና ሀሳቦችን በደብተራችሁ በመጻፍ በንቃት አዳምጡ።

### አዳምጦ መረዳት

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ቤተሰብን በሥራ ማገዝ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን የሚያስከትል ይመስላችኋል?

ለ. «ሕጻናትን ለጉልበት ብዝበዛ ከሚያጋልጧቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ድህነት ነው» የሚለውን ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ አብራርታችሁ ተናገሩ።

**ተግባር 2**

የሚከተሉትን ያልተቋጩ ሀሳቦች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት አሟልታችሁ ተናገሩ።

ሀ. የሕጻናት ሥራ...

ለ. የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ግን ...

ሐ. ሕጻናት በወላጆቻቸው ግፊትና ተፅዕኖ...


መ. ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች ...

## ሰዋስው

### ተውሳከግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መመሥረት

### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት ተውሳከግሶችን በመጠቀም ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።




ምሳሌ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰሚራ | ሁልጊዜ | ለስላሳ | ትጠጣለች። |
| ቸሩ | አንዳንድ ጊዜ | ለስላሳ | ይጠጣል። |
| ከድርና ቸርነት | አልፎአልፎ | ለስላሳ | ይጠጣሉ። |

### ተግባር 2

የተለያዩ ተውሳከግሳዊ ቃላት በመጠቀም አምስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

## ማንበብ

### የሕጻናት የሥራ ዕድሜ

### ቅድመንባብ

### ርዕስን ተመልክቶ የምንባብን ይዘት መገመት

#### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «የሕጻናት የሥራ ዕድሜ» ከሚለው የምንባብ ርዕስ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. ሕጻናት ዕድሜያቸው ለሥራ ደረሰ የሚባለው ስንት ዓመት ሲሆናቸው ነው?

ሐ. ሕጻናት ዕድሜያቸው ለሥራ እስኪደርስ ምንም ዓይነት ሥራ መሥራት የለባቸውም ትላላችሁ? ለምን?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

«የሕጻናት የሥራ ዕድሜ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የእያንዳንዱን አንቀጽ ሀሳብ በአዕምሯችሁ እያጠቃለላችሁ አንብቡ።

### የሕጻናት የሥራ ዕድሜ

ሥራን ለማከናወን ዕውቀት፣ ጉልበትና መሣሪያ እንደሚያስፈልግ ሁሉ ዕድሜም ወሳኝነት አለው። ዕድሜ እየጨመረ በሄደ መጠን አእምሮ ይዳብራል፣ አካል ይጠነክራል። በአስተሳሰብም ላይ ለውጥ ስለሚመጣ ሥራን በዕውቀትና በብልሃት ለማከናወን ይቻላል። ሕጻናት በለጋ ዕድሜያቸው ሥራ እንዲሠሩ ማድረግ ግን በአካላቸውም ሆነ በአዕምሯቸው ላይ ጫና መፍጠር ነው። ለዚህም ሲባል ሕጻናት ለሥራ የሚሰማሩበት የዕድሜ ገደብ በዓለማቀፍና በአገርአቀፍ ደረጃ ተደንግጓል።

የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛን በጽኑ ከሚቃወሙት ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት። የሕጻናትን መብትና ደህንነት ለማስጠበቅ ዓለማቀፍ ድንጋጌዎችንና ስምምነቶችን በማጽደቅ እየሠራች ትገኛለች። በኢትዮጵያ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑት ሰዎች በሕጻናት ምድብ ውስጥ ይካተታሉ። በዚህም መሠረት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌ ዕድሜያቸው ከ14 ዓመት በታች የሆነ ሕጻናት በማንኛውም ሥራ ላይ እንዳይሰማሩ ይከለክላል። በአዋጁ

እንደተመለከተው ምንም እንኳን ከ14 እስከ18 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕጻናት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ቢፈቀድላቸውም፣ ጥበቃ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ይደነግጋል፤

**ሕጻን ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው።**

እነዚህ ታዳጊዎች በቀን ከሰባት ሰዓት በላይ እንዲሠሩም አይፈቀድም። ይህንን ድንጋጌ ተላልፈው የሚገኙ ግለሰቦችም ከፍተኛ ቅጣት ይጠብቃቸዋል። ይሁን እንጂ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ በሕጻናት ላይ ሰብዓዊነት የጎደላቸው ተግባራትን የሚፈጽሙ ህገወጦች በርካታ ናቸው።

ሕጻናትን ያለዕድሜያቸው በከባድ ሥራ ላይ ማሰማራትና ጉልበታቸውን መበዝበዝ እዚህ ቦታ ላይ ብቻ ይከናወናል ብሎ ለማለት ያስቸግራል። አንዳንድ አካባቢዎች ሕፃናቱን በአቅራቢነት ሌሎች አካባቢዎች ደግሞ በተቀባይነት ወይም ለሕፃናቱ ዝውውር መሸጋገሪያ በመሆን ይሳተፋሉ። በመሆኑም በከተማም ሆነ በገጠር ደረጃውና ዓይነቱ ይለያይ እንጂ፣ የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ይካሄዳል። በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጻናት ዕድሜያቸው ለሥራ ሳይደርስ የምሽትና ከባድ የሸክም ሥራ እንዳይሠሩ፣ በሌሎች ሥራዎች ላይ ሲሳተፉም የሥራ ሰዓታቸው ከዓዋቂዎች እኩል እንዳይሆን ቢደነግግም በከተሞች አካበቢ በተለያዩ አስቸጋሪ ሥራዎች ተሰማርተው ረጂም ሰዓት ሲሠሩ ይታያሉ። ለሠሩበትም ተመጣጣኝ ክፍያ ስለማያገኙ ጉልበታቸውን በከፍተኛ ደረጃ ይበዘበዛሉ።

ከዚህም ሌላ ሕጻናት የዓለም የሥራ ድርጅት ከሚያወግዛቸውና አስከፊ የጉልበት ብዝበዛ ብሎ ከሚመድባቸው መጥፎ ሥራዎች ላይ ሳይቀር ሲሳተፉ ይታያሉ። በአልኮል ንግድ፣ በዝሙት፣ በእፅ ማዘዋወርና በመሣሠሉት ተግባራት ተሰማርተው ይገኛሉ። የእነዚህን ተግባራት ጎጅነት ሕፃናቱ ካለማወቃቸውና ካለመገንዘባቸው የተነሳ ሌሎች ስለሚፈጽሟቸው ብቻ እነሱም በለጋ ዕድሜያቸው ይፈጽሟቸዋል። በዚህም የተነሳ ገና ያለ ዕድሜያቸው የሱስ ተገዥ በመሆን ህይወታቸውን ያበላሻሉ።

በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍሎችም የሕጻናት የጉልበት ብዝበዛ ይዘወተራል። ሕጻናት እርሻ ያርሳሉ፤ ሰብሎችን በቀንና በሌሊት ይጠብቃሉ፤ ከጫካ የማገዶ እንጨት ይለቅማሉ። በአሁኑ ጊዜ እየተሻሻለ ያለ ቢሆንም ከብቶችንም ያግዳሉ። በነዚህና በመሣሠሉት ሥራዎች ስለሚሰማሩ ከፍተኛ የጉልበት ብዝበዛ ይደርስባቸዋል።

በዓለማችን 215 ሚሊዮን ያህል የሚገመቱ ሕጻናት ለጉልበት ብዝበዛ ተዳርገው አስከፊ ህይወትን እየመሩ እንደሚገኙ የዓለም ሥራ ድርጅት በ2010 (እ.አ.አ) ያወጣው ዓመታዊ ዘገባ ይገልጻል። ከነዚህ ውስጥ 115 ሚሊየን የሚሆኑት ለደህንነታቸውና ለጤንነታቸው እጅግ አደገኛና ጠንቀኛ በሆኑ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው፣ የትምህርት ዕድል ሳያገኙ ሰብዓዊ ክብራቸው ተነፍጎ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኙ ዘገባው በተጨማሪ ያትታል።

በአጠቃላይ ዕድሜ የአካልና የአዕምሮ ብስለትን ሊያሳይ ይችላል። በመሆኑም ሕጻናት በሥራ ላይ ለመሠማራት በአካልና በአዕምሮ መብሰል አለባቸው። ነገርግን

በርካታ ሕጻናት በከፍተኛ የጉልበት ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ይታያሉ። ይህም በአካላቸውና በሥነልቦናቸው ላይ ጫና ይፈጥራል። ስለሆነም በሕጻናት ላይ የሚደርስ ብዝበዛን ለማስወገድ ዕድሜያቸውን በትክክል ማወቅ ይጠቅማል። ለዚህም የልደት ምዝገባ ባህልን ማዳበር ያስፈልጋል። የወላጆችና የማኅበረሰቡን ግንዛቤ በማዳበር ያለዕድሜያቸው ለከፍተኛ እንግልትና ስቃይ የሚዳረጉ ሕጻናትን መታደግ ይገባል።

(ከዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ድረገጽ፣ ሰኔ 22፣ 2006 ዓ.ም. ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የመጀመሪያውን አንቀጽ ሀሳብ ጨምቃችሁ በአንድ ወይም በሁለት ዓረፍተነገር ጻፉ።

ለ. የሁለተኛውን አንቀጽ ሀሳብ በሁለት ዓረፍተነገር አጠቃላችሁ ጻፉ።

ሐ. የአንቀጽ ሁለትን ሀሳብ አጠቃላችሁ ስትጽፉ ሀሳባቸው በአንቀጹ አጠቃላይ ሀሳብ ሊጠቃለሉ ያልቻሉ ዓረፍተነገሮች አጋጥመዋችኋል? አጋጥመዋችሁ ከሆነ ምን ይጠቁሟችኋል?

# 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር 1

በ«ሀ» ረድፍ የተዘረዘሩትን በ«ለ» ረድፍ ከተዘረዘሩት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ።

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1. ብልሀት | ሀ. ሕጻን፣ ያልበሰለ |
| 2. ስቃይ | ለ. ችግር፣ መከራ |
| 3. ለጋ | ሐ. የዕድሜ ደረጃ |
| 4. ገደብ | መ. ስልት፣ ጥበብ |
| 5. በጽኑ | ሠ. በጥንካሬ |
| 6. ምድብ | ረ. ጥፋት ማስተካከያ ርምጃ |
| 7. ቅጣት | ሰ. ወሰን |

## ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ፍቺ ስጡ።

ሀ. ተነፍጎ (አንቀጽ «6»)

ለ. ጠንቀኛ (አንቀጽ «6»)

ሐ. መሸጋገሪያ (አንቀጽ «3»)

መ. ጫና መፍጠር (አንቀጽ «1»)

ሠ. ህገወጦች (አንቀጽ «2»)

ረ. የጎደላቸው (አንቀጽ «2»)

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች ድርሰት መጻፍ

## ተግባር

በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን ባዘጋጃችሁት የቢጋር ሠንጠረዥ መሠረት «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ ዓይነቶች» በሚል ርዕስ በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች መዋቅር ስልት ድርሰት ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም መጻፍ

## ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አንቀጽ አዳምጣችሁ ፊደላትን ሳትገድፉ፣ ቃላትን ሳትደጋግሙ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ጻፉ።

# 6ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የሕጻናት የሥራ ዕድሜ

## ቅድመንባብ

## ተግባር

የሚከተሉትን የቅደመንባብ ተግባራት ሥሩ።

ሀ. በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ» በሚል የቀረበውን ምንባብ ስታነቡ በደቂቃ ስንት ቃላት አንብባችሁ ነበር?

ለ. አሁንስ የማንበብ ፍጥነታችሁን የምትጨምሩ ይመስላችኋል? በደቂቃ ስንት ቃላት ለማንበብ እንደምትፈልጉ አቅዱ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ሀ. «የሕጻናት የሥራ ዕድሜ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁን እየተከተላችሁ ለአንድ ደቂቃ አንብቡ።

ለ. አሁን ደግሞ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ አንዳችሁ ስታነቡ አንዳችሁ ደቂቃ በመያዝ ፍጥነታችሁን በፍጥነት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ ላይ አስፍሩ። በመቀጠል ሁላችሁም በየግላችሁ ለአንድ ደቂቃ ያህል አንብቡና ፍጥነታችሁን መዝግቡ።

ሐ. ከመጀመሪያውና ከሁለተኛው ንባባችሁ በየትኛው ነው የተሻለ ፍጥነት ያላችሁ?

# መናገር

## በተሰጠ ርዕስ ተዘጋጅቶ ንግግር ማድረግ

### ተግባር

«የሕጻናት መብት ድንጋጌዎችና ተጨባጭ እውነታዎች» በሚል ርዕስ ተዘጋጅታችሁ ንግግር አድርጉ።

# ሰዋስው

## ጠቋሚ መስተዓምር

### ተግባር

የሚከተሉትን የሰዋስው ተግባራት ሥሩ።

ሀ. በ2ኛው ሳምንት፣ በ4ኛው ቀን «የሕጻናት የሥራ ዕድሜ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ አራት ጠቋሚ መስተኣምሮችን አውጥታችሁ ጻፉ፣ የሚገኙበትን ቦታ ጠቁሙ።

ለ. ጠቋሚ መስተዓምር የሚገኝባቸው አምስት ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| | ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | እየ-ተደረገ-ል-ላቸው | እየተደረገላቸው |
| ለ | መብት-ኦች-አቸው-ን | መብቶቻቸውን |
| ሐ | ዓለም-አቀፍ-ኣዊ | ዓለምአቀፋዊ |
| መ | ይ-አስ-ፈልግ-ኣቸው-ኣል | ያስፈልጋቸዋል |
| ሠ | ል-ይ-ኣጋጥም-ኡ-ኣቸው | ሊያጋጥሟቸው |
| ረ | ትምህርት-ቤት-ኦች-ን | ትምህርትቤቶችን |
| ሰ | ልጅ-ኦች-ኣቸው-ን | ልጆቻቸውን |
| ሸ | ሕጻን-ኣት-ኡ-ን | ሕፃናቱን |
| ቀ | ይ-ፈፀም-ብ-ኣቸው-ኣል | ይፈፀምባቸዋል |

## ማንበብ

### የሕጻናት መብት


**ቅድመንባብ**

**የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ**

**ተግባር**


ሀ.«የሕጻናት መብት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት፣ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት፣ የቢጋር ምስሉን አሟልታችሁ ተናገሩ።

ምሳሌ፡-




ሰብዓዊ
ሀሳብ የመግለጽ
በህይወት
የመኖር
የመኖር
የመማር
መብት
የሴቶች
የዜግነት
የመምረጥ
የሕፃናት


ሀ.




ቅጣት


ለ.




እንክብካቤ

ሐ.




መ.




ለ. «የሕጻናት መብት» ከሚለው ርዕስና ከስዕሉ ተነስታችሁ ምንባቡ ስለምን ሊገልጽ እንደሚችል ገምታችሁ ተናገሩ።


## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«የሕጻናት መብት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የማታውቋቸውን ቃላት እየመዘገባችሁና የየአንቀጹን ሀሳብ በአዕምሯችሁ እያጠቃለላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## የሕጻናት መብት

ሕጻናት፣ ሐገር ተረካቢ በመሆናቸው ልዩ እንክብካቤ እየተደረገላቸው በሥርዓት ማደግ ይኖርባቸዋል። ስለሆነም በመጀመሪያ ወላጆች በሁለተኛ ደረጃ ማኅበረሰቡ በአጠቃላይ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ሕጻናት ገና በለጋ ዕድሜያቸው አዕምሯዊና አካላዊ ጫና ካለባቸው ሁለንተናዊ ዕድገታቸው ይጎዳል። ስለሆነም መንፈሳዊና አካላዊ እድገታቸውን የተሻለ ለማድረግ የመኖር፣ እንክብካቤ የማግኘት ወዘተ መብቶቻቸውን ማክበር ይገባል።




የሕጻናት መብት ዓለማቀፋዊ ባህርይ አለው። በህይወት መኖር አንዱ የሕጻናት መብት ነው። ሕጻናት በህይወት መኖር እንዲችሉ ከፅንሰት ጀምሮ ጤንነታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል። እናቶች በእርግዝና ጊዜ የሃኪሞች ክትትልና ምክር ያስፈልጋቸዋል። ለዚህም የጤና ተቋማት በበቂ ሁኔታ በየአካባቢው መስፋፋት አለባቸው። የጤና ተቋማት መስፋፋት ሕጻናት ከተወለዱ በኋላም ጤናማ ሆነው እንዲያድጉ፣ በተከታታይ የክትባት አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል። የሕጻናት ንፅህና በየጊዜው መጠበቅ ይኖርበታል። ልብሶቻቸው፣ መኝታቸውና መመገቢያ ቁሳቁሶቻቸው ሁሉ በንጽህና መያዝ አለባቸው። ጤንነታቸውን በመጠበቅ የሞት መጠንን መቀነስና የሕጻናትን በህይወት መኖር ማረጋገጥ ይቻላል።

**ሕጻናት በህይወት የመኖር፣ ትምህርት የማግኘት፣ ከኃይል ጥቃትና ጉልበት ብዝበዛ ነፃ የመሆን መብት አላቸው።**

ሌላው ሕጻናት በህይወት መኖር እንዲችሉ በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ኃላፊነት አለበት። ሕጻናት በጨዋታና በመዝናኛ ቦታዎች ከዕድሜ አለመብሰልና ካለማወቅ የተነሳ የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ። ስለሆነም ሕጻናትን መምከር፣ ማስተማርና ከተለያዩ ችግሮች መታደግ ከማኅበረሰቡ ይጠበቃል።

ሕጻናት አውቀውም ሆነ ባለማወቅ ወንጀል ሊፈጽሙ ይችላሉ። ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙም የሚወሰድባቸው የእርምት እርምጃ ከአዋቂዎች የተለየ መሆን እንዳለበት

በህግ ተደንግጓል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የህግ ባለሙያዎች ይህንኑ ከግምት እንዲያስገቡ ይጠበቃል። በሕጻናት ላይ የሚወሰዱት ህጋዊ ርምጃዎች አስተማሪና ለወደፊት ህይወታቸው ጠቃሚ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

የሕጻናት ሌላው መብት ትምህርት የማግኘት መብት ነው። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ የቤተሰብ ድጋፍና በጎ አመለካከት ወሳኝ ነው። አንዲት ሀገር ማደግና መበልጸግ የምትችለው ዜጎች በትምህርት ልቀው ሲገኙ ነው። ስለሆነም ዜጎች የትምህርት ዕድል ማግኘት ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ትምህርትቤቶችን በየአካባቢው በጥራት ማስፋፋት ያስፈልጋል። የትምህርትቤቶች መስፋፋት ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕጻናትን የመማር ዕድል ያሰፋል። ሕጻናት ጥራት ባለው ትምህርት ሲታነፁ የአስተሳሰብ አድማሳቸው ይሰፋል፣ የፈጠራ ችሎታቸው ይዳብራል፣ ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ ዜጎች ይሆናሉ። በመሆኑም ወላጆች ልጆቻቸው በጥራትና በብቃት የሚማሩባቸውን ሁኔታዎች የማመቻቸት ኃላፊነት አለባቸው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ወላጆች የሕጻናትን ጉልበት ለመጠቀም በመፈለግ ልጆቻቸውን ወደትምህርትቤት ከመላክ ይልቅ ጊዜያዊ ችግራቸውን ለመፍታት የልጆቻቸውን ጉልበት መጠቀም ይመርጣሉ። ይህንንም ለማስወገድ ወላጆችን በማስተማር የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል። በዚህም የማስተማር ግዴታቸውን በትክክል እንዲወጡ ማድረግ ይቻላል።

ከማንኛውም የኃይል ጥቃት ነፃ መሆን ሌላኛው የሕጻናት መብት ነው። ይሁን እንጂ ይህ መብት እንደሌሎቹ መብቶች ሲከበርላቸው አይታይም። ለምሳሌ ልጆችን በሥነምግባር አንጾ ለማሳደግ ይረዳል በሚል አጉል ልማድ ልጆችን መቅጣት በአብዛኛው የተለመደ ነገር ነው። ወላጆችና ሌሎች ለሕጻናት ቅርበት ያላቸውም ሆኑ ቅርበት የሌላቸው ሰዎች በልጆች ላይ የተለያዩና ተደራራቢ አካላዊ ቅጣቶችን ይፈፅማሉ። መቆንጠጥ፣ በአርጩሜ ወይም በአለንጋ መግረፍ፣ ሲከፋም በበርበሬ ጪስ ማጠንና በስለት መውጋት የተለመዱ ቅጣቶች ናቸው። ሕጻናት ስሜታቸውን ሊጎዱ በሚችሉ ስድቦች ይሰደባሉ። እነዚህና መሰል ቅጣቶች በሕፃናቱ አዕምሮ ሥነልቦናዊ ጫናን ይፈጥራሉ። የሕፃናቱን መብቶች በከፍተኛ ደረጃ ይጋፋሉ።

ከተጠቀሱት በተጨማሪ ሕጻናት ከጉልበት ብዝበዛ ነፃ የመሆን መብት አላቸው። ሆኖም ሕጻናትን ከዕድሜያቸው በላይ በማሠራት ይህ መብታቸው ሲጣስ ይታያል። በከተማ አካባቢ በሸማ ሥራ፣ በጫማ ጠረጋ፣ ከባድ በሆኑ የቤትውስጥ ሥራዎች ሕጻናት ጉልበታቸው ይበዘበዛል። በገጠር አካባቢዎችም ያለአቅማቸው በጫካ ውስጥ የማገዶ እንጨት በመልቀም፣ ውኃ በመቅዳትና በመሳሰሉት ከባድ ሥራዎች ይጠመዳሉ። ብዙ ሕጻናትም ለቤተሰቦቻቸው ገቢ መደጎሚያ ሲባል፣ ብዙ ዓይነት ብዝበዛዎች ይፈጸሙባቸዋል። በመሆኑም እነዚህን የሕጻናት መብት የሚጥሱ ተግባራትን በመቆጣጠር የሕፃናቱን ደህንነት መጠበቅ ያስፈልጋል።

የሕጻናት ሰብዓዊ መብት እንዲጠበቅ በአጠቃላይ ከማኅበረሰቡ በተለይ ደግሞ ከወላጆች ከፍተኛ ኃላፊነት ይጠበቃል። ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ወላጆችንና ማኅበረሰቡን ማስተማርና ማሳወቅ ያስፈልጋል። ሕጻናት መብታቸው ተጠብቆ ካደጉ ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻቸው ብሎም ለሀገራቸው ጠቃሚ ዜጎች ይሆናሉ። ስለዚህ የሕጻናትን መብቶች በመጠበቅ ውጤታማ ዜጎችን ማፍራት ይቻላል።

(የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን። 1999። *ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሠነዶች፣* (የአማርኛ ትርጉም)ለምንባብ እንዲያመች ሆኖ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በምንባቡ የተገለፁትን የሕጻናት መብቶች በራሳችሁ አባባል ግለፁ።

ለ. «ሕጻናት ሐገር ተረካቢ ናቸው» ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ሐ በምንባቡ ውስጥ በአንቀጽ ሁለትና በአንቀጽ ሦስት የቀረቡትን የሕጻናት መብቶች አንድነትና ልዩነት አስረዱ።

መ. የአንቀጽ ሦስትን ዋና ሃሳብ ጨምቃችሁ በአንድ ዓረፍተነገር ጻፉ።

ሠ. በአንቀጽ ስድስትና ሰባት የቀረቡትን የሕጻናት መብት በማነፃጸር ግለጹ።

# 8ኛ ቀን


## ቃላት


### ቃላትን በተለያዩ ዐውዶች መጠቀም

### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት ቃላትን በተለያዩ ዐውድ በመጠቀም የቢጋር ክቡን አሟሉ

ምሳሌ፦




## ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ዐውድ መሠረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ጻፉ።

ሀ. አለመብሰል (አንቀጽ 3)

ለ. እርምት (አንቀጽ 4)

ሐ. ተቋማት (አንቀጽ 2)

መ. በጥራት (አንቀጽ 5)

ሠ. መበልፀግ (አንቀጽ 5)

ረ. በጎ አመለካከት (አንቀጽ 5)

ሰ. ሊጠበቅላቸው (አንቀጽ 2)

ሸ. ሁለንተናዊ (አንቀጽ 1)

ቀ. የአስተሳሰብ አድማሳቸው(አንቀጽ 5)

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና ዝርዝር ሀሳቦች የተደራጁ ሀሳቦችን መከለስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የድርሰት መገምገሚያ መስፈርቶች በመጠቀም በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን «የሕጻናት ጉልበት ብዝበዛ አይነቶች» በሚል ርዕስ የጻፋችሁትን ድርሰት በመከለስ አስተካክላችሁ ጻፉ።

የድርሰት መገምገሚያ (ማረሚያ) መስፈርቶች

ሀ. ርዕስ ጠብቆ መጻፍ

ለ. የአንቀጹን ዋና ሀሳብ በግልጽ ማሳየት

ሐ. ዋናውን ሀሳብ በተገቢ መዘርዝሮች መግለጽ

መ. ሀሳብን በቅደምተከተል ማደራጀት

ሠ. ቃላትን በአግባቡ መጠቀም

ረ. አንባቢዎች ሊረዱቸው የሚችሏቸው ዓረፍተነገሮች መጠቀም

ሰ. የተሟላ ዓረፍተነገር መጠቀም

ሸ. ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በተገቢ ቦታ መጠቀም

ቀ. የሀሳብ አንድነትና ግጥምጥምነት ያላቸው አንቀጾች ማዋቀር።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችን መጠቀም

**ተግባር**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አንቀጽ እያዳመጣችሁ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም በትክክል ጻፉ።

## 9ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የሕጻናት መብት

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

ሀ. በ3ኛው ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን «የሕጻናት መብት» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሷቸውን ዋናዋና ሀሳቦች ጥቀሱ።

ለ. «የሕጻናት መብት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ስታነቡ በደቂቃ ስንት ቃላት እንዳነበባችሁ ታስታውሳላችሁ? ፍጥነታችሁ በፊት ከነበራችሁ ፍጥነት ጨምሯል ወይስ ቀንሷል? ለምን ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ሀ. «የሕጻናት መብት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ፍጥነታችሁን እየመዘገባችሁ አንብቡ።

# መናገር

### ዋናዋና ሀሳቦችን በማደራጀት መናገር

**ተግባር**

«የሕጻናት ሥራ» በሚል ርዕስ ዋናዋና ሀሳቦችን በሚከተለው የቢጋር ሠንጠረዥ በማደራጀት ንግግር አድርጉ።

| በሕጻናት የሚሠሩ ሥራዎች | በሕጻናት የማይሠሩ ሥራዎች |
|---|---|
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |
| • | • |

## ሰዋስው

### ተውሳከግሶችን መለየት

**ተግባር**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ተውሳከግሶችን ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።

ሀ. በቀለ አምና ሰባተኛ ክፍል ነበረ።

ለ. መሠረትና ሀዊ ነገ ደብረዘይት ይሄዳሉ።

ሐ. ፈለቀች ሁልጊዜ ስለሕጻናት መብት ታስተምራለች።

መ. ሁሴን አልፎአልፎ ሐዋሳ ይሄዳል።

ሠ. ወይዘሮ እናኑ ትናንት ሕጻናትን ለማነጋገር ፈልገው ነበር።

ረ. ፈይሳ ቶሎቶሎ በመራመድ ካሰበው ቦታ ደረሰ።

ሰ. ሀሌማ አንዳንድ ጊዜ መዝሙር ትዘምራለች።



# ምዕራፍ 8 የሴቶችን አቅም መገንባት

ሥርዓተጾታና ትምህርት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### ውስብስብ ቃላትን በመነጠልና በማጣመር ማንበብ

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ቃላት በመጀመሪያ ነጣጥላችሁ፣ በመቀጠል የመድረሻ ቅጥያዎችን ብቻ አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | መድረሻ ቅጥያቸው ማንበብ |
|---|---|
| ይደርስ-ብ-ኣችው-ኣል | -ኣል |
| ይቀንስ-ብ-ኣት-ኣል | -ኣል |
| ይኖር-ብ-ሽ-ኣል | -ኣል |
| ያግዝ-ኣችሁ-ኣል | -ኣል |

**ተግባር 2**

የሚከተሉትን ቃላት በመጀመሪያ በመነጣጠል ጽፋችሁ አንብቡና መድረሻ ቅጥያቸውን አውጥታችሁ ጻፉ።

| የተጣመሩ ቃላት | ነጣጥለው በመጻፍ ማንበብ | መድረሻ ቅጥያዎችን ብቻ መጻፍ |
|---|---|---|
| ይቀርብሃል | | |
| ይፈልግሻል | | |
| ይመክሩናል | | |
| ይፈልገኛል | | |

## ማንበብ


## ሥርዓተጾታና ትምህርት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር 1

«ለውጥ»ና «ተኮር» የሚሉትን ቃላት ከዚህ በታች በቀረበው ምሳሌ መሠረት በተለያዩ ዐውዶች ተጠቀሙ።




### ተግባር 2

የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም «ጾታ»ና «ሥርዓተጾታ» በሚሉት ቃላት መካከል ስላለው አንድነትና ልዩነት ተናገሩ።

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ጥንድ ጥንድ በመሆን «ሥርዓተጾታና ትምህርት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የመጀመሪያውን አንቀጽ ዓረፍተነገር በዓረፍተነገር በየተራ አንብቡ። አንዳችሁ አንድ ዓረፍተነገር አንብባችሁ ስትጨርሱ፣ አንዳችሁ የዓረፍተነገሩን ሀሳብ አብራሩ። ቀሪዎቹን አንቀጾች በግላችሁ አንብቡ።



### ሥርዓተጾታና ትምህርት

ሥርዓተጾታና ጾታ የተለያዩ እሳቤዎች ናቸው። ጾታ በወንድና በሴት መካከል ያለን የተፈጥሮ ልዩነት የሚያሳይ ነው። ሥርዓተጾታ ደግሞ በሰዎች የመኖር ሂደት በማኅበረሰቡ አማካይነት ተፈጥሮ ያደገ ብሎም የማኅበረሰቡ ምጣኔሀብታዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ሲኖር አብሮ ሊቀየር የሚችል አስተሳሰብ ነው። ስለሆነም የሥርዓተጾታ ጽንሰሀሳብ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ያልተመጣጠነ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለመግለጽ ያገለግላል።

የተዛባ የሥርዓተጾታ አመለካከት የሰፈነበት ማኅበረሰብ የተዛባ አመለካከቱ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ እንዲሄድ ባህል ትልቅ መሠረት ይሆናል። ይህም

በሴትና ወንድ ልጆች አስተዳደግ ይንጸባረቃል። ወንዶች ልጆች የተሻለ ዕውቀትና ሙያ ባለቤት እንዲሆኑ የቤተሰቡ አባል ሁሉ ደፋ ቀና ይላል። ለሴት ልጆች ግን የቤት ውስጥ ባልትና ብቻ ካወቀች በቂ እንደሆነ ስለሚገመት ከዚያ ያለፈ እገዛ ላይደረግ ይችላል። በዚህም የተነሳ የሴቶች የመማር፣ የመመራመርና አዲስ ነገር የመፍጠር ኃይል ውስን ይሆናል።

አድሏዊ የሥርዓተጾታ አመለካከትና ማኅበራዊ ዕሴቶች፣ ደንቦችና እምነቶች የሴቶችን የመማር መብት እውንነት ያደናቅፋሉ። በዚህም የተነሳ ከዝቅተኛ እስከከፍተኛ የትምህርት ደረጃዎች የሚማሩ ሴቶች ቁጥር ያነሰ ይሆናል። ቤተሰብ የአንድ ማኅበራዊ ትስስር የሚጀምርበት መነሻ ተቋም እንዲሆን የሚጠበቅ ቢሆንም፣ አድሏዊ ሥርዓተጾታ ባለበት ማኅበረሰብ የመብት ረገጣ የሚጀመርበትና የሚበረታታበት ሆኖ ሲያገለግል ይታያል። በዚህም ወላጆች ወንዶች ልጆቻቸውን ጎበዝ፣ ሴቶቹን ደግሞ ሰነፍ አድርገው ይቆጥራሉ። ወንዶችን ይደግፋሉ፣ ያበረታታሉ። ለወንዶች የሚደረግላቸው ድጋፍ መነሳሳትን በመፍጠር የክፍል ተሳትፏቸውን ለማዳበር ያግዛቸዋል። ሴቶች ልጆች ደግሞ ትምህርትቤት ሄደው ከመማር ይልቅ በቤት ውስጥ ሙያን እንዲለማመዱ ይደረጋሉ። ከመኖሪያቸው ርቆ በሚገኝ ትምህርትቤት የሚማሩትም በመንገድ ላይ ወሲባዊ ጥቃት ሊያጋጥማቸው ይችላል። በዚህም አስገዳጅነት ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ሊገደዱ ይችላሉ። በቤት ውስጥም የእኩልነት መብታቸው በመነፈጉና እንደወንዶች «ታውቃላችሁ»፣ «ትችላላችሁ» እየተባሉ ባለማደጋቸው በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል። በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ይቀንሳል፣ በራስ መተማመናቸውም ይጎዳል። በአጠቃላይ እነዚህና መሰል ሥርዓተጾታዊ አድሎዎች የሴት ተማሪዎችን ውጤታማነት በእጅጉ ይፈታተናሉ።

ትምህርትቤቶችም በሥርዓተጾታ ምክንያት ለሚፈጠረው የትምህርት ልዩነት ምክንያት ይሆናሉ። ወንድ ተማሪዎች በትምህርትቤት ያላቸው ነፃነት ሰፊ ነው። በብዙ ትምህርትቤቶች መጻዳጃቤቶች፣ የቤተሙከራ (የላቦራቶሪ) መቀመጫዎች፣ የስፖርት ሜዳዎች ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የተመቹ ናቸው። የመማሪያ መጻሕፍትም በሴቶች ትምህርት ላይ ያላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም። በመጻሕፍቱ ውስጥ ያሉት ተግባራትና የቋንቋ አጠቃቀሞች በአብዛኛው ወንድ ተኮር ናቸው። ምሳሌዎቹም ወንዶችን ዶክተር፣ ኢንጂነርና ፓይለት አድርገው ያቀርባሉ። ሥዕሎቹም እንዲሁ ወንዶቹን ሲዝናኑ፣ ሲጫወቱና ሲመራመሩ ያሳያሉ። ሴቶቹን ግን በቤት ውስጥ ተግባራት ተሰማርተው ቤት ሲጠርጉ፣ ልብስ ሲያጥቡ፣ ምግብ ሲያዘጋጁና ዝቅተኛ በተባሉ

> **ሴቶች የመማር ዕድሉን ካገኙ የራሳቸውን ፍላጎት በራሳቸው የመወሰን፣ የሚፈልጉትን ሥራ የመሥራት፣ በራሳቸው ተማምነው የመኖርና ለሀገር ዕድገት ትልቅ ሚና የመጫወት ብቃት ይኖራቸዋል።**

ሥራዎች ላይ ሲሳተፉ ያሳያሉ። በዚህ ዓይነት የሴቶችን ሚና አሳንሶ ማቅረብና ማሳየት፣ ሴቶች በትምህርት ልቀው ራሳቸውን አሻሽለው በከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ ቦታዎች ላይ የመሳተፍ ህልማቸውን ይጎዳል።

ስለሆነም የሴቶችን ድርብ ኃላፊት ለማቃለልና የሥራ ተነሳሽነታቸውን የበለጠ ለማጎልበት መማር የሚገባቸውን ሁሉ ለማስተማር ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። የባህርይ፣ የአስተሳሰብና የአሠራር ለውጥ ማምጣት የሚቻለው በትምህርት ነው። ሴቶች የመማር ዕድሉን ካገኙ የራሳቸውን ፍላጎት በራሳቸው የመወሰን፣ የሚፈልጉትን ሥራ የመሥራት፣ በራሳቸው ተማምነው የመኖር ብቃት ይኖራቸዋል። በመማራቸው የዕድገት እንቅፋት የሆኑት ኋላቀር አመለካከቶች ቀስበቀስ ይወገዳሉ። ይህ ይሆን ዘንድ ለሁለቱም ጾታዎች ፍትሃዊ ትምህርት እንዲያገኙ «ትምህርት ለሁሉም» የሚለውን መርህ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ለተግባራዊነቱም ሴት ልጆች ትምህርት ጀምረው እንዳያቋርጡ ትምህርትቤቶችን ከመኖሪያ አካባቢ በቅርብ መገንባት ይጠቅማል። የመማሪያ መጻሕፍት፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ቤተሙከራዎች፣ መጸዳጃቤቶች ወዘተ ለሴት ተማሪዎች ምቹ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪ በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ ሴቶችን በአርአያነት ማቅረብም ጠቀሜታ አለው።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንበቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ሴቶች የሚሠሯቸው ወንዶች ግን የማይችሏቸው፣ ወንዶች ብቻ የሚሠሯቸው ሴቶች ደግሞ የማይችሏቸው ሥራዎች አሉ» በሚለው አመለካከት ላይ የምትስማሙ ወይም የማትስማሙ መሆናችሁን ተናገሩ።

ለ. ወላጆች፣ ሴት ልጆቻቸውን እንደወንድ ልጆቻቸው «ታውቃላችሁ፣ ትችላላችሁ» በማለት የማያሳድጓቸው ስለሚያዳሉ ይመስላችኋል?

ሐ. የአራተኛውን አንቀጽ ሀሳብ አሳጥራችሁ ተናገሩ።

መ. በሶስተኛውና በአራተኛው አንቀጽ መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ተናገሩ።

## 2ኛ ቀን


## ቃላት

### የቃላት አጠቃቀም

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመጠቀም በምሳሌው መሠረት የተለያዩ ሐረጋትን አዋቅሩ።

ምሳሌ፡-




ሀ. የተዛባ ትርጉም

ለ. የተዛባ ኑሮ

ሐ. የተዛባ አመራር

መ. የተዛባ ህይወት

ሠ. የተዛባ አሠራር

ረ. የተዛባ ቅደምተከተል

ሰ. የተዛባ መመሪያ

ሸ. የተዛባ ንግግር

ሀ. ኋላቀር ለ. ኃላፊነት ሐ. የፆታ


## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች አወቃቀር ስልት በጋራ ድርሰት መጻፍ

**ተግባር**

ሀ. «ወንዶች የሴቶችን ሥራ መሥራት አይችሉም?» በሚል ርዕስ በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች አወቃቀር ስልት ድርሰት ለመጻፍ የሚያስችሉ ሀሳቦችን በሚከተለው ሥዕል አደራጁ።




ለ. «ወንዶች የሴቶችን ሥራ መሥራት አይችሉም?» በሚል ርዕስ በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች አወቃቀር ከመምህራችሁ ጋር የጻፋችሁትን ድርሰት በመከለስ አስተካክላችሁና አስፋፍታችሁ ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ዓረፍተነገሮችን እያዳመጡ ሥርዓተነጥቦችን አሟልቶ መጻፍ

**ተግባር**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች በማዳመጥ ፊደል ሳትገድፉ፣ ቅርጽ ሳትቀይሩ፣ ቃል ሳትዘሉ፣ ተገቢ ሥርዓተነጥቦችን በመጠቀም ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### ሥርዓተጾታና ትምህርት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

ሀ. «… በትክክል አንብቡ» የሚል መመሪያ ብዙ ጊዜ አንብባችሁ ይሆናል። ለመሆኑ «በትክክል ማንበብ» ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. በደቂቃ ምን ያህል ቃላት በትክክል እንደምታነቡ ለክታችሁ ታውቃላችሁ? ከሆነ እንዴት ነበር የለካችሁት?

## ማንበብ

### ተግባር

«ሥርዓተጾታና ትምህርት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በደቂቃ ምን ያህል ቃላት በትክክል እንዳነበባችሁ በመመዝገብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

## ማዳመጥ

## ስኬት በጥረት

### ቅድመማዳመጥ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ዛሬ የምታዳምጡት ምንባብ ርዕስ «ስኬት በጥረት» የሚል ነው። ከምንባቡ ርዕስ ተነስታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. በቤታችሁ ወላጆቻችሁን በምን በምን ሥራዎች ታግዛላችሁ?

ሐ. በአካባቢያችሁ አዘውትረው ወደትምህርትቤት የሚሄዱት ወንዶች ናቸው ወይስ ሴቶች? ለምን ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ሂደት

### ተግባር

መምህራችሁ «ስኬት በጥረት» በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ ያነቡላችኋል፤ ዋናዋና ሀሳቦችን በደብተራችሁ በመጻፍ በንቃት አዳምጡ።

### አዳምጦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ወንዱ ልጅ እንዲማር ሴቷ ልጅ እንዳትማር ያደረገው ማን ነው?

ለ. የወይኒቱ እናት ልጇን ለመዳር ለምን ፈለገች?

ሐ. ወይኒቱን ተንሰቅስቃ እንድታለቅስ ያደረጋት ምንድን ነው?

መ. የወይኒቱ ወላጆች ልጃቸውን ሳይሆን ሰዎች የነገሯቸውን የሰሙት ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት «ወተት አመላላሽነት ለመሀንዲስነት አበቃ» የሚለውን አባባል አብራሩ።


## ሰዋስው

### ሀላፊ ጊዜና የአሁን/የትንቢት ጊዜ

### ተግባር 1

በ«ሀ»ና በ«ለ» ረድፍ የቀረቡት ቃላት የሚለያዩባቸውን ቅርጾችና የቅርጾቹን ፍቺ ተናገሩ።

ሀ ለ







### ተግባር 2

በምንባቡ ውስጥ እንደ«ያገለግላል፣ ይቀንሳል...» ዓይነት ቅርጽ ያላቸውን በኢ-ኃላፊ ጊዜ የተነገሩ ቃላት ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።

## ማንበብ

### የሥራ ክፍፍል

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በቤተሰባችሁ ውስጥ የሥራ ክፍፍል አለ? የእናንተ የሥራ ድርሻ ምንድን ነው?

ለ. «የሥራ ክፍፍል» ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁና ሥዕሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

ቀጥሎ «የሥራ ክፍፍል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ አራተኛና አምስተኛ አንቀጾችን ጥንድ ጥንድ በመሆን አንዳችሁ አንድ አንቀጽ በማንበብ የአንቀጹን ሀሳብ ጨምቃችሁ ስታቀርቡ፣ አንዳችሁ ተጨማሪ ጭምቅ ሀሳብ በመስጠት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተራበተራ አንብቡ።

### የሥራ ክፍፍል

ሥርዓተጾታዊ የሥራ <u>ክፍፍል</u> ከህጻንነት ጀምሮ በሰዎች አእምሮ ውስጥ የሚከናወን መለማመድ ነው። መለማመዱ ማኅበረሰቡ በልምድ በመደበው መሠረት ይከናወናል። ሴት ልጅ እናቷ ስታደርገው ያየችውንና በተለምዶ «የሴት» የተባለውን ሥራ በጨዋታ በመለማመድ ታዳብረዋለች። ወንዱም እንዲሁ ከአባቱ የተመለከተውን ይለማመዳል። ሁለቱም ከተመደበላቸው ውጪ ሲሠሩ ቢታዩ እንዳይደግሙት ማስጠንቀቂያ ይሰጣቸዋል። ከዚህ አልፎ ሴቷ ለወንድ የተባለውን ከሠራች «<u>ወንዳወንድ</u>» ተብላ ትዘለፋለች። ወንዱም የሴቷን ከሠራ «<u>ሴታሴት</u>» ይባላል። በሕጻንነት በዚህ መልክ የተጀመረው መለማመድ ከአደጉ በኋላም በመቀጠል አብሮ ይኖራል።



የቤተሰብ መሠረት ሁለቱ ጾታዎች የሚፈጥሩት አንድነት ነው። በመሆኑም ባል ሚስቱን በሥራ ቢረዳት፣ በቤት ውስጥ ቢያግዛት፣ የባል የበላይነት ቀርቶ የሚስት ተጨቋኝነት ተወግዶ፣ በእኩልነት ቢኖሩ የተሻለ ህይወትን ይመራሉ። ባሎች በልጆች አስተዳደግ፣ በማዕድቤት አስተዳደር፣ የቤት ቀለብ በመግዛት ቢሳተፉ መተሳሰብ ይፈጠራል። በባልና በሚስት መካከል ያለን መተጋገዝና መተሳሰብ እያዩ ያደጉ ሕጻናትም በሥራ እኩልነት ያምናሉ። «ይሄ የወንድ፣ ይሄ የሴት» ሥራ ብለው አይመድቡም። ለተተኪው ትውልድም በዚህ መሠረት ይተላለፋል።

ማኅበረሰቡ ባልነትን የሚገልፀው ሦስት ነገሮችን መሠረት አድርጎ ነው። እነዚህም አባዎራነት፣ ወንዴነትና ወንድነት ናቸው። ወንዴነት ተፈጥሯዊ ጾታን የሚገልጽ፣ ወንድነትና አባዎራነት ደግሞ ማኅበረሰቡ የሚፈጥረው ነው። በመሆኑም በጾታዋ ሴት የሆነችው አስደናቂ ሥራ ስትሠራ «ወንድ» ተብላ ትደነቃለች። እንዲሁም ሴቴነት በተፈጥሮ የሚገኝ ጾታ ሲሆን ሴትነት ደግሞ ማኅበረሰቡ የሚፈጥረው ነው። አንድ ወንድ ለሴት ተብሎ የተመደበውን ሥራ ቢሠራ መሳቂያ መሳለቂያ ይሆናል። በዚህ ሁኔታ ማኅበረሰቡ ለሥራ ክፍፍሉ የሚሰጠው የራሱ ልማዳዊ አመዳደብ አለው። ወንድነትን አደባባይ ከመዋል፣ ኃይል ከመጠቀም፣ ከጀግንነትና ከአሸናፊነት ጋር ያያይዘዋል። ሴትነትን ደግሞ ከአይናፋርነት ከአልቃሻነት፣ ቤት ከመዋል፣ ከማጀት ሥራና ከተሸናፊነት ጋር ያቆራኘዋል።

> **ወንዴነትና ሴቴነት ተፈጥሯዊ ሲሆን ወንድነትና ሴትነት ደግሞ ማኅበረሰቡ የሚፈጥረው ነው።**

ወንድነትን በመጀመሪያ የሚፈጥሩት ራሳቸው ሴቶች ናቸው። «ወንድ ነህ» እያሉ ከሚሰጡት ማሞካሻ ጀምሮ ወደማጀታቸው የተጠጋውን ልጅ «ሴታሴት! እዚህ ጓዳ ውስጥ ምን ያርመጠምጥሀል» እያሉ እስከማባረር ይደርሳሉ። የሥራ ክፍፍሉንም በልዩነት ገና በልጅነቱ ያለማምዱታል። ሴት ልጆቻቸውን የቤት ሙያ ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት ለወንድ ልጆቻቸው አያደርጉትም። ወንዶች ልጆች ለመሥራት ቢያስቡ እንኳን «አንተ ወጡን ሠርተህ ሚስትህ ምን ልትሠራ ነው?» እያሉ ይከለክሏቸዋል። አንዳንድ ወላጆች ለማለማመድ ቢሞክሩም ማኅበረሰቡ ይቃወማቸዋል። «ልጁን የቤት ሠራተኛ አደረገችው፤ ልጁ ከእንግዲህ ሚስት ነው ባል የሚያገባው?» በማለት ይሳለቁባቸዋል። የመሥራት ፍላጎታቸውንም ይጎዱባቸዋል።

የምዕራባውያን ባሎች ግን ከኢትዮጵያውያን በተሻለ የጓዳውን ሥራ ይሠሩታል። ጓደኞቻቸውም ይህንን ቢያውቁ ምንም አይመስላቸውም። እነሱም ያንን ያደርጉታልና። ቤት በመዋላቸውና የማድቤት ሥራ በመሥራታቸው «ሴታሴት» ብሎ የሚሰድባቸው የለም። በጾታቸው ከእኛ ሀገር ወንዶች ጋር ልዩነት የላቸውም። ልዩነቱ አንድ ዓይነት ጾታ ኖሯቸው ማኅበረሰቡ በፈጠረው አመለካከት ነው። በሀገራችን ብዙ ሴቶች ባሎቻቸው የኩሽና ሥራ ለመሥራት ቢፈልጉ እንኳ ፈቃደኛ አይሆኑም። የዚህም ምክንያት ባሎቻቸው በማኅበረሰቡ የሚሰጣቸውን «የሴታሴትነት» ስያሜ በመፍራት ነው። በምዕራቡ ዓለም ሁለቱም ጾታዎች አንድ ዓይነት ሥራ ተለማምደውና ሠርተው ያድጋሉ። የኛዎቹ ግን በማኅበረሰቡ የሥራው ዓይነት ተመድቦላቸው ይለማመዳሉ። አስተዳደጉና ልምምዱ ለልዩነቱ ምንጭ ሆኗል።

የማኅበረሰቡን ትችት ችሎ በየአካባቢው ቀድሞ የነቃ ቤተሰብ ያላቸው ብዙ ባሎች በአመለካከት ተቀይረው ሥራን «የወንድ፣ የሴት» ብለው ሳይመድቡ እኩል የሚሠሩ አሉ። የኩሽና ሙያን ለአንድ ጾታ ብቻ ሳይተው ኩሽና ገብተው ጉድጉድ በማለት ለኪሳቸው፣ ለጤንነታቸውና ለፍቅራቸው የሚሠሩ አልታጡም። የሕጻናትን ንፅህና የሚጠብቁ፣ የሚመግቡና የሚያዝሉ ባሎች እየተበራከቱ መጥተዋል። የባሎችን ሥራ የሚያበረታቱ፣ የአሠራር መመሪያዎችን የሚያቀርቡ የቴሌቪዥን መርሐግብሮች፣ መጽሔቶች፣ መጽሐፎችና ድረገጾች በጣም ተበራክተዋል።

የሴቶችን ማኅበረሰባዊ <u>ሚና መጋራት</u> የባልነት አንዱ ተግባር መሆኑን የሚያምኑ ወንዶች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። እነዚህን ዓይነት ባሎች መፍጠር የሚቻለው ከዛሬዎቹ ሕጻናት ነው። ከዛሬዎቹ ሕጻናት እንዲህ ዓይነት ባሎችን መቅረጽ የዛሬው ማኅበረሰብ ኃላፊነት ነው። በሕጻንነታቸው ያልተማሩትን ሥራ፣ በልጅነታቸው ያልተረከቡትን ኃላፊነት በኋላ ከየት ያመጡታል? ስለዚህ በሥርዓተጾታ ያለውን የሥራ ክፍፍል ለማስተካከል ወላጆች በልጆች ህይወት ላይ መሠረት መጣል ይኖርባቸዋል።

(ዳንኤል ክብረት። 2005። <u>የኔ ጀግናና ሌሎች</u>፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «የሥራ ክፍፍል» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን አንቀጽ ሀሳብ በማነጻጸር ልዩነታቸውን አስረዱ።

ለ. «የባሎቻቸውን ወንድነት የሚፈጥሩት ሴቶች ናቸው» በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? መስማማት አለመስማማታችሁን በምክንያት አስረዱ።

ሐ የምዕራባውያንና የኢትዮጵያውያንን ባሎች ከማጀት ሥራ አንፃር በማወዳደርና በማነጻጸር አስረዱ።

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም

### ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት/ሐረግ በምሳሌው መሠረት በዓረፍተነገር ውስጥ ተጠቀሙ።

ምሳሌ፡- ቃሉ፡- ሴታሴት (አንቀጽ «1»)

ዓረፍተነገር፡- ምዕራባውያን ወንዶች ጓዳ ውስጥ ገብተው ሥራ ቢሠሩ ሴታሴት ተብለው አይናቁም።

ሀ. ወንዳወንድ (አንቀጽ «1»)

ለ. አደባባይ (አንቀጽ «3»)

ሐ. ማጀት (አንቀጽ «3»)

መ. ሚና (አንቀጽ «7»)

ሠ. ልማዳዊ (አንቀጽ «3»)

ረ. የጓዳውን (አንቀጽ «5»)

ሰ. መጋራት (አንቀጽ «7»)

ሸ. ክፍፍል (አንቀጽ «1»)


## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

«ምዕራባውያንና ኢትዮጵያውያን እናቶች» በሚል ርዕስ ከሥርዓተጸታ አንጻር በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት ለመጻፍ የሚያስፈልጉ ነጥቦችን በሚከተለው የቢጋር ምስል አደራጁ።



## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አዳመጦ መጻፍ

**ተግባር**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት አዳምጣችሁ ፊደል ሳትገድፉ በትክክል ጻፉ።

6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

**የሥራ ክፍፍል**

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

«የሥራ ክፍፍል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን በአቀላጥፎ ማንበብ በደቂቃ ምን ያህል ቃላት ነበር  በትክክል ያነበባችሁት?

ለ. በደቂቃ በፍጥነት ካነበባችሁትና በትክክል ካነበባችሁት የትኛው ይበልጥ ነበር? የልዩነቱ ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

### ማንበብ

**ተግባር**

ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ አንዳችሁ ስታነቡ፣ አንዳችሁ ደቂቃ እየያዛችሁና በትክክል የማንበብ ፍጥነታችሁን እየመዘገባችሁ «የሥራ ክፍፍል» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አንብቡ።

## መናገር

### ሀሳብን በመደገፍ/በመቃወም መከራከር

**ማስታወሻ**

ክርክር ስታዘጋጁና ስታቀርቡ ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ስጡ።

- የምትደግፉትን ሀሳብ ምረጡ፣
- ለምትከራከሩበት ርዕስ በቂ መረጃ አሰባስቡ፣
- የመከራከሪያ ነጥቦችን ተራችሁን ጠብቃችሁ አቅርቡ፣
- ተከራካሪዎቻችሁን አክብሩ፣
- በተሰጠው የመከራከሪያ ጊዜ በአግባቡ ተጠቀሙ፣

**ተግባር**

በቡድን ተከፋፍላችሁ ሥርዓተጾታዊ የሥራ ክፍፍል መኖርን በመደገፍና በመቃወም ተከራከሩ።

## ሰዋስው

### የቅርብ ሀላፊ ጊዜና የሩቅ ሃላፊ ጊዜ

**ተግባር**

ሀ. የሚከተሉትን ጥንድ ቃላት በምሳሌው መሠረት በማርባት ጻፉ።

ምሳሌ፡-

| | ሀ | | ለ |
|---|---|---|---|
| 1. | ይኖራል | → | ኖሯል |
| | ይኖር ነበር | → | ኖሮ ነበር |
| 2. | ይፈልጋል | → | ፈልጓል |
| | ይፈልግ ነበር | → | ፈልጎ ነበር |

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ሀ. ያገለግላል | ______________ |
| ያገለግል ነበር | ______________ |
| ለ. ይቀንሳል | ______________ |
| ይቀንስ ነበር | ______________ |
| ሐ. ይመክራል | ______________ |
| ይመክር ነበር | ______________ |

ለ. ከላይ በጻፋችኋቸው ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ጊዜ አመልካች ቅርጾች ለይታችሁ ጻፉ።

# የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ማክበር

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
| --- | --- |
| ወላጅ-አች-ኡ-ኣ-ን | ወላጆቿን |
| አስተሳሰብ-ኡ-ኣ-ን | አስተሳሰቧን |
| ቀረበ-ች-ኣቸው | ቀረበቻቸው |
| ገጠመኝ-አች-ኣቸው-ን | ገጠመኞቻቸውን |
| አርአያ-ነት-ኣቸው-ን | አርአያነታቸውን |
| አጋር-አች-ኣቸው | አጋሮቻቸው |
| አሠሪ-ዎች-ኣቸው | አሠሪዎቻቸው |
| መሰናክል-አች | መሰናክሎች |

**ተግባር 2**

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ደጋግማችሁ በፍጥነት አንብቡ።

| | | | |
| --- | --- | --- | --- |
| የወለደችበትን | መሰናክሎች | የሚቃወሙትም | የበኩሯ |
| አቅራቢያዋ | ሥርዓተጾታዊ | በትምህርትቤቷ | |
| መኮብለሏ | ሲገልጹላት | ከዩኒቨርሲቲ | |

## ማንበብ

### የሥርዓተጾታ እኩልነትን ማክበር

#### ቅድመንባብ

ቁልፍ ቃላትንና ሥዕልን መሠረት አድርጎ የምንባብን ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

የሚከተሉትን ቃላት ፊደሎቻቸውን በማጥበቅና በማላላት አንብቡ፤

ሀ. መጻር　　　　መ. ነጻ　　　　ሰ. ባላት

ለ. በርካታ　　　　ሠ. አደራ　　　　ሸ. ያሏቸው

ሐ. ቁጥር　　　　ረ. እንዳሉ


## ተግባር 2

ስዕሉን ተመልከታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

# የማንበብ ሂደት

## ተግባር

ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ «የሥርዓተጾታ እኩልነትን ማክበር» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አንዳችሁ አንቀጽ ስታነቡ አንዳችሁ የአንቀጹን ሀሳብ እያስረዳችሁ ተራበተራ አንብቡ።



## የሥርዓተጾታ እኩልነትን ማክበር

እስከዳር የተወለደችበትን ቀንና ዓመተምሕረት ባታውቀውም በደርግ ዘመን እንደተወለደች ወላጆቿ ነግረዋታል። የተወለደችው በአነስተኛ የገጠር መንደር ነው። ወላጆቿ አርሶአደር ናቸው። ስድስት ልጆች ያሏቸው ሲሆን የበኩሯ እስከዳር ናት።

ቤተሰቡ ውስጥ ተሰሚነትና ወሳኝነት ያላቸው አባቷ እንዳትማር ጫና ቢፈጥሩባትም በአጎቷ ጥረት ትምህርትቤት ለመግባት ቻለች። ሆኖም በአቅራቢያዋ ትምህርትቤት

ባለመኖሩ በየቀኑ ረጅም ሰዓት በእግሯ ለመጓዝ ትገደድ ነበር። የሶስተኛ ክፍል ተማሪ እንዳለች ቤተሰቦቿ ሊድሯት መወሰናቸውን ስላወቀች በድቅድቅ ጨለማ ከቤት ጠፍታ ከተማ ወደሚኖረው አጎቷ ቤት ኮበለለች።

አባቷ በመኮብለሏ ባይደሰቱም እስከዳር አጎቷ ቤት በመሆን ያቋረጠችውን ትምህርት ቀጠለች። የተለያዩ መሰናክሎች ቢያጋጥሟትም ሁሉንም እንደምንም ተቋቁማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆነች። በመጀመሪያና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቆይታዋም ከሥነዜጋና ከሥነምግባር ትምህርት ያገኘችው ዕውቀት አስተሳሰቧን ለወጠው። ከዚያም ከልጅነት ዕድሜዋ ጀምሮ በአካባቢዋ በርካታ ሴቶች ይደርስባቸው የነበረውን መብት ረገጣ በማስታወስ ለለውጥ ተነሳሳች። በጓደኝነት የቀረበቻቸው ሴቶች ያለባቸውን ጫና ሲገልጹላት ከራሷ ህይወት ጋር በማያያዝ ልቧ አብሮ አዘነ። ይህም በትምህርትቤቷ በተቋቋመው የሥርዓተጾታ ክበብ ውስጥ ለመመዝገብ ገፋፋት። በክበቡ ውስጥ ሁለቱም ጾታዎች አባል ቢሆኑም ሴቶቹ በቁጥር ይበልጣሉ። በክበቡ መሳተፏ ለእስከዳር የሴት ተማሪዎችን ችግር ለመለየት መንገድ ከፈተላት። የክበቡ አበላትም የላቀ ተሳትፎዋን በማየት ከፍተኛ ኃላፊነት ጣሉባት። እስከዳር ያጋጠሟትን ችግሮችና የህይወት ተሞክሮዋን በግልጽ በመናገር በር ስለከፈተችላቸው የክበቡ አባላት ገጠመኞቻቸውን ሳይደብቁ መናገር ቻሉ።

**ሴቶችን ማስተማር ማኅበረሰብን ማስተማር ነው።**

የክበቡ አባላት ወንድ ተማሪዎችም የሥርዓተጾታ እኩልነትን በማክበር አርአያነታቸውን በተግባር አስመሰከሩ። በየሳምንቱ አርብ አርብ ከትምህርት ሰዓት በኋላ በመገናኘት ስለሥርዓተጾታዊ ፖሊሲ፣ ሴቶች በሀገሪቱ ምጣኔሀብታዊና ፖለቲካዊ ውሳኔ ሰጭነት ላይ ስለሚኖራቸው ኃላፊነትና የመሳሰሉት ጉዳዮች በስፋት ይወያያሉ። አልፎአልፎ በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን ለሚያቋርጡ ተማሪዎች የትምህርትቤቱን ማኅበረሰብ በማስተባበር ትምህርታቸውን የሚቀጥሉባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻሉ።

እስከዳር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በማኅበረሰብ ውይይት በመገኘት ስለሴቶች መብት ለማሳወቅ ጥረት ታደርጋለች። በወንድ የበላይነት ምክንያት የሚፈጸምባቸውን በደሎች እንዲታገሉ ታስተምራለች። ይህን ሀሳቧን የሚደግፉ እንዳሉ ሁሉ የሚቃወሙም አልታጡም። ተቃውሞው ግን ይበልጥ ጠንካራ አቋም እንዲኖራት አደረጋት። በዚህ መካከል ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ጥሩ ውጤት ማስመዝገቧ፣ በራስ መተማመኗንና ብቃቷን እያጎለበተላት መጣ።

እስከዳር የሴቶችን መብት ለማስከበር ባላት ጽኑ ፍላጎት በተመደበችበት ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ለመማር ወሰነች፤ ተሳካላትም። በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ በተማሪ መማክርት የኮሚቴ አባል ሆና ተመረጠች። በተፈጠረላት አጋጣሚም በሴት ተማሪዎች ላይ የሚደርሱ በደሎችን በመቃወም ለመብታቸው ታገለች።

ከዩኒቨርሲቲ ተመርቃ እንደወጣችም ሴቶች በፍትህ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የበኩሏን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበረከተች። በየጊዜው የተለያየ በደል ደርሶባቸው ወደህግ የሚመጡ፣ የህግ ዕውቀት የሌላቸውና ጠበቃ ቀጥረው መከራከር የማይችሉ ሴቶች ያጋጥሟታል። ይህን ችግር ለማቃለል ከሌሎች የሥራ አጋሮቿ ጋር በመሆን ነጻ የህግ አገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት አቋቋመች። በዚህም በርካታ በደሎች የደረሰባቸው ሴቶችን ተጠቃሚ አደረገች። በትዳር አጋሮቻቸውና በአሠሪዎቻቸው የሚደርስባቸውን በደል ለመግለጽ ድፍረት አጥተው የቆዩ ሴቶች በጽ/ቤቱ በመምጣት ተጠቃሚ ሆኑ። ይህን ነጻ የህግ አገልግሎት በሌሎች አካባቢዎች ተጨማሪ ቢሮዎችን በመክፈት የሴቶችን ችግሮች ለመፍታት አገልግሎቷን አስፋፋች።

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ተሰሚነትና ወሳኝነት ያላቸው እናቷ ቢሆኑ ኖሮ የእስከዳር የመማር ጥያቄ ምላሽ ምን ይሆን ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?

ለ. በእስከዳር ቤተሰብ ውስጥ ተሰሚነትና ወሳኝነት ያላቸው አባቷ፣ እንድትማር ጥረት ያደረጉላት ደግሞ አጎቷ መሆናቸው ምን ያስተምራል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ሐ. የምንባቡ ይዘት/ሀሳብ ከርዕሱ ጋር ያለውን አንድነት ወይም ልዩነት አስረዱ? ከዚህ የተሻለ ርዕስ መስጠት ትችላላችሁ? ምን የሚል?

መ. የምንባቡ ርዕስ መግለፅ የተፈለገውን ሀሳብ የገለጸ ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተነገር መመሥረት

### ተግባር 1

በምሳሌው መሠረት የሚከተሉት ቃላት ሁለት ፍቺ እንዲሠጡ በማድረግ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ:- ቃል:- ተቋቁማ

ዓረፍተነገር:-

ሀ. አገርነሽ በወላጆቿ ሞት የደረሰባትን ችግርና መከራ ተቋቁማ ቤተሰብ ለመመሥረት በቃች።

ለ. ሀይማኖት ከባንክ ብድር በመውሰድ ተቋቁማ ፣ ዛሬ አሉ ከሚባሉት ሀብታም ነጋዴዎች ተርታ ተመድባለች።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ቀጠለች | ሐ. አስመሰከሩ | ሠ. አበረከተች |
| ለ. ለወጠው | መ. አጋጣሚ | ረ. ድፍረት |

## ተግባር 2

የሚከተሉት ቃላት ፊደሎች ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን የፍቺ ልዩነት በምሳሌው መሠረት በዓረፍተነገር አሳዩ።

ምሳሌ፡- ቃል፡- አደራ

ሲጠብቅ = ዓለማየሁ ድሩን <u>አደራ</u>።

ሲላላ = ዓለማየሁ እህቱን <u>አደራ</u> አላት።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ባላት | ሐ. መዳር | ሠ. ነጻ |
| ለ. ቁጥር | መ. በርካታ | ረ. እንዳሉ |

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ

## ተግባር

ሀ. በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን በቢጋር ሠንጠረዥ ያደራጃችኋቸውን ሀሳቦች በመጠቀም «ምዕራባውያንና ኢትዮጵያውያን እናቶች» በሚል ርዕስ ከሥርዓተጸታ አንጻር በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ድርሰት ጻፉ።

ለ. የጻፋችሁትን ድርሰት በድርሰት መገምገሚያ መስፈርቶች መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተነገሮችን በትክክል መጻፍ

## ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት፣ ሐረጋትና ዓረፍተነገሮች በትክክል አዳምጣችሁ ፊደል ሳትገድፉ የፊደላትን ቅርጽ ጠብቃችሁ ጻፉ።

9ኛ ቀን

# አቀላጥፎ ማንበብ

## የሥርዓተጾታ እኩልነትን ማክበር

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅደመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በ3ኛው ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን «የሥርዓተጾታ እኩልነትን ማክበር» በሚል ርዕስ ካነበባችሁት ምንባብ የምታስታውሷቸውን ዋናዋና ነጥቦች ጥቀሱ።

ለ. በ2ኛው ሳምንት፣ በ6ኛው ቀን የአቀላጥፎ ንባባችሁ፣ ምን ያህል ቃላት ነበር በደቂቃ በትክክል ያነበባችሁት?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

በቡድን ተከፋፍላችሁ «የሥርዓተጾታ እኩልነትን ማክበር» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ተራበተራ አንብቡ። አንዳችሁ ስታነቡ አንዳችሁ ስህተት በመመዝገብ አንባቢው/ዋ በደቂቃ ስንት ቃላት በትክክል እንዳነበበ/ች እያሰላችሁ ውጤቱን መዝግቡ።

# መናገር

## በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ንግግር ማድረግ

**ተግባር**

ከሚከተሉት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ በመዘጋጀት በማወዳደርና በማነጻጸር ስልት ንግግር አድርጉ።

ሀ. የምዕራባውያንና ኢትዮጵያውያን የልጅ አስተዳደግ፣

ለ. ኢትዮጵያዊ እናትነትና አባትነት

ሐ. ሥርዓተጾታዊ እኩልነት በምዕራባውያንና በኢትዮጵያውያን

## ሰዋስው

### ጊዜ አመልካቾችን መለየት

**ተግባር**

በሚከተሉት በ«ሀ»ና በ«ለ» ምድብ የቀረቡ ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ጊዜ አመልካቾች ለይታችሁ አውጡ፤ የሚወክሉትን የጊዜ ዓይነትም ግለጹ።

ሀ.

ዘለቃሽ ፎቶ እየተነሳች ነው።

ዘለቃሽ ፎቶ እየተነሳች ነበር።

አቤል ዘለቃሽን ፎቶ እንድትነሳ እየገፋፋት ነው።

አቤል ዘለቃሽን ፎቶ እንድትነሳ እየገፋፋት ነበር።

ፎዚያ ሀሳቧን እየለወጠች ነው።

ፎዚያ ሀሳቧን እየለወጠች ነበር።

ለ.

ገመቹ ፎቶ ይነሳል።

ገመቹ ፎቶ ይነሳ ነበር።

ሳሙኤል፣ ገመቹ ሀሳቡን እንዲለውጥ ይገፋፋዋል።

ሳሙኤል፣ ገመቹ ሀሳቡን እንዲለውጥ ይገፋፋው ነበር።

ሁሴን ለአካባቢው ልማት ድርሻውን ያበረክታል።

ሁሴን ለአካባቢው ልማት ድርሻውን ያበረክት ነበር።



# ምዕራፍ 9 የአየር ንብረት

## የአየር ንብረት ለውጥ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### በመነጠልና በማጣመር ማንበብ

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ተጣምረው የቀረቡ ቃላት በምሳሌው መሠረት ነጣጥላችሁ ከጻፋችሁ በኋላ አንብቡ።

ምሳሌ፡-

ካርቦንዳይኦክሳይድ → ካርቦን-ዳይ-ኦክሳይድ

ሀ. መቆጠብ
ለ. ውቅያኖሶች
ሐ. ንብረቷ
መ. አሳይቷል
ሠ. አድርጓል
ረ. ሚሊሜትር

→

ሀ. __________
ለ. __________
ሐ. __________
መ. __________
ሠ. __________
ረ. __________

## ተግባር 2

በቡድን ሆናችሁ የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ደጋግማችሁ አንብቡ።

| | |
|---|---|
| ሜትሮሎጅ | ከባቢ አየር |
| መለስ ቀለስ | ተመራማሪዎች |
| ዲግሪ ሴንቲግሬድ | ሃዋኢ |
| ሲያኮማትራት | ግሪንላንድ |
| ሲያነዳት | ሲዋኸቅ |

## ማንበብ

# የአየር ንብረት ለውጥ

### ቅድመንባብ

### ቃላትን በዐውድ መጠቀምና ፍቺ መስጠት

## ተግባር

«የአየር»ና «የባህር» የሚሉትን ሐረጋት ከተለያዩ ቃላት ጋር እያቀናጃችሁ የተስፋፋ ሐረግ በመጻፍ ፍቻቸውን ተናገሩ።

| የአየር | + | = | ትርጉም |
|---|---|---|---|
| የአየር | ሀ. ___ንብረት | ሀ. የአየር ንብረት | ሀ. በአንድ አካባቢ ለብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የሚከሰት የአየር ሁኔታ |
| | ለ. ___ሁኔታ | ለ. ____________ | ለ. ____________ |
| | ሐ. ___ርጥበት | ሐ. ____________ | ሐ. ____________ |
| | መ. ___ፀባይ | መ. ____________ | መ. ____________ |
| | ሠ. ___ምርምር | ሠ. ____________ | ሠ. ____________ |
| | ረ. ___ጉዞ | ረ. ____________ | ረ. ____________ |
| | ሰ. ___ሙቀት | ሰ. ____________ | ሰ. ____________ |
| | ሸ. ___ማረፊያ | ሸ. ____________ | ሸ. ____________ |
| | ቀ. ___መቃወሚያ | ቀ. ____________ | ቀ. ____________ |
| | በ. ___መልዕክት | በ. ____________ | በ. ____________ |

| የባህር | + | = | ፍቺ |
|---|---|---|---|
| | ሀ. ___ ወለል | ሀ. የባህር ወለል | ሀ. የባህር ወለል፣ የመሬት ከፍታ ወይም የውቅያኖስን ጥልቀትን ለመለካት እንደመነሻ ነጥብ የሚያገለግል ከውቅያኖስ ውኃ ከላይኛው አካል ጋር ትይዩነት ያለው የመሬት ንጣፍ። |
| | ለ. ___ ጠለል | ለ. ___ | ለ. ___ |
| | ሐ. ___ ጉዞ | ሐ. ___ | ሐ. ___ |
| | መ. ___ ዳር | መ. ___ | መ. ___ |
| | ሠ. ___ ዛፍ | ሠ. ___ | ሠ. ___ |
| | ረ. ___ እንስሳት | ረ. ___ | ረ. ___ |
| | ሰ. ___ እፅዋት | ሰ. ___ | ሰ. ___ |
| | ሸ. ___ ድንበር | ሸ. ___ | ሸ. ___ |
| | ቀ. ___ ጥልቀት | ቀ. ___ | ቀ. ___ |
| | በ. ___ ስፋት | በ. ___ | በ. ___ |
| | ተ. ___ ሙቀት | ተ. ___ | ተ. ___ |
| | ቸ. ___ አረም | ቸ. ___ | ቸ. ___ |
| | ኀ. ___ ኃይል | ኀ. ___ | ኀ. ___ |
| | ነ. ___ ወሽመጥ | ነ. ___ | ነ. ___ |
| | ኘ. ___ ማሽላ | ኘ. ___ | ኘ. ___ |
| | አ. ___ ዕቃ | አ. ___ | አ. ___ |
| | ከ. ___ አሞራ | ከ. ___ | ከ. ___ |

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ጥንድ ጥንድ በመሆን «የአየር ንብረት ለውጥ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በየንዑስ ርዕሱ ሊተላለፍ በተፈለገው ሀሳብ ላይ እየተነጋገራችሁ አንብቡ።

## የአየር ንብረት ለውጥ

### የአየር ንብረት ምንነት

የአየር ንብረት ለረዥም ዘመን የዘለቀ አማካይ የአየር ሁኔታን ይመለከታል። በከባቢ አየር ውስጥ የሚታዩ የሜትሮሎጂ ክስተቶች ለምሳሌ የዝናብ፣ የደመና፣ የንፋስ፣ የሙቀትና የቅዝቃዜ ሁኔታዎች የአየር ንብረት ይባላሉ። ከሰው ልጆች ቁጥር መጨመርና ከምጣኔ ሀብት ዕድገት ጋር ተያይዞ የአየር ንብረት ከጊዜ ወደጊዜ፣ ይቀያየራል።

ከነበረው አማካይ የአየር ሁኔታ የተለየ ሌላ ለረዥም ጊዜ የሚዘልቅ አዲስ አማካይ የአየር ሁኔታ ሲኖር የአየር ንብረት ተለወጠ ይባላል። የነበረው አማካይ የሙቀት

መጠን ተቀይሮ በሌላ የሙቀት መጠን ሲተካ ሌሎች የአየር ሁኔታ ለውጦች ይከሰታሉ። ለውጦቹም የዝናብ መጠንና ሥርጭት፣ የአየር ርጥበት መጠንና የንፋስ ዝውውር አቅጣጫ ናቸው። ይህ ዓይነቱ መቀያየር ወይም መለዋወጥ እንደአየር ፀባይ መለስ ቀለስ የሚል ሳይሆን ቋሚ ነው። አማካይ የአየር ሁኔታ በረዥም ጊዜ የብዙ ቀናት፣ ወራት፣ ዓመታት አማካዮች ተጨምቆ ይሰላል። በመሆኑም አዲስ አማካይ የአየር ሁኔታ እውን የሚሆነው ከብዙ አሥርት ዓመታት በኋላ ይሆናል።

**ሙቀት ሲጨምር የውኃ ትነት ይጨምራል።**


የአየር ንብረት ለውጥ ሂደት ይበልጥ አስቸጋሪ ገጽታው ጎልቶ የሚታየው ከፊተኛው አማካይ ወደአዲሱ አማካይ በሚያደርገው ሽግግር ነው።

## የአየር ንብረት ለውጥ ታሪክ

ምድር ከተፈጠረች ጀምሮ የአየር ንብረቷ ሲለዋወጥ ኖሯል፤ እየተለዋወጠም ይገኛል። የመሬት የሙቀት መጠን ከ10 እስከ30 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲዋዥቅ መኖሩን የጂኦሎጂ ጥናቶች አመላክተዋል። በአንድ ጂኦሎጂካዊ ዘመን (በሚሊዮኖች ዓመታት) መሬትን ቅዝቃዜ ሲውጣትና ሲያኮማትራት፣ በሌላው ጂኦሎጂካዊ ዘመን ሙቀት ሲያነዳት ኖራለች። በዚህ ዓይነት የአየር ንብረት ለውጥ በሰው ልጆች አኗኗር ላይ ተፅዕኖ ቢያሳድርም በዕጽዋትና በእንስሳት ዝርያዎች ላይ ሲያስከትል የኖረው ለውጥ ግን እጅግ ብዙ ነው። ለውጡን መቋቋም ያቃታቸው ነባር ዝርያዎች ጠፍተዋል፤ መቋቋም የሚችሉ አዳዲስ ዝርያዎች ተከስተዋል። በሌላ መልኩም ነባር ዝርያዎች ካዲሱ የአየር ንብረት ጋር ለመስማማት በሚያስችላቸው ሁኔታ የአካል ቅርጽና የይዘት ለውጥ ሲያደርጉ ኖረዋል።

## የዘመናችንን የአየር ንብረት ለውጥ ክስተቶች መገንዘብ

ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተገናዘቡ የከባቢ አየር ለውጦችን ማስተዋል የተጀመረበት ጊዜ ከ50 ዓመት አይበልጥም። በከባቢ አየር ውስጥ የካርቦንዳይኦክሳይድ መጠን መጨመር ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀው በ1950 ዓ.ም. ነው። ይህንንም ያረጋገጡት የሃዋኢ አለማቀፍ የአየር ምርምር ጣቢያ ተመራማሪዎች ነበሩ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የከባቢ አየር የጋዞች ይዘት ምጥጥን ላይ የሚደረገው ክትትል ቀጠለ። በተደረገው ክትትልም የምድር ከባቢ አየር አማካይ ሙቀት በ0.13 ዲግሪ ሴንቲግሬድ መጨመሩ ተረጋገጠ። የጭማሪው አንዝ ግን በሁሉም ሀገሮቹ ተመሳሳይ አልነበረም። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ላለፉት 55 ዓመታት የሙቀት መጠኑ እየጨመረ መጥቷል። ጭማሪውም በየ10 ዓመታት ልዩነት 0.37 ድግሪ ሴንቲግሬድ መሆኑን የሚከተለው ግራፍ ያሳያል።




በኢትዮጵያ ከዓመት ወደዓመት የሚታየው የሙቀት መጠነ ለውጥ
(የብሔራዊ ሜትሮሎጅ ኤጀንሲ. 2007:3)

የሰሜን ዋልታ አካባቢ ከዓለማቀፋዊው አማካይ የሙቀት መጠን ጭማሪ በሁለት እጅ ከፍ ያለ ነበር። ሆኖም ከሙቀቱ ጭማሪ አብዛኛውን ድርሻ በመያዝ ላይ ያሉት ውቅያኖሶች ናቸው።

እስካሁን በተከሰተው የሙቀት መጨመር ባለፈው ግማሽ ምዕተዓመት የባህር ጠለል በአማካይ የሁለት ሚሊሜትር ጭማሪ አሳይቷል። ይህም የባህር ጠለሉን ከፍታና የውቅያኖሶችን ሙቀት ከፍ አድርጓል። በሙቀት መጨመር ምክንያት የዋልታዎች አካባቢና የተራራ ላይ ግግር በረዶዎች እየቀለጡ ከባህሮች በመቀላቀል የጎርፍ ማጥለቅለቅን አስከትለዋል። በአንዳንድ አካባቢ የዝናብ መጠን ጨምሮ የውኃ ማጥለቅለቅ ሲደርስ፣ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ዝናብ በመቀነሱ ድርቅ ሊከሰት ችሏል።

**የሙቀት መጠን በአየር ንብረት ለውጥ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።**

የአየር ንብረት ለውጥ በሙቀት መጨመር ይከሰታል። ሙቀት ደግሞ ከሰዎች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዘው በሚመጡ ምጣኔሀብታዊ እንቅስቃሴዎች አንፃር ይፈጠራል። በዋልታዎች አካባቢ ያለው ሙቀት ከፍ ሲል ግግር በረዶዎች እንዲቀልጡና የውቅያኖሶች ውኃ እንዲጨምር በማድረጉ የተለያዩ ክስተቶች ይታያሉ። ክስተቶቹም በሰዎችና በሌሎች ፍጥረታት አኗኗር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ። ስለዚህ ለተፅዕኖዎቹ ምክንያት የሆኑትንና ሙቀት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን በመቆጣጠር የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የግድ ይሆናል።

(ዮሐንስ አበራ፣ 2003። *የአየር ንብረት ለውጥ፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።*)

### አንብቦ መረዳት

#### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የአየር ንብረት ተለወጠ የሚባለው ምን ሲከሰት ነው?

ለ. የነበረ አማካይ የሙቀት መጠን በሌላ የሙቀት መጠን ሲተካ ምን ይከሰታል? አብራሩ።

ሐ. የአየር ንብረት ለውጥ ሂደት ይበልጥ አስቸጋሪ የሚሆነው መቼ ነው?

መ. የጎርፍ ማጥለቅለቅ፣ የዝናብ መቀነስ... እንዳይኖር መቆጣጠር የሚገባን ምንን ነው?

ሠ. «ለውጦችን መቋቋም የቻሉ ይኖራሉ፤ መቋቋም ያልቻሉ ይጠፋሉ» የሚለውን አብራርታችሁ ግለጹ።

ረ. «የአየር ንብረት መለወጥ የጀመረው በበለፀጉ አገሮች ኢንዱስትሪ መስፋፋት ምክንያት ነው» ቢባል በዚህ ሀሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

ሰ. በአየር ንብረትና በአየር ፀባይ መካከል ያለውን ልዩነት አስረዱ።

ሸ. የሜትሮሎጂ ባለሙያዎች የዛሬውን ዕለት የአየር ንብረት ሊነግሩን የሚችሉ ይመስላችኋል? ለምን?

## 2ኛ ቀን

### ቃላት

### ለቃላት ፍቺ መስጠት

#### ተግባር

ለሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ ውጭ ያላቸውን ፍቺ ጻፉ

ምሳሌ፡-

ሲያነዳት ⟶ «ሲያበሳጭ»፣ «ሲያናድዳት»

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ንብረት | ሠ. ርጥበት | በ. ምጥጥኑ |
| ለ. ፀባይ | ረ. ዙር | |
| ሐ. መቋቋም | ሰ. ውቅያኖስ | |
| መ. ምርምር | ሸ. ዋልታ | |


## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት መጻፍ

#### ተግባር

የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ «ሰውሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች» በሚል ርዕስ በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት ጻፉ።




### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትን አዳምጦ በትክክል መጻፍ

#### ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ውስብስብ ቃላት አዳምጣችሁ ፊደላትን ሳትገድፉና ሳትደጋግሙ በትክክል ጻፉ።

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የአየር ንብረት ለውጥ

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

እስካሁን ባደረጋችሁት ልምምድ ከፍተኛው የንባብ ፍጥነታችሁ በደቂቃ ስንት ቃላት ነው? በትክክል የማንበብ ፍጥነታችሁስ?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

ቀጥሎ «የዓለም ሙቀት መጨመር ተፅዕኖ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በፍጥነት አንብባችሁ አንብቦ የመረዳት ችሎታችሁን፣ ፍጥነታችሁንና ትክክለኛ ንባባችሁን በምሳሌው መሠረት ለኩ።

### የዓለም ሙቀት መጨመር ተጽዕኖ

የዓለማችን ሙቀት በየብስም ሆነ በባህር እየጨመረ ይገኛል።የሙቀቱ መጨመርም ትነት እንዲጨምርና የአፈር ርጥበት እንዲሟጠጥ በማድረግ ድርቅን እያባባሰ ነው። የባህር በረዶ ከአርክቲክ ዙሪያ ጠረፍ እየሸሸ ነው። በአል'ፕስ፣ በአላስካ፣ በግሪንላንድና በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የተራራ ሠንሠለቶች የሚገኘው የበረዶ ግግር በፍጥነት እየቀለጠ ነው፤ የባህር ወለልም ከፍ እያለ ነው። የሙቀት መጨመርን ተከትሎ የእንስሳትና የዕጽዋት ዝርያዎች ወደምድር ዋልታዎች አቅጣጫ በመሸሽ ከፍታ ባላቸው ቦታዎች መታየት ጀምረዋል። በባህር ዳርቻዎች በሚገኙ ከተሞች የሚኖሩ በርካታ ሰዎች በባህር ወለል መጨመር ምክንያት ለሚመጣ ማዕበል ተጋላጭ ሆነዋል።በባህር ዳርቻዎችና በዝቅተኛ ቦታዎች ላይ የሚገኙ ደሴቶች ለትልቅ ስጋት ተዳርገዋል። ከአሁኑ ለመቀነስ ጥረት ካልተደረገና አስፈላጊ ርምጃዎች ካልተወሰዱ በተደጋጋሚና ረዘም ላለ ጊዜ የሚከሰት ጠንከር ያለ/ሙቀት የብዙ ሰዎችን ህይወት ለህልፈት የሚዳርግ ይሆናል።በሚቀጥሉት አሥርት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የከባቢ አየር ሙቀት፣ የትነት ሁኔታ መዛባት፣ ከፍተኛ የሆነ የአፈር ርጥበት መቀነስ…በብዙ አካባቢዎች የግብርና ሥራዎችን ለማካሄድ በጣም አስቸጋሪ ያደርጋሉ፤ በውኃ ሀብት እጥረትም ከፍተኛ ውጥረት ይፈጠራል።

ፍጥነት=98

ትክክለኛ ንባብ=92

| የቃላት ብዛት | አንባቢዎች/ የንባብ ድግግሞሽ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ | 6ኛ |
| 6 | \ | --- | --- | --- | --- | --- |
| 11 | \ | --- | --- | --- | --- | --- |
| 17 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 25 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 31 | \ | --- | --- | --- | --- | --- |
| 37 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 44 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 48 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 54 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 60 | \ | --- | --- | --- | --- | -- |
| 67 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 73 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 79 | \ | --- | --- | --- | --- | -- |
| 84 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 89 | \ | --- | --- | --- | --- | -- |
| 95 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 102 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 107 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 115 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 121 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 127 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 134 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 136 | --- | --- | --- | --- | --- | --- |

### አንብቦ መረዳት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት «ትክክል» ከሆነ (✓) ወይም «ስህተት» ከሆነ (×) በማለት በቃላችሁ መልሱ።

___ 1. የባህር ወለል ከፍ የሚለው በበረዶ መቅለጥ እንጂ በሙቀት ምክንያት አይደለም።

___ 2. በሙቀት መጨመር ምክንያት እንስሳት ውኃ ወደሚገኝበት ወደባህር እየሸሹ ነው።

___ 3. በባህር ዳርቻ የሚኖሩ ህዝቦች የሙቀት መጨመር አያሰጋቸውም።

___ 4. ሙቀት ስለጨመረና ትነት ስለበዛ የባህር ጥልቀት እየጨመረ ነው።

___ 5. በሚቀጥሉት አሥርት ዓመታት በሙቀት ምክንያት በውኃ ሀብት እጥረት ውጥረት ይፈጠራል፤ ሰዎችም ለሞት ይዳረጋሉ።

ማስታወሻ

«የዓለም ሙቀት መጨመር» ተፅዕኖ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በምሳሌነት ያነበበችውን/ያነበበውን ተማሪ ውጤት ለመረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች አስተውሉ።


1. አንባቢዋ/ው አንድ ደቂቃ ሲያልቅ የቆመችበት/የቆመበት ቦታ በእዝባር (/) ምልክት ተመልክቷል፡
2. እዝባሩ ድረስ የተነበቡት ቃላት ብዛት 98 (102-4=98) ነው። «102» አንባቢዋ/ው የቆመበት መሥመር ድረስ ያሉትን ቃላት ብዛት ሲያሳይ፣ «4» ደግሞ ከዝባሩ በኋላ መሥመሩ ውስጥ ሳይነበቡ የቀሩትን ቃላት ብዛት ያሳያል። ስለዚህ የአንባቢዋ/ው ፍጥነት በደቂቃ 98 ቃላት ነው።
3. «አንባቢዎች» በሚለውና «1ኛ» በሚለው ሥር የሚታዩት ምልክቶች (\) የአንባቢዋን/ውን ስህተቶች ያሳያሉ። ብዛታቸው 6 ነው። ስለዚህ የአንባቢዋ/ው ትክክለኛ ንባብ 92(98-6) ቃላት በደቂቃ ነው።
4. «አንብቦ መረዳት» በሚለው ሥር አራት የትክክለኛነት (✓) ምልክቶች ይታያሉ። የአንባቢዋ/ው የአንብቦ መረዳት ችሎታ $^4/_5$ መሆኑን ያሳያል።

ፍጥነት ⟶ 98

ትክክለኛ ንባብ ⟶ 92

አንብቦ መረዳት ⟶ $^4/_5$

በዚህ መንገድ የምታገኟቸውን መረጃዎች እንደሚከተለው በቢጋር ሠንጠረዥ ማስፈር ትችላላችሁ።




## ማዳመጥ

## የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት?

### ቅድመማዳመጥ

### ከርዕስ የምንባብን ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

ሀ. «የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት?» ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁ የምታዳምጡት ምንባብ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

መምህራችሁ «የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት? በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን ምንባብ የማታውቋቸውን ቃላት እየመዘገባችሁና ፍቻቸውን ከዐውዳቸው ለመረዳት እየሞከራችሁ አዳምጡ።

## አዳምጦ መረዳት

### ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃል መልሱ።

ሀ. ኦዞን ምንድን ነው? ምንስ አገልግሎት አለው?

ለ. የኦዞን ንጣፍ መሳሳት ምን ማለት ነው? ለዓለማችን ያለው አንድምታ ምንድን ነው?

ሐ. ዋናዋናዎቹ በኦዞን ላይ ጥፋት አድራሾች ምን ምን ናቸው?

መ. የካርቦንን ቀለበታዊ ዝውውር ሂደት አብራሩ።

ሠ. ተፈጥሯዊና ሰውሠራሽ የካርቦን አመነጫጩትን ግለጹ።

ረ. «የግሪን ሀውስ ጋዞች የሚሞቁት ከፀሐይ በቀጥታ በሚመጣ ሙቀት ነው» በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

### ተግባር 2

ስለግሪን ሀውስ ጋዞች ምንነት በቃለመጠይቅ ከባለሙያ (ከመምህራን) መረጃ ሰብስባችሁ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።

## ሰዋስው

## ጥገኛ ሐረጎችን መለየት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ጥገኛ ሐረጎችን ለይታችሁ ጻፉ።

ሀ. አንድ የከባቢ አየር ሙቀት መጠን ሲቀየር በሌላ የከባቢ አየር ንብረት ሙቀት ይተካል።

ለ. የአየር ፀባይ በአጭር ጊዜ መለስ ቀለስ ሲል የአየር ንብረት ግን ለረዥም ዘመን ይዘልቃል።

ሐ. የአየር ንብረት ከተለወጠ በሰዎች አኗኗር ላይ ተፅዕኖ ያደርሳል።

መ. ነባር ዝርያዎች የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም ካቃታቸው በአዳዲስ ዝርያዎች ይተካሉ።

ሠ. የዋልታዎች ግግር በረዶ ሲቀልጥ የባህር ጠለል ከፍ ይላል።

## ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥገኛ ሐረጎች ከሚስማሟቸው ነጠላ ዓረፍተነገሮች ጋር በማቀናጀት የተስፋፉ ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

| ጥገኛ ሐረጎች | ነጠላ ዓረፍተነገሮች |
|---|---|
| 1. የአየር ንብረት ከተለወጠ | ሀ. በሌሎች አካባቢዎች ዝናብ በመቀነሱ ድርቅ ይከሰታል። |
| 2. መሬት በአንድ ጂኦሎጂካዊ ዘመን ቅዝቃዜ ሲያከማትራት | ለ. የጎርፍ ማጥለቅለቅን ያስከትላሉ። |
| 3. አንዳንድ ነባር ዘሮች ከአዲስ የአየር ንብረት ጋር ለመስማማት የቅርፅና ይዘት ለውጥ ሲያደርጉ | ሐ. የተለያየ ጉዳት ያደርሳል። |
| 4. በአንዳንድ አካባቢዎች የውኃ ማጥለቅለቅ ሲደርስ | መ. ሌሎች ነባር ዘሮች ግን ጠፍተዋል። |
| 5. በረዶዎች በመቅለጥ ከባህሮች ከተቀላቀሉ | ሠ. በሌላ ጂኦሎጅካዊ ዘመን ሙቀት ያንዳታል። |

## ማንበብ

### የአየር ንብረት ለውጥና መንስኤዎቹ

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

**ተግባር**

የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች «እውነት» ወይም «ሀሰት» በማለት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ሰውሠራሽ ናቸው።

ለ. የሕዝብ ቁጥር መጨመር ለአየር ንብረት መለወጥ መንስኤ ይሆናል።

ሐ. ኢንዱስትሪዎች ለሰው ልጆች ጠቃሚ እንጂ ጎጂ አይደሉም።

መ. ከብዙ ሚሊዮኖች ዓመታት በፊት አህጉራት አንድ ላይ የተገጣጠሙ ነበሩ።

ሠ. ከመሬት ወደከባቢ አየር የሚለቀቁ በካይ ጋዞች ከዝናብ ጋር ተዋህደው ወደመሬት በመመለስ ጉዳት ያደርሳሉ።

ረ. እሳተገሞራ ለቅዝቃዜ መንስኤ ይሆናል።

ሰ. ከፀሐይ የሚመነጨው የብርሃን መጠን ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ነው።

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

«የአየር ንብረት ለውጥና መንስኤዎቹ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በየንዑስ ርዕሱ ያልገባችሁን ደግማችሁ እያነበባችሁ ወይም መምህራችሁን እየጠየቃችሁና የቅድመንባብ መልሶቻችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ።



## የአየር ንብረት ለውጥና መንስኤዎቹ

የአየር ንብረት ለውጥ ሙሉ በሙሉ ሰውሠራሽ ነው ባይባልም ለለውጡ የሰዎች ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው። የሕዝብ ቁጥር ሲጨምርና ኢንዱስትሪዎች ሲስፋፉ የኃይል ምንጭ አጠቃቀምና የጥሬ እቃዎች ፍጆታ ይጨምራል። ይህም በበኩሉ ጎጂ ኬሚካላዊ ነገሮች እንዲመረቱና በከባቢ አየር ውስጥ እንዲገቡ ምክንያት ይሆናል። በተለይም በከባቢ አየር ውስጥ የሚከማቸው የግሪን ሃውስ ጋዝ መንስኤው ሰውሠራሽ ነው።

**ድንገተኛ የውቅያኖስ ዝውውር ለውጥ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲከሰት ያደርጋል።**

የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ የሕዝብ ቁጥር መጨመር ብቻ አይደለም፤ በአህጉራት መፈራቀቅ፣ በእሳተገሞራ ፍንዳታና በፀሐይ ብርሃን መጠን መለዋወጥም የአየር ንብረት ለውጥ ሊከሰት ይችላል። የአየር ንብረት ለውጥ መንስኤዎችን በተናጠል እንደሚከተለው እንመለከታለን።

## የሕዝብ ቁጥር መጨመር

የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር የመኖሪያቤት ግንባታ ፍላጎት ይጨምራል፤ የኢንዱስትሪዎች ግንባታ ይካሄዳል፤ የመሠረተልማት አውታሮች ይስፋፋሉ። እነዚህን የተለያዩ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባልም ደኖች ይመነጠራሉ። አካባቢው ይራቆታል፤ የአካባቢ ብክለትም ይፈጠራል። ከተለያዩ ፋብሪካዎች በካይ ጋዞች ይለቀቃሉ። በካይ ጋዞችና ኬሚካሎች ከንፁህ አየር ጋር ተቀላቅለው ንፁሁን

አየር ከመበከላቸውም በተጨማሪ ርስበርሳቸውም ኬሚካላዊ ውሑድ ይፈጥራሉ። በርግጥ የአየር ዝውውርና ነውጥ የአንዳንዶቹን በካዮች ኃይል ስለሚያዳክም ጉዳት ላያደርሱ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ግን ረጅም ርቀት በመጓዝ ከከባቢ አየር ውስጥ ይቆያሉ። ከዚያም በጠጣር ወይም በፈሳሽ መልክ ከዝናብ ጋር ተዋህደው ወደመሬት ተመልሰው ብዙ ጉዳት ያደርሳሉ።

## የአህጉራት መፈራቀቅ

አሁን ያሉት አህጉራት፣ ምድር ስትፈጠር ከነበራቸው አቀማመጥ አሁን ያላቸው አቀማመጥ የተለየ ነው። ከመቶ ሚሊዮኖች ዓመታት በፊት ደቡብና ሰሜን አሜሪካ፣ እስያ፣ አውስትራሊያና አንታርቲካ አህጉራት አፍሪካን ማዕከል አድርገው አንድ ላይ የተገጣጠሙ ነበሩ። ቀስበቀስ ግን በትልቁ አህጉር ውስጥ መፈራቀቅ እየተፈጠረ ትልልቅ የመሬት አካላት እየተገመሱና እየራቁ ሲሄዱ በመሃላቸው ውቅያኖሶች ተፈጠሩ። ለምሳሌ ደቡብ አሜሪካና ሰሜን አሜሪካ ከአፍሪካና ከአውሮፓ ሲገነጠሉ፣ በመሃላቸው አትላንቲክ ውቅያኖስ ገባ። አሁን በኢትዮጵያ የአፋርን ስምጥ ሸለቆ ይዞ እየተከሰተ ያለው የመሬት መሰንጠቅና መፈራቀቅ አህጉሮችን ከፈጠረው ሂደት ጋር ተመሳሳይነት አለው። የአህጉራት የመፈራቀቅ እንቅስቃሴና የውቅያኖሶች አቀማመጥ ለውጥ ውቅያኖሶች ሙቀትና ርጥበት በመላው ዓለም የሚያሰራጩበትን የዝውውር ሥርዓት ይቀይረዋል።

## የእሳተገሞራ ፍንዳታ

የእሳተገሞራ ፍንዳታ በሁለት መንገድ የከባቢ አየር ለውጥ መንስኤ ይሆናል። አንደኛ ከእሳተገሞራው ጋር የሚተፉ ብናኞች የፀሐይ ብርሃንን በመጋረድ ቅዝቃዜን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ሆኖም ብናኞቹ ከባቢ አየር ውስጥ ለረዥም ዓመታት ስለማይቆዩ ዘላቂ የአየር ንብረት ለውጥ በማምጣት ላይ ያላቸው ሚና ውስን ነው። ሁለተኛ እሳተገሞራ ካርቦንዳይኦክሳይድ ጋዝን በብዛት ስለሚለቅ ለዘላቂ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

## የፀሐይ ብርሃን መጠን መለዋወጥ

ከፀሐይ የሚመነጨው የብርሃን መጠን ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አይደለም። መጠኑ ይቀያየራል፣ ይጨምራል፣ ይቀንሳል። የፀሐይ ዑደት በመባል የሚታወቀውና በየአስራአንድ ዓመቱ የሚቀያየረው የፀሐይ ብርሃን ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ይሆናል። ለምሳሌ ከ500 ዓመት በፊት ተከስቶ የነበረው የበረዶ ዘመን መንስኤው የፀሐይ ብርሃን መቀነስ እንደሆነ ታውቋል። አሁንም ቢሆን እየተከሰተ ያለው የሙቀት መጨመር መንስኤው ከሰውሠራሽ ችግር ይልቅ የፀሐይ ብርሃን መጨመር መሆኑን ሊቃውንት ያስረዳሉ።

(ዮሐንስ አበራ። 2003። *የአየር ንብረት ለውጥ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የልማት ጥናት ተቋም። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።*)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የሰው ልጆች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር ከሰውሠራሽና ተፈጥሯዊ ምክንያቶች በየትኛው ላይ ቢሠሩ ያዋጣቸዋል?

ለ. የእሳተገሞራ ፍንዳታ በከባቢ አየር ላይ የሚያስከትላቸውን ለውጦች ጠቅሳችሁ የተፅዕኗቸውን ዓይነትና ደረጃ አስረዱ።

ሐ. የፀሐይ ብርሃን መጠን መለዋወጥ እንዴት ለአየር ንብረት ለውጥ መንስኤ እንደሚሆን አብራሩ።

መ. የተፈጥሯዊና የሰውሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችን እያነጻጸራችሁ አስረዱ።

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ቃላትንና ሐረጋትን በተመሳሳይ መተካት

### ተግባር

ከሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት መካከል ተገቢ የሆኑትን መርጣችሁ በጽሑፉ ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት ተኩ።

| | |
|---|---|
| መከፈል | እየታየ |
| የሚያዛምቱበትን | የተያያዙ |
| ሲለያዩ | ስትገኝ |
| መነጣጠል | በመሀል |

አሁን ያሉት አህጉራት፣ ምድር ስትፈጠር ከነበራቸው አቀማመጥ አሁን ያላቸው አቀማመጥ የተለየ ነው። ከመቶ ሚሊየኖች ዓመታት በፊት ደቡብና ሰሜን አሜሪካ፣ እስያ፣ አውስትራሊያና አንታርቲካ አህጉራት አፍሪካን ማዕከል አድርገው አንድ ላይ የተገጣጠሙ ነበሩ። ቀስ በቀስ ግን በትልቁ አህጉር ውስጥ መፈራረቅ እየተፈጠረ ትላልቅ የመሬት አካላት እየተገመሱና እየራቁ ሲሄዱ በመሃላቸው ውቅያኖሶች ተፈጠሩ። ለምሳሌ ደቡብ አሜሪካና ሰሜን አሜሪካ ከአፍሪካና ከአውሮፓ ሲገነጠሉ፣ በመሃላቸው አትላንቲክ ውቅያኖስ ገባ። አሁን በኢትዮጵያ የአፋርን ስምጥ ሸለቆ ይዞ እየተከሰተ ያለው የመሬት መሰንጠቅ፣ መፈራረቅ

አህጉሮችን ከፈጠረው ሂደት ጋር ተመሳሳይነት አለው። የአህጉራት የመፈራቀቅ እንቅስቃሴና የውቅያኖሶች አቀማመጥ ለውጥ ውቅያኖሶች ሙቀትና ርጥበት በመላው ዓለም የሚያሰራጩበትን የዝውውር ሥርዓት ይቀይረዋል።

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ድርሰትን ከልሶ መጻፍ

**ተግባር**

በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን «ሰውሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች» በሚል ርዕስ የጻፋችሁትን ድርሰት ከልሳችሁ እንደገና ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል መጻፍ

**ተግባር**

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላትና ሐረጋት ፊደል ሳትገድፉ በትክክል አዳምጣችሁ ጻፉ።

# 6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የአየር ንብረት ለውጥና መንስኤዎቹ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ1ኛው ሳምንት፣ በ3ኛው ቀን አቀላጥፎ የማንበብ ፍጥነታችሁና ትክክለኛ ንባባችሁ በደቂቃ ስንት ቃላት ነበር? ከአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችስ ስንቱን በትክክል መለሳችሁ?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

በ1ኛው ሳምንት፣ በ3ኛው ቀን «የዓለም ሙቀት መጨመር ተጽዕኖ» በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ በቡድን ተደራጅታችሁ በማንበብ ፍጥነታችሁን፣ ትክክለኛ ንባባችሁንና አንብቦ የመረዳት ችሎታችሁን በመለካት ተለማመዱ።

## መናገር

### ተዘጋጅቶ ንግግር ማድረግ

#### ተግባር

«ሰዎች ለድርቅና ለመሬት መጥለቅለቅ ምክንያት እንዴት ይሆናሉ?» በሚል ርዕስ ተዘጋጅታችሁ ንግግር አድርጉ። በመነሻነት በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን በምክንያትና ውጤት ስልት ድርሰት ለመጻፍ የተዘጋጀውን የቢጋር ሠንጠረዥ ተጠቀሙ።

## ሰዋስው

### ስማዊ ሐረጎችን በመሙያነት መጠቀም

#### ተግባር

ስማዊ ሐረጎችን በመሙያነት በመጠቀም አምስት ዓረፍተነገሮች በምሳሌው መሠረት መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

ወይዘሮ አስካለ ባለሙያ ሴት ናቸው።

## የቃላት ጥናት

### መነጠልና ማጣመር

**ተግባር**

1. የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት መድረሻ ቅጥያዎቻቸውን ነጥላችሁ በመጻፍ አንብቡ።

ምሳሌ፡-

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ይታደጋል | ሠንጠረዦች | ምድራችን | አብዛኞቹ |
| ↓ | ↓ | ↓ | ↓ |
| ይታደግ-ኣል | ሠንጠረዥ-ኦች | ምድር-ኣችን | አብዛኞች-ኡ |

| ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|
| ይሆናል | ደኖች | ዘመናችን | ዋነኞቹ |
| ይራቆታል | ስሮች | ጥናታችን | ብዙዎቹ |
| ይቀንሳል | ጥናቶች | አካላችን | አንዳንዶቹ |

2. ከ«ሀ-መ» ያሉትን ቃላት የሚመስሉ መድረሻ ቅጥያዎች ያሏቸው ሌሎች አምስት አምስት ቃላት ጽፋችሁ መድረሻ ቅጥያዎቻቸውን ነጥላችሁ አንብቡ።

## ማንበብ


### የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ

### ቅድመንባብ

### ንዑስ ርዕሶችን በማየት ዝርዝር ሀሳቦችን መገመት

**ተግባር**

«የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ» ከሚለው ርዕስ፣ «የደን ጭፍጨፋን መቀነስ»ና «ደንን ማልማት» ከሚሉት ንዑስ ርዕሶችና ከሚከተለው የቢጋር ክብ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።




## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

«የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በየንዑስ ርዕሱ ጥያቄ እየጠየቃችሁ እየደጋገማችሁ አንብቡ።

### የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ

የአየር ንብረት ለውጥ፣ ባልተለመደ መልኩ ምድራችንን እየተፈታተናት የመጣ የዘመናችን የተፈጥሮ አደጋ ነው። ለውጡ የተፈጥሮ ሚዛንን በማዛባት፣ የምድራችንን የውኃ ትነት መጠን በከፍተኛ ደረጃ እንዲባባስ አድርጓል። በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የአብዛኞዎቹ የውኃ አካላት መጠን ቀንሷል፤ አንዳንዶቹ የውኃ አካላት ደግሞ ጠፍተዋል። ይህም በሰው ልጆች የዕለትተዕለት ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚፈጥር ጤናማ ያልሆነ የሙቀት መጨመር እንዲከሰት አድርጓል።

ከነዚህ ተፅዕኖዎች ለመላቀቅ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ በሚያስችሉ ተግባራት ላይ መሰማራት ተገቢ ይሆናል። ከተግባራቱም መካከል የደን ጭፍጨፋን መቀነስና የደን ሽፋንን መጨመር ዋነኞቹ ናቸው።

### የደን ጭፍጨፋን መቀነስ

ደኖች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ ከፍተኛ ሚና አላቸው። በተለይ በምድር ወገብ አካባቢ የሚገኙ ትሮፒካል ደኖች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። እነዚህ ደኖች ከፍተኛ የሆነ የካርቦን ጋዝን በግንዳቸውና በሥራቸው ይዘው በማስቀረት ልቀትን ይቆጣጠራሉ፤ አካባቢን ከብክለት ይታደጋሉ።

የደን ጭፍጨፋ፣ በዛፍ ግንዶችና ሥሮች ተይዞ የነበረውን ካርቦን፣ ወደከባቢ አየር እንዲለቀቅ በማድረግ ከፍተኛ የካርቦንዳይኦክሳይድ ክምችት ይፈጥራል። ጭፍጨፋው የደኖች መመናመንን ስለሚፈጥር አካባቢ ይራቆታል፤ ጎርፍ ይከሰታል፤ የላይኛው የአፈር ክፍል በጎርፍና በነፋስ እየተጠረገ ስለሚሄድ ምርት ይቀንሳል፤ ድርቅም ይከሰታል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ደኖችን ባለመጨፍጨፍ በየዓመቱ 4.8 ቢሊዮን ቶን የሚደርስ ካርቦንዳይኦክሳይድ ይዘው እንዲያስቀሩ ማድረግ ይቻላል። ይህም በየዓመቱ ከሚቀጣጠለው ነዳጅ ጋር በተያያዘ ከሚኖር የካርቦን ልቀት 18 በመቶ ያህል ይሆናል።

በደን መጨፍጨፍ ምክንያት ኢትዮጵያም የአየር ንብረት ለውጥ ታይቶባታል። በተለያዩ አካባቢዎች ጎርፍ ተከስቷል፤ መሬት ለምነቱን አጥቷል፤ ድርቅ ተከስቷል። ለዚህም ምክንያት የሆነው የደን ሽፋን መጠን ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ ነው። የሚቀጥለው ሠንጠረዥ አስረጂ ሊሆን ይችላል።

የደን ሥርጭት በኢትዮጵያ በስኴየር ኪሎሜትር ከ1973-1990

| የደን ዓይነት | የደን ሽፋን | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ከ1973-1976 ዓ.ም. | | ከ1986-1990 ዓ.ም. | |
| | ስፋት (ስ.ኪ.ሜትር) | የደን ሽፋን በመቶኛ | ስፋት (ስ.ኪ.ሜትር) | የደን ሽፋን በመቶኛ |
| ጥቅጥቅ ደን | 30,243 | 2.64 | 2,346 | 0.2 |
| በመጠኑ የተመናመነ ደን | 14,158 | 1.24 | 7,466 | 0.65 |
| በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነ ደን | 10,009 | 0.87 | 35,243 | 3.08 |
| ጠቅላላ | 54,410 | 4.75 | 45,055 | 3.93 |

(*የብዝኃ ህይወት ሀብት በኢትዮጵያ*። 1998)

ከላይ እንደተገለፀው የደን መጨፍጨፍ በርካታ ችግሮችን ያስከትላል። በመሆኑም የደን መጨፍጨፍ የሚያስከትለውን ችግር ለመግታት ደንን መጠበቅና ማልማት ያስፈልጋል።

## ደንን ማልማት

ደን ማልማት የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታትና የአካባቢ ሥርዓተምህዳርን ለመጠበቅ ያስችላል። በዝርዝር ሲታይ ደንን ማልማት የአፈር መከላትን በመከላከል የመሬት ለምነትን ያስጠብቃል፤ የውኃ ሀብት እጥረት እንዳይኖርና ንፁህ ውኃ ለማግኘትም ይረዳል። ለዱር እንስሳትና ለአዕዋፍ በመኖሪያነትና በምግብ ምንጭነት ያገለግላል። የአካባቢ ውበትን ይጠብቃል፤ በተጨማሪም

ለመናፈሻ አገልግሎትም ይውላል። እንዲሁም የደን ልማትን በማስፋፋት የካርቦን ልቀትን በመቀነስ የአየር ንብረት ለውጥን መግታት ይቻላል።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት ሚና ካላቸው መካከል በግብርናና በደን ሀብት ዘርፍ የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል።

የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት ሚና ያላቸውና ልቀት የሚቀንሱ አሠራሮች

| ዘርፍ | የሚከናወኑ ዋናዋና ተግባራት |
|---|---|
| ግብርና | • የአፈርን ካርቦን የማጠራቀም አቅም ለመጨመር የሚያስችል የተሻሻለ የሰብልና የግጦሽ መሬት አያያዝና አጠቃቀምን መከተል<br>• ለምነቱን ያጣ መሬት እንዲያገግም የማድረግ ዘዴ መጠቀም<br>• ምርጥ ዘር በመጠቀም አካባቢን ማልማት፣ |
| የደን ሀብት ልማት | • ዛፎችን መትከል<br>• የተራቆቱ ቦታዎችን በደን መሸፈን<br>• የደን ሀብት ጥበቃ/እንክብካቤ ማድረግ<br>• የደን ጭፍጨፋን መቀነስ<br>• በእንጨት ምርቶች ላይ ቁጥጥር ማድረግ |

በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ የደን ጭፍጨፋን መቆጣጠር ያስፈልጋል። በዚህም ሊከሰት የሚችለውን የአየር ሚዛን መዛባት ችግር ማስተካከል ይቻላል። በተጨማሪም በተጨፈጨፉ ደኖች ምትክ ችግኞችን መትከልና የተራቆቱ ቦታዎችን ማልማት ችግሩን ለመቋቋም ይጠቅማል።

(<u>የኢትዮጵያ ሥነሕዝብ፣ ጤናና አካባቢ ጥምረት</u>፣ 2006። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች «የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የአየር ንብረት ተጋላጭነትን የሚቀንሱ ተግባራትን ዘርዝራችሁ አስረዱ።

ለ. የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት መንግሥት ምን መሥራት እንደሚችል አስረዱ።

ሐ. «የደን ጭፍጨፋን መቆጣጠርም፣ ደን ማልማትም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ ድርሻ አላቸው» የሚለውን ሀሳብ አብራሩታችሁ አስረዱ።

መ. የደንን ሥርጭት በሚያሳየው ሠንጠረዥ መሠረት ከደን ዓይነቶች በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ የታየው በየትኛው ነው? ለውጡ ለአየር ንብረት ጠቃሚ ነው ወይስ ጎጂ?

ሠ. ከ1973-1990 አጠቃላይ የደን ሽፋን በመቶኛ ምን ያህል ቀንሷል?

ረ. ከደን ዓይነቶች መካከል በጣም በአስደንጋጭ ሁኔታ የቀነሰው የትኛው ነው? በመቶኛ ምን ያህል ነበር? በመቶኛ ምን ያህል ቀረ? ከዚህ ሁኔታ ምን ትረዳላችሁ?

## 8ኛ ቀን


## ቃላት

### ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ በመስጠት ዓረፍተነገር መመሥረት

**ተግባር 1**

በክቡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን በመፈለግ አዛምዷቸው።

ምሳሌ፡-




ተመሳሳይ ፍቺ

ሀ. ታይቷል → ተከስቷል
ለ. ለማስቀረት → ለመግታት

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ባልተለመደ | እንዲጨምር |
| ተጋላጭ | በመኖሪያነት |
| በመጠለያነት | መጠበቅ |
| መከበር | ባልተዘወተረ |
| እንዲባባስ | ተጎጂ |

## ተግባር 2

ከዚህ በታች በሠንጠረዡ ለቀረቡት ቃላት ፍቺ በመስጠት በፍቻቸው ዓረፍተነገር መሥርቱ።

| ተራ ቁ. | ቃል | ተመሳሳይ ፍቺ | በተመሳሳይ ፍቹ የተመሠረተ ዓረፍተነገር |
|---|---|---|---|
| ሀ | መስፋፋት | መሰራጨት | አንዳንድ ቦታዎች ላይ ተላላፊ በሽታ በፍጥነት መሰራጨት ጀምሯል። |
| ለ | ለመግታት | | |
| ሐ. | መላቀቅ | | |
| መ | መኖሪያ | | |
| ሠ | ክምችት | | |
| ረ | ምንጭ | | |
| ሰ | በሚቀጥለው | | |

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### ድርሰትን በቡድን አሻሽሎ መጻፍ

**ተግባር**

«ሰውሠራሽ የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ውጤቶች» በሚል ርዕስ በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን ከልሳችሁ የጻፋችሁትን ድርሰት በቡድን መርጣችሁና አሻሽላችሁ አንድ የቡድን ድርሰት ጻፉ።

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ዓረፍተነገሮችን አስተካክሎ መጻፍ

**ተግባር**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ስህተት ያለባቸውን ቃላትና ሥርዓተነጥቦች አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. የአየር ንብረት ለውጥ መነቀስ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ እንመለከታለን!

ለ. በምድር ወገብ አካባቢ የሚገኙ ትሯፒኮል ደኖች በጣም ጥቅጥቅ ያሉ ናቸው¡

ሐ. ደንን ማልማት የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታትና ምህዳርንሥርዓት ለመጠበቅ ያስችላል.

መ. ደኖችን ባለማጨፍስፍጨ በየዓመቱ 4.8 ቢሊዮን ቶን የሚደርስ የካርቦዳይኦስካይድ ይዘው እንዲያስቀሩ ማድረግ ይቻላል…

ሠ. ደኖች ለዱር እንስሳትና አዕዋፍ በመኖርነት በምግብነት ያገለግላሉ፣

ረ. የተረመጠ ዘርን በመጠቀም አካባቢን ማልማት ጠቃሚ ነው።

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የአየር ንብረት ለውጥን መቀነስ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ2ኛው ሳምንት፣ በ6ኛው ቀን ፍጥነታችሁና ትክክለኛ ንባባችሁ በደቂቃ ስንት ቃል ነበር? ፍጥነታችሁና ትክክለኛ ንባባችሁ ከ1ኛው ሳምንት፣ ከ3ኛው ቀን

ምንባብ፣ በምን ያህል ቃላት ተሻሽሏል? ዛሬ የበለጠ የምታሻሽሉ ይመስላችኋል? እንዴት?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

በቡድን በቡድን በመሆን በ1ኛው ሳምንት፣ በ3ኛው ቀን «የዓለም ሙቀት መጨመር ተጽዕኖ» በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ፍጥነታችሁንና ትክክለኛ ንባባችሁን እየለካችሁ አንብቡ።

# መናገር

## በቢጋር ሠንጠረዥ ሀሳብ አስፍሮ ንግግር ማድረግ

### ተግባር

በ3ኛው ሳምንት፣ በ7ኛው ቀን ለቅድመንባብ የቀረበውን የቢጋር ሠንጠረዥ መነሻ በማድረግ ተዘጋጅታችሁ «የደኖች ጥቅም» በሚል ርዕስ ንግግር አድርጉ።

# ሰዋስው

## ጥገኛ ሐረጎችንና ስማዊ ሐረጎችን ማውጣት

### ተግባር

ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ጥገኛ ሐረጎችንና እንደመሙያ ያገለገሉ ስማዊ ሐረጎችን አውጥታችሁ ጻፉ።

ሀ. የአየር ንብረት ሲለወጥ የውኃ አካላት መጠን ይቀንሳል።

ለ. የዓለምን ከፍተኛ አካል የያዙ የውኃ አካላት ናቸው።

ሐ. ደን ስለተጨፈጨፈ የአየር ንብረት ተለውጧል።

መ. የላይኛው የአፈር ክፍል በጎርፍ ከተጠረገ የመሬት ምርታማነት ይቀንሳል።

ሠ. ለከባቢ አየር መለወጥ የሚጠየቁት የበለጸጉ አገሮች ነበሩ።


ረ. ይቺ ዛፍ ትንሽ ችግኝ ነበረች።

ሰ. ዛፎች ሲቆረጡ ካርቦን ወደከባቢ አየር ይለቀቃል።

ሸ. ደን ሲለማ የአካባቢ ውበት ይጠበቃል።

ቀ. የምርት መጠንን የሚጨምረው ምርጥ ዘር ነው።

በ. ደንን የሚንከባከብ ብልህ ሰው ነው።



# ምዕራፍ 10

# ተውኔት

## የሠርጉ መዘዝ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

## የቃላት ጥናት

### በመነጠልና በማጣመር ማንበብ

#### ተግባር 1

የሚከተሉትን ተነጣጥለው የተጻፉ ቃላት አጣምራችሁ በመጻፍ አንብቡ።

| ተ.ቁ. | ተነጣጥለው ሲጻፉ | ተጣምረው ሲጻፉ |
|---|---|---|
| ሀ | አስ-ቦጭቅ-ኝ | |
| ለ | አል-ት-አዝንብ-ብ-ኝ | |
| ሐ. | መንቀሳቀሻ-ዬ-ን | |
| መ | ይ-አካፋ-ብ-ሽ | |
| ሠ | እስክርቢቶ-ኣቸው-ን | |

#### ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት በፍጥነት ደጋግማችሁ አንብቡ።

ኮሜዲያ
ቋጠር ፈታ
ያጋዝኩበትን
አጨፍግገው
እያራራክ
ስለንዳቢስ
ባጋዘኝ
ደፍ
ዳርዳርታ
ተዋዋል
መፈናፈኛ
ቁሳቁሶች

## ማንበብ

## የሠርጉ መዘዝ

### ቅድመንባብ

### ርዕስና የቀደመ ዕውቀት በመጠቀም የምንበብ ሀሳብ መገመት

#### ተግባር

ሀ. «የሠርጉ መዘዝ» ከሚለው ርዕስ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

ለ. የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም «ገፀባህርያት፣ መቼት፣ ድርጊት፣ ግጭት፣ ጡዘት፣ ልቀት፣ አላባውያን የሚሉትን ቃላት ፍቺ ተናገሩ።

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

«የሠርጉ መዘዝ» የሚለውን ተውኔት ሥርዓተነጥቦችን እየተከተላችሁና የገፀባህርያቱን ንግግር እያስመሰላችሁ አንብቡ።

## የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት አንድ



መጋረጃው ሲከፈት ሰፊው ሳሎን ሶፋ፣ ኮሜዲኖ የመሳሰሉ ዕቃዎችን አሟልቶ ይታያል። በስተቀኝ ከውጭ የሚያስገባ ሌላ በር ከአጠገቡ በመጋረጃ የተሸፈነ መስኮት ይታያል። አቶ በላይሁን ሶፋ ላይ ቁጭ ብለው በጭንቀት ፊታቸውን

ቋጠር ፊታ እያደረጉ በያዙት የሂሳብ ማሽን ላይ አፍጠዋል። እስኪርቢቶና ወረቀት ፊት ለፊታቸው አስቀምጠዋል። ሙሉ ልብስ ለብሰዋል። ክራባት አድርገዋል፤ ፀጉራቸው ነጭ የወረረው ሆኖ ወደኋላ ተበጥሯል።

አቶ በላይሁን፡- (የሂሳብ ማሽኑን ቁጭ አድርገው እስክርቢቷቸውን ይይዛሉ። ወረቀት ላይ ከመዘገቡ በኋላ እንደገና ማሽኑን አንስተው ይነካካሉ። እጃቸውን አገጫቸው ላይ ያደርጉና ፊታቸውን በጭንቀት አጨፍግገው ይቆያሉ።) ውይ!... ውይ!... ውይ!... (ከተቀመጡበት ይነሳሉ።) ውይ!... ውይ!... ውይ!... (ቦታ ቀይረው ይቀመጣሉ። በሩ ተከፍቶ ወይዘሮ አየለች ይገባሉ። ደልደል ባለ ሰውነታቸው ላይ የሀገር ልብስ ለብሰው ፈካ ባለ ሻሽ ፀጉራቸውን ሸብ አርገው በፈገግታ ተሞልተዋል።)

ወ/ሮ አየለች፡- ውይ! በላዬ? ብቻህን ነህ እንዴ?

አቶ በላይሁን፡- ሄዱኮ ሁሉም ሠርጌን፣ ድግሴን በልተው ሄዱኮ...ማን ቀረ?

ወ/ሮ አየለች፡- እሱማ ያለ ነው፣ ... ሰው ለምዶ በአንዴ ቤቱ እንዲህ ጭር ሲል፤

አቶ በላይሁን፡- እንደሱ ማለቴ አይደለም። እኔና ዕዳዬ ብቻ ቀረን፤ ሰው ዓለሜን አይቶ ድግሴን በልቶ ሄደ፤ እኔ መከራዬን ላይ ነው... የሰው ዕዳ፣ ብድር መከራዬን ሊያሳየኝ ነው ማለቴ ነው፤ ይገባሻል?

ወ/ሮ አየለች፡- ጀመርክ እንግዲህ!

አቶ በላይሁን፡- ጀመረኛ!... ልጀምር እንጂ...! ገና ቤት መልሱ ሳይደገስ... የሠርጉ ድግስ ሽታ ሳይጠፋ ጀመረኛ!... ባለዕዳው ሁሉ በስልክ አጣደፈኝ... መቀመጫ አሳጣኝ።

ወ/ሮ አየለች፡- ምናባታቸው ሊሆኑ? ኤዲያ...!

አቶ በላይሁን፡- ዕቃውን ካልመለሳችሁ፣ ሌላ ውል ፈጽሙ ነው የሚሉታ! (በመቆጣት)

ወ/ሮ አየለች፡- ተዋዋል እንጂ! ታዲያ ሰው ምን ላይ ይቀመጣል?

አቶ በላይሁን፡- ለምን ይመጣል? ለምን ይቀመጣል? በቃ መልሱ ቢቀርስ?

ወ/ሮ አየለች፡- ምን? (በንዴት አፍጠው) በል አስበላኛ!... አስቦጭቀኛ! በል እንጂ!

አቶ በላይሁን፡- አልልም! ምን እምለው አለኝና? በቃ! (ያቀረቅራሉ)

ወ/ሮ አየለች፡- ወይ ጉድ!... «ፊቱን ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ»... አሉ (ወደውስጥ ይገባሉ)

አቶ በላይሁን፡- ፊቱን ይደቆስ ይደለዝ ያልሽው... አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው... ነው ነገሩ። (ስልክ ይጮሃል፣ ከውጪ ደመና ይገባል፤ ከውስጥ መሠረት ትወጣለች። መሠረት የቤት ሠራተኛ ስትሆን፣ የለበሰችው ቀሚስ በውኃ ረጥቧል። ደመና ራሰበራ የተዝረከረከ አለባበስ ያለው ሽምገል ያለ የቤቱ ዘበኛ ነው።)

ደመና፡- (ሮጦ ስልኩን ያነሳና) ሀሎ... ሀሎ... ማን ልበል? አሉ...! እሺ (ስልኩን ይዘጋል)።

አቶ በላይሁን፡- ማን ነው የደወለው ደመና?

ደመና፡- በላቸው ነው።

አቶ በላይሁን፡- እሱ ደሞ ምን አለ?

ደመና፡- ከአርብ ጀምሮ ወንበሮችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያጋዝኩበትን ሂሳብ ይስጡኝ ነው የሚል።

አቶ በላይሁን፡- ምነው ጅብ ባጋዘኝ ዘንድሮ!...?

ደመና፡- ቅድም እኮ! የሻውም ደውሎ ነበር።

አቶ በላይሁን፡- ምነው ደመና ባሳዝንህ!... ኧረ! እያራራክ ንገረኝ! ልፈነዳብህ ነው'ኮ...!

ደመና፡- ኧረ አዝኜ ነው ጋሼዬ! ከረር መረር ያሉትን ትቼ ነው።

አቶ በላይሁን፡- በማርያም አታዝንብብኝ፣ ውጣልኝ!

ደመና፡- እሺ... እሺ ...ኢ!...ይ (ያዝናል) ምነው ደምኜ በቀረሁ... ዋ! (ሊወጣ ሲል ወይዘሮ አየለች ከውስጥ ብቅ ይላሉ፤ ቆም ይላል። ከወደውስጥ መሠረት ብቅ ትላለች...)

መሠረት፡- እትዬ... እትዬ... ዓለም መታ ነበር... ፤ «መንቀሳቀሻዬን ቀምተው ምነው ዝም አሉኝ?» ብላለች።

ወ/ሮ አየለች፡- ኤዲያ! ይቺ ደግሞ! ሰለንዳቢስ!...(ይቀመጣሉ) አንቺ ደሞ ለኔ ከምትነግሪኝ ለበላይ አትነግሪውም ታዲያ?

አቶ በላይሁን፡- እኔ ላይማ ዘንበብኝ! ያካፋብሽ ብላ ይሆናላ!? ዶፉ እንዳይገለኝ!

ወ/ሮ አየለች፡- እኔ እምለው...ሰንጋዎቹን አመጣልህ ወይ...?

አቶ በላይሁን፡- (እንዳቀረቀሩ) እኔ...እንጃ...

ወ/ሮ አየለች፡- ታዲያ መቼ ሊመጣ ነው? የምን ዳር ዳርታ ነው እቴ?

አቶ በላይሁን፡- ወይ መፈናፈኛ ማጣት! ወይ መጨናነቅ!

ወ/ሮ አየለች፡- እ... ህ... !(ፋታ) አንቺ መሠረት!... መሠረት! ኧረ መሠረት!

መሠረት፡- (ብቅ ትላለች) እመት እትዬ...

ወ/ሮ አየለች፡- ምሳ አቅርቢ፤ (አቶ በላይሁን ተነስተው ወደበሩ መራመድ ይጀምራሉ) ወዴት ነው? ምሳ ብላ እንጂ!

አቶ በላይሁን፡- አልበላም በቃኝ! (ወደበሩ ይወጣሉ)

ወ/ሮ አየለች፡- እኔም ስመለስ እበላለሁ። ወደሱቅ ልሂድና አንዳንድ ነገሮችን ልገዛዛ (ወደውጪ ይወጣሉ።)

መሠረት፡- በሠርግ መዘዝ የዕዳ ቁልልና መጨናነቅ ይገርማል...

ደመና፡- እኔ የሚገርመኝ፣ ወዳው እሱ ቤት ከርማ የዓመት ልጅ ካደረሰች በኋላ እንደገና ሽማግሌ ላከ፣ ከዚያ በኋላ «ወደናል... ከወደደች» አይበቃም ነበር?

መሠረት፡- ወግ ነዋ!

ደመና፡- ምን ይሂ ይገርማል... ሆሆይ...! አሁድ የሄደችውን እንደገና ቤት መልስ ብለው ሊመልሱ አይደል እንዴ?

መሠረት፡- እምቢ ካሉ ወደቤት አስገብቶ ልጁን ማሳየት ነዋ! በቃ! (እየተሳሳቁ ሲያወሩ በሩ በኃይል ተበርግዶ አቶ በላይሁን ዘወር ሳይሉ በፍጥነት እየተራመዱ ወደውስጠኛው ክፍል ይገባሉ። መሠረትና ደመና ደንግጠው ወደውጪ ይወጣሉ። አቶ በላይሁን በክፍሉ ውስጥ ትንሽ ከተንጎራደዱ በኋላ ወደውጪ ሲወጡ ከወይዘሮ አየለች ጋር በመንገድ ላይ ይገናኙና ተፋጠው ይቆማሉ።) መጋረጃ ይዘጋል።

(ረሺድ ጀማል። 2001። «*ከባለዳስ ዕዳዎች*» መቅረዝ፣ ቁ 7 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተውኔቱ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «ሳሎኑ ሶፋ፣ ኮሜዲኖና እቃዎች አሟልቷል። ... አቶ በላይሁን ሙሉ ልብስና ክራባት አድርገው በጭንቀት ፊታቸውን ቋጠር ፊታ እያደረጉ ከሂሳብ ማሽን ላይ አፍጠዋል። እስክርቢቶና ወረቀት ፊት ለፊታቸው አስቀምጠዋል።» የሚለው ገለጻ ዋና መልዕክቱ ምንድን ነው?

ለ. «አቶ በላይሁን ... በጭንቀት ፊታቸውን ቋጠር ፊታ እያደረጉ ሂሳብ ማሽኑ ላይ አፍጥጠዋል... ወይዘሮ አየለች ... የሀገር ልብስ ለብሰው ፈካ ባለ ሻሽ ፀጉራቸውን ሸፍነው በፈገግታ ተሞልተዋል» የሚለው አገላለጽ ስለተውኔቱ ምን የሚጠቁም ይመስላችኋል?

ሐ. በዋናዎቹ ገጸባህርያት መካከል የተፈጠረ ግጭት ምንድን ነው? የግጭቱ መንስኤ ምን ይመስላችኋል?

መ. ለመጀመሪያ ጊዜ ግጭት መፈጠሩን የሚጠቁመውን የገጸባህርያት ምልልስ ለይታችሁ ጻፉ።

ሠ. በተውኔቱ ግጭቱ እያደገ መሄዱን የሚያሳዩ ምልልሶችን ለይታችሁ ጻፉ።

ረ. የአንድ ጽሑፍ (ተውኔት) ታሪክ የመጀመሪያ፣ መካከለኛና መጨረሻ ክፍል ለይቶ ማወቅ ምን ጠቀሜታ አለው? እንዴትስ መለየት ይቻላል?

ሰ. በታሪኩ መጀመሪያ የተካተቱትን አላባውያን በሚከተለው የቢጋር ሠንጠረዥ ላይ አስፍሩ።

| መጀመሪያ | | መካከል | | መጨረሻ | |
|---|---|---|---|---|---|
| አላባውያን | ዝርዝር | አላባውያን | ዝርዝር | አላባውያን | ዝርዝር |
| ገፀባህርያት | | የድርጊት ማደግ መወሳሰብ | | | |
| መቼት | | | | | |
| ችግር | | ጡዘት | | | |

## 2ኛ ቀን

### ቃላት

### ለቃላት በዐውድና ከዐውድ ውጭ ፍቺ መስጠት

#### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላት/ሐረግ ከምንባቡ ውስጥና ውጪ ያላቸውን ፍቺ ስጡ።

ሀ. መንቀሳቀሻዬን ቀምተሁ ምነው ዝም አሉኝ?

ለ. ፀጉራቸው ሽበት የወረረው ሆኖ ወደኋላ ተበጥሯል።

ሐ. ዕቃውን ካልመለሳችሁ ሌላ ውል ፈርሙ ነው የሚሉት።

መ. እኔ ላይማ ዘነበብኝ! ያካፋብኝ ብሎ ነዋ!

ሠ. አቶ በላይሁን እንደገና ሽማግሌ ላኩ።

ረ. አበዳሪዎቹ ገንዘባችንን መልሱ በማለት አቶ በላይሁንን መፈናፈኛ አሳጧቸው።

#### ተግባር 2

ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት በተመሳሳይና በተቃራኒ ፍቻቸው ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡- ደልደል ያለ → ወፈር ያለ → ተመሳሳይ ፍቺ

ወይዘሮ አየለች ወፈርባለ ሰውነታቸው የሀገር ልብስ ለብሰዋል።

ደልደል ያለ → ከሳ ያለ → ተቃራኒ ፍቺ

ወይዘሮ ዓለምነሽ ከሳ ባለ ሰውነታቸው ላይ የለበሱት ቀሚስ ያምራል።

ሀ. ማጋዝ

ለ. ቁልል

ሐ. ተሸፈነ

መ. ተበጥሯል

ሠ. አጣደፈኝ

ረ. እንዳቀረቀሩ

## መጻፍ

### ድርሰት መጻፍ

### የተውኔት የመጀመሪያ ክፍል መጻፍ

**ተግባር**

ሀ. አንድ የተውኔት ርዕስ መርጣችሁ የተውኔቱን የመጀመሪያውን ክፍል ጻፉ።

ለ. በጻፋችሁት ተውኔት የመጀመሪያ ክፍል ያሉትን አላባውያን በሚከተለው ሠንጠረዥ «መጀመሪያ» በሚለው አምድ ሥር ዘርዝራችሁ ጻፉ።

| መጀመሪያ | | መካከል | | መጨረሻ | |
|---|---|---|---|---|---|
| አላባውያን | ዝርዝር | አላባውያን | ዝርዝር | አላባውያን | ዝርዝር |
| ገፀባህርያት | | የድርጊት ማደግ መወሳሰብ | | | |
| መቼት | | | | | |
| ችግር | | ጡዘት | | | |

### የአጻጻፍ ሥርዓት

### ሥርዓተነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀም

**ተግባር**

የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ችግሮች አሉባቸው። ችግሮቹን በመለየት ሥርዓተነጥቦችን አስተካክላችሁ ዓረፍተነገሮቹን እንደገና ጻፏቸው።

ሀ. የተውኔት አላባውያን ገፀባህርያት ታሪክ መቼት ትልም ምክንያትና ውጤትና ግጭት ናቸው

ለ. ወይዘሮ ሐመልማል የታደለ መኝታ ክፍል ተከፍቶ ሲያዩት ታደለ እንደምን ዋልክ ልጄ የት ጠፍተህ ውለህ ነው አሉ ወደውስጥ ገባ እያሉ

ሐ. ገጸባህርያት ማለት ምን ማለት ነው

መ. ዕድሜ ይስጠን ለወደፊት እንደርስበታለን ደህና ይዋሉ አያ ቦጋለ በማለት አቶ አየለ ተሰናበቷቸው

ሠ. አልማዝ ከትምህርትቤቱ ውስጥ ታዋቂ ተዋናይ ናት

ረ. የተውኔት ጸሐፊ ጸሐፌተውኔት በመባል ይታወቃል

ሰ. ጥሩ ተዋንያን ለመምረጥ የሚከተሉት መስፈርቶች አስፈላጊ ናቸው እነሱም

የንግግር ችሎታ

የማስታወስ ችሎታ

የማንበብ ችሎታ

የትወና ችሎታ

የመግባባት ችሎታ ናቸው

## 3ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት አንድ

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን «የሠርጉ መዘዝ» በሚል ርዕስ ያነበባችሁት ተውኔት፣ ከዚያ በፊት ካነበባችኋቸው ምንባቦች በምን በምን ይለያል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር 1**

«የሠርጉ መዘዝ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት ሥርዓተነጥቦችን ተከትላችሁ፣ የገፀባህርያትን ንግግር አስመስላችሁ ተራበተራ በንግግርአከል ንባብ አንብቡ።

**ተግባር 2**

ተውኔቱን ከክፍል ውጪ ተለማምዳችሁ በመምጣት ሥርዓተነጥቦችን ተከትላችሁ፣ የገጸባህርያቱን ንግግር አስመስላችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ።

# ማዳመጥ

## ያልተፈረደባት ነፍስ

### ቅድመማዳመጥ

### ከርዕስ ተነስቶ የተውኔትን ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ዛሬ የምታዳምጡት «ያልተፈረደባት ነፍስ» በሚል ርዕስ የተጻፈ ተውኔት ነው። ከርዕሱ ተነስታችሁ ተውኔቱ ስለምን እንደተጻፈ ገምቱ።

ለ. «ያልተፈረደባት ነፍስ» የሚለው ሐረግ ፍቺ ምን ይመስላችኋል?

ሐ. ከአሁን በፊት በሬዲዮ ካዳመጣችኋቸው ወይም በቴሌቪዥን ከተመለከታችኋቸው የምታስታውሷቸውን ገጸባህርያት በመጥቀስ እንዴት ማስታወስ እንደቻላችሁ ተናገሩ።

### የማዳመጥ ሂደት

**ተግባር**

መምህራችሁ «ያልተፈረደባት ነፍስ» በሚል ርዕስ የቀረበ ተውኔት ሲያነቡላችሁ ገፀባህርያቱን፣ መቼቱን፣ ግጭቱን፣ የታሪኩን ፍሰት በተመለከተ ማስታወሻ በመያዝ በትኩረት አዳምጡ።

### አዳምጦ መረዳት

**ተግባር**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ተውኔት መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «የሰው ልጅ ለመተዋወቅ አንድ ቀን ይበቃዋል» በሚለው የመስፍን ሀሳብ ትስማማላችሁ? ለምን?

ለ. «መስፍን እስከመቼ በድብብቆሽ እንኖራለን?» ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?

ሐ. አቶ ክንፈ ሃይማኖት ከመስፍን ጋር ቶሎ ግንኙነት እንድትፈፅም የፈለጉት ለምን ይመስላችኋል?

መ. ሃይማኖት መስፍንን የማትወደው ይመስላችኋል? ለምን?

ሠ. እናንተ ሃይማኖትን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

ረ. በተውኔቱ በጣም ያጓጓችሁ ነገር ምንድን ነው? እንዴት?

ሰ. መስፍን ብዙዬ በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መያዟን ስትናገር የደነገጠው ለምን ይመስላችኋል?

ሸ. ብዙዬና ሃይማኖት እህትማማቾች መሆናቸውን መስፍን ያላወቀው ለምን ይመስላችኋል?

ቀ. ከተውኔቱ ምን ተረዳችሁ?

## ሰዋስው

### ጥገኛ ሐረጎችን መለየት

**ተግባር**

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ጥገኛ ሐረጎች ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ:- «እኔ ላይ ሲዘንብብኝ፣ አንቺ ላይ ያካፋል» በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ «እኔ ላይ ሲዘንብብኝ» የሚለው ጥገኛ ሐረግ ነው።

ሀ. አቶ በላይሁን በጭንቀት ተውጠው የሂሳብ ማሽን ላይ አፍጥጠዋል።

ለ. ሰው አለሜን አይቶ እኔ መከራዬን ላይ ነው።

ሐ. እቃውን ካልመለሳችሁ ሌላ ውል ፈጽሙ።

መ. የሀገር ልብስ ለብሰው ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቷል።

ሠ. መሠረት የቤት ሠራተኛ ስትሆን ልብሷ በውኃ ረጥቧል።

ረ. ደመና ሽምገል ያለ የቤት ዘበኛ ነው።

ሰ. ወንበሮችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ያጋዝኩበትን ሂሳብ ይስጡኝ።

ሸ. አቶ በላይነህ ተነስተው ወደበሩ መራመድ ይጀምራሉ።

ቀ. እኔ ስመለስ ምሳ እበላለሁ።

በ. የዓመት ልጅ ካደረሰች በኋላ ሽማግሌ ላከ።

## ማንበብ

### የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሁለት

### ቅድመንባብ

### የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

#### ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች የቀደመ ዕውቀታችሁን በመጠቀም በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ስለተውኔት አጻጻፍ የምታውቋትን ተናገሩ።

ለ. በተውኔት ጽሑፉና በሌላ ጽሑፍ መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

ሐ. ተውኔት እንዴት ይነበባል?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

«የሠርጉ መዘዝ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ተውኔት «ትዕይንት ሁለት» ገፀባህርያቱን ተከፋፍላችሁ በመወከል፣ ንግግራቸውን አስመስላችሁ ሥርዓተነጥቦችን ጠብቃችሁ አንብቡ።

### የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሁለት

አቶ በላይሁንና ወ/ሮ አየለች ተከታትለው እንደወጡ ምሕረት ወደቤት ይገባል። ጠቆር ያለ ሱሪና ነጭ ሸሚዝ የለበሰ ወጣት ነው። ቆም ብሎ ከአቶ በላይሁን ጋር ላፍታ ከተያየ በኋላ ቅሬታ እየተነበበበት አልፏቸው ይገባል። አቶ በላይሁን መለስ ብለው ከገረመሙት በኋላ ትተውት ከቤት ይወጣሉ።

መሠረት፡- ምሳ ላቅርብልህ?

ምሕረት፡- አይ! አልበላም። (ስልክ ይጮህል፣ መሠረትና ደመና ከጓዳ መጥተው ስልኩን ለማንሳት ሲተያዩ ምሕረት ስልኩን ያነሳዋል። ስልኩን ዘግቶ) ወይ ጉድ! እስቲ በሠርግ መዘዝ የዕዳ ቁልል...! (ይተነፍሳል፣ ወዲያውኑ አቶ በላይሁን በጣም እየተናደዱ ከውጭ ወደቤት ገብተው እሶፋው ላይ ዝም ብለው ይቀመጣሉ።)

አቶ በላይሁን፡- (ራሳቸውን በጣታቸው በንዴት መታ መታ ያደርጋሉ።) «ውይ! ውይ! ውይ! ማነህ ምሕረት!? በዚህ ቁጥር ደውልልኝ» በማለት

ቁጥር ይነግሩታል። ፈጠን በል! ፈጠን በል! እናትህ አናቴ ላይ ሳትወጣ ደውልልኝ! (ይደውላል)

ምሕረት፡- ሃሎ! ቆይ አንድ ጊዜ…፣ ምን? (አባቱን ያያል)

አቶ በላይሁን፡- «መልሱ አልቀረም፤… ወንበሮቹ እስከመልሱ ይቆያሉ፤ ብሏል በላይ» በለው።

ምሕረት፡- (የተባለውን ይላል። ስልኩን ይዘጋል)

አቶ በላይሁን፡- ያው! …ነፍስሽ መለስ ትበል… አዎ! የኔ ነፍስ ግን በዕዳ ተጨፍልቃ፣ ተጨማልቃ ወይ በአፌ… ወይ በጆሮዬ ዱብ ትልልሻለች። ወይኔ በላይሁን! (ረዥም ዝምታ)

ምሕረት፡- አ..ባባ!

አቶ በላይሁን፡- ምነው? አስተምረኝ ልትል ነው እንደልማድህ?

ምሕረት፡- በዚህ ሰዓት አንተ ከዕዳ የምትወጣበት፣ ከጭንቀት የምትድንበት እንጂ፣ የኔ መማር አላሳሰበኝም።

አቶ በላይሁን፡- ጎሽ!… የኔ ልጅ! እሽ ለምን ጠራሽኝ?

ምሕረት፡- ቪዲዮ ቀራጩ ደውሎ ነበር።

አቶ በላይሁን፡- ያው ነው!…ምንም አልረዳሽኝም። (ይጣራሉ) መሠረት! አንቺ መሠረት!

ወ/ሮ አየለች፡- ፊልሙን የቀረጸው ነው አይደል?

ምሕረት፡- አዎ!

ወ/ሮ አየለች፡- እግዜር ይስጠው…ሠርጉን ሠርግ ያስመሰለው እሱ ነው።

አቶ በላይሁን፡- አቤት!…አቤት! አዳሜ ቀበቶውን እያላለ ድግሴን ሲበላ…በሶፍት ግንባሩን እየጠረገ ሲያገሳ…ወንበር ላይ ቆሞ ባውዛ እያበራ ስለዞረ ነው? ወይኔ በላይ! መሠረት ያቺን የምጠጣትን አምጭልኝ።

ወ/ሮ አየለች፡- ኸረ እህሉን ብላ ቀድመህ?

አቶ በላይሁን፡- የለም! የለም! አልበላም፤ አሞኛል። (መሠረት የታዘዘችውን ይዛ ትገባለች) ለመሆኑ ስንት ነው አለ?

ምሕረት፡- 600 ብር

አቶ በላይሁን፡- (ባለቤታቸውን) እንዲህ ነው እንዴ የተነጋገርሽው አንቺ? ባንድ ሰው አንድ ብር?

ወ/ሮ አየለች፡- በአገር ዋጋ ትሠራለህ ነው ያልኩት።

አቶ በላይሁን፡- አገሬውን ታስከፍይ እንደሆነ አያለሁ…ውይ! ውይ! (መሠረት በመለኪያ አረቂውን ትቀዳላቸዋለች።)

ምሕረት፡- እና እስከኤዲቲንጉ አንድ ሽህ ብር… መልሱን ከሠራ ደግሞ…

አቶ በላይሁን፡- ምነው የበላሁት በተመለሰ! … እሺ?

ምሕረት፡- አንድ ሽህ ስድስት መቶ ብር!

አቶ በላይሁን፡- (ዝም ብለው እየጠጡ) ስማ ኤዲቲንጉን ይተወው።

ወ/ሮ አየለች፡- እኮ ለምን?

አቶ በላይሁን፡- መጀመሪያ እኔ ያለብኝ ዕዳ ኦዲት ይደረግ።

ወ/ሮ አየለች፡- እንዴት! እንዴት! የመልሱ ዕለት ቤተዘመድ የሚያይ መስሎኝ?

አቶ በላይሁን፡- እዩ ካላልን በግድ እንይ አይል ቤተዘመድ? (እየጨሱ ዝም ብለው ቀድተው ይጠጣሉ) እሺ…! መልሱ እንዳይቀረፅ! አይጠቅምም።

ወ/ሮ አየለች፡- እንዴት አይጠቅምም?

አቶ በላይሁን፡- ድግግሞሽ ነዋ! የሠርጉ ዕለት ይበሉ ከነበሩት ገሚሶቹ በድጋሚ ሲበሉ ነው የሚታየው። የገበታ መዓት ምን ይሠራል?

ወ/ሮ አየለች፡- አይሆንም!

አቶ በላይሁን፡- (ከተቀመጡበት ተነስተው እየዞረባቸው ወደኋላቸው ተራምደው ቆም እንዳሉ ደመና ዘው ብሎ ይገባል)

ደመና፡- ጋሼዬ!

አቶ በላይሁን፡- አቤት! (ያቀረቅራሉ)

ደመና፡- እ…! (ወይዘሮ አየለች አፉን ጥርቅም አድርገው ዝም ካደረጉት በኋላ በጀርባው ወለሉ ላይ ይጥሉታል። አቶ በላይሁን እንዳቀረቀሩ ወደበሩ ተንደርድረው ደመናን ረግጠው ሲወጡ ባለቤታቸውም ተከታትለው ይወጣሉ። ምሕረትና መሠረት በደመና ሁኔታ ይሳሳቃሉ። ደመና እንደተኛ በጎኑ ገልበጥ ብሎ እጁን ይደገፋል) መሠረት አረቂ ቅጅልኝ።

መሠረት፡- (ጠርሙስ አምጥታ እየሳቀች በመለኪያ ትቀዳለታለች) ተዘረርክ አይደል?

ደመና፡- ኧረ ጅዶ! አንዳንዴ ሌሊት አረቄ ጭንቅላቴ ላይ ወጥቶ የዘለልኩትን ጉድጓድ ጧት ሳዬው ይገርመኛል። እሜቴምኮ ሃሳብና ጭንቀት አናታቸው ላይ ወጥቶ እንጂ፣ በደህናው ቀን አይዘርሩኝም ነበር።

ምሕረት፡- (ለራሱ) እስኪ! ቢቀርስ?

ደመና፡- ምን ያድርጉት!?… ወግ ነው… የማኅበረሰቡ ልማድ፣

ምሕረት፡- እንዴት?

ደመና፡- እውቅና አይሰጥማ፤ ህዝቡ ታልበላ!... ደግሰህ ካልዳርክ!... ልጅህ ጋለሞታ፣ የልጅ ልጅህ ደግሞ ዲቃላ ነው የሚባሉት። ከደገስክ ደሞ በደንብ ነው። ካለዚያ ሠርግህ ቦጭቧጫ...አንተ ደሞ ቆጭቋጫ ትባላለህ።

ምሕረት፡- ይገርማል!

ደመና፡- ለልቅሶም ቢሆን ይኸው ነው። ለሞት...ሳርባ፣ ለሙት ዓመት... እየደገስክ ሐውልት ሠርተህ ካላስመረክ እርም በላ እየተባልክ በያለበት ትቦጨቃለህ።

መሠረት፡- ከሌለኝስ?

ደመና፡- ነይ ቅጂ! (ትቀዳለች) ትዘጋጃለሻ! አሁን የኔ አባት... መብራት፣ ውኃ እሚከፍለው እያጣ ይቆረጣል እንጂ... የፈለገ ቢሆን ዕድር አይቋረጥም ነበር። «ሂድ ዕድር ክፈል» ይለኝ ነበር። እውነትም ሲሞት...ድንኳን ተጣለ፤ ተበላ፤ ዕድሩ በሰጠን ገንዘብ ሐውልት ተሠራ፤ ... ተመረቀ።

ምሕረት፡- እና አባትህ ምን ተጠቀሙ?

ደመና፡- ባባቴ መቀለዴ እንዳይመስልህ...ቀስቅሼ ብጠይቀው ደስ ይለኝ ነበር። ታሞ...፤ ጠያቂ ጠፍቶ፣ መታከሚያ አጥቶ ሲሞት ሰው ሲተራመስ፣ እህል ተርፎ ሲፈስ፣ በኋላ እኛ የምንበላው አጣን፤ እባካችሁ ተውኝ። (ድንገት ወ/ሮ አየለችና አቶ በላይሁን እንደተከራረፉ ወደቤት ይገባሉ)

መጋረጃ ይዘጋል

(ረሺድ ጀማል። 2001። «*ከባለዳስ ዕዳዎች*» መቅረዝ፣ ቁ 7 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተውኔቱ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. «የገበታ መዓት ምን ይሠራል?» የሚለውን አገላለጽ አብራሩ።

ለ. ደመና ዕድርን በተመለከተ ከተናገረው ምን ተረዳችሁ?

ሐ. የተውኔቱ ግጭት በዋናነት የተፈጠረው በየትኞቹ ገጸባህርያት መካከል ነው? የግጭታቸውስ መንስኤ ምን ይመስላችኋል?

መ. አቶ በላይሁንና ወይዘሮ አየለች «የምሕረትም አስተምሩኝ ጥያቄ ትተው ሠርግ በመደገስ ከፍተኛ ዕዳ ውስጥ መዘፈቃቸው ምንን ያሳያል?

ሠ. አቶ በላይሁን እንደማንኛውም ወላጅ ሠርገው የዳሯትን ልጅ ምላሽ መጥራት የማይፈልጉ ይመስላችኋል?

ረ. በ1ኛው ሳምንት፣ በ1ኛው ቀን የተውኔቱን መጀመሪያ የሚያሳዩ አላባውያንን በቢጋር ሠንጠረዥ ላይ አስፍራችኋል። አሁን ደግሞ የተውኔቱን «የመካከል ክፍል» የሚያሳዩ አላባውያንን ቀጥሎ ባለው የቢጋር ሠንጠረዥ አስፍሩ።

| መጀመሪያ | | መካከል | | መጨረሻ | |
|---|---|---|---|---|---|
| አላባውያን | ዝርዝር | አላባውያን | ዝርዝር | አላባውያን | ዝርዝር |
| ገፀባህርያት | | የድርጊት ማደግ መወሳሰብ | | | |
| መቼት | | | | | |
| ችግር | | ጡዘት | | | |

## 5ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ለሐረጋት ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሰመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ስጡ።

ሀ. አዳሚ ቀበቶውን እያላላ ድግሴን ሲበላ… ወንበር ላይ ቆሞ ባውዛ እያበራ ስለዞረ ነው?

ለ. ኧረ እህሉን ብላ ቀድመህ?

ሐ. በአገር ዋጋ ትሠራለህ ነው ያልኩት።

መ. መጀመሪያ እኔ ያለብኝ ዕዳ አዲት ይደረግ።

ሠ. እየጨሱ ዝም ብለው ቀድተው ይጠጣሉ።

ረ. የሠርጉ ዕለት ይበሉ ከነበሩት ገሚሶቹ በድጋሚ ሲበሉ ነው የሚታየው።

ሰ. የገበታ መዓት ምን ይሠራል?

ሸ. በደህና ቀን አይዘርሩኝም ነበር።

ቀ. ደግሰህ ካልዳርክ!... ልጅህ ጋለሞታ የልጅ ልጅህ ደግሞ ዲቃላ ነው የሚባሉት።

በ. ከደገስክ ደግሞ በደንብ ነው፤ ካለበለዚያ ሠርግህ ቦጭቧጫ... አንተ ደግሞ ቆጭቋጫ ትባላለህ።

## ተግባር 2

በሚከተሉት ቃላት በተመሳሳይና በተቃራኒ ፍቺቻው ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ሀ. ገረመሙት

ለ. ይጥሉታል

ሐ. ላፍታ

መ. ተራምደው

ሠ. ጓዳ

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

## የተውኔቱን የመካከል ክፍል መጻፍ

### ተግባር

ሀ. በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀን የጀመራችሁትን ተውኔት የመካከል ክፍሉን ጻፉ።

ለ. የተውኔቱን «የመካከል ክፍል» የሚያሳዩ አላባውያንን በቢጋር ሠንጠረዥ ላይ አስፍሩ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

## ተገቢ ሥርዓተ ነጥቦችን መጠቀም

### ተግባር

ቀጥሎ በቀረበው ጽሑፍ ያሉትን ቁጥሮች በተገቢ ሥርዓተነጥቦች ተክታችሁ አንቀጹን እንደገና ጻፉት።

«ምን ኖሯል እባክህ 1 ሞተ ታዲያ 2» ብዬ ጠየቁት 3 ምን ይሞታል 4 እኔ ከጓዳ ጋሼን ምን ነካቸው ብዬ ሮጬ መጣሁና «ምነው ጋሼ 5» አልኳቸው 6 ጋሼም

ቁና ቁና እየተነፈሱ «አይጣልብሽ 7 እንዲያው 8 እንደሱ የምጠላው ነገር የለም። በየት በኩል መኝታ ቤቴ ገብቶ ተኛ 9 እያሉ 10 አልጋውን ይደበድቡታል። «ውይ በሞትኩት 11 ምነው ጋሼ 12 ምንሆኑ 13» ብዬ ጠየኳቸው 14 ራሴም ደንግጬ 15 ጋሼም ምንም መልስ ሳይሰጡኝ አልጋቸውን መደብደብ ቀጠሉ 16 ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ 17

(ፕሮጀክት 17000። 1992። *የሥነጽሑፍ መግቢያ፣* ገፅ 81)

6ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሁለት

### ቅድመንባብ

#### ተግባር

በ1ኛው ሳምንት፣ በ3ኛው ቀን አቀላጥፎ ንባብ ወቅት ሥርዓተነጥቦችን የመጠበቅና የገፀባህርያትን ንግግር አስመስሎ የማንበብ ችሎታችሁ እንዴት ነበር? ደጋግማችሁ ተለማምዳችኋል?

### የማንበብ ሂደት

#### ተግባር

በቡድን በቡድን ሆናችሁ የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ (ሩብሪክ) በመጠቀም «ንግግርአከል» ንባባችሁን እየመዘናችሁ የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሁለት ተውኔትን አንብቡ።

| የንግግርአከል ንባብ መመዘኛ |
|---|
| ደረጃ 4፡-<br>• ሙሉ በሙሉ ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ ማንበብ።<br>• ሙሉ በሙሉ የገፀባህርያትን ንግግር አስመስሎ ማንበብ፣<br>• ሙሉ በሙሉ ሳይቆሙ ቃላትን በትክክል በመጥራት ማንበብ፣ |

ደረጃ 3፡-

- በአብዛኛው ሥርዓተነጥቦችን ጠብቆ ማንበብ፤
- ጥቂት ሥርዓተነጥቦችን ጠብቆ አለማንበብ።
- በአብዛኛው የገፀባህርያትን ንግግር አስመስሎ ማንበብ ጥቂት ገጸባህርያትን አስመስሎ አለማንበብ።
- በአብዛኛው ሳይቆሙ ቃላትን በትክክል ማንበብ
- ጥቂት መቆምና ቃላትን በትክክል አለመጥራት፡

ደረጃ 2፡-

- በከፊል ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ ማንበብ፣
- በከፊል ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ አለማንበብ፣
- በከፊል የገፀባህርያትን ንግግር ማስመሰል፣ በከፊል አለማስመሰል።
- በመጠኑ በየመካከሉ መቆም
- ቃላትን በትክክል አለመጥራት።

ደረጃ 1፡-

- በብዛት ሥርዓተነጥቦችን ተከትሎ አለማንበብ፣. በብዛት
- የገፀባህርያትን ንግግር አስመስሎ አለማንበብ፣
- በብዛት በየመካከሉ መቆም፣
- ቃላትን በትክክል አለመጥራት/አለማንበብ፣

## መናገር

### ገፀባህርያትን አስመስሎ መናገር

#### ተግባር

በ«የሠርጉ መዘዝ» ትዕይንት ሁለት ተውኔት መሠረት የወንዶችን ገጸባህርይ ወንዶች፣ የሴቶችን ገጸባህርይ ሴቶች ንግግራቸውን አስመስላችሁ በክፍል ውስጥ በቃላችሁ ተናገሩ።

## ሰዋስው

### አያያዦችንና መጠይቃዊ ቃላትን ተጠቅሞ ዓረፍተነገር መጻፍ

#### ተግባር 1

አያያዦችን በመጠቀም ሁለት ተዛማጅ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

አቶ በላይሁን በመልሱ ጉዳይ በጣም ተጨንቀዋል፤ ይሁን እንጂ ከባለቤታቸው ጋር ገና አልተነጋገሩበትም።

#### ተግባር 2

መጠይቃዊ ቃላትን በመጠቀም ሁለት ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

1. የመልሱ ድግስ ቀርቷል እንዴ?
2. ምሳ በላሽ ወይ?

## የቃላት ጥናት

### ውስብስብ ቃላትን ነጣጥሎ በመጻፍ ማንበብ

**ተግባር 1**

የሚከተሉትን ቃላት ነጣጥላችሁ በመጻፍ አንብቡ

| | አጣምሮ ማንበብ | ነጣጥሎ ማንበብ |
|---|---|---|
| ሀ | ዐይናቸውን | |
| ለ | እየሳቀች | |
| ሐ | ቆሌያቸው | |
| መ | ወዳጅነቴን | |
| ሠ | ቅስማቸው | |
| ረ | አለመደገሳችን | |
| ሰ | ይቀዳላቸዋል | |
| ሸ | ነገርኳት | |

**ተግባር 2**

የሚከተሉትን ቃላት በፍጥነት ደጋግማችሁ አንብቡ።

| | | |
|---|---|---|
| ተንደርድሮ | ጠረጴዛው | ይገቢያዩ |
| ልታስገዝተው | ያንከራትታሉ | በቤዛይቷ |
| ሲቅበጠበጡ | የተበደርኳቸው | ክራባታቸውን |

## ማንበብ

### የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሦስት

#### ቅድመንባብ

### ከቀደሙት የተውኔት ክፍሎች ተነስቶ ቀሪውን ሀሳብ መገመት

**ተግባር**

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «የሠርጉ መዘዝ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ትዕይንት «አንድ»ና ትዕይንት «ሁለት»ን ስታነቡ በተውኔቱ የመጀመሪያና የመካከለኛ ክፍል ከሚገኙት አላባውያን መካከል ለመለየት ያስቸገሯችሁ የትኞቹ ናቸው?

ለ. የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት «ሦስት» ተውኔት የትኛውን የተውኔት ክፍል የሚያካትት ይመስላችኋል? በዚህ ክፍል የሚጠቃለሉት አለባውያን ምን ምን ይመስሏችኋል?

## የማንበብ ሂደት

### ተግባር

በገፀባህርያት ላይ የሚታዩ የባህርይ ለውጦችን፣ በተውኔቱ መጨረሻ የሚገኙ አላባውያንንና የግጭቱን መፍትሔ ወይም ማጠቃለያ እያስተዋላችሁ የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት «ሦስት» ተውኔትን አንብቡ።

### የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሦስት

በሰፊው ሳሎን ውስጥ አቶ በላይሁን በጭንቀት ከሶፋው ላይ ሲነሱ ሲቀመጡ ሲቅበጠበጡ ይቆዩና ተመልሰው ሶፋው ላይ አረፍ ይላሉ። እንደገና ተነስተው ወንበር ላይ ይቀመጣሉ። ከዚያም ከግድግዳው ጥግ በሚያሳዝን ሁኔታ ቁጢጥ ብለው ዓይናቸውን ከወዲያ ወዲህ ያንከራትታሉ። ስልክ ይደወላል። ስልኩ ሲጠራ እየገላመጡ ዝም ይላሉ። መሠረት ከውስጥ ብቅ ብላ ወደስልኩ ስታመራ ይተያያሉ።

አቶ በላይሁን:- (በምልክት ጭምር) የ.ለ.ሁ.ም!

መሠረት:- (ታነሳለች) ሃሎ…! አዎ…! የሉም…! ወጣ አሉ…እኔ'ንጃ! … እሺ በቃ… እነግራለሁ። (ትዘጋለች) ጋሼ!

አቶ በላይሁን:- ተዪው፤ ሰምቻለሁ ግቢ።

መሠረት:- (ፈራ ተባ እያለች) ጋሼ!… (ያቋርጧታል) ትገባለች። (ረጅም ዝምታ! በድጋሚ ስልክ ይጠራል። መሠረት አልመጣችም… ደመና ተንደርድሮ ገብቶ ያነሳል። አላያቸውም።)

ደመና:- ሃሎ!… የሉም!… አዎ የሉም፤…አይ!… አልነግርም፤ እረሳለሁ። አይ! አልተማርኩም፤…አልጽፍም! (ይዘጋል)

መሠረት:- (ተንደርድራ እየገባች) ውይ… የሉም አልክ?

ደመና:- መሠረት የሉም 'ኮ! … ቢኖሩስ ምን አሉ? አሉ ይባላል እንዴ አሁን? ያን መሳይ ኩሩ ሰው ቆሌያቸው ተገፎ…! ይቺን አክለው…! (በጣቱ እያሳየ) ውይ! ውይ! እትዬ ምነው ቢያስቡላቸው…? የገቡት ዕዳ ሳያልቅ? ልሙትልሽ! አሁን ደግሞ ከደጃፍ ቆመው ወደገቢያ የሚያልፈውን ኩበትና እንጨት የጫነ አርሶአደር ሁሉ እያስቆሙ

ይገቢያዩና «ሂሳቡን ሌላውን ሸጣችሁ ስትመለሱ ትወስዳላችሁ፣ አንተ ደመና! ይህን ኩበት... ይህን እንጨት አራግፍና አህዮቹን እሰር» (በእሳቸው ድምፅ አስመስሎ ሲናገር መሠረት እየሳቀች፣ አቶ በላይሁን ዓይናቸውን አፍጥጠው ሲመለከቱት ከቆዩ በኋላ ድንገት እመር ብለው ይነሳሉ።)

አቶ በላይሁን፡- እ...ንዴ?

ደመና፡- (ደንግጧል) ውይ! ጋሼዬ አሉ'ንዴ?

አቶ በላይሁን፡- አለሁ! ባልኖርም አለሁ! ግን ምን አለች ነው ያልከው? ይከፈላል፣ አራግፍና እሰር...?

ደመና፡- ኧረ! አዎ ጌታዬ...! ሳራግፍ፣ ሳሥር ዋልኩ፣ ከእንግዲህ እንጉረቤት ካላሰርኩ ስፍራም አይበቃም።

አቶ በላይሁን፡- ትሰማለህ ደመና? ከሰማሽኝ....ከወደድከኝ...

ደመና፡- ምን ላርግ? ግራ ገባኝ...

አቶ በለይሁን፡- እኔ አልቻልኩም፣ ከቻልክ አህዮቹን ፍታና ራሷን አየሉን እሰራት!... ላንድ አርሶአደር የምከፍለው ገንዘብ የለኝም።

ደመና፡- አ...ይ! እማይሆነውን ጋሼ!

አቶ በላይሁን፡- እሺ! ምናባቴ ልሁን ደመና? ም...ን...ልሁን?

ደመና፡- (ያዝናል) እንደኔ እንደኔ ጋሼዬ...! የወዳጅነቴን ካልተቀየሙኝ...፣ እንግዳው አህዮቹንም እትዬንም ሳይሆን ሙሽሮቹን ነበር እንዳይመለሱ ማሰር! (ስልክ ይጠራል)

አቶ በላይሁን፡- የለሁም፣ ደመና አንሳው።

ደመና፡ (ያነሳል) ሃሎ...! አዎ...! የሉም...! ምን? (ደንግጧል) ማነህ አንተ? አሀ!...ቆይ እንጂ አንተ (ስልኩን እንደያዘ) ኧረ ፉከራ! እንዴ? (ያስቀምጣል ስልኩን) ኧረ ዛቻ!

አቶ በለይሁን፡- ማነው ደመና?

ደመና፡- የሙሽሮቹን መቀመጫ መድረክ መሥሪያ የሚሆን ያጋዘው።

አቶ በላይሁን፡- (ሳያስቡት በመጮህ) እ... ንዴ!... አየሉ... (ይጣራሉ) አንቺ አየሉ! ጥራት ደመና! ፍጠን። (ደመና ሊወጣ ሲል ወ/ሮ አየለች በመግባታቸው ይመለሳል) በይ እንጂ! ቆይ...ቆይ...የዚያን ቀን ቢያመኝስ? በይ እንጂ! የሰሞኑ ጭንቀት... ሃሳብ... ጨጓራ ስኳር...? ግጥም ብልስ?

ወ/ሮ አየለች፡- የምን መዓት ነው ሰውዬ…? ይህን ለምን ትላለህ?

አቶ በላይሁን፡- ለምን አልልም? በያ! ቆይ… ለምን…ለምን አሁን እያየሽኝ! (በቤቱ ዙሪያ አንዳች ነገር እየፈለጉ) እርር… ኩምትር አልልም… እንደምጣድ ቂጣ… እ…! ቆይ… ለምን ጢል… አልልም…!? (ጠረጴዛው ላይ ይወጡና ክራባታቸውን ወደኮርኒሱ እየጎተቱ) ለምን እንደቋንጣ… ተንጠልጥዬ…

ወ/ሮ አየለች፡- አበድክ እንዴ?

ደመና፡- (ደንግጦ ተንደርድሮ) እንዴ ጋሼየ! ኧረ አይሆንም! (በእግራቸው መሃል አንገቱን አሾልኮ…በሁለት እጆቹ እግራቸውን አንቆ ይይዛል) በቤዛይቷ የኔ ጌታ! (ምሕረት ይገባል፤ ያየዋል) ቶሎ በል አንተ ባልቦላ ኮረንቲ አጥፋ!... ጋሼዬ…!

ምሕረት፡- ምንድነው እሱ? (ይደነግጣል)

ወ/ሮ አየለች፡- እንዴ!...ኧረ እባክህ አንተ ሰው? ምኑን አመጣብህ…? እንዴ ምን መጣ?

አቶ በላይሁን፡- ከዚህ በላይ ምን ይምጣ? ውይ! ውይ! ውይ! ... ይወርዳሉ። (ደመና አንገቱን እያሻሸ ይቆማል)

ምሕረት፡- ያው በዛው በፈረደበት የድግስ ጣጣ ነው?

አቶ በላይሁን፡- (ቅስማቸው ስብር ብሎ ሶፋው ላይ በሀዘን ተውጠው ይቀመጣሉ። ረጅም ዝምታ) እሺ! መልሱ ይደገስ፤ ሰውም ይጠራ፤ ምናልባት ከሞት ብተርፍም፣ በዛ ቀን አልገኝም፤ ህዝቡንም ሙሽሮቹንም ይቅርታ ጠይቁልኝ።

ወ/ሮ አየለች፡- የት ልትሄድ… አንተ?

አቶ በላይሁን፡- ሁሉም የተበደርኳቸው፣ ዱቤ የወሰድኩባቸው ያሳስሩኛል። ምሕረት፣ የጥሪ ወረቀቱን በተንክ… ለመልሱ?

ምሕረት፡- አልበተንኩም?

አቶ በላይሁን፡- ም…ነው… አልክ?

ምሕረት፡- በአጉል ልማድና በይሉኝታ ታጥረን፣… እቤታችን ይህ ሁሉ ጉድ እያለ፣… ላይላዩን መልስ ጠርተን መጨፈራችን አልገባኝም። ለመጨረሻ ጊዜ ብናስብበት ብዬ አዘገየሁት። እማማ!… ውሳኔው የናንተው ነው።

ወ/ሮ አየለች፡- አ... ይ...! ይደገስስ ቢባል እስከድግሱ ማን ቆይቶ ምሕረት? እኔም አባትህ ተበረታ ተስፋ እንዳላስቆርጠው ብዬ ትር ትር እላለሁ እንጂ ተሱ ብሻለሁ 'ኮ! ጨልሞብኛል።

ደመና፡- መቼስ አብረን ኖረናል... ባንዛመድ ያንጀት ወዳጅ ነኝ... ምን አገባህ ባትሉኝ ጋሼዬ! ሰው ያለውን ይበል... ቤታችን አይፍረስ፤ መልሱ ይቅር።

ወ/ሮ አየለች፡- እንደው የሰውስ ይቅር...! ላንድ ሰሞን ቡና መጠጫ አርጎ ይተወኛል... ልጅስ ምን ትል ይሆን?

ምሕረት፡- ደውዬ ነገርኳት።

አቶ በላይሁን፡- ምኑን ምሕረት?

ምሕረት፡- በሠርጉ ድግስ ጣጣ ቤት...ማጀታችን መራቆቱን! በዕዳ ቤት ንብረታችን ሊሸጥ እንደሚችል...በግልፅ ነገርኳት።

ወ/ሮ አየለች፡- ምነው? ...ለምን? ... መልሱ ቀረ አልካት ...?

ምሕረት፡- ደውላ ልታስቀረው... አባባን ልታስገዝተው ወስና ነበር፤ አትጥራ ያለችኝ እሷ ነች።

አቶ በላይሁን፡- እንዴት? ይቅር ብላ ነው?

ምሕረት፡- አዎ አባባ! «ለኔ ሠርግ ያደረገው ዓለሜ ሳይሆን ሞቴ ነው። የጠፋው ጠፋ፤ ግን መልሱን ደግሶ ከጠራኝ... ቤተሰቡንም እኔንም እንደገደለኝ ይቁጠረው» ብላለች።

አቶ በላይሁን፡- አውቅ ነበር...፤ እንኳን መልሱ ሠርጉ ቢቀር አይከፋትም ነበር።

ወ/ሮ አየለች፡- እኔ የሷ መቼ አሳሰበኝ፤ የወጉ የልማዱ እንዳይቀር...። ከሰው እንዳላንስ ነበር እንጂ ... «ዓለሜ ሳይሆን ሞቴ ነው» አለች? እውነቷን ነው፤ ቢቀርስ... (ይተክዛሉ)

አቶ በላይሁን፡- ጐሽ! (ይተነፍሳሉ) ማነህ ደመና ...ያቺን የምጠጣትን አምጣትማ! (አረቂውን አምጥቶ ይቀዳላቸዋል)

ወ/ሮ አየለች፡- ወይ ጣጣ! የስንቱ ቤት ሲታመስ ኖሯል?

ምሕረት፡- (ሁለቱንም ተራበተራ እያየ) መልስ አለመደገሳችን አቅማችንን ማወቃችን እንጂ የሚያሳማን አይሆንም። እንዲያውም በተንዛዛ ድግስ ሃብት ንብረቱን ለሚያባክነው ማኅበረሰብ ምሳሌ እንሆናለን።

መጋረጃ ይዘጋል።

(ረሺድ ጀማል። 2001። *«ከባለዳስ ዕዳዎች»* መቅረዝ፣ ቁ 7 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

## አንብቦ መረዳት

### ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች «በሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሦስት» ተውኔት መሠረት ከሀ-ረ ያሉትን በቃላችሁ የቀሩትን በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከአቶ በላይሁን ከሶፋ ወደወንበር መውረድ፣ ከወንበር ወርዶ መሬት ላይ ቁጢጥ ማለት ምን ትረዳላችሁ?

ለ. አቶ በላይሁን፡- (በምልክት ጭምር) «የ.ለ.ሁ.ም!» ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? ከዚህ ምን ትማራላችሁ?

ሐ. « … አህዮቹንም እትዬንም ሳይሆን ሙሽሮቹን ነበር እንዳይመለሱ ማሰር» የሚለውን የ«ደመና» ንግግር መልዕክት በራሳችሁ አገላለጽ አብራሩ።

መ. «በአጉል ልማድና በይሉኝታ ታጥረን …» የሚለውን የምሕረት ንግግር ሰፋ አድርጋችሁ አብራሩ።

ሠ. ቤተሰቦች ዕዳ ውስጥ የሚዘፈቁት ልጆቻቸው «ሠርጋችሁ ዳሩን» በማለት ስለሚያስገድዷቸው ነው» በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? በተውኔቱ መልዕክት (ዐውድ) መሠረት መልሱ።

ረ. «ሃሎ … የሉም … አዎ የሉም … አይ! አልነግርም እረሳለሁ። አያይ! አልተማርኩም … አልጽፍም» የሚለውን የደመና ንግግር አብራሩ። … መልዕክት መናገር አይችልም፣ ይረሳል፣ መጻፍም አይችልም፣ ማለት ነው?

ሰ. የተውኔቱን መልዕክት በአጭሩ በአንድ አንቀጽ ግለጹ።

ሸ. በተውኔቱ የመጨረሻ ክፍል የተካተቱትን አላባውያን በቢጋር ሠንጠረዥ አስፍሩ።

## 8ኛ ቀን

## ቃላት

### ለቃላትና ለሐረጋት ፍቺ መስጠት

### ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ይህን ኩበት … ይህን እንጨት አራግፍና አህዮቹን እሰር።

ለ. ሁሉም የተበደርኳቸው፣ ዱቤ የወሰድኩባቸው ያሳስሩኛል።

ሐ. አቶ በላይሁን ከግድግዳው ጥግ በሚያሳዝን ሁኔታ ቁጢጥ ብለው ተቀምጠዋል።

መ. እንደኔ እንደኔ ጋሻዬ ... የወዳጅነቱን ካልተቀየሙኝ ልናገር።

ሠ. ... ማጀታችን መራቆቱን! በዕዳ ቤት ንብረታችን ሊሸጥ እንደሚችል ... በግልጽ ነገርኳት።

## ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ በሰጣችኋቸው ፍቺዎች ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ሀ. እመር

ለ. ልታስገዝተው

ሐ. ያንጀት

መ. ሲታመስ

ሠ. ፊራ ተባ

ረ. ያጋዘው

ሰ. ተንጠልጥሎ

ሸ. የሚያሰማን

# መጻፍ

## ድርሰት መጻፍ

### የተውኔቱን የመጨረሻ ክፍል መጻፍ

## ተግባር

ሀ. በ1ኛው ሳምንት፣ በ2ኛው ቀንና በ2ኛው ሳምንት፣ በ5ኛው ቀን የጀመራችሁትን ተውኔት የመጨረሻ ክፍል በመጻፍ አጠናቁ።

ለ. በጻፋችሁት ተውኔት የመጨረሻ ክፍል የሚካተቱ አላባውያንን በቢጋር ሠንጠረዥ አስፍሩ።

ሐ. ከዚህ በፊት በተውኔቱ መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ ያሰፈራችኋቸውን አላባውያን በአንድ የቢጋር ሠንጠረዥ አጠቃላችሁ አስፍሩ።

## የአጻጻፍ ሥርዓት

### ዓረፍተነገሮችን በቅድምተከተል አስተካክሎ መጻፍ

## ተግባር

ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች በቅደምተከተል በማስተካከል ሥርዓተነጥቦችን አሟልታችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

ሀ. ወይዘሮ እልፍነሽ ባለቤታቸው ከቤት ወጣ እንዳሉ አሂሂ ደሞ ጀምረዋል ይህንን ፀሎት

ለ. በጎቹን ላሞቹን ፍየሎቹን ማን ሊያሰማራላቸው ነው እያሉ ተነጫነጩ

ሐ. እንደተቀመጡ ጋቢያቸውን አስተካክለው የፀሎት መጽሐፋቸውን በአንድ እጃቸው በመያዝ ድምጽ ሳያሰሙ ያነበንባሉ።

መ. ከዚያም ፊታቸውን ተጣጥበው የፀሎት መጽሐፋቸውን ይዘው ይቀመጣሉ።

ሠ. ማንበባቸው የሚታወቀው በከንፈራቸው እንቅስቃሴ ብቻ ነው።

ረ. አለቃ የማነህ በጧት ከእንቅልፋቸው እንደተነሱ ፀሎት ከማድረሳቸው በፊት ወደሽንትቤት ይሄዳሉ

ሰ. ወዲያው አለቃ ጸሎታቸውን ጨርሰው ምራቃቸውን እንትፍ እንትፍ ብለው ፊታቸውን አባብሰው ከመቀመጫቸው ተነሱ

## 9ኛ ቀን

## አቀላጥፎ ማንበብ

### የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት ሦስት

### ቅድመንባብ

**ተግባር**

የሠርጉ መዘዝ ትዕይንት «አንድ»ና ትዕይንት «ሁለት» ተውኔትን ስታነቡ ሥርዓተነጥቦችን ጠብቆ ከማንበብና የገፀባህርያትን ንግግር ከማስመሰል የትኛው ነበር ያስቸገራችሁ? ዛሬ የሠርጉ መዘዝ ተውኔት ትዕይንት «ሦስት»ን ስታነቡ የምታሻሽሉ ይመስላችኋል?

### የማንበብ ሂደት

**ተግባር**

በቡድን በቡድን ሆናችሁ አንዳችሁ ስታነቡ አንዳችሁ ስህተቶችን በመመዝገብ የሠርጉ መዘዝ «ትዕይንት ሦስት»ን ተራበተራ አንብቡ። የትክክለኛ ንባብ ደረጃችሁንም በሚከተለው ቢጋር መስመር አስፍሩ።

| | ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| ሥርዓተነጥብ ጠብቆ ማንበብ | | | | |
| የገፀባህርያትን ንግግር ማስመሰል | | | | |
| ሳይቆሙ/ሳይደግሙ በትክክል ማንበብ | | | | |

## መናገር

### ተውኔቱ ያሳደረውን ስሜት በንግግር መግለጽ

**ተግባር**

«የሠርጉ መዘዝ» በሚል ርዕስ በሶስት ትዕይንቶች ተከፋፍሎ የቀረበውን ተውኔት መሠረት አድርጋችሁ ሀሳባችሁን በሚከተለው የቢጋር ክብ አደራጅታችሁ ንግግር አድርጉ።



## ሰዋስው

### ጥገኛ ሐረጎችን፣ ነጠላ ዓረፍተነገሮችንና ስማዊ ሐረጎችን መለየት

#### ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ፡-

ሀ. ጥገኛ ሐረጎችን፣

ለ. ነጠላ ዓረፍተነገሮችና

ሐ. እንደመሙያ ያገለገሉ ስማዊ ሐረጎችን ለይታችሁ ፃፉ።

1. የሂሳብ ማሽኑን ሲነካኩ ጭንቀታቸው ይጨምራል።
2. እቃውን መልሱ ወይም ሌላ ውል ፈጽሙ።
3. ወይዘሮ አየለች ጠንካራ ሴት ናቸው።
4. አቶ በላይሁን ኩሩ ሰው ነበሩ?
5. ወይዘሮ አየለች ሲመጡ መሠረት ወደውሰጥ ገባች።
6. ሴትዮዋ ጭንቅላቱ ላይ ብትወጣም ወንበሮቹ እስከምላሹ ይቆያሉ።
7. አንዳንድ ሰዎች በመልሱ ጊዜ ስጦታ ያመጣሉና አስተናጋጆች በደንብ ይቀበሏቸው።
8. መልሱም በቪዲዮ ሊቀረጽ ነበር።
9. መሠረትና ደመና ታማኝ ሠራተኞች ናቸው?
10. ሰው እንደልማዱ ይማ እንጂ የመልሱ ድግስ ይቅር።

## ሙዳየቃላት

**ሀሳብ ማጋራት** (Think-aloud)፡- በአርዓያነት እያነበቡ እያሉ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ቆም እያሉ ስለአንድ ነገር/ጉዳይ እንዴት እያሰቡ እንደሆነ ለሌላ ሰው ሀሳብን ማካፈል፣

**መለየት/ማንበብ** (Decoding)፡- የተጻፉ ቃላትን (ጽሑፍን) ወደንግግር ቋንቋ ለመቀየር የፊደል ድምፅ ግንኙነትንና የቃላት ዕውቀትን መጠቀም፣

**መላልሶ ማንበብ** (Repeated reading)፡- በትክክለኛና በፍጥነት የማንበብ ችሎታን ለማጎልበት በግብረመልስ እየታገዙ ደጋግሞ የማንበብ ሂደት

**መልሶ ማንበብ** (Reread)፡- በማንበብ ሂደት ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ሀሳቡን መረዳት እስኪቻል ድረስ ወደኋላ እየተመለሱ ማንበብ፣

**መልዕክት ሰጪ ንባብ** (Prosody)፦ አንድ ጽሁፍ በትክክለኛው ወይም በተገቢው የድምፅ ቅላፄ ማንበብ፣

**መምህር መር ንባብ** (Guided Reading)፦ ለደረጃው የቀረበውን ጽሑፍ በትክክል ማንበብ እንዲቻል መምህራን አንብበው በማሳየት ንባቡን የሚያስቀጥሉበት ሂደት፣

**መረዳት** (Comprehension)፡- የንግግርን ወይም የጽሑፍን ቋንቋ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ሂደት፣

**መነጠል** (Segmenting)፡- አንድን ሙሉ ቃል ወይም ሐረግ በተናጠላዊ ፊደሎች ወይም በአነስተኛ የቃል ክፍልፋዮች የመነጣጠል ሂደት

**መገመት** (prediction)፡- ከማንበብ/ከማዳመጥ በፊት ወይም በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት ቀጥሎ ምን ሊመጣ ወይም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፤ ስለገፀባህርያቱና ስለሴራው ድምዳሜ መስጠት፣

**የማዳመጥ ቃላት** (Listening vocabulary)፡- ሰዎች በንግግር ጊዜ አዳምጠው የሚረዷቸው ቃላት፣

**ማጠቃለል/ማሳጠር** (Summarizing)፡- የምንባብን አቢይ ሀሳብ ጨምቆ የማውጣት ሂደት፣

**ማጣመር** (blending)፡- በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ፊደሎች ተነጣጥሎ የቀረበን ቃል በአንድ ላይ አጣምሮ የመናገር፣ የማንበብ ወይም የመጻፍ ሂደት፣

**ራስን የመከታተያ ስልት** (Self-checking strategy)፡- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ መረዳታቸውን የሚያረጋግጡበት ብልሃት፣

**ቃላት በደቂቃ (ቃበደ)** (WPM)፡- በአንድ ደቂቃ በፍጥነት የተነበቡ ቃላት ብዛት፣ በአንድ ደቂቃ በትክክል የተነበቡ ቃላት

**ብዛት** (WCPM ቃላት ትክክል በደቂቃ (ቃትበደ))፣ (የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ደረጃ ለመወሰን ያገለግላል።)

**ቃላት ትንተና** (Word analysis)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ቅጥያዎች በመተንተን ለማንበብ የሚጠቀሙበት ስልት፣

**ቅጥያ** (Affix)፡- በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚቀጠሉ ትርጉም አዘል ቅጥያዎች፣ (በቃል መጀመሪያ ሲቀጠሉ ቅድመአምድ ቅጥያ (Prefix)፣ በቃል መጨረሻ ሲቀጠሉ ድህረአምድ ቅጥያ (Suffix) ይባላሉ።)

**ቅጽበታዊነት** (Automaticity)፡- ፊደላትን፣ ድምጾችንና ቃላትን ያለችግር፣ ሳያመነቱ፣ ሳያወላውሉ፣ በቅጽበትና በትክክል የመለየትና የማንበብ ችሎታ፣

**ቀጥተኛ ጥያቄ** (Explicit question)፡- መልሱ በቀጥታ ከምንባብ ወይም ከንግግር የሚገኝ ጥያቄ ዓይነት፣

**ቃላትን መረዳት/ማወቅ** (Word Recognition)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን ለመለየት የሚጠቀሙበት ስልት

**በማንበብ ሂደት መቆምና ማሰብ** (Stop and think)፡- በማንበብ ሂደት ምን እየተነበበ እንደሆነ ቆምብሎ ማሰብ፣ ስለተነበበው ምንባብ ምንም ነገር ማስታወስ ካልተቻለ ወደፊት ከማንበብ ይልቅ ቆም ብሎ የተነበበውን ሀሳብ በአዕምሮ ለመረዳት መሞከር፣

**በቢጤ መማማር** (Peer tutoring)፡- ተማሪዎች ትምህርታዊ ክሂሎችን ርስበርስ የሚማማሩበት ሂደት

**የቢጋር ሠንጠረዥ** (Graphic organizer)፡- የሀሳብን ግንኙነት በሥዕል ወይም በግራፍ ወይም በሠንጠረዥ ማደራጃ፣

**በትብብር መማር** (Cooperative learning)፡- አንድን የትምህርት ይዘት በጋራ እየተረዳዱ የመማር ሂደት፣

**ቤት መምታት** (Rhyme)፡- በተመሣሣይ ፊደሎች/ድምጾች የሚጨርሱ ቃላት/ የግጥም ቤት፣

**በጋራ ማንበብ** (Choral reading)፡- በርካታ ተማሪዎች ባንድ ላይ፣ በአንድ ጊዜ ድምፅ እያሰሙ ምንባብ የሚያነቡበት ሂደት፣ አተገባበሩም የክፍሉ ተማሪዎች በሙሉ ከመምህር ጋር በማንበብ፣ መምህር ዓረፍተነገር ወይም አንቀጽ ሲያነቡ ተማሪዎች የሚቀጥለውን ዓረፍተነገር ወይም አንቀጽ በማንበብ፣ በአንድ አካባቢ/ወንበር የተቀመጡ ተማሪዎች በአንድ ላይ በማንበብ፣ ግማሽ የክፍሉ ተማሪዎች የምንባቡን አንድ ክፍል ሲያነቡ ግማሹ ተማሪዎች ሌላው ክፍል በማንበብ ወዘተ ሊሆን ይችላል።

**ተራኪ ጽሑፍ** (Narrative text)፡- ታሪክን በጊዜ ወይም በቦታ ወይም በድርጊት ቅደምተከተል የሚያሳይ የጽሑፍ መዋቅር

**የታሪክ መዋቅር** (Story structure)፡- እንደመቼት፣ ድርጊት፣ ሁነት፣ ችግርና መፍትሄ ያሉትን አላባውያን የሚያካትት የድርሰት መዋቅር

**ትክክለኛነት** (Accuracy)፡- አንድን ቃል ወይም ሐረግ ወይም ዓረፍተነገር ያለስህተትና ያለማወላወል የማንበብ ችሎታ፣

**ንባብን ወደፊት መቀጠል** (Read ahead)፡- አሻሚ ሀሳብ ሲያጋጥም ግልፅ እንዲሆን ወደፊት ያሉትን ዓረፍተነገሮች ማንበብ፤ የተወሰኑ ዓረፍተነገሮች ተነበው ሀሳቡ ግልፅ ካልሆነ ሌላ ስልት መፈለግ፣

**አመራማሪ ጥያቄዎች** (Implicit/inferential Questions)፡- ተማሪዎች በሚያነቡት/ በሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር በማገናኘት መልስ የሚሰጡባቸው የአንብቦ/የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

**አስረጂ ጽሑፍ** (Expository text)፡- መረጃ ሰጪ የሆነ ጽሑፍ ሆኖ ስለአንድ ርዕሰጉዳይ ወይም እውነት ለማስተማር/ለማስረዳት የሚያገለግል ጽሑፍ፣

**አቀላጥፎ ማንበብ** (Fluency)፡- ፊደላትን፣ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጭ በመሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ፣

**አንብቦ መረዳት** (Reading comprehension)፡- አንድ ጽሑፍ አንብቦ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ችሎታ፣

**አዕምሯዊ ምሥል** (Mental picture)፡- የገፀባህርያት፣ የቦታና የሁነቶች ገለፃን በተመለከተ በአዕምሮ ምሥል እየፈጠሩ ማንበብ፣

**አዳምጦ መረዳት** (Listening comprehension)፡- ንግግርን ወይም ጽሑፍን አዳምጦ መረዳትና ትርጉም የመስጠት ችሎታ፣

**የአጻጻፍ ሥርዓት** (Writing convention)፡- የፊደላትን ቅርጽ፣ አሰዳደር፣ የአጻጻፍ አቅጣጫና የሥርዓተነጥብን አጠቃቀም የሚያሳይ የአጻጻፍ ሥርዓት፣

**ዋና ሀሳብ/ዐቢይ ሀሳብ** (Main idea)፡- ከምንባብ ተጨምቆ የሚወጣ አቢይ ወይም ዋና ሀሳብ፣

**ዐውድ** (Context)፡- ለአንድ እንግዳ ቃል ፍቺ ፍንጭ የሚሰጡ ከቃሉ በፊት ወይም በኋላ የሚገኙ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ዓረፍተነገሮች፣

**ዘውግ** (Genre)፡- በልዩ መዋቅሩ ወይም ባህሪያቱ የሚታወቅ የጽሑፍ መዋቅር፤ ምሳሌ፡- ተውኔት፣ ገላጭ ድርሰት፣ ተራኪ ድርሰት፣

**ዘዬ** (dialect)፡- በንበት/በድምጽ፣ በቃል ወይም በሰዋስው የሚከሰት አካባቢያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት፣

**የጥንድ ንባብ** (partner reading)፡- በጥንድ ሆኖ ተራ በተራ የማንበብ ሂደት

**ጥያቄ መጠየቅ** (ask question)፡- ጥያቄ እየጠየቁ ማንበብ፣ ምንባቡን ለመረዳት ይጠቅማል። ለጥያቄዎች ምላሽ ማፈላለግ ያነበቡትን ለመረዳት ይረዳል፣

- ምንባቡ ስሜት ሰጥቶኛል?
- የማነበው ለምንድን ነው?
- ስለዚህ ምንባብ ምን የማውቀው ነገር አለኝ?
- ካነበብኩ በኋላ የምማረው ምንድን ነው?
- የዘለልኩት ነገር አለ?
- ምን ምን ጥያቄዎች አሉኝ?
- ስለምንባቡ ምን አስባለሁ? እስማማለሁ? ግራ ተጋብቻለሁ?
- ፍጥነቴን መቀነስ ነው ያለብኝ ወይስ መጨመር?

**የጽሑፍ መዋቅር** (text structure)፡- በጽሑፍ ውስጥ የይዘቶች አደረጃጀት

# ዋቢዎች

## ምዕራፍ 1

ደ/ብ/መ/ማ/ሙ/ማ ኮሌጅ ማህበራዊ ሳይንስ ት/ክፍል፣ ለሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ለመለያ 212 ኮርስ ማስተማሪያነት የተዘጋጀ ሞጁዩል:: (ያልታተመ)

## ምዕራፍ 2

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ:: 2007። ባህል ቱሪዝም። ገፅ 32-33 መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎ የተወሰደ።

Elissa Jobson. 10 September 2013 WWW. The aforican report.

## ምዕራፍ 3

ትምህርት ሚኒስቴር:: 2003:: *የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት 7ኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ።* ዱባይ፤ የአል-ጉሬር አታሚና አሳታሚ ድርጅት፣

## ምዕራፍ 4

አረጋሽ ሰይፉና ሌሎች:: 1990:: *እኛ 170 ግጥሞች።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

ከበደ ሚካኤል:: 1999 *ተረትና ምሳሌ ፩ኛ መጽሐፍ፡፤*(2ኛ እትም::)ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት

ዘሪሁን አስፋው:: 1992:: *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን።* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

## ምዕራፍ 5

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ፣ 2002:: የሥነሕዝብና የቤተሰብ ሕይወት:: *ለሁለተኛ ደረጃ መምህራንና ወጣት ተማሪዎች የተዘጋጀ አጋዥ መጽሐፍ።*

ዳኛቸው ወርቁ:: 1988:: *የጸሁፍ ጥበብ መመሪያ።* አዲስ አበባ፤ ሜጋ ህትመት ኢንተርፕራይዝ::

## ምዕራፍ 6

ፊሊጶስ አይናለም:: 2006:: *የደንልማት ጥበቃ።* ቁጥር 199::

Jerry L.Johns and Roberta L. Berglund, fluency. Strategies & Assessments (3rded) 2006 Kendall/Hunt publishing Company.

## ምዕራፍ 7

ኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የተባበሩት መንግሥታት የሕጻናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ):: 1999:: *የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሰነዶች (የአማርኛ ትርጉም)።* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ:: 2004:: *አማርኛ መማሪያ 8ኛ ክፍል።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ::

ጌታሁን ወርቁ፣ ሰኔ 24/2006፣ *ሪፖርተር ጋዜጣ፣* ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ግንቦት 2005::

Jerry L.Johns and Roberta L. Berglund, fluency. Strategies & Assessments (3rded) 2006 Kendall/Hunt publishing Company

## ምዕራፍ 8

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ:: 2004:: *ጀንደር።* ቅጽ1 ቁጥር 9:: ባህር ዳር፤ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማተሚያ ቤት::

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ:: 1999:: *ሰላም መጽሔት።* ቅጽ1 ቁጥር2::

ዳንኤል ክብረት:: 2005:: *የኔ ጀግናና ሌሎች።* አዲስ አበባ፤ አገዮስ ኅትመትና ጠቅላላ ንግድ ኃ.የተ.የግል ማህበር::

Jerry L.Johns and Roberta L. Berglund. 2006. fluency. Strategies & Assessments (3rded) Kendall/Hunt publishing Company.

## ምዕራፍ 9

ኮድ ኢትዮጵያ:: 2009:: *አካባቢን መገንዘብ። አዲስ አበባ።*

በማስታወቂያ ሚኒስቴር ፕሬስና ኦዲዮቪዥዋል መምሪያ:: 1998:: *የብዝሃ ሕይወት ሀብት በኢትዮጵያ።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት::

ዮሐንስ አበራ አየለ:: 2003:: *የአየር ንብረት ለውጥ፤ ክስተቱ፣ መንስኤው፣ መፍትሔው* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የልማት ጥናት ተቋም:: አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት::

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ፣ 2002:: *የሥነሕዝብና የቤተሰብ ሕይወት።* ለሁለተኛ ደረጃ መምህራንና ወጣት ተማሪዎች የተዘጋጀ አጋዥ መጽሐፍ::

የኢትዮጵያ ሥነሕዝብ ጤናና አካባቢ ጥምረት:: 2006:: *በሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ዙሪያ ትምህርት ቤቶች የአካባቢ ክበባት የአየር ንብረት ለውጥ መረጃ።* (Toolkit) አዲስ አበባ::

Jerry L.Johns and Roberta L. Berglund. 2006. fluency. Strategies & Assessments (3rded) Kendall/Hunt publishing Company.

National Meteorological Agency. 2007. *Climate Change National adaptation programme of Action (NAPA) of Ethiopia.* Addis Ababa. Ethiopia.

## ምዕራፍ 10

ረሺድ ጀማል:: 2001 «ባለዳስ ዕዳዎች::» *በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ የባ/አስ/ተቋ/ጥ/ል/አጠቃቀም የሥራ ሂደት። መቅረዝ።* አዲስ አበባ፤ (ልዩ እትም) ቁጥር 7፣ ከገጽ 341-377::

ትምህርት መገናኛ ዘዴዎች ድርጅት ትምህርት ሚኒስቴር:: 1992:: *ፕሮጀክት 17000 የአንደኛ ደረጃ የሁለተኛ ሳይክል መምህራን የርቀት ትምህርት ፕሮጀክት። የሥነጽሑፍ መግቢያ::* አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማማ.ድ::

አንዱዓለም አባተ:: 1995:: *ጠጣር ፍሬ።* አብክመ የወጣቶች ባህልና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ የባህል ጥናት ማስፋፊያ ቡድን:: መቅረዝ:: (ልዩ እትም) ቁጥር 4:: አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ከገጽ 323-354::

Jerry L.Johns and Roberta L. Berglund. 2006. *fluency. Strategies & Assessments (3rded)* Kendall/Hunt publishing Company.